# የሥነ ምግባር መርሖ

ለልጄ፡ መሓሪ ታደሰ፡

ከጸሓፊው፡ ትእዛዝ፡ ተስፋዬ ሮበሌ

ወዳጄ፡ ዕይ፡ እግዚአብሔር

እምላካችን፡ በነገር፡ ሁሉ፡

እንደሚገርመን፡ ምሪቱ፡

ደስታ፡ ነው።

ከተስፋዬ ሮበሌ

ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር

የመልእክት ሣጥን ቁጥር 23045 ኮድ 100

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

*የሥነ ምግባር መርሐ*
አሳታሚ©1996 ከተስፋዬ ሮበሌ
አሳታሚው ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር ነው::
የመልእክት ሣጥን ቍጥር 23045 ኮድ 1000
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው:: ያሳሳታሚው ፈቃድ አብዝቶ ማሳተምም ሆነ የተወሰነን ክፍል በተለያዩ መንገዶች ማራባት በጥብቅ የተከለከለ ነው:: በማንኛውም መልኩ መረጃን ለመውሰድ ከተፈለገ በትክክል ሥርዐቱን ጠብቆ ሊጠቀስ እንዲሁም በግርጌ ማስታወሻ ሊመላከት ይገባዋል::

የመጀመሪያ ዕትም 1996 ዓ.ም (ወርኀ ታኅሣሥ)

የታተመው በአዲስ አበባ ኢትዮጵያ ነው::

*Ethical Principles*
Copyright © 2004 by Tesfaye Robele

Published by Tesfa Evangelical Society For Apologetics
Post Office Box 23045, Code 1000
Addis Ababa, Ethiopia.
E-mail: tesfa_apologetics@yahoo.com

All rights Reserved. No part of this publication may be reproduced, stored in a retrieval system, or transmitted in any form or by any means-electronic, mechanical, photocopying, recording, or otherwise-without the prior written permission of the publisher and copyright owners.

First printing 2003

Printed in the Addis Ababa, Ethiopia

# DEDICATION

Mr. Paul Carden, Executive Director The Centers For Apologetics Research and Rev. Luke P. Wilson, Executive Director Institute for Religious Research.

Thank you so much for benig part of my life and ministry and for your willingness to continue to be part of my future. Your generosity, encouragement, and friendship continue to be a testimony to your commitment. It is a privilege and a blessing to be a recipient of your personal and professional virtue.

---

# ምስጋና

ይህን መጽሐፍ በማዘጋጅበት ወቅት ያበረታቱኝን፣ ረቂቁን በማንበብ ከበርካታ ስሕተት የታደጉኝን ሰዎች ማመስገን እወዳለሁ:: እንዲያም ሆኖ በመጽሐፉ ላይ ስሕተት ቢገኝ፣ የስሕተቱ ተወቃሽ እኔው እንጂ እነዚህ ሰዎች አይደሉም:: አቶ ማሞ ገብረመስቀል፣ አቶ ብርሃኑ ደረሰ፣ አቶ መስፍን ኩመራ፣ መጋቢ ሙሉጌታ ታደሰ፣ ወይዘሮት ነጻነት ሽፈራው፣ አቶ ስሜ ታደሰ፣ አቶ ንጉሤ ቡልቻ፣ አቶ ቁምላቸው ፋንታሁን እግዚአብሔር ያክብርልኝ፣ ዕድሜና ጤና ይስጥልኝ::

# ማውጫ

1. የሥነ ምግባር መርሖን ማጥናት ለምን አስፈለገ? 1
2. የብሉያትና የሐዲሳት ሥነ ምግባር 7
3. የሥነ ምግባር መርሖችና የግብረገብ ሙግቶች አካሄድ 27
4. ግብረገባዊ አንጻራዊነት 43
   4.1. ግብረገባዊ አንጻራዊነት ምንድን ነው? 47
   4.2. የአንጻራዊነት ጐራዎች 52
   4.3. ባህላዊ ወይም ተገላጭ አንጻራዊነት 55
   4.4. ዐዋጃዊ ወይም ግዕዛናዊ ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት 60
   4.5. ግብረገባዊ ፋይዳዎችን "በሌላው ላይ መጫን" ተገቢ ነው? 64
   4.6. ግብረገባዊ አንጻራዊነትን የማንቀበለው ለምንድን ነው? 68
5. ግብረገባዊ የወል ስሜት 84
6. ግብረገብ ከየት መጣ? 88
7. ግብረገባዊ ፍጹማዊነት 93
   7.1. ኢተጣራሽ ፍጹማዊነት 97
   7.2. ተጣራሽ ፍጹማዊነት 103
   7.3. ተዋረዳዊ ፍጹማዊነት 107
8. ሥነ ምግባርን አስመልክቶ ውሳኔ ላይ የሚደረሰው እንዴት ነው? 119
9. ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር፣ መጽሐፍ ቅዱስና የትርጓሜ መርሖች 127
10. ሙዳየ ቃላት 143
11. ዋቢ መጻሕፍት 155

# 1

## የሥነ ምግባር መርሖ

የዚህ መጽሐፍ ዐቢይ ትኩረት የሥነ ምግባር መርሖችን ማስተዋወቅ፣ ትክክለኛ የሆነው *የሥነ ምግባር መርሖ* የትኛው እንደ ሆነ ማሳየት፣ ትክክለኛ የሆነውን ምግባራዊ ውሳኔ እንዲወስኑ መርዳት፣ ሠናይ የሆነ ሥነ ምግባራዊ ሕይወት እንዲኖር ማስቻል ነው። የሥነ ምግባር ጕዳይ የሕይወት ቀዳማይ ጕዳይ አይደለም ብሎ የሚያስብ ሰው፣ ይህ መጽሐፍ ለእርሱ የተጻፈ ስላልሆነ፣ ይህንን መጽሐፍም ሆነ በሥነ ምግባር ላይ የተጻፉ ማናቸውንም ዐይነት መጻሕፍት ማንበብ አይኖርበትም። ነገር ግን የሥነ ምግባር ጕዳይ የሕልውና ጕዳይ ነው የሚል አቋም ያለው ሰው፣ ሥነ ምግባራዊ መርሖችን በተመለከተ ከዚህ መጽሐፍ የተወሰነ ዕውቀት ሊገበይ እንደሚችል እምነት አለን።

የሰው ልጅ (ቢያንስ አብዛኛው ሰው) መልካም ሆኖ መገኘት ይፈልጋል። አንድ ሰው ማጅራት እየመታና ኪስ እያወለቀ "ሁሉ ብእጁ ሁሉ በደጁ" ቢሆን፣ "የተሳካለት ሰው ነው!" ብሎ ማሰብ አስቸጋሪ አይሆንም? የትዳር አጋሩን የሚደበድብ፣ ልጆቹን የሚያሠቃይ፣ የአልኮል መጠጦችን ያለልክ እየጠጣ አንደበቱን፣ አስተሳሰቡንና ምግባሩን የማይገራውን ሰው፣ "ግሩም ሰው ነው!" ማለት እንዴት ይቻላል? በአንጻሩ ደግሞ እንደ እማሆይ ቴሬሳ ያሉ፣ ሕይወታቸውን ለሌሎች ጥቅም አፍስሰው ያለፉትን የሥነ ምግባር ጀግኖች የማያደንቅ ማነው? በዕለት ተዕለት ኑሮው የሥነ ምግባር ምርጫዎች የማይቀርብለት የዓለማችን ነዋሪስ የትኛው ነው (ገዳም የገባውን መናኝ ጨምሮ)? በተለይ ለክርስቲያን በግብረገብ የመታነጽና ያለመታነጽ ጕዳይ፣ በዐጸደ ሥጋ የመኖርና ያለመኖር ጥያቄ ነው ቢባል አንዳችም እብለት አይኖርበትም። "ብርሃንና ጨው" እንዲሆን የተፈጠረ ፍጡር፣ ጨለማና አልጫ ሊሆን እንደምን ይችላል? ይህ እውነት ከሆነ የሥነ ምግባር ጕዳይ ከእህልና ከውሃ ጕዳይ በላይ መሆኑ ቅቡል ይሆናል። ሠለጠነ የሚባለው ይህ ዘመናዊው ኅብተረሰብ፣ በሥልጣኔው እንዲገፋበት ቢያንስ ፍትሕን፣ እውነትንና ርኅራኄን ገንዘቡ ሊያደርጋቸው ይገባል። "በሥነ ምግባር የታነጸ ዜጋ ማፍራት" የሚለው የመንግሥታችን የዘውትር አነጋገር፣ እነዚህንና ከእነዚህ ጋር ተዛማጅ የሆኑትን እውነታዎች ታሳቢ ያደረገ ይመስለናል። እነዚህ ነገሮች እውነት ከሆኑ፣ እነዚህን ነገሮች አጥርተን እናይ ዘንድ ፋና የሚወጋልን የሥነ ምግባር ጥናት፣ እንደምን ክቡር እንደምንስ ቅዱስ ርእሰ ጕዳይ ሊሆንልን አይችልም?

ልባም ሰዎች ከመቼውም የታሪክ ዘመን ይልቅ ይህ ትውልድ ሥነ ምግባር በእጅጉ እንደሚያስፈልገው ይገልጻሉ:: የቴክኖሎጂው ልቀትና የሳይንሱ ምጥቀት፣ የራሱ የሆነ የሥነ ምግባር ጥያቄዎችን ይዞ መምጣቱ የዕለት ተዕለት ክሥተት ሆኖአል:: ጀኔቲክ ኢንጂነሪንግ፣ የተለያዩ ዐይነት የመራቢያ ቴክኖሎጂዎች፣ የሸልን ኅብረ ሕዋስ በመጠቀም የተለያዩ በሽታዎችን መፈወስ ወዘተርፈ ያሉ ግብረገባዊ ርእሶች፣ የሰሉ የግብረገብ ክርክሮችን የሚያስነሡ ርእሰ ጉዳዮች ናቸው::

ከሳይንሱና ከቴክኖሎጂው ምጥቀት በተጨማሪ፣ የኅብረተሰባችን የግብረገብ ሕይወት ከድጡ ወደ ማጡ እየሆነ የመምጣቱ ጉዳይ፣ በርካታ ሰዎች ሥነ ምግባርን ለማጥናት ከፍተኛ ፍላጎት እንዲያድርባቸው አድርጓል:: የወጣት ጥፋተኝነት መበራከት፣ ከየትኛውም የዕድሜ ክልል ይልቅ በዐሥራዎቹ የዕድሜ ክልል ያሉ ወጣቶች በኤች. አይ. ቪ/ኤድስ ክፉኛ መጠቃታቸው፣ የፍቺ መበራከት፣ የአደንዛዥ ዕፅ ዝውውር የዓለማችን ችግር እየሆነ መምጣት፣ የአደገኛና የረቂቅ ወንጀሎች መስፋፋት፣ የሙስና መበራከት፣ የንግድና የሙያ ሥነ ምግባር መውደቅ ወዘተ የኅብረተሰባችንን ሕልውና ክፉኛ እየተፈታተኑት ይገኛሉ:: "ሙያተኛነትና ሥነ ምግባር" እሳትና ጭድ፣ "ንግድና ሥነ ምግባር" ዐይንና ናጫ ሆነዋል፡ አንዱ ባለበት ቦታ ሌላውን ማንሣት በተፈሮአቸው ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን ለማዋሐድ እንደ መሞከር ተደርጎ ነው የሚታሰበው::

ዓለማችን በእነዚህ ሁሉ ገዳይ በሽታዎች በጠና ታማ የመገኘቷ ጉዳይ ያሳሰባቸው ሰዎች፣ "ፀረ ሙስና ኮሚሽን" እንደሚባለው የመንግሥት ውቅር፣ ለእያንዳንዱ የሥነ ምግባር ሕግ ዘብ የሚቆም ኮሚሽን ስለማናቋቁም (እናቋቁምም ብንል ጉልበቱም ሆነ ችሎታው ስለማይኖረን) እንዲሁም እኩይ ፍሬ የታየው የት ቦታ ነው እያሉ ፍሬውን መልቀም አድካሚ ስለሆነ፣ እኩዩ ዘር እንዳይዘራ በተለያዩ ጊዜያትና ምክንያቶች የተዘራውም ዘር እንዳይበቅል፣ የፍሬውን እኩይነት በትምህርት ማሽ ግልጥልጥ አድርጎ ማሳየት በብዙ ጐኑ ጠቀሜታው ታላቅ ነው የሚለው ምክራቸው ሚዛን የሚደፋ ይመስለናል:: ይህ ደግሞ ለሥነ ምግባር ትምህርት ትኩረት የሚሰጥ ነው:: ትልልቅ የሚባሉትን የትምህርት ተቋማት ጨምሮ፣ በተለያዩ ደረጃ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች፣ የበሰለና የጠለለ የሥነ ምግባር ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ ሁነኛ የመፍትሔ ጅማሮ ነው::

## የሥነ ምግባር ፈርጆች

ሥነ ምግባር አራት ቅርንጫፎች አሉት:: እነርሱም 1) *ተገላጭ ሥነ ምግባር* 2) *ገላጭ ሥነ ምግባር* 3) *ዲበ ሥነ ምግባርና* 4) *አርኤቲክ ሥነ ምግባር* ናቸው:: ይህ



መጽሐፍ ትኩረት ሰጥቶ የሚመለከተው፣ ገላጭ ሥነ ምግባርን ቢሆንም የገላጭ ሥነ ምግባር ባላንጣ ናቸው የሚባሉትንም የሥነ ምግባር አካሄዶች ሰፊ ቦታ ሰጥቶ ይመረምራል::

አንደኛ:- ተገላጭ ሥነ ምግባር፣ የሰዎችን ባህል በማጥናት የማኅበረሰብን ግብረገብ ይገልጻል:: የሥነ ሰብ ምሁራን፣ የአንድ ባህል ከሌላው ባህል በምን እንደሚለይ ይገልጻሉ::

ሁለተኛ:- ገላጭ ሥነ ምግባር በግብረገብ ሕግጋት ላይ ትኩረት በማድረግ ውጤቱን ይተልማል:: ገላጭ ሥነ ምግባር ለአንድ ማኅበረሰብ ወይም ግለሰብ ሠናይ ወይም እኩይ የሆነው ሥነ ምግባር የቱ ነው የሚለውን ጉዳይ ይተነትናል:: ገላጭ ሥነ ምግባር የሥነ ምግባር መሠረት የሆኑትን ገብረገባዊ ሕግጋት (መርሖ) ሲያጠና፣ ተገላጭ ሥነ ምግባር ግን፣ እነዚህ ሕግጋት መሠረት ያደረጉበት ባህል እንዴት ይገለጻል የሚለውን ጉዳይ ይተነትናል::

ሦስተኛ:- ዲበ ሥነ ምግባር የሚባለው የሥነ ምግባር ዘርፍ፣ የግብረገብ ቃላትን ትርጉም የሚመረምር የጥናት ዘርፍ ወይም የሥነ ምግባር *ሥነ ዕውቀት* ነው:: ዲበ ሥነ ምግባር በሥነ ምግባር ውስጥ የሚገኙትን መሠረታዊ ቃላት ማለትም ሠናይ፣ እኩይና ፍትሕ የሚሉትን ቃላት በስፋት ይመረምራል:: ዲበ ሥነ ምግባር እነዚህ ቃላት የሰዎችን ምርጫ የሚያሳዩ ናቸው ስለሚል ግብረገብን አንጻራዊ ያደርገዋል::

አራተኛ:- አርኤቲክ ሥነ ምግባር በሰዎች የባሕርይ ቀረጻ ላይ ትኩረት የሚያደርግ የሥነ ምግባር ዘርፍ ነው:: አርኤቲክ የሚለው ቃል የተወሰደው ከግሪክ ቃል ሲሆን፣ በእንግሊዝኛ "Virtue Theory" የሚል አቻ ትርጉም ተሰጥቶታል:: ይህ የሥነ ምግባር ዘርፍ፣ አወዛጋቢና ረቂቅ የሆኑ ግብረገባዊ ውሳኔዎችን እንዴት መወሰን ይቻላል በሚለው ሳይሆን፣ የሰዎችን ባሕርይ እንዴት ማሻሻል ይቻላል በሚለው ጉዳይ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው::

ግብረገባዊ ብያኔዎችን ለማድረግ አልያም አንድ ግለሰብ ምግባር ሠናይ ነው ወይም እኩይ ነው ለማለት፣ ቢያንስ አራት መሠረታዊ ነጥቦችን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይኖርብናል[1]::

[1] Louis Pojman, *Ethics: Discovering Right and Wrong* (Belmont, California: Wadsworth, 1990), 7-10.

አንደኛ:- ምግባሩን መመርመር:: ይህ ለግብረገባዊ ብያኔ መሠረታዊ ነጥብ ነው:: ነገር ግን ብቸኛ ጉዳይ አይደለም:: ሁለተኛ:- የግለሰቡን የልብ ፍላጎት (motive) ማወቅ:: ለምሳሌ:- ለአንድ ሰው ገንዘብ መስጠታችን ልግስና ነው ወይስ ሙስና የሚለውን ጉዳይ የሚወስነው የልብ ፍላጎትን በመመርመር ነው:: ሦስተኛ:- ምግባሩ ወይም ውሳኔው የሚያስከትለውን ውጤት መመርመር:: ነገር ግን አንድ ምግባር እኩይ ነው ወይም ሠናይ ነው ስንል፣ የሚያስከትለውን ውጤት ታሳቢ አድርገን እንዳልሆነ ልብ ይሏል:: ለምሳሌ:- በባሪያ ፍንገላ አማካይነት የተወሰኑ አገሮች ከፍተኛ የሆነ የምጣኔ ሀብት ዕድገት አሳይተዋል (ለምሳሌ:- የአሜሪካን ደቡባዊ ክፍል) በሚል፣ ባርነት ሠናይ ምግባር ነው ወደሚለው ድምዳሜ አንደርስም፤ ውጤቱ አማረ ማለት ግብሩ ሠናይ ነው ማለት አይደለም:: አራተኛ:- የግለሰቡን ባሕርይ መመርመር:: በአንጻራዊነት ሲታይ ከመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ይልቅ፣ ይህ ብዙ ድካም ይጠይቃል:: ባሕርይ ማለት ግለሰቡ ለረጅም ጊዜ ያሳየውና የግለሰቡ ጠባይ ይህ ነው ተብሎ ሊተነበይ የሚችለው ባሕርይው ነው:: አርኤቲክ ሥነ ምግባር የባሕርይን ቀረጻ ተኩረት የማያደርግ ሥነ ምግባር ሙሉዕ አይደለም ባይ ነው:: እንደ አርኤቲክ ሰዎች ዐልፎ ዐልፎ የሚገጥማቸውን ግብረገባዊ ቅራኔዎች በመፍታቱ ላይ ብቻ የሚያጠነጥን ሥነ ምግባር ለባሕርይ ቀረጻ ጊዜ ስለማይኖረው፣ ጭንቅላትን እንጂ ግብረገብን አያሳድግም::

## የሥነ ምግባር መርሖች

ሥነ ምግባራዊ መርሖች ***ምግባረ ተኩርና አርኤቲክ ተኩር*** በሚል ለሁለት ዐቢይ ክፍል ይከፈላሉ:: በእነዚህ ዐበይት ክፍሎች ሥር፣ ሥነ ምግባራዊ መርሖች በሦስት ንዑሳን ክፍሎች ይከፈላሉ:: ይኸውም ***መርሖ ተኩር፣ ውጤት ተኩርና አንጻራዊነት*** ናቸው::

አንደኛ:- መርሖ ተኩር ሥነ ምግባር፣ የአንድ ምግባር (ባሕርይ፣ ድርጊት፣ የልብ ፍላጎት) ሠናይነትና እኩይነት የሚወሰነው ሥነ ምግባራዊ መርሖችን መሠረት በማድረግ ነው፣ የሚል የግብረገብ አካሄድ ነው:: በመርሖ ተኩር ሥነ ምግባር ወስጥ የሚካተቱት (1) ***የመለኮት ትእዛዝ ንድፈ ሐሳብ*** (2) ***የተፈጥሮ ሕግና*** (3) ***ሥነ ምግባራዊ ምክኑያዊነት*** ናቸው:: ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር መሠረት የሚያደርገው ፍጹማን በሆኑት የአምላክ ትእዛዛት ላይ ስለሆነ ክርስቲያኖች የሚከተሉት መርሖ ተኩር የሚባለውን የሥነ ምግባር አካሄድ ነው::

ሁለተኛ:- ውጤት ተኩር ሥነ ምግባር፣ የአንድ ምግባር ሠናይነትና እኩይነት የሚወሰነው በሚያስከትለው ውጤት ነው የሚል የግብረገብ አካሄድ ነው:: የምግባርን



ሠናይነትና እኩይነት የሚወስነው የግብረገብ መርሖች ሳይሆኑ፣ ምግባሩ ያስከትለዋል በተባለው ውጤት ከሆነ፣ አንድም ምግባር በራሱ እኩይም ሆነ ሠናይ አይደለም ማለት ነው:: አንድ ምግባር ከሚያስከትለው ጉዳት ይልቅ መልካምነቱ የሚበዛ ከሆነ ሠናይ ምግባር ይሆናል:: በውጤት ተኩር ሥነ ምግባር ውስጥ ካሉት ቅርንጫፎች መኻል ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዘው፣ ***የበለጠ መልካምነት ለበለጠ ቍጥር*** የሚለው የሥነ ምግባር አካሄድ ነው:: በዚህ የሥነ ምግባር አካሄድ አንድ ግብረገብ ሠናይ ነው የሚባለው፣ የበለጠ መልካምነት ለበለጠ ቍጥር የሚያስገኝ ከሆነ ነው:: በውጤት ተኩር ሥነ ምግባር ወስጥ የሚካተተው ሌላው፣ ***ሥነ ምግባርዊ እኔነት*** በመባል የሚታወቀው የሥነ ምግባር አካሄድ ነው:: ሥነ ምግባራዊ እኔነት የሰዎችን ፍላጎት የሚያረካው ግብር ሁሉ ሠናይ ነው ይላል::

ሦስተኛ:- በ***ግብረገባዊ አንጻራዊነት*** የሥነ ምግባር አካሄድ፣ ሠናይነትና እኩይነት ፍጹማንና የማይለወጡ አይደሉም፤ ነገር ግን እንደየ ባህሉና *(ባህላዊ ወይም ተገላጭ አንጻራዊነት)*፣ እንደየ ሰዉ ምርጫ *(ግላዊ ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት ወይም ሥነ ምግባራዊ ኀሊናዊነት)* የሚለያዩ ናቸው:: ዛሬ በርካታ ሰዎች ይህን የግብረገብ አካሄድ በስፋት ይከተላሉ:: በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ይህ ጉዳይ ሰፊ ሽፋን ያገኘበትም ዋነኛ ምክንያት ይኸው ነው::

# 2

## የብሉያትና የሐዲሳት ሥነ ምግባር[1]

የብሉያትና የሐዲሳት ሥነ ምግባር የሚያጠነጥነው፣ እግዚአብሔር ልዩ በሆነ መንገድ በገለጣቸው ትእዛዛቱ ዙሪያ ነው:: የነገረ መለኮት ምሁራን እግዚአብሔር ሥነ ምግባራዊ የሆኑ መለኮታዊ ትእዛዛትን እንመራባቸው ዘንድ ለመስጠቱ ተመሳሳይ አቋም ቢኖራቸውም፣ "አንድ ነገር ትክክል የሆነው እግዚአብሔር ስላዘዘው ነው ወይስ እግዚአብሔር ያዘዘው ነገሩ ትክክል ሆኖ ስለተገኘ ነው?" በሚለው ጥያቄ ላይ ግን ለሁለት ይከፈላሉ፤ በሌላ አገላለጽ የእግዚአብሔር ትእዛዝ አንድን ነገር ትክክል እንዲሆን ያደርገዋል ወይስ አንድ ነገር ትክክል መሆኑን ይገልጻል (ይጠቁማል) ማለት ነው:: ይህን ጥያቄ ለመጀመሪያ ጊዜ የጠየቀው *አፍላጦን* ሲሆን፣ ጥያቄውን የጠየቀው ዮቴፍሮ በመባል በሚታወቀው ተዋስኦ (ቃለ ምልልስ) ላይ ነው:: ከዚህ የተነሣ ይህ ጥያቄ፣ *"የዩቴፍሮ ውጥረት"* በመባል ይታወቃል:: የዩቴፍሮን ውጥረት በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ በስፋት የምንመለከተው ጉዳይ ይሆናል::

### የብሉያት ሥነ ምግባር[2]

የብሉያት መጻሕፍት *የሥርዐታዊ ነገረ መለኮት* መጻሕፍት ሳይሆኑ፣ በተለያዩ ርእሰ ጉዳይ ላይ ትኩረት ያደረጉና በተለያየ *ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ* የተጻፉ ትምህርቶች ጥንቅር እንደ ሆኑ ሁሉ፣ ሥነ ምግባርንም ደርዝ ባለው መልክ የሚተነትኑ መጻሕፍት አይደሉም:: ነገር ግን የተለያዩ ግብረገባዊ ርእሰ ጉዳዮችን፣ የተለያየ ዐይነት *የግብረገባዊ ሙግቶች አካሄድ* በመጠቀም የእኩይነታቸውንም ሆነ የሠናይነታቸውን ጉዳይ ይሞግታሉ:: እስራኤል ሕይወቷን የምታስተዳድርበትን በርካታ ሥነ ምግባራዊ አካሄዶችን የያዘው የሙሴ ሕግ ነው:: የብሉይ ኪዳን ነቢያት የትንቢት ማእከልም እነዚህ መጻሕፍት ነበሩ:: እነዚህ በሙሴ መጻሕፍት ውስጥ የሰፈሩትን በርካታ ሥነ ምግባራዊ ሕግጋት ስንመለከት፣ ብሉያት ሠናይነትንና እኩይነትን የሚወስኑት *ውጤትን ታሳቢ አድርገው* ሳይሆን፣ *መርሖን ታሳቢ አድርገው* እንደ ሆነ እንግራለን::

---

[1] ልዩ መግለጫ ካልተሰጠ በስተቀር ይህ ክፍል በአብዛኛው የተወሰደው ከ Scott B. Rae, *Moral Choices: An Introduction To Ethics* (Grand Rapids: Zondervan, 1985), 19-42 ላይ ነው::

[2] ስለ ብሉያት ሥነ ምግባር የመለጠ ማብራሪያ ከፈለጉ Walter C. Kaiser Jr., *Toward Old Testament Ethics* (Grand Rapids: Zondervan, 1983) ይመለከቷል::

የቅኔ መጻሕፍት ሙግት ደግሞ፣ መልካም የሆኑ ሥነ ምግባራዊ አካሄዶች ሠናይ ውጤት እንደሚያስከትሉና መጥፎዎቹ ደግሞ እኩይ ውጤት እንደሚያመጡ የሚያብራሩ ናቸው:: የቅኔ መጻሕፍት ጸሓፍያን ጥበብን ያሞካሻሉ፤ ምክንያቱም ጥበብ መልካም ውጤትን ስለሚያስከትል፤ በአንጻሩ ደግሞ ጅልነትን (ተላላነትን) ክፉኛ ይነቅፋሉ አሉታዊ ውጤትን ያስከትላልና:: የቅኔ መጻሕፍት በሙሴ ሕግ ላይ መሠረት ያደረጉ ስለሆነ፣ በመርሖች ላይ መሠረት ያደረጉ ናቸው ማለት ይቻላል:: በአጠቃላይ የቅኔ መጻሕፍት ውጤትንም ሆነ ወደ ውጤት የሚያደርሰውን መርሖ ትኩረት ያደረጉ ናቸው::

ብሉያት የእስራኤል ብሔራዊ ጥበቃና ግብርና አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ውጤት ሊያስከትል የሚችለው፣ እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ባላት መልካም ግንኙነት ነው (ዘዳግም 27-30):: ኪዳኗን በመታዘዟ በረከት፣ ባለመታዘዟ ደግሞ መርገም ይመጣባታል:: ነቢያቶቿ በኪዳኗ ለእግዚአብሔር ታማኝ ትሆን ዘንድ፣ ለኪዳን መታመን የሚያስከትለውን በረከትና ያለመታዘዝ የሚያስከትለውን ጥፋት በማስረዳት፣ ከጠማማ መንገዷ እንድትመለስ ያስጠነቅቋታል:: ይህ በረከትና እርግማን በእስራኤል ሥነ ምግባር ውስጥ ከፍተኛ ቦታ እንዳለው አመላካች ነው:: የበረከትና የርግማን አካሄድ ***የሰብአውያንን ፍላጐት የሚያረካ ውጤት ተኰር አካሄድ ነው***:: ይህ ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሰብአውያንን ወይም የአምላክን ፍላጐት ማሟላት ብቻ በራሱ፣ ብቁ የሆነ የሥነ ምግባር መርሖ ነው ማለቱ አይደለም፤ ነገር ግን በመርሖዎች ላይ መሠረት ያደረገው አካሄድ ውጤቱ የአምላክንም ፍላጎት እንደሚያረካ የሚገልጽ ነው::

የብሉያት ሥነ ምግባር የተፈጥሮ ሕግጋትንም መሠረት ያደረገ ነው:: ለምሳሌ መጽሐፈ ምሳሌ የትክክልና የስሕተትን (ጥበብንና ቂልነትን) ውጤት የሚተነትነው፣ የተፈጥሮ ሕግጋትን (ምሳ 6÷6-11፤ በተጨማሪም መዝ 19÷1-6 ይመለከቷል) እንዲሁም የሰብአውያንን ግንኙነት ማእከል ባደረገ ሁኔታ ነው (ምሳ 24÷30-34):: የተፈጥሮ ሕግጋት ***ጽንፈ ዓለማዊ*** የሆነውን መርሖ መሠረት ያደረገ ነው፤ ስለዚህ ሁል ዐቀፍ (ጽንፈ ዓለማዊ) የሆኑት ግብረገባዊ ***ፋይዳዎች (መርሖች)፣ በልዩ መገለጥ*** ብቻ የሚገኙ አይደሉም:: ለምሳሌ:- በአሕዛብ ላይ የተነገሩት ***ንግሮች*** (ኢሳ 13-23፤ ኤር 46-51፤ ሕዝ 25-32) መጽሐፍ ቅዱስ የተፈጥሮ ሕግጋትንም ማእከል እንዳደረገ አመላካቾች ናቸው:: እንደ እስራኤል የሙሴ ሕግ የሌላቸው አሕዛብ፣ እስራኤል በተወነጀለችባቸው ኀጢአቶች (ስሕተቶች) (ለምሳሌ:- ኢፍትሓዊነት፣ ድኾችን መጨቆንና ዐመፀኝነት) እነርሱም ሲወነጀሉ ይታያል:: ከዚህ የምንረዳው ነገር፣ እነዚህ መንግሥታት በተወሰነ መልኩ ወንጀለኝነታቸውን ጠንቅቀው እንደሚያውቁት ነው:: ይህ ባይሆን ኖሮ እግዚአብሔር በጥፋታቸው ባልኰነናቸው ነበር:: እግዚአብሔር ወንጀለኛ ያደረጋቸው፣ በሙሴ ሕግ ሳይሆን፣ ግብረገባዊ ግዴታቸውን ሊያውቁ በሚችሉበት ***አጠቃላይ መገለጥ*** ወይም የተፈጥሮ ሕግ ነው::



በአጠቃላይ ብሉያት እግዚአብሔር በልዩ መንገድ የገለጣቸው ትእዛዛት፣ ከተፈጥሮ ሕግ ጋር የሚቃረኑ እንዳልሆኑ (ወይም እንደሚጣጣሙ) የሚገልጽ ነው::

## ሕግጋቱ የብሉያት ሥነ ምግባር መሠረት ናቸው

የብሉይ ኪዳን ሥነ ምግባር መሠረት ያደረገው በእግዚአብሔር ሕግጋት ላይ ነው:: አንዳንድ ምሁራን ሕግ የሚለውን ቃል የሚጠቀሙት ዐሥርቱ ትእዛዛትን በሚያመለክት መንገድ ብቻ ነው (ዘፀአት 20÷1-17፤ ዘዳግም 5÷1-21):: እኛ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሕግ የሚለውን ቃል የምንጠቀመው ብሔረ ኦሪትን (ፔንታቱክን)[3] በሚያሳይ መልኩ ነው፤ በተለይ በዚህ ምዕራፍ የሚከተሉትን ክፍሎች በሚያሳይ መልኩ ነው ዘፀአት 20-40፤ ዘሌዋውያን 5፤ ዘዳግም 5-30::

እስራኤል የምትተዳደርበት ሕግ በሦስት ዐበይት ክፍሎች ይከፈላሉ፤ ይኸውም:-

1. ***ግብረገባዊ ሕግ (Moral Law)***፣
2. ማኅበራዊ ግንኙነቶችንና አስተዳደራዊ ጉዳዮችን የሚመለከተው ***ሕዝባዊ ሕግ (Civil Law)***፣
3. እስራኤል ያህዌን እንዴት ማምለክ እንዳለባት የሚገልጸው ***የሥርዐት አምልኮ ሕግ (Ceremonial Law)***ናቸው::

ሊቃውንት የብሉያት ሥነ ምግባር መሠረት ያደረገው፣ ግብረገባዊ ሕጉንና ሕዝባዊ ሕጉን እንደ ሆነ ይስማማሉ:: የሥርዐት አምልኮ ሕግ፣ ሃይማኖታዊ ሥርዐቶች እንዴት መሆን እንዳለባቸው የሚገልጽ እንጂ፣ ከሥነ ምግባር ጋር የሚያያዝ አይደለም::

የብሉያት ሥነ ምግባር መታየት ያለበት ከሕጉ አንጻር ብቻ ነው:: ከቅኔ መጻሕፍት መኻል በተለይ መጽሐፈ መዝሙራት (መዝሙረ ዳዊት) አምልኮተ እግዚአብሔር የሚቀርብበት ዋነኛ ምክንያት፣ እግዚአብሔር ራሱን በሕጉ አማካይነት በመግለጡ እንደ ሆነ ያስተምራል:: የቅኔ መጻሕፍት የሕጉን አስፈላጊነት ለተቀረው ዓለም በሚመች መልኩ የሚገልጹ (የሚያቀርቡ) ናቸው:: ነቢያት በእስራኤል ላይ በሚበይኑት ብያኔ መሠረት የሚሆናቸው ሕጉ ነው::

---

[3] የብሉይ ኪዳን የመጀመሪያዎቹ አምስት መጻሕፍት ብሔረ ኦሪት፣ ፔንታቱክ፣ የሕግ መጻሕፍት ወዘተ በመባል ይጠራሉ::

ነቢያት የሕጉ ሰባኪያንና ጉብኞች (ጠባቂዎች) ናቸው:: በሕጉ ላይ የተቀመጠውን አጠቃላይ መርሖ ያስተምራሉ፤ የብልጽግናንም ሆነ የድኽነትን የመንሥኤና የተግብሮት ግንኙነት ይተነትናሉ (ዘዳግም 27-30)::

በብሉይ ኪዳን እስራኤል በእግዚአብሔር አገዛዝ ሥር የምትተዳደር አምላክ ገዝ (Theocratic)[4] አገር ነች:: በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔር ሕግ የምድሪቱም ሕግ ነው:: ግብረገባዊ ሕግጋቶችም የሚቀዱት ከዚሁ ሕግ ነው:: የዛሬዪቱ ቤተ ክርስቲያን፣ እንደ እስራኤል በሕዝባዊ ሕጉ (Civil Law) እንዲሁም በሥርዐተ አምልኮ ሕጉ (Ceremonial Law) ሥር አይደለችም:: ነገር ግን እነዚህ ሕጎች ሁሉ መሠረት ባደረጉበት ግብረገባዊ ሕግጋት (Moral Law) ሥር እንጂ::

## የብሉያት ሥነ ምግባር
## ቅድስናን መሠረት ያደረገ ነው

የብሉያት ሥነ ምግባር መሠረት ያደረገው በቅድስና ላይ ነው:: ቅዱስ የሚለው የአማርኛ ቃል፣ "ቋዶሽ" ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል ጋር አቻ ትርጉም አለው፤ ትርጕሙም፣ "መለየት" ወይም "የተለየ" ማለት ነው:: ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን፣ "መቀደስ" (Sanctification) ለሚለው ዘር አንቀጽ መሠረታዊ ሐሳብ ነው:: እስራኤል እንደ ሕዝብ የእግዚአብሔርን ባሕርይ በአምልኮዋ፣ በማኅበራዊ ግንኙነቷና በአስተዳደሯ ታንጸባርቅ ዘንድ ለእግዚአብሔር ተለይታለች:: እግዚአብሔር ሕጉን ለእስራኤል የሰጠበት ቀዳማይ ዐላማ፣ እስራኤልን ከአረማውያን ጐረቤቶቿ ለመለየት (የተለየች ለማድረግ) ነበር፣ "እናንተ ለእኔ የመንግሥት ካህናት የተቀደሰ ሕዝብ ትሆናላችሁ..." (ዘፀአት 19÷6):: እስራኤል ለእግዚአብሔር መለያቷን የሚያበሥሩት በርካታ ትእዛዛት የሚገኙት በዘዳግም መጽሐፍ ሲሆን፣ ሕጉም በእስራኤልና በጥንት ቅርብ ምሥራቅ አገሮች በሚገኙ የእስራኤል ጐረቤቶች መኻል የመለያ አጥር ነው:: ከዚህ በመቀጠል የምናቀርባቸው አስረጆች ይህንኑ የሚያሳዩ ናቸው::

1. ዘዳግም 17÷16-17 የእስራኤል ነገሥታት የነጋሢነታቸው ክልል እምን ድረስ እንደ ሆነ የሚያመለክት ክፍል ነው:: ይኸውም ንጉሡ ከፍተኛ ሀብትና የጦር ኀይል ማከማቸት እንደሌለበት እንዲሁም እስራኤልን ለመጠበቅ ከሌሎች አሕዛብ መንግሥታት ጋር መተባበር እንደማይገባው (ከአሕዛብ

---

[4] የጥንቷ እስራኤል ትተዳደርበት የነበረው ሕዝባዊና ሥርዐተ አምልኮ ሕግ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስለነበር፣ አምላክ ገዝ (Theocratic) አገር ትባል ነበር:: እንደ ኢራንና ሳውዲ ሀረብያ ያሉ እስላማዊ አገሮች ሕዝባዊና ሥርዐተ አምልኮ ሕጋቸው የእግዚአብሔር ቃል ነው በሚሉት ከቍርዓን የተቀዳ ስለሆነ፣ አምላክ ገዝ መንግሥታት ተብለው ይጠራሉ::



ሴቶች ጋር በጋብቻ መጣመር እንደሌለበት) ያዛል:: የዚህ ሕግ መሻር እስራኤል በእግዚአብሔር ላይ ያላትን ጥገኝነት (ታማኝነት) ያዳክመዋል:: የእስራኤል ነገሥታት መታመን የሚኖርባቸው በልዑል እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ይህም ሁኔታ ጐረቤቶቿ፣ ያህዌ እንደ እነርሱ አማልክት ጣዖት እንዳልሆነ የሚያስገነዝባቸው ነው:: ምክንያቱም ንጉሥ የልዑል እግዚአብሔር አገልጋይ ነው::

2. ዘዳግም 21÷10-14 በጦርነት ጊዜ የሚማረኩ ሴቶች እንዴት መያዝ እንዳለባቸው የሚገልጸው ሕግ፣ በዚህም ረገድ እስራኤል ከጐረቤቶችዋ የተለየች እንደ ሆነች አመላካች ነው:: በጥንቱ ዓለም በምርኮ የሚወሰዱ ሴቶች፣ ከፍተኛ የሆነ የወሲብ ጥቃት ይደርስባቸው ነበር:: እስራኤል ግን ሰብአዊነት በሞላበት ርኅራኄ እንድትይዛቸው ያህዌ ያዛል:: እስራኤላውያን የተማረኩትን ሴቶች የማግባት ፍላጎት ካላቸው፣ በሥርዐቱ የሕግ ሚስቶቻቸው ሊያረጓቸው ይችላሉ፤ ነገር ግን ሕጉ ምርኮኞችን ባሪያ አድርጎ መሸጥ በጥብቅ ይከለክላል:: በአጠቃላይ ሕጉ ምርኮኞች የወሲብ ጥቃት እንዳይደርስባቸው እንዲሁም ባሪያ በመሆን ሊደርስባቸው ከሚችለው የሥራ ጫና ይታደጋቸዋል::

3. ዘሌዋውያን 25÷25-29:35-43፤ ዘዳግም 15÷1-11 ከጥንቱ ዓለም ጋር ሲነጻጸር የእስራኤል የባሪያ አያያዝ ሥርዐት ሰብአዊነትን የተሞላ ነበር:: ባሮች ከስድስት ዓመት አገልግሎት በኋላ ዐርነት ይወጣሉ (በፈቃዳቸው አብረው ለመኖር እስካልወሰኑ ድረስ):: ዐርነት በሚወጡበትም ጊዜ፣ ለመቋቋሚያ የሚሆናቸውን ንብረት አሳዳሪዎቻቸው እንዲሰጧቸው ሕጉ ያዛል (ዘዳ 15÷12-18):: በምድሪቱ ላይ የሚገኙትንም ድኾች በተመለከተ ሕጉ ከዚህ ጋር ተዛማጅነት አለው (ዘሌዋውያን 25÷25-29:35-34፤ ዘዳግም 15÷1- 11)::

4. ዘዳግም 18÷9-13 እስራኤል ለእግዚአብሔር መለየቷን ከሚያሳዩ ምግባሮች መኻል አንዱ፣ ለእግዚአብሔር የምታቀርበው አምልኮ ነው:: ሕጉ እስራኤል የከነዓናውያን ባዕድ አምልኮ የሚያዘውን ትእዛዝ እንዳትከተል በጽኑ ይከለክላል (ለምሳሌ:- ጥንቈላ፣ ኮከብ ቈጠራ፣ መተት፣ አስማት ወዘተ)::

5. ዘፀአት 20÷1-6 ከዐሥርቱ ትእዛዛት (ከግብረገባዊ ሕግጋት) መኻል የመጀመሪያዎቹ ሕግጋት ጣዖታትን ማምለክ በጽኑ የሚቃወሙ ናቸው:: በሕጉ ውስጥ የሚገኙት ሌሎች ትእዛዛት ደግሞ የጐረቤቶቿን አምልኮተ ጣዖት ልምምዶችን የሚያወግዙ ናቸው:: ለምሳሌ የአሮን ልጆች በመገናኛው

ድንኳን ውስጥ፣ "ባልተፈቀደ እሳት" መሥዋዕት በማቅረባቸው እግዚአብሔር እንደ ቀሠፋቸው እንመለከታለን (ዘሌዋውያን 10÷1-5):: ምሁራን ይህን ክፍል በተመለከተ የተለያየ ትንተና ቢኖራቸውም፣ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያለውና ከክፍሉ ትምህርት ጋር የሚጣጣመው፣ እነዚህ ሰዎች ባዕድ የሆነ ሥርዐተ አምልኮን፣ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ መፈጸማቸው የመቀሠፋቸው ምክንያት ሊሆን ይችላል የሚለው ነው:: ልክ እንደዚሁ ሁሉ፣ "ጠቦት ፍየልን በእናቱ ወተት አትቀቅል" (ዘፀአት 23÷19) የሚለው ትእዛዝ ጤና ነክ ሳይሆን፣ የከነዓናውያንን የጣዖት አምልኮ ሥርዐት ስለሚያመለክት ነው:: በከነዓናውያን አምላክ በዓል አምልኮተ ሥርዐት ወቅት ወሲባዊ ግንኙነት ማድረግ የአምልኮ ሥርዐቱ አንድ ክፍል ነበር፤ ይህ ዐይነቱ ወሲባዊ ግንኙነት በሕጉ ተወግዞአል (ዘሌዋውያን 18፤ ዘኊልቁ 25÷1-3):: በአጠቃላይ የብሉያት ሥነ ምግባር መሠረት ያደረገው እስራኤል ለእግዚአብሔር በመለየቷ ላይ ነው:: ለዚህ ነው እስራኤል እንደ ተቀሩት አሕዛብ ንጉሥ መለመኗ (1ሳሙኤል 8) የንጉሥ ካህንና ቅዱስ ሕዝብ እንድትሆን የተፈለገበትን የእግዚአብሔር ዕቅድ ያበላሸው::

እስራኤል ለሕጉ እንድትታዘዝ የመጠየቁ ምክንያት፣ ለእግዚአብሔር መለየቷ ነው:: መታዘዟ ብቻ እንደ መጨረሻ ግብ የሚወሰድ አይደለም፤ ነገር ግን መታዘዟ ራሱ *ለእግዚአብሔር ያላትን ታማኝነት* (loyalty) የሚያሳይ ነው:: በብሉያት ሥነ ምግባር ውስጥ አጽንዖት ያገኘው ይህ ጉዳይ ከጥንቱ ዓለም ሕግ የተለየ እንዲሆን ያደርገዋል:: ሕጉ ከጥንቱ ዓለም ሕግ ጋር በብዙ መልኩ ተመሳሳይነት ቢኖረውም (ለምሳሌ፡- ከባቢሎናውያኑ የሐሙራቢ ሕግ) እግዚአብሔርን ማእከል ማድረጉ ከሌሎቹ ሕግጋት እንዲለይ ያደርጉታል፤ ይህም ሕጉን ሳይሆን ሕጉ ማእከል ያደረገውን አምላክ መታዘዝን ነው:: ትኩረቱም ሕጉን መታዘዝ ሳይሆን፣ የሕጉ ጠንሳሽ የሆነውን እግዚአብሔርን መታዘዝን ላይ የምናገኛቸው ዐረፍተ ነገሮች፣ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት ዐርነት እንዳወጣቸው የሚያስታውሱ ናቸው:: ይህ እግዚአብሔር ባለውለታቸው እንደ ሆነ የሚገልጹት እነዚህ ዐረፍተ ነገሮች ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ለምን ታማኝ መሆን እንዳለበት የሚያስረዱ ናቸው (ዘፀ 20÷2-3)::

ቀዳማይ የሚባሉት የሕግ መጻሕፍት ማለትም ኦሪት ዘፀአትና ኦሪት ዘዳግም እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለው *መግቦት* (Provision) እንዲታዘዙት ከሰጣቸው ሕግ ቀዳሚ እንደ ሆነ ያስረዳሉ:: ኦሪት ዘፀአት ከምዕራፍ አንድ እስከ ምዕራፍ ዐሥራ ስምንት ያለው ክፍል፣ እግዚአብሔር በመግቦቱ የራሱ የሆነውን ሕዝብ ከግብፅ ባርነት እንዴት ዐርነት እንዳወጣቸውና ራሳቸውን የቻሉ *ሕዝቦች* (nation) እንዳደረጋቸው በዝርዝር ይገልጻል:: ትድግናውንና መግቦቱን ካሳያቸው በኋላ፣ ይታዘዙት ዘንድ ሕግን እንደ ሰጣቸው የኦሪት ዘፀአት መጽሐፍ በስፋት ያስተምራል:: እርሱ ለሕዝቡ ያለውን



ታማኝነት በሥራ እንዳሳየ፣ እነርሱም ለአምላካቸው ያላቸውን ታማኝነት በሥራ ያሳዩ ዘንድ፣ ሊታዘዙት የሚገባቸውን ሕግ ሰጣቸው:: በሌላ አነጋገር እስራኤል ከሕግ በፊት ያየችው አምላኳ እግዚአብሔርን ነው:: ልክ እንደዚሁ ሁሉ፣ በኦሪት ዘዳግም መጽሐፍ በመጀመሪያዎቹ አራት ምዕራፎች፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን መግቦት ከዘረዘሩ እንዲሁም ማንነቱን በግልጽ ካሳዩ በኋላ፣ በተቀሩት ክፍሎች ሕግጋቱን ይዘረዝራሉ:: በአጠቃላይ በዘዳግም መጽሐፍ የምንማረው ሕዝቡ ለአምላኩ ያለው ታማኝነትና እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለው ታማኝነት ተያያዥ ጉዳዮች እንደ ሆኑ፣ ለእርሱ ያላቸው ታማኝነትም ከሚሰጣቸው ሕግ እንደሚቀድም ወይም ሕጉ የእግዚአብሔርን ታማኝነት መሠረት ያደረገ መሆኑን የሚያስረዳ ነው::

የኦሪት ዘዳግም መጽሐፍ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ሊኖረው ስለሚገባው ታማኝነት፣ ለእግዚአብሔር ከመታዘዙ ጋር የተቈራኘ መሆኑን ያስተምራል:: በኦሪት ዘዳግም የምናገኘው የእግዚአብሔርና የሕዝቡ የኪዳን ግንኙነት፣ በጥንቱ ዓለም ተዘውትሮ ይደረግ የነበረው ዐይነት የኪዳን ግንኙነት ነው (ይህ ኪዳን የሱዚራዊያን ኪዳን ወይም ስምምነት "Suzerainty treaty" በመባል ይታወቃል)[5]:: ይህ ዐይነቱ ኪዳን በአንድ ንጉሥና ንጉሡ በሚገዛው ሕዝብ መካከል የሚደረግና ንጉሡ ከሕዝቡ የሚጠበቀውን (የሚፈለገውን) ነገር የሚዘረዝር የኪዳን ዐይነት ነው:: ይህ ኪዳን ለንጉሡ ታማኝ መሆንና ለሕግጋቱ መታዘዝን የሚገልጽ የኪዳን ዐይነት ነው:: ኦሪት ዘዳግም መጽሐፍ በእንዲህ ዐይነት ኪዳን የተዋቀረ መሆኑ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ለእግዚአብሔር ሊኖረው የሚገባው ታማኝነት፣ ሕጉን ከመታዘዝ ጋር የተቈራኘ መሆኑን አመልካች ነው::

## የብሉያት ሥነ ምግባር ማኅበራዊ ጕን

እግዚአብሔር እስራኤልን የንጉሥ ካህንና ቅዱስ ሕዝብ አድርጐ መምረጡ፣ እስራኤል ከሌሎች መንግሥታት ፍጹም ልዩ ያደርጋታል:: ሕጉም የባሕርይ ለውጥ ለማምጣት ኅብረተሰቡን ይቀርጻል:: ይህም ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዲያንጸባርቁ ያደርጋቸዋል:: ሕጉም ማኅበረሰቡንና የግለሰቡን ሕይወት ሊቀርጽ በሚችል መልክ የተዘጋጀ ነው::

የማኅበረሰቡን ግንኙነትና አስተዳደራዊ ሥርዐት የሚወስነው ሕዝባዊ ሕግ ነው:: ይህ ሕግ ኅብረተሰቡን ሥርዐት ባለው መንገድ የሚያዋቅርና ፍትሕ እንዲሰፍን ዕገዛ የሚያደርግ ነው (ለምሳሌ ዘፀአት 21-23፤ በተለይ ደግሞ 20÷12-17፤ ዘሌዋውያን 18-20:25፤ ዘዳግም 19-25 ይመለከቷል):: እስራኤላውያን

---

[5] ስለ ሱዘሬውያን ኪዳን ይበልጥ ለመረዳት Meredith Kline, *The Structure of the Biblical Authority* (Grand Rapids: Eerdmans, 1972) ይመልከቱ::

በተስፋዪቱ ምድር በሚኖሩበት ጊዜ ለእግዚአብሔር እንዳይታዘዙ ፈተና የሆነባቸው፣ የንዋይ ጉዳይ ስለ ነበር ሕዝባዊ ሕጉ ንብረት አያያዝና ስለ ገንዘብ አጠቃቀም ሰፊ ቦታ ሰጥቶታል:: የሥርዐት አምልኮ ሕጉም በዳበረ ሁኔታ በዝርዝር የቀረበ ነው (ለምሳሌ ዘፀአት 24-40፤ ዘሌዋውያን 1-10:22-23፤ ዘዳግም 5-16)::

የነቢያት መጻሕፍትም ለብሉያት ሥነ ምግባር የራሱ የሆነ ድርሻ አለው:: ነቢያቱ የማኅበራዊ ሕጉ ሲጣስ፣ እስራኤልን ይኰንኑ ነበር:: ጭቆና፣ የፍትሕ መጓደል፣ የድኾች መበዝበዝ ወዘተ የሕጉን መሻር እንዲሁም ከእርሱ ተቃራኒ የሆነውን አካሄድ መከተላቸውን ያሳያል (ለምሳሌ አሞጽ 4÷1፤ 5÷11-13፤ ሚክያስ 2÷2፤ ዕንባቆም 1÷4):: የነቢያቱ ግብ እስራኤል ሥርዐት የሰፈነባትና እግዚአብሔር የሚመለከባት እንድትሆን ነው:: ለዚህ ዐይነተኛው ምሳሌ:- በትንቢተ ኢሳይያስ ውስጥ የሚገኙት የአገልጋይ መዝሙሮች በመባል የሚታወቁት ክፍሎች ናቸው (ምዕራፍ 42:49:50 እንዲሁም 53):: በተለይ ምዕራፍ 42÷1-4 ያለው ክፍል አገልጋይ የተባለው መሲሕ፣ ፍትሕና ርትዕን እንዲሁም ሥርዐት የሞላበትን ማኅበረሰብ እንደሚያመጣ ይገልጻል:: እስራኤል ማምጣት ያቃታትን ይህን ሥርዐት መሲሑ ያመጣል::

ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ ሃያ አምስት ስለ መሬትና የንብረት አያያዝ ሕግ በዝርዝር የያዘ ነው:: ለብሉይ ኪዳን የግብርና ምጣኔ ሀብት፣ መሬት መሠረታዊው ጉዳይ ስለነበር፣ ይህ ሕግ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው:: ክፍሉ መሠረታዊ የሆኑ ርእሰ ጉዳዮችን ይተነትናል:: ከእነዚህም ውስጥ የሰባተኛው ዓመት ዕረፍት (ዘሌ 25÷1-7) የኢዮቤልዩ ዓመት (25÷8-24:35-46) እንዲሁም የመቤዠት ዓመት (25÷25-34:47-55) ይገኙበታል:: የሰባተኛው ዓመት ዕረፍት፣ በየሰባት ዓመቱ መሬቱ ሳይዘራበት ጦሙን እንዲያድር ያዛል:: ይህ እስራኤል ዘርን ባልዘራችበት ወቅት እንኳ እግዚአብሔር አጥግቦ እንደሚያሳድራት፣ ለዕለት ምግቧ እንኳ፣ እግዚአብሔርን እንደምትታመን ለጉረቤቶችዋ የሚያስገነዝብ ነው::

የኢዮቤልዩ ሕግ (25÷8-24:35-46) ከሌሎቹም ይልቅ ሥር ነቀል የሆነ ሕግ ነው፤ ይኸውም በየሃምሳ ዓመቱ መሬት ለመጀመሪያ ባለቤቱ እንዲመለስ ያዛል፤ ባሮች ሁሉ ዐርነት ይወጣሉ:: የኢዮቤልዩ ሕግ ሰዎች ሁሉ የመሬት ባለቤት እንዲሆኑና በመሬታቸውም ላይ እንዲኖሩ ዐላማ ያደረገ ሕግ ነው:: ግብርናን መተዳደሪያው ላደረገ ማኅበረሰብ ይህ ዋነኛ ነገር ነው:: ይህ ሕግ መሬት የእግዚአብሔር ስለሆነ በቋሚነት ሊገዛና ሊሸጥ እንደማይችል የሚገልጽ ሕግ ነው (25÷23)::

የመቤዠት ሕግ (25÷25-34:47-55) አንድ ሰው በችግር ምክንያት መሬቱን ቢሸጥ ወይም ራሱን ለባርነት ቢያስገዛ፣ የቅርብ ዘመዱ መሬቱን በግዢ



ሊያስመልስለት ወይም ከተገዛለት ባርነት ይቤዠው ዘንድ ግድ ይላል:: ነገር ግን ይህ መሆን ሳይቻል ቢቀርና ግለሰቡ ራሱን ለባርነት ቢያስገዛና መሬቱን ቢሸጥ፣ ከላይ በተዘረዘሩት ሕጎች ራሱንም ሆነ መሬቱን ማስመለስ የሚቻልበት ሁኔታ (ዕድል) አለው:: ይህ ሁኔታ ግለሰቡ ራሱን ችሎ እንዲሠራ የሚያግዝ እንዲሁም ባርነትን የሚኰንን ነው:: የመቤዠት ሕግ በመጽሐፈ ሩት ውስጥ በግልጽ የሚታይ ነው:: ቦዔዝ ሩትን ማግባቱ ብቻ ሳይሆን የባልዋ ንብረት የሆነውን መቤዠት ይጠበቅበታል (የቅርብ ዘመድ የሆነ ሰው ልጅ ያልወለደችውን የዘመዱን መበለት ሊረዳት ይችላል)::

ድኾችን የሚረዳው ሌላው ሕግ የቃርሚያ ሕግ (ዘሌዋውያን 19÷9-10) በመባል የሚታወቀው ነው:: በመከር ጊዜ ገበሬው ሰብሉን አንድ ጊዜ ብቻ እንዲሰበስበው በማድረግ፣ የተቀረውን ክፍል (ምርት) ድኾችና መጻተኞች እንዲቃርሙት ያደርጋል:: ይህ ድኾች "ሠርተው የሚረዱበትን" ሁኔታ የሚፈጥር ነው:: ይህ "የምግብ ለሥራ" የርዳታ አካሄድ በመጽሐፈ ሩት ውስጥ ተጠቅሶ ይገኛል፤ ቦዔዝ መበለቲቱ ሩት ከዕርሻው በቃረመችው ቃርሚያ ራሷንና ዐማቷን እንድትረዳ አድርጓታል::

ሕዝባዊ ሕጉ የሚያዛቸው ሌሎች በርካታ ሕጎች አሉ፤ ከእነዚህም ውስጥ በአራጣ ያለማበደርን (ዘፀ 22÷25፤ ዘሌ 25÷35-37) ጉቦ በመቀበል ጠማማ ፍርድ ያለመፍረድን (ዘፀአት 23÷1-2፤ ዘዳግም 18-20) እንዲሁም ዘፀአት 20÷16 ላይ የሰፈረው ዘጠነኛ ሕግ በሐሰት መመስከርን በጽኑ ያወግዛል:: ሕጉ የግለሰብን ባሕርይ እንዲሁም የማኅበረሰብን አወቃቀር ይወስነዋል፤ ይኸውም እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ያላትን የቃል ኪዳን ግንኙነት መሠረት ያደረገና እግዚአብሔር በእስራኤል መካከል እንደሚኖር አመልካች ሰንደቅ ነው::

## የሐዲሳት ሥነ ምግባር

የአዲስ ኪዳኑ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከሕግ በታች አይደለም:: የብሉይ ኪዳኑ ሥርዐተ አምልኮ ሕግ በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ የተሻረ ሲሆን፣ ሕዝባዊ ሕጉም ከአዲስ ኪዳኑ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በቀጥታ አይያያዝም፤ ምክንያቱም በአዲስ ኪዳን የሚገኘው የእግዚአብሔር ሕዝብ ከነገድና ከቋንቋ የተሰበሰበና በየትኛውም ክፍለ ዓለም የሚገኙ እንጂ፣ እንደ ብሉይ ኪዳኗ እስራኤል *አምላክ ገዝ* የሆነ አስተዳደር የሚያስፈልጋት አይደለችም:: በአዲስ ኪዳን አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የሚፈጥርበት መንገድ ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውም ተልእኮ ተለውጦአል:: ለሕግጋቱ ምስክሮች በመሆን እግዚአብሔርን ማክበር የሚለው ዕንሰ ሐሳብ የሁለቱም ኪዳኖች የጋራ ነጥብ ሲሆን፣ ተፈጻሚ በሚሆንበት አካሄድ ላይ ግን ልዩነት አለ:: እስራኤል በሕጉ ሥር የምትገኝ የእግዚአብሔር መንግሥት ነች:: ቤተ

ክርስቲያን ግን ከዘር፣ ከቋንቋ ወዘተ የተሰበሰቡ፣ ብሔራዊ ክልል የሌላቸው ሰዎች ስብስብ ነች። እንደ ብሉይ ኪዳኗ እስራኤል ቤተ ክርስቲያንም የእግዚአብሔርን ሕያውነት የምትመሰክር መሲሓዊ ማኀበረ ሰብ ነች። ነገር ግን ለቤተ ክርስቲያን የተሰጣት ትእዛዝ ቤተ ክርስቲያን እንደ እስራኤል አስተዳደራዊ መዋቅር እንዲኖራት የሚፈልግ አይደለም። ይህ ማለት ወንጌል ማኅበራዊ አስተምህሮ የለውም ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን የብሉይ ኪዳን ዐይነት አስተዳደራዊ መዋቅር እንዲኖራት ሙከራ አያደርግም ማለት ነው።

ቤተ ክርስቲያን በማኅበረሰቡ ውስጥ መዋቅራዊ ለውጥ እንዲመጣ ሙከራ ታደርጋለች። እንዲያውም ይህ ስለእግዚአብሔር መንግሥት የተሰጠው ትምህርት አንዱ ክፍል ነው። የብሉይ ኪዳኑ የእግዚአብሔር መንግሥት ግላዊም ሆነ ማኅበራዊ ገጽታ ነበረው። ኢየሱስ፣ "መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና" ብሎ ሲሰብክ፣ የብሉይ ኪዳን ስለእግዚአብሔር መንግሥት የሚያስተምረው ትምህርት፣ መሠረታዊ በሆነ መልኩ መለወጡን አመላካች አይደለም። መልእክቱን ያደምጡ የነበሩት ደቀ መዛሙርቱና ሌሎች ሰዎች ስለእግዚአብሔር መንግሥት የሚሰጠውን ትምህርት ይሰሙ የነበረው፣ በብሉይ ኪዳን ዐውድ (መቸት) ውስጥ ነበርና። ወደፊት የእግዚአብሔር መንግሥት ሙሉ ለሙሉ (በሙላት) ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ፣ ግላዊና ማኅበራዊ ገጽታ ይኖረዋል።

የብሉይ ኪዳን ንባባት ስለ ሚመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት የነበራቸው ገለጻ ማኅበራዊ ነበር፣ ይኸውም መጻኢው የእግዚአብሔር መንግሥት ሥርዐት የሰፈነበት፣ ከኢፍትሓዊነት፣ ከጭቆናና ድኾችን ከመበዝበዝ ፍጹም የጠራ ይሆናል። ለኢፍትሓዊነት ምክንያት የሚሆነው አስተዳደር (መዋቅር) ፈጽሞ ይወገዳል። የእግዚአብሔር መንግሥት ጅማሬው ማኅበራዊ ገጽታ ካለውና በፍጻሜው ደግሞ ይህ ማኅበራዊ ገጽታ አብቦ ፍሬ የሚያፈራበት (ወደ ፍጽምና የሚደረሰበት) ከሆነ፣ በጅማሬውና በፍጻሜው ዘመን መኻል ያለው ይህ ጊዜ፣ ማኅበራዊ ገጽታ እንዳለው ማሰብ ፍጽም ትክክል ነው።

ሐዲሳት የብሉያትን ያህል ለማኅበራዊ ገጽታ ቦታ አይሰጡም ማለት፣ ወንጌል ማኅበራዊ ትምህርት የለውም ማለት አይደለም።

ከዚህ በመቀጠል የሐዲሳትን ሥነ ምግባር ዐበይት ትምህርቶች በቅኝት መልክ እናያቸዋለን። የአዲስ ኪዳንን ነገረ መለኮት ሁሉ ተንትኖ ማስቀመጥ አስቸጋሪ እንደ ሆነ ሁሉ፣ የሐዲሳትንም ሥነ ምግባር በሙሉ መተንተን አስቸጋሪ ነው። ከዚህ በመቀጠል የምናቀርበው በሐዲሳት ሥነ ምግባር ውስጥ ትኩረት ያገኙትን የሥነ ምግባር ትምህርቶች ነው።



# የሐዲሳት ሥነ ምግባር
# መርሖን መሠረት ያደረገ ነው

በውጤት ላይ ሳይሆን በመርሖ ላይ መሠረት ያደረገው ክርስቲያናዊ አስተምህሮ የአዲስ ኪዳኑ ሥነ ምግባር መሠረት ነው። ኢየሱስ ፈሪሳውያን ትክክል ባልሆነ መንገድ የተረዱትን ሕግ ሲያብራራላቸውና እንዴት ከሕይወት ጋር መዛመድ እንደሚችል ሲያስረዳቸው ይታያል። ለምሳሌ ኢየሱስ በተራራው ስብከቱ ላይ (ማቴ 5-7) ሕግን ሲቃወም አንመለከትም፤ የፈሪሳውያኑን የአፈታት መንገድና ከሕይወት ጋር የሚያዛምዱበትን ስልት እንጂ። ኢየሱስ በሕጉ የተቀመጡት መስፈርቶች በተቀረው ሕዝብ ላይ ተፈጻሚ መሆን ያለበትን ያህል በፈሪሳውያኑም ምግባርና ዐላማ ላይ ተፈጻሚ መሆን እንዳለበት አስረድቶአል። ለምሳሌ ኢየሱስ እጁ የሰለለችበት ሰው በሰንበት ቀን በፈወሰ ጊዜ (ማቴ 12÷1-14) ተከታዮቹ ጌታ ሰንበትን የሻረ ስለመሰላቸው ሰንበትን ሽረሃል ሲሉ ከሰሱት። ኢየሱስ የሰንበትን ትእዛዝ አልታቀወመም፤ ነገር ግን ፈሪሳውያኑ በተሳሳተ መንገድ በመረዳታቸው አዘነ። ኢየሱስ የዕብራውያንን ሃይማኖታዊ ትውፊት ምን ያህል ጉዳት እንደሚያስከትል በምሳሌ አስረዳቸው። ለምሳሌ በአዲስ ኪዳን ዘመን ቍርባን በገንዘብ ተገዝቶ የሚቀርብ መሥዋዕት ስለነበር፣ ከዚህ የተነሣ ገንዘብ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ፣ ለምንም ነገር መዋል የማይገባው ነገር ነው የሚል አመለካከት ነበራቸው። ስለዚህ አንድ ሰው ቤተ ሰቦቹን ለመርዳት ገንዘብ መስጠት የለበትም። ኢየሱስ ፈሪሳውያኑ ሕጉን ትክክል ባልሆነ መንገድ በመተርጐማቸው አዘውትሮ ሲገሥጻቸው ይታያል።

የሐዋርያቱም ትምህርት መርሖ ተኰር መሆኑ፣ ከኢየሱስ ትምህርት ጋር አንድ ያደርገዋል። ሐዋርያቱ ይገጥማቸው የነበረው እሰጣገባ እንደ ኢየሱስ ከፈሪሳውያኑ ጋር ሳይሆን፣ ከወንጌል ትምህርት ካፈነገጡ መናፍቃዊ እንቅስቃሴዎች ጋር ነበር። ለምሳሌ ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜና በገላትያ ያገኛቸውን፣ "ሐሰተኛ ወንድሞች" ("ሐሰተኛ ወንድሞች" ከይሁዲ እምነት ወደ ክርስትና የመጡ፣ ነገር ግን ክርስቶስን በማመን ብቻ ሳይሆን፣ የብሉይ ኪዳን ሥርዐተ አምልኮ በማክበር ደኅንነት ይገኛል ብለው ያስተምሩ የነበሩ ሰዎች ናቸው) ቅድሚያ በመስጠት የሚያስረዳቸው፣ ክርስቲያኖች ሊከተሉት የሚገባቸውን ክርስቲያናዊ የሥነ ምግባር ሕይወት ያውቁት ዘንድ ነው፡ ይኸውም ቅድስና በሰዎች ጥረት ብቻ እንደማይገኝ፤ እውነተኛ ቅድስና ሊገኝ የሚችለው፣ በእምነት አማካይነት በጸጋ ነው። በዚህም መልክ ብቻ ነው ሰዎች ወደ ዘላለማዊ ሕይወት ሊመጡ የሚችሉት (ገላ 3÷1-3)። ሐዋርያው በቈላስይስ በነበረው ቆይታ ደግሞ፣ ኖስቲሲዝም ከሚባለው መናፍቃዊ እንቅስቃሴ ጋር ሲፋጠጥ ይታያል። ይህ መናፍቃዊ ትምህርት ወደ መንፈሳዊ ፍጽምና መድረስ የሚቻለው፣ ብዙ ዕውቀት በማካበት ነው የሚል አስተምህሮ የሚያራምድ እንቅስቃሴ ነው። ሐዋርያው መንፈሳዊ ዕውቀት ሊመጣ የሚችለው፣ በዕውቀት ብቻ ሳይሆን፣ ኢየሱስ

ክርስቶስ በአማኙ ሕይወት ውስጥ በሚሠራው ሥራ እንደ ሆነ ያስረዳቸዋል (ቈላ 1÷27)፡፡ ሐዋርያው ቊርጥ ያለ የሥነ ምግባር መመሪያ በሌላቸው ጒዳዮች እንኳ (ሮሜ 14÷15፤ 1ቆሮ 8-10) "ደካሞችን ላለማሳዘን" የሚለውን መመሪያ ሲጠቀም ይታያል፡፡ በአጠቃላይ የሐዋርያቱ ትምህርት እንደ ኢየሱስ መርሖ ተኰር እንደ ሆነ ማስተዋል ይቻላል፡፡ እንዲያውም የሐዋርያቱ ትምህርት ከኢየሱስ ትምህርት በቀጥታ የተቀዳና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊከሠቱ ለሚችሉ ችግሮች ሁሉ መፍትሔ የሚሆን ነው፡፡

ይህ ጒዳይ በግልጥ የሚታየው በአንደኛ ቆሮንቶስ ላይ ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ጥቃቅን የሚባሉ ርእስ ጒዳዮችንም እንኳ የሚፈታው መርሖን መሠረት አድርጎ ነው፡፡ በአማኞች መካከል የተከሠተውን መከፋፈል (ምዕራፍ 1-4) ያስተማረው፣ በክርስቶስ አካል ውስጥ ያለውን አንድነት መርሖ አድርጎ ነው፡፡ ዘማዊነታቸውን ለማቅናት ደግሞ መርሖ ያደረገው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊኖር የሚገባውን የቅድስና መሠረት መመሪያ አድርጎ ነው (ምዕራፍ 5-6)፡፡ በጋብቻ መጣመርንና ሳያገቡ መኖርን ያስተማረው ደግሞ በማናቸውም ሁኔታ ውስጥ በመጠን መኖርን መሠረት አድርጎ ነው (ምዕራፍ 7)፡፡ ለጣዖት የተሰዋን ሥጋ መብላትን በተመለከተ (ምዕራፍ 8-10)፣ ደካማ ወንድሞችን ያለማሰናከል የሚለውን መርሖ ተጠቅሞአል፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊሆን የሚገባውን ሥርዐተ አምልኮና መንፈሳዊ ስጦታን በተመለከተ መርሖ ያደረገው (ምዕራፍ 12-14) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚካሄዱት ማናቸውም ነገሮች መካሄድ ያለባቸው በሥርዐት ነው የሚለውን መሠረት በማድረግ ነው፤ በዚህም የአምልኮው ተካፋዮች ሁሉ ይታነጻሉ፡፡ ጳውሎስ ተግባራዊ የሚያደርጋቸው መርሖች የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ቀድሞውንም የሚያውቋቸውና ኢየሱስ ካስተማራቸው መርሖች ጋር ተጣጥመው የሚሄዱ ናቸው፡፡

## በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ መኖር

በአዲስ ኪዳን፣ የሥነ ምግባር መርሖ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ሊከተሉት የሚገባ መርሖ ነው፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወትና በግብረ ገባዊ ሕይወት መካከል ያለው ልዩነት እንብዛም አይደለም፡፡ ግብረገባዊ ሕይወት አማኞች በቤተ ክርስቲያን ውስጥና በተቀረው ዓለም ውስጥ ያላቸውን ኀላፊነት ሲያሳይ፣ መንፈሳዊ ሕይወት ደግሞ ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡትን አምልኮ ያመለክታል፡፡ ከአዲስ ኪዳን ንባባት የምንማረው ቊም ነገር፣ እነዚህ ነገሮች እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚሄዱ ነገሮች መሆናቸውን ነው፤ ይኸውም ኢየሱስና ሐዋርያቱ በቅድሚያ የመንግሥትን ወንጌል ሰበኩ፣ ከዚያም በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ሊኖራቸው የሚገባውን ሥነ ምግባር አስተዋወቁ፡፡ ክርስትናን የተቀበለ ማንኛውም ሰው፣ ክርስቲያናዊ የሆነውን ሥነ ምግባር እንዲኖር ይጠበቅበታል፡፡



ይህን እውነት በግልጥ የምንማርበት ክፍል የማቴዎስ ወንጌል ነው፡፡ ከኢየሱስ ውልደትና ከአገልግሎት ዝግጅቱ በኋላ (ማቴ 1÷1-4÷11)፣ በግልጥ የሰበከው፣ "መንግሥተ ሰማይ ቀርባለች" (4÷17) የሚለውን ስብከተ ወንጌል ነው፡፡ የመጀመርያዎቹ ደቀ መዛሙርት ወደ እርሱ መጡ፣ ብዙ ሕዝብም እርሱን ይከተለው ጀመር (4÷23-25)፡፡ ብዙ ሕዝብ ከተከተለውና ትምህርቱ በስፋት ተቀባይነት ማግኘት ሲጀምር፣ "የተራራው ስብከት" (4-5) በመባል የሚያወቀውን ትምህርት አስተማረ፡፡ ይህ ክፍል በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች የሚጠበቅባቸውን ሥነ ምግባራዊ መስፈርት የሚዘረዝር ነው፡፡ በሮሜ መጽሐፍ ውስጥ የምናገኘው የመቀደስ ትምህርት (ምዕ 6-8፤ እንዲሁም ምዕ 12-15) ጽድቅ በእምነት ብቻ እንደሚገኝ ከተገለጸና ይህም ትምህርት ከተቃዋሚዎች ከለላ ካገኘ በኋላ የቀረበ ነው (ምዕ 1-5)፡፡ እንደ ጳውሎስ ትምህርት፣ ዳግም የተወለዱ ሰዎች ያላቸው የግብረገብ ደረጃ፣ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ከሚጠብቀው ሥነ ምግባር እጅግ የመጠቀ ነው፡፡

## የፍቅር ሥነ ምግባር

ፍቅር ማዕከላዊ ያልሆነበት ግብረገብ ለአዲስ ኪዳኑ ሥነ ምግባር ባዕድ ነው፡፡ ኢየሱስም ሆነ ሐዋርያቱ እግዚአብሔርንና ጐረቤትህን ውደድ የሚለው ትምህርት የሕግ ማእከላዊ ትምህርት እንደ ሆነ አስረድተዋል፣ "አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹምም ነፍስህ፣ በፍጹምም ኀይልህ ውደድ" (ዘዳ 6÷5)፡፡ ከደጉ ሳምራዊ ታሪክ (ሉቃ 10÷25-37) የምንማረው ክርስቲያንም ሆኑ ክርስቲያን ያልሆኑ ጐረቤቶቻችንን በሚያስፈልጋቸው ሁሉ መርዳት እንደሚጠበቅብን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ኢየሱስ "ሕግ ዐዋቂ" ለተባለው ሰው የመለሰው መልስ፣ እግዚአብሔርንና ባልንጀራን መውደድ ዋነኛ ነገር እንደ ሆነ የሚያስረዳ ነው (ሉቃ 10÷25-29፤ እንዲሁም ማቴ 10÷34-40 ያለውን ክፍል ይመለከቷል)፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ሕግ ሁሉ ፍቅር በሚባል ዐቢይ ርእስ ሥር እንደሚጠቃለል አስተምሮአል፤ ይኸውም ፍቅር ሕግን ሙሉ እንደሚያደርገው (ሮሜ 13÷8-10፤ ገላ 5÷14)፡፡

## የአዲስ ኪዳን ሥነ ምግባር ለድኾች ልዩ ቦታ አለው

በአዲስ ኪዳን ንባባት ውስጥ ድኾች ትልቅ ትኩረት አግኝተዋል፡፡ ኢየሱስ ብዙ ጊዜውን የሚያጠፋው ከደቀ መዛሙርቱም ይልቅ ኅብረተሰቡ ካገለላቸው ሰዎች ጋር ነበር፡፡ ድኾች በማንኛውም ኅብረተሰብ ውስጥ ዘወትር የሚገኙ ናቸው (ማቴ 26÷11)፡፡ ልንከባከባቸው እንጂ ልናገላቸው ግን አይገባም፡፡ በአዲስ ኪዳን ድኾች ወንጌልን ልዩ በሆነ መንገድ የተቀበሉ ሰዎች መሆናቸው ተጠቅሶአል (ማቴ 11÷5፤ ሉቃ 4÷18)፤ በዚህም በረከትን አግኝተዋል (ሉቃ 6÷20)፡፡ እንደ ወንጌላቱ ሁሉ፣ መልእክቶችም ድኾችን ስለመከባከብ ትልቅ ስፍራ ሰጥተዋል፤ በተለይም በቤተ

ክርስቲያን ውስጥ ለሚገኙ (ክርስቲያን ለሆኑ) ድኾች (ሮሜ 15÷26 2ቆሮ 8÷1-7፤ 9÷1-5፤ ያዕ 2÷1-13)።

ኢየሱስ ድኾችን መከባከብ አስፈላጊ መሆኑን ገልጾአል (ሉቃ 14÷12-14)። አንድ ሰው ባዘጋጀው ግብዣ ላይ እንዲታደሙ ሊጋብዝ የሚገባው ድኾችንና በኅብረተሰቡ ውስጥ የተናቁትን ሰዎች ነው። ሌሎች የኅብረተሰቡ አካላት ግን እንደ ተጋበዙ ሁሉ መጋበዝ ይችላሉ፤ ድኾች ግን "ብድር ከፋይ" ስላልሆኑ እነርሱን የሚጋብዝ ሰው እግዚአብሔር ዋጋውን እንደሚከፍለው የተረዳ ሰው ብቻ ነው (ሉቃ 14÷14)። ስለዚህ ለድኾች በቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ ቸርነት በማድረግ የእግዚአብሔርን ፍቅር ልናሳይ ይገባል። ቤተ ክርስቲያን ለድኾች ሊኖራት የሚገባው ፍቅር፣ እግዚአብሔር ለእግኞች ያለውን፣ በቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተገደበ ፍቅር አመላካች ሊሆን ይገባዋል።

## መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ሕይወት ውስጥ መኖሩ

የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች ትልቅ ትኩረት የሚሰጡት በቅድስና ለማደግ ራስን ለመንፈሳዊው ነገር ማስለመድ ዋነኛ ነገር መሆኑን ነው። ግሪኮቹ ደግሞ ግብረገብን ለመላበስ ዕውቀት ቀዳማይ ነገር ነው የሚል እምነት አላቸው። የአዲስ ኪዳን ሥነ ምግባር ግን እነዚህ ሁለት ነገሮች በራሳቸው በቂ እንዳልሆኑ ታሳቢ ያደረገ ነው። ከዚህ ይልቅ መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ሕይወት ውስጥ መኖሩ፣ አንድ ሰው መንፈሳዊ ብስለት እንዲኖረው ያደርገዋል። ይህ ትምህርት በወንጌላት ላይ የተጀመረና (ዮሐ 13-17) በመልእክቶች ውስጥ (በተለይ በጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ) የጐለበተ ትምህርት ነው። ለምሳሌ በሮሜ 8 ላይ መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዱ አማኝ ሕይወት ውስጥ የሚጫወተውን ሚና በስፋት ይተነትናል። መንፈስ ቅዱስ የሌለበት ሰው መንፈሳዊውን ነገር ተቀብሎ ከሕይወቱ ጋር ሊያዛምደው አይችልም (1ቆሮ 2÷14)። መንፈሳዊ ዕድገት ሊኖር የሚችለው፣ በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ ብቻ ነው (2ቆር 3÷18)። በመንፈስ የሚመሩ ብቻ፣ አዳማዊ ባሕርያቸውን በማሸነፍ መንፈሳዊ ፍሬ ማፍራት ይችላሉ (ገላ 5÷16:22-23)። አዲስ ኪዳን መንፈሳዊ ብስለት ሊመጣ የሚችለው፣ መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ሕይወት ውስጥ ከሚሠራው ሥራ የተነሣ እንደ ሆነ በግልጽ ያስተምራል።

## አሬቲክ ሥነ ምግባር

*አሬቲክ ሥነ ምግባር* በባሕርይ ቀረጻ ላይ ትኩረት የሚያደርግ የሥነ ምግባር ዘርፍ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ መርሖ ተኰር ቢሆንም፣ ለባሕርይ ቀረጻም ከፍተኛ ቦታ



ይሰጣል። ክርስቲያን በአስተሳሰቡ፣ በአነጋገሩና በምግባሩ ክርስቶስን እንዲመስል ተጠ ረቶአል። በመጽሐፍ ቅዱስ ወስጥ የመንፈስ ፍሬና (ገላ 5÷22-23) የእርሱ ተቃራኒ የሆነው የሥጋ ሐሳብ (ገላ 5÷19-21) ተነጻጽረዋል። በተለይ ማር 7÷20-23 እንዲሁም 1ቆሮ 6÷9-10 ባሉት ክፍሎች የመንፈስ ፍሬዎች በዝርዝር ተጠቀሰዋል። ይህ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ለባሕርይ ቀረጻ ከፍተኛ ትኩረት እንደሚያደርግ አመላካች ነው።

## የመለኮት ትእዛዝ ንድፈ ሐሳብ

ግብረገብ የተገለጠው የእግዚአብሔር ፈቃድ ወይም በቃለ እግዚአብሔር ውስጥ የሚገኘው የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው የሚለው አመለካከት፣ *የመለኮት ትእዛዝ ንደፈ ሐሳብ* በመባል ይታወቃል።

### ነገሮች መልካም የሚሆኑት ለምንድን ነው?

የተፈጥሮ ትእዛዝ ንድፈ ሐሳብን የሚከተሉት ክርስቲያኖች ብቻ አይደሉም፤ የይሁዲ እምነትና የእስልምና ሃይማኖትን ጨምሮ በርካታ የጥንት መድበለ አማልክት የሚመለኩባቸው ሃይማኖቶችም፣ ለሥነ ምግባራቸው መሠረት የሚያደርጉት የተፈጥሮ ትእዛዝ ንድፈ ሐሳብን ነው። በተፈጥሮ ትእዛዝ ንድፈ ሐሳብ ውስጥ የሚገኘው ፍልስፍናዊ ውይይት አሀዱ ተብሎ የተጀመረው በዘመነ *አፍላጦን* ነው። አፍላጦን ዩቴፍሮ በተባለው ተዋስኦ (ቃለ ምልልስ) ላይ የጠየቀው ጥያቄ፣ የተፈጥሮን ትእዛዝ ንድፈ ሐሳብ የሚከተሉ ሰዎች ሁሉ ራሳቸውን ሊጠይቁት የሚገባ ተገቢ ያቄ ነው። እግዚአብሔር (ለአፍላጦን አማልክት) ነገሮችን ያዘዘው ነገሮቹ መልካም ስለሆኑ ነው ወይስ እግዚአብሔር ስላዘዘ ነገሮች መልካም የሚሆኑት? በሌላ አገላለጽ የእግዚአብሔር ትእዛዝ አንድን ነገር መልካም እንዲሆን ያደርገዋል ወይስ የእግዚአብሔር ትእዛዝ አንድ ነገር መልካም መሆኑን ይጠቁማል? *"የዩቴፍሮ ውጥረት"* በመባል ይታወቃል።

ይህን ጕዳይ በምሳሌ ላብራራ፤ ሩት የሁለተኛ ክፍል ተማሪ ናት፤ መምህራቸው ከክፍሉ ስትወጣ ተማሪዎቹ የማስተማሪያ ዕቃዎችዋን በሙሉ አደጅ አውጥተው ይጫወቱበት ጀመር። በመሠረቱ ልጆቹ ዕቃዎቹን ከቦታው ያነሡት፣ በአግባቡ ተጫውተውበት ለመመለስ ነበር፤ ነገር ግን ከዕቃዎቹ መካከል አንዱ ስለተሰበረባቸው ዕቃዎቹን አስገብተው በነበሩበት ቦታ አስቀመጧቸው። አስተማሪዋ ተመልሳ ስትመጣ የተሰበረውን ዕቃ አየች። አስተማሪዋ ከሩት የክፍል ጓደኞች አንዷ የሆነችውን ልጅ ዕቃውን ማን እንደ ሰበረው ጠየቀቻት፤ ልጅቱም ዕቃውን ማን እንደ ሰበረው እንደማታውቅ ገለጸችላት። ኋላም አስተማሪዋ ሩትን ጠየቀቻት፤ ሩትም እውነቱን ፍርጥርጥ አድርጋ ለመምህሯ ነገረቻት፤ ሩት እውነቱን በመናገሯ የክፍል ጓደኞችዋ "አቃጣሪ" እያሉ ሰደቧት። ምንም እንኳ የክፍል ጓደኞችዋ ሩት ባደረገችው

ነገር ደስ ባይሰኙም አንድ ቀን ሟት እውነቱን መናገሯ ትክክል እንደ ነበረ ገለጥሁላት:: ከዚያም:-

- "ሩት፣ መዋሸት ለምን ስሕተት ሆነ?" ስል ጠየቅኋት
- እርሷም፣ "ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ መዋሸት ስሕተት ነው ይላል" ስትል መለሰችልኝ::
- "መጽሐፍ ቅዱስ ውሸትን መናገር ስሕተት ነው ለምን አለ?"
- "ምክንያቱም እግዚአብሔር ውሸትን እንዳትናገሩ ብሎ ስላዘዘ ነው"::
- "እግዚአብሔር ውሸትን አትናገሩ ብሎ ያዘዘው ለምንድን ነው?"
- "እኔ አላውቅም" አለችኝ::

ዐንገቷን ዕቅፍ አድርጌ ዐይኔን እንደርሷ ጨፍኜ፣ "አየሽ ሩት እግዚአብሔር እውነት ነው፣ እውነት ከእርሱ ባሕርይ የሚመጣ ነው፣ ከእግዚአብሔር ባሕርይ ጋር የሚቃረንም ነገር ሁሉ ኀጢአት ነው" ስል መለስሁላት[6]:: በዚህ ቦታ ላይ ለሩት የተሰጣት መልስ፣ እግዚአብሔር ነገሮችን ያዘዘው ባሕርያቱን መነሻ አድርጎ እንደ ሆነ፣ ከእርሱ ባሕርይ ጋር የማይጣጣም ነገር ኀጢአት እንደ ሆነ ተደርጎ ነው:: እግዚአብሔር ያዘዘው ባሕርያቱን መሠረት አድርጎ ከሆነ፣ ነገሮችን ትክክል ወይም ስሕተት የሚያደርጋቸው ከባሕርያቱ ጋር መጣጣማቸው ወይም ያለመጣጣማቸው እንጂ፣ አድርጉ አታድርጉ ብሎ ማዘዙ አይደለም:: ስለዚህ በዚህ ቦታ የተሰጠው መልስ፣ እግዚአብሔር ነገሮችን ያዘዘው ነገሮቹ በራሳቸው መልካም ስለሆኑ እንዲሁም ትእዛዛቱ ነገሮች ሠናይ ወይም እኩይ መሆናቸውን የሚጠቁሙ ናቸው የሚለውን አካሄድ የተከተለ ነው::

አንደኛ እግዚአብሔር ነገሮችን ያዘዘው ነገሮቹ በራሳቸው መልካም ስለሆኑ ነው ከተባለ፣ የእግዚአብሔር ትእዛዝ የነገሮቹን መልካምነት ብቻ የሚጠቁም ድግግሞሽ ይሆናል (ሰዎች ሁሉ መልካምነቱን የሚያውቁትን ነገር የሚያጸና ድግግሞሽ):: ነገሮች መልካም የሚሆኑት እግዚአብሔር ስላዘዘ ነው የሚባል ከሆነ፣ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ግብታዊ (በዘፈቀደ የሚታዘዝ ትእዛዝ) ይሆናል:: እግዚአብሔር ያሻውን ነገር የማዘዝ ሥልጣን አለው፣ ይህ ትእዛዝ ኅብረተሰቡ ከተቀበለው ወይም ከሚያምንበት ግብረገባዊ መርሖ ጋር የሚጣረስ ቢሆንም እንኳ ማለት ነው:: ለምሳሌ እግዚአብሔር ስላዘዘ ብቻ ነገሮች ትክክል የሚሆኑ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ልጆቻችንን እንድናሠቃያቸው ቢያዝን ትክክል ሊሆን ነው ማለት ነው፣ ነገር ግን ይህ ጉዳይ ማንኛውም ሰው ከተቀበለው እውነት ጋር የሚጻረር ስለሆነ እንዲህ ዐይነቱን አምላክ ማምለክ አዳጋች ይሆናል::

---

[6] ተስፋዬ ሮበሌ፣ *ትክክልና ስሕተትን በተመለከተ ልጆች የሚጠይቋቸው 103 ያቄዎችና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልሶቻቸው!* (አዲስ አበባ፣ ራዕይ አሳታሚ፣ 1992) ገጽ 4:: የስም ለውጥ አድርጌአለሁ::



ነገሮች መልካም የሆኑት እግዚአብሔር ስላዘዘ ነው የሚለው አመለካከት፣ *"ሥነ ምግባራዊ ፈቃደኛነት"* (Ethical Voluntarism) በመባል ይታወቃል:: በርካታ የመለኮት ትእዛዝ ንድፈ ሐሳብ ሐያስያን፣ ሥነ ምግባራዊ ፈቃደኝነትን ነው የሒሳቸው ዒላማ የሚያደርጉት::

የእስልምና ሃይማኖት ሥነ ምግባር፣ ለሥነ ምግባራዊ ፈቃደኛነት ጥሩ ምሳሌ ነው:: ብዙ ሙስሊሞች የአላህን ሉዓላዊነት አጠንክረው ይገልጻሉ፣ ስለዚህም አላህ ለማንም ሆነ ለምንም ተጠያቂ አይደለም:: ይህ ሉዓላዊ አምላክ ያሻውን ለማዘዝ ይችላል፣ ይህም ትእዛዝ ነገሮችን መልካምም ሆነ መጥፎ ያደርጋቸዋል:: በእስልምና ሥነ ምግባር ላይ ሒስ የሚሰነዝሩ ሰዎች ይህ አቋም አላህ ያሻውን የሚፈጽም ግብታዊ (arbitrary) አምላክ፣ ትላንት ያዘዘውን እንኳ ዛሬ የሚቃረን አምላክ ያደርገዋል ባይ ናቸው:: በርካታ ክርስቲያኖች የመጽሐፍ ቅዱሱን አምላክ በዚህ መልክ ለማሰብ ይቸገራሉ፣ ስለዚህ ሥነ ምግባራዊ ፈቃደኛነት ከቃለ እግዚአብሔር ጋር ይጣጣማል ብሎ ማሰብ አዳጋች ነው::

እግዚአብሔር ያዘዘው ነገሮች በራሳቸው መልካም ስለሆኑ ነው የሚለው አመለካከት የይሁዲ እምነትና የክርስትና አቋም ነው:: እግዚአብሔር ያሻውን የሚያዝ አምላክ ሳይሆን በባሕርዩ የሚወሰን ወይም ከባሕርዩ ጋር አንድ ዐይነት የሆነውን ነገር ብቻ የሚያዝ አምላክ ነው:: ይህ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት የሚቃረን ሳይሆን፣ ከባሕርይው ጋር ተጣጥሞ የሚሄድ ነው:: ስለዚህ የግብረገብ መሠረት የእግዚአብሔር ትእዛዝ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ውስጥ የተገለጠው የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው:: በሌላ አገላለጽ በፍቅር የተሞላው እግዚአብሔር የሚያዘው ትእዛዝ ሁሉ መልካም ነው፣ ትእዛዛቱ ሁሉ ከባሕርዩ ጋር የሚጣጣሙ ናቸው:: እግዚአብሔር ከባሕርዩ ጋር የሚቃረኑ ነገሮችን ስለማያዝ፣ አማኞች ለትእዛዙ በሙሉ ልብ መታዘዝ ይጠበቅባቸዋል::

## መልካምነትና አጠቃላይ መገለጥ

የዩቴፍሮን ውጥረት የምንመልስበት ሌላኛው መንገድ፣ የእግዚአብሔር *ልዩ መገለጥ* ማለትም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጠው የእግዚአብሔር ትእዛዝ *ከአጠቃላይ መገለጥ* ወይም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የተገለጠው የእግዚአብሔር ትእዛዝ ጋር ተጣጥሞ ይሄዳል የሚለው እውነታ ነው:: ከተፈጥሮ ሕግጋት የምንማረው እውነት፣ ነባራዊ የሆኑት ግብረገባዊ ፋይዳዎች በቃለ እግዚአብሔር ውስጥ ከመጠቀሳቸው በፊት፣ በአጠቃላይ መገለጥ ውስጥ እንደ ተገለጡ ነው:: ይህ ማለት ቃለ እግዚአብሔር ከመሰጠቱ በፊት፣ ለሰው ልጆች ሁሉ በአጠቃላይ መገለጥ ውስጥ እንደ ተገለጡ የሚያሳይ ነው:: ቃለ እግዚአብሔር ከመሰጠቱ በፊትም መሠረታዊ የሚባሉት

ግብረገባዊ ፋይዳዎች በተፈጥሮ ሕግጋት ውስጥ ተገልጠዋል፤ ስለዚህም ግብረገባዊ ፋይዳዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ብቻ ጥገኛ ያልሆኑ ራሳቸውን የቻሉ ሕግጋት መሆናቸውን ነው:: ይህ ክርስቲያኖች ሠናይ የሚሉት ፋይዳ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተገለጠውም እውነት ዘልቆ እንደሚሄድ አመላካች ነው:: እግዚአብሔር ሳይንሳዊ እውነታዎችን ከቃለ እግዚአብሔር ውጪ እንደ ገለጣቸው ሁሉ፣ ግብረገባዊ እውነታዎችንም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ገልጦአቸዋል::

ግብረገባዊ ፋይዳዎችን በተመለከተ የተፈጥሮ ሕግ አጠቃላይ መገለጥ ነው:: ይህ እውነት የመለኮት ትእዛዝ ትውርትን የሚያጠናክር ነው፤ ይኸውም እግዚአብሔር በዘፈቀደ እንደማያዝ አመላካች ነው:: ትእዛዛቱ ከባሕርያቱ ጋር መጣጣማቸው ብቻ ሳይሆን፣ ትእዛዛቱ እግዚአብሔር በአጠቃላይ መገለጥ ውስጥ ከገለጣቸው ፋይዳዎች ጋር አንድ ዐይነት መሆናቸውንም ጭምር አመላካች ነው:: ራሱን ልዩ በሆነ መንገድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የገለጠው እግዚአብሔር ማመን ምክንያታዊ ከሆነ፣ ከአጠቃላይ መገለጥ ጋር የሚጣጣመውን የመለኮት ትእዛዝ ትውርት ማመን አግባብ ይሆናል::

## በመለኮት ትእዛዝ ሥነ ምግባር ላይ ይታያሉ የሚባሉ ችግሮች

የዩቴፍሮ ውጥረት በዚህ መልኩ ምላሽ ያግኝ እንጂ፣ በመለኮተ ትእዛዝ ሥነ ምግባር ላይ የሚስተዋሉና መመለስ የሚገባቸው ሁለት ዐበይት ጉዳዮች አሉ:: አንደኛው:- አንዳንድ የመለኮት ትእዛዝ ንድፈ ሐሳብ ሐያስያን እግዚአብሔርን፣ "መልካም ነው" ማለት የምንችለው፣ ስለ "መልካምነት" ከእግዚአብሔር የተለየና ከሃይማኖት ውጪ የሆነ የቅድሚያ ግንዛቤ ሲኖረን ብቻ ነው ይላሉ[7]:: ነገር ግን ይህ ሒስ እርስ በርስ መቀላቀል የሌለባቸውን ሁለት የፍልስፍና መሠረታዊ ሐሳቦችን የሚቀላቅል ነው፤ ይኸውም የአንድ ነገር ማንነትና አንድን ነገር የምናውቅበት ዕውቀት—*ሥነ ኑባሬንና ሥነ ዕውቀትን*:: አንድ ሰው እግዚአብሔር መልካም ነው ከማለቱ በፊት "መልካምነትን" በቅድሚያ ሊያውቅ ይገባዋል የሚለው የሙግት ነጥብ፣ መልካምነት ከእግዚአብሔር የተለየ ነውና ራሱን የቻለ ነው እንድንል አያደርገንም:: እኔ ከአዲስ አበባ ተነሥቼ ወደ ጂማ ከተማ ለመሄድ ብፈልግ፣ ነገር ግን ወደዚያ እንዴት መሄድ እንዳለብኝ በትክክል የማላውቅ ከሆነ፣ ከአዲስ አበባ ተነሥቼ ወደ ጂማ እንዴት መሄድ እንዳለብኝ የሚጠቁመኝን፣ አቅጣጫ ጠቋሚ ካርታ ልጠቀም እችላለሁ:: ይህ ማለት ግን አቅጣጫውን የጠቈመኝ ካርታ፣ ከጂማ ከተማ በፊት ነበር ማለት አይደለም:: እኔም ስለጂማ የሚኖረኝ ዕውቀት፣ ከከተማዋ ሕልውና በፊት ነው ማለት አይደለም:: ልክ እንደዚሁ ስለመልካምነት የማውቀው እግዚአብሔርን መልካም

[7] ለምሳሌ Kai Nielsen, Ethics Without God (New York: Prometheus Press, 1985), ምዕራፍ 2::



ነህ ከማለቴ በፊት ነው ማለት፣ ግብረገብ ከእግዚአብሔር ወጪ ነው ማለት አይደለም::

የመለኮት ትእዛዝ ትውርትን በተመለከተ የሚጠየቀው ሁለተኛው ጥያቄ፣ ሁለት ግብረገባዊ ትእዛዛት በተወሰነ ሁኔታ ውስጥ በአንድ ጊዜ እንድንታዘዛቸው በምንጠየቅባቸው ሁኔታዎች ውስጥ፣ ለአንዱ ግብረገባዊ ትእዛዝ ስታዘዝ ሌላኛውን ግብረገባዊ ትእዛዝ መፍረስ አይቀሬ ይሆናል:: የመለኮት ትእዛዝ ትውርት ይህን መሰሉን ጥያቄ የመፈታት ዐቅም የለውም የሚለው ሒስ ሁለተኛው ነው:: በሥነ ምግባር ላይ የሠሩ ምሁራን፣ እነዚህን መሰል ጉዳዮች ግብረገባዊ ግጭቶች ይሏቸዋል:: ግብረገባዊ ግጭት ማለት፣ እግዚአብሔር የሰጠን ***ግብረገባዊ ግዴታዎች*** (ሕግጋት) በአንድ ሁኔታ ውስጥ እርስ በርሳቸው ሲጋጩ፣ ግብረገባዊ ግጭት ብለን እንጠራቸዋለን:: የመለኮት ትእዛዝ ትውርትን የሚከተሉ ምሁራን ይህን ጥያቄ ወይም ሒስ በተመለከተ የተለያየ አስተያየት አላቸው:: ይህን "ግብረገባዊ ፍጹማዊነት" በሚለው ክፍል ሥር በስፋት የምንመለከተው ጉዳይ ነው::

# 3

## የሥነ ምግባር መርሖችና የግብረገብ ሙግቶች አካሄድ[1]

ሥነ ምግባራዊ ርእሰ ጉዳዮች ሁሉ መሠረት የሚያደርጉት፣ በሥነ ምግባራዊ መርሖች ላይ ነው:: ይህ መጽሐፍ የሥነ ምግባር መርሖችን በቀዳሚነት ሊያይ የመረጠበት ምክንያት፣ ርእሰ ጉዳዮችን መሠረት ካደረጉባቸው መርሖቻቸው ነጥሎ መወያየት አዳጋች ስለሚሆን ነው:: የምንከተላቸው ግብረገባዊ መርሖች የምንደርስበትን ግብረገባዊ ውሳኔ ወይም ምርጫ መወሰናቸው አይቀሬ ነው::

ሰዎች ሥነ ምግባራዊ ርእሰ ጉዳዮች ላይ የተለያየ አቋም የሚይዙበት ዐቢይ ምክንያት፣ የተለያየ ዐይነት የግብረገብ መርሖችን ስለሚከተሉ ነው:: ሥነ ምግባርን አስመልክቶ የሚካሄዱ ውይይቶች ፍሬ አልባ የሚሆኑበት ምክንያትም፣ ተወያዮቹ ከሚወያዩባቸው ርእሰ ጉዳዮች ይልቅ፣ ለመርሖዎቹ ትልቅ ትኩረት በመስጠት ያለመግባባቱን ከምንጩ ለማድረቅ በመርሖቹ ላይ ለመወያየት ስለማይሞክሩ ነው:: ይህ መጽሐፍ ለሥነ ምግባራዊ መርሖች ሰፊ ቦታ የሰጠው፣ ግብረገባዊ ርእሰ ጉዳዮች ሁሉ መሠረት ያደረጉት ግብረገባዊ መርሖዎችን ስለሆነና ውይይታችንን ከእነርሱ መጀመር ተገቢ ሆኖ ስላገኘነው ነው:: ስለዚህ አንድ ሰው ግብረገባዊ መርሖችን ማወቁ፣ ግብረገባዊ ርእሰ ጉዳዮችን ከምንጮቹ (ከመሠረታቸው) እንዲመረምራቸውና እንዲመዝናቸው ይረዱታል::

ይህን ጉዳይ በግልጽ ማየት እንችል ዘንድ፣ የተለያዩ ግብረገባዊ መርሖችን የሚከተሉ ሰዎች፣ "ውርጃን ሕጋዊ እናድርጋለንን?" በሚል ርእስ በተጠራ የመድረክ ውይይት ላይ፣ ለመድረክ ውይይቱ የተጋበዙት ተናጋሪዎች የሚያቀርቡትን የሐሳብ ናሙና በዋቢነት እናቅርብ:-

በመድረክ ውይይቱ ላይ እንዲናገሩ የተጋበዙት[2]:-

1. ሐኪም በማሕፀንሽ ያለውን ፅንስ በጥቂት ወራት ውስጥ ካላስወረድሽ ልትሞቺ ትችያለሽ ያላት እናት፤

---

[1] ልዩ መግለጫ ካልተሰጠ በስተቀር ይህ ክፍል በአብዛኛው የተወሰደው ከ Scott B. Rae, Moral Choices: *An Introduction To Ethics* (Grand Rapids: Zondervan, 1985) ላይ ነው::

[2] ዝኒ ከማሁ፣ ከ 73-97:: ለውይይቱ የቀረበው ርእሰ ጉዳይ ጨምሮ በርካታ ሐሳቦች ተቀይረዋል::

2. የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር ንቁ አባል፤
3. ውርጃን የሚደግፉ የማሕፀን ሐኪም፤
4. ውርጃን ክፉኛ የሚቃወሙ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቄስ፤
5. በእግዚአብሔር መኖር የማያምን የዩኒቨርስቲ መምህር፤
6. የሕግ አማካሪ፤
7. በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የምትገኝ የአንዲት ቤተ ክርስቲያን ወንጌላዊ፤

እያንዳንዱ ታዳሚ የራሱን አቋም ትክክለኛነት ለማስረገጥ የሚያቀርበውን ሐሳብ እንዲሁም ሙግቱን ለማዋቀር መሠረት ያደረገበትን መርሖ እንመልከት፤

## 1. ሐኪም በማሕፀንሽ ያለውን ፅንስ በጥቂት ወራት ውስጥ ካላስወረድሽ ልትሞቺ ትችያለሽ ያላት እና

(እኝህ እናት መሠረት ያደረጉት *"ሥነ ምግባራዊ እኔነት"* በመባል የሚታወቀውን የሥነ ምግባር መርሖ ነው)

ይህ ጉባኤ የከተመበት ርእሰ ጉዳይ ከማንም ይልቅ ለእኔ ትልቅ ቦታ አለው:: እኔ ሐኪም በማሕፀንሽ ያለውን ሽል የማታስወጪ ከሆነ፣ ልትሞቺ ትቺያለሽ ያለኝ ሰው ነኝ:: እኔ ከዚህ ውይይት የምጠብቀው ነገር፣ ሕይወቴን ከአደጋ የሚታደገውንና አሁን በሥራ ላይ ያለውን የወንጀለኛ መቅጫ ሕጋችንን የሚያጸናውን ነገር ነው:: በዛሬው ውይይት ሚዛን መድፋት ያለበት፣ የእኔን ፍላጎት የሚያረካው ነገር ብቻ ነው:: በዚህ የውይይት ስፍራ ቦታ ሊሰጠው የሚገባው፣ ሂፖክራተስ ለሐኪሞች ያዘጋጀው ቃለ መሓላ ወይም አትግደል የሚለው የሙሴ አምስተኛው ሕግ አይደለም:: እነዚህ ሕግጋት ለተቀረው ሕዝብ ጠቃሚነት ሊኖራቸው ይችላል፤ እኔ ግን በሕይወትና በሞት መካከል ያለው ሰው ነኝ:: ስለዚህ ውይይቱ ከማንም ይልቅ እኔን ይነካኛል፤ የእኔ ውሳኔ በበላይነት መታየት ያለበትም ምክንያት ይኸው ነው::

በመሠረቱ አገራችን ኢትዮጵያ የምትተዳደርበት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ፣ እናቲቱን በአደጋ ላይ የሚጥል ፅንስ መቋረጥ እንዳለበት ይደነግጋል፤ ይህ ለእኔ ትልቅ ስፍራ አለው:: በዚህ መልኩ በሥራ ላይ ያለው ሕግ የግል ፍላጎቴን የሚያረካ ነው:: ነገር ግን ከዚህም ባለፈ መልኩ እናቲቱ ባሻት ጊዜ ሁሉ ፅንሱን ማቋረጥ ትችል ዘንድ፣ ሕጉ ከዚህም በላይ ሊሻሻል ይገባዋል::



## 2. የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር ንቁ አባል

(እኝህ ሴት *"መርሕ ተኮር"* የተባለውን የሥነ ምግባር መርሖ ይከተላሉ)

እኔ የመጀመሪያዋ ተናጋሪ ካቀረቡት ሙግት ጋር በመሠረተ ሐሳብ ደረጃ እስማማለሁ:: ነገር ግን የምስማማው ማለትም ውርጃ በማናቸውም ምክንያትና ጊዜ ይፈቀድ የምልበት ምክንያት፣ እርሳቸው ሙግታቸውን ባስቀመጡበት አቅጣጫ በመጓዝ አይደለም:: እርሳቸው ውርጃ ይፈቀድ ለማለት ያቀረቡት የሙግት አካሄድ ትክክል አይደለም::

በሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ የምንገኝ ሰዎች፣ ልንከተለው የሚገባን መርሖ እያንዳንዱ ግለሰብ ይጠቅመኛል ወይም ይበጀኛል የሚለውን ነገር በራሱ ላይ መወሰን አለበት የሚለውን መርሖ ነው:: የዲሞክራስያዊ አስተዳደር መሠረቱም ሆነ ውቅሩ የግለሰቦችን ፈላጎት ማርካት ነው:: ዲሞክራት ነኝ የሚል ማንኛውም ሰው ይህን መቃወም ከቶውንም አይችልም:: አንድ ሰው ሌላውን ሰው እስካልጐዳ ድረስ በራሱ ላይ ያሻውን ነገር የማድረግ ሙሉ መብት አለው:: አንድ ግለሰብ በሕይወት የመኖርንና ያለመኖርን ጉዳይ በራሱ ላይ የሚበይነው እርሱ ራሱ ነው—ማንንም ሰው እስካልጐዳ ድረስ፤ ከእርሱም ሌላ ማንም ጣልቃ ሊገባ አይገባውም::

የሰው ልጅ ክቡር ፍጥረት መሆኑን ካመንን፣ የግለሰቦችን ምርጫ ማርካት በዋነኛነት ልንከተለው የሚገባን ጉዳይ ነው:: እኔም እየተናገርሁ ያለሁት ግለሰቦች በራሳቸው ላይ ያሹትን ነገር የመምረጥ መብታቸው ሊነፈጋቸው አይገባም የሚለውን መርሖ መሠረት አድርጌ ነው:: እኔ ይህን መርሖ መቀበሌ ውርጃን እንድደግፍ ያደርገኛል፤ ስለዚህ መንግሥት ውርጃን መፍቀድ አለበት የሚል የጸና እምነት አለኝ::

## 3. ውርጃን የሚደግፉ የማሕፀን ሐኪም

(እኝህ ሐኪም *"የበለጠ መልካምነት ለበለጠ ቍጥር"* የተባለውን የሥነ ምግባር መርሖ የሚከተሉ ናቸው)

እኔ ከብዙ ሁኔታዎች የተነሣ ውርጃን እደግፋለሁ:: ነገር ግን ውርጃ ሕጋዊ ይሁን የምለው፣ ከእኔ በፊት የነበሩት ሁለት ተናጋሪዎች ውርጃን በደገፉበት መልክ አይደለም::

እኔ ፍጹማን የሆኑ፣ መልካምነትንና እኩይነትን የሚወስኑ መርሖች አሉ የሚል ቅንጣት ታህል እምነት የለኝም:: ነገር ግን የአንድ ድርጊት እኩይነትና ሠናይነት መወሰን ያለበት፣ በሚያስከትለው ውጤት ነው:: አንድ ድርጊት ወይም ውሳኔ መልካም ውጤት የሚያስከትል ከሆነ ሊፈቀድ ይገባዋል:: ይህን ሐሳብ በሌላ

መልክ ለማቅረብ ያህል፣ አንድ ደርጊት ከሚያስከትለው ጉዳት ይልቅ ጥቅሙ በልጦ ከተገኘ፣ ሠናይ የሆነና ልንከተለው የሚገባን ምግባር ነው። ውርጃን በተመለከተ ከእኔ በፊት የተናገሩት ሰዎች የሄዱበት አካሄድ ትክክል አይደለም። ሥነ ምግባርን በተመለከተ ልንከተለው የሚገባን አካሄድ "የበለጠ መልካምነት ለበለጠ ቊጥር" የሚለውን መርሖ ነው። ውርጃን በተመለከተ ልንከተለው የሚገባን አካሄድ፣ የምናካሂደው ውርጃ የበለጠ መልካምነት ለበለጠ ሰው (ቊጥር) ያስገኛልን? የሚለውን ጥያቄ ነው።

እንደ እኔ እምነት አብዛኛውን ጊዜ በተመሰከረለት ሐኪም የሚካሄድ ውረጃ ከብዙ አቅጣጫ ብዙ መልካም የሆነን ነገር ያመጣል። አንደኛ:- ውርጃው እንዲቋረጥ የእናቲቱ ፈላጎት እስከ ሆነ ድረስ፣ ውርጃው የእናቲቱን ፈላጎት ያረካል። ሁለተኛ:- ውርጃ አልተፈቀደም ማለት ሰዎች በስውር ማስወረዳቸውን ያቆማሉ ማለት አይደለም፤ ይህ እውነት ከሆነ ደግሞ፣ እናቶች በስውር በሚያካሂዱት ውርጃ ባልተፈለገ መድኀኒት ሕይወታቸውን ያጣሉ። ሦስተኛ:- በእናቲቱ ላይ በሚደርሰው አካላዊ፣ ሥነ ልቡናዊና ምጣኔ ሀብታዊ ቀውስ የእናቲቱ ቤተሰቦች ይጐዳሉ። አራተኛ:- ከዕቅድ ውጪ በሆነው ወሊድ የቤተሰቡና የአገር ሀብት ይጐዳል ወዘተርፈ። በአጠቃላይ ውርጃ መፈቀዱ ከሚያስከትለው ጉዳት ይልቅ፣ ያለመፈቀዱ በግለሰብና በአገር ላይ የሚያመጣው ችግር በእጅጉ የበለጠ ነው። ለዚህ ውርጃ መፈቀድ ያለበት ጉዳይ ነው። አንድ ግብረገብ በአገርና በሕዝብ ላይ የሚያስከትለው ጉዳት በቅጡ ሳይመዘን የሚወሰደው ርምጃ ታላቅ ችግር ሊያስከትል እንደሚችል ልብ ልናደርግ ይገባል።

## 4. ውርጃን የሚቃወሙ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቄስ

*(እኚህ ቀሲስ "መርሖ ተኰር" የተባለውን የሥነ ምግባር መርሖ የሚከተሉ ናቸው)*

እኔ ውርጃን የምቃወመው ለዓለማችን ሥልጣኔ ሁሉ መሠረት የሆነውን ዐቢይ መርሖ መሠረት አድርጌ ነው። ይህ መርሖ ዓለማችን አሁን ለምትገኝበት ፈርጀ ብዙና ታላቅ ሥልጣኔ መሠረት ነው። ሃይማኖትን መሠረት ያላደረገ የትኛውም ሥልጡን ማኅበረሰብ፣ "አትግደል" የሚለውን ግብረገባዊ መርሖ በሙሉ ልቡ የሚቀበለው ጉዳይ ነው። እኔ ይህ መርሖ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለሰው ልጆች የተሰጠ ትእዛዝ ነው የሚል እምነት አለኝ። ነገር ግን በእግዚአብሔር መኖር የሚያምን ሰው እንኳ፣ "አትግደል" የሚለውን ሕግ ፍጹም ትክክል መሆኑን በሙሉ ልቡ ይቀበላል።

ለእኔ ውርጃ ማለት፣ "በደል አልባ የሆነን የሰው ልጅ አሰቃቂ በሆነ መንገድ መግደል" ማለት ነው። የተወሰነ ግለሰብ ንጹሕ ደምን ማፍሰስ ፈልጓል በሚል ኅብረተሰባችን ግድያን መደገፍ የለበትም። "አትግደል" ወይም ንጹሕ ደምን አታፍስ የሚለው ሕግ የሰውን ክቡርነት አመላካች ነው። ደግሜ ማለት የምፈልገው ነገር፤



ክቡር የሆነውን የሰውን ልጅ ማክበር ይኖርብናል፤ ምክንያቱም ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አምሳል ነውና። ነገር ግን ይህን መሠረታዊ የግብረገብ ሕግ ለመቀበል የግድ በእግዚአብሔር መኖር ማመን ላያስፈልጋችሁ ይችላል። ሰዎች ራሳቸው ከማናቸውም አደጋ የመጠበቅ ውስጣዊ ፍላጎት አላቸው፤ ይህም ነው ንጹሕ ደምን ማፍሰስ እንደሌለብን የሚያስተምረን። ከኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር እንደ መጡት እኅቴ፣ እኔም ግብረገባዊ መርሖች እንዳሉ እንዲሁም ለመርሖቹ ትልቅ ቦታ በመስጠት መታዘዝ እንዳለብኝ አምናለሁ። ከእኅቴ የሚለየኝ ግን፣ መርሖው ከዕለት ተዕለት ሕይወት ጋር እንዴት መዛመድ አለበት በሚለው ነጥብ ላይ ነው። ይኸውም ክቡር የሆነውን የሰው ልጅ ማክበር ማለት ያሻውን ነገር እንዲያደርግ መፍቀድ ማለት አይደለም። በደል አልባ የሆነውን የሰው ልጅ ሕይወት መግደል የለብንም፤ ምክንያቱም ነፍስ ክቡር ነች። የሰውን ነፍስ ማጥፋትም የሰው ልጆች መብት አይደለም።

## 5. በእግዚአብሔር መኖር የማያምን የዩኒቨርስቲ መምህር፤

(እኚህ ምሁር *"ስሜታዊነት"* የተባለውን የሥነ ምግባር መርሖ የሚከተሉ ናቸው)

ከእኔ በፊት የነበሩት ተናጋሪዎች አንድን ምግባር ትክክል ነው ወይስ ስሕተት ነው ለማለት፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተወሰነ መስፈርት ሲያስቀምጡ ይታያል። ነገር ግን ይህ ትክክል አይመስለኝም። ሰዎች የግል ምርጫቸውን ለማሳየት በቻ ነው "ትክክል" እና " ስሕተት" የሚሉትን ቃላት የሚጠቀሙት። ምን ማለቴ እንደ ሆነ ላብራራ፤ ማንኛውም ሰው ትክክልና ስሕተት የሚለውን ቃል የሚጠቀመው ደርጊቱን ሲጠላው አልያም ሲወደው ብቻ ነው። የመጀመሪያዎቹ ሦስት ተናጋሪዎች ውርጃን እንደሚደግፉ ገልጸዋል። ቄሱ ደግሞ ውርጃን ማካሄድ እንደሚቃወሙ ገልጸዋል። እነዚህ ሰዎች የግላቸውን ምርጫ ነው የተናገሩት። ነገር ግን ሁሉም፣ መልካም ነው ብሎ የመረጠውን ነገር በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ፣ የግብረገብ ቃላትን በመጠቀም ሙግቱን ያጠናክራል።

## 6. የሕግ አማካሪ፤

(እኚህ ሰው *"አንጻራዊነት"* የተባለውን የሥነ ምግባር መርሖ የሚከተሉ ናቸው)

እኔ፣ ከእኔ በፊት ከነበሩት ምሁር አቋም ጋር በአብዛኛው እስማማለሁ። ነገር ግን እንዳንድ ነጥቦች ከእርሳቸው ጋር ሙሉ ለሙሉ እንዳልስማማ ያደርጉኛል። እኔ እንደ እርሳቸው፣ ትክክልና ስሕተት የሚባል ነገር በጭራሽ የለም የሚል እምነት የለኝም፤ ነገር ግን ዓለም ዐቀፋዊ የሆነ በሁሉም ቦታ፣ ጊዜና ሁኔታ ውስጥ ሳይቀያየሩ ተግባራዊ መሆን አለባቸው የሚባሉ የግብረገብ ሕግጋት በጭራሽ የሉም የሚል እምነት አለኝ። አንድ ነገር መልካም ወይም ትክክል ነው የሚባለው፣ እንደየ ሁኔታውና እንደየ

አካባቢው ነው:: ለምሳሌ ውርጃን በተመለከተ አንድ ማኅበረሰብ በስምምነት ውርጃ ይፈቀድ ቢል ይፈቀዳል፤ ማኅበረሰቡ እስኪተስማማበት ጊዜ ድረስም ሊፈቀድ የማይችልበት አንዳች ምክንያት የለም:: ነገር ግን ማኅበረሰቡ ደርጊቱን ከጠላው፣ ውርጃን በመፍቀድ ማኅበረሰቡ እንዲቀበለው ማድረግ ትክክል አይመስለኝም:: በአሜሪካን አገር ውርጃ ለ30 ዓመት ተፈቅዶ ሲሠራበት ቆይቶአል፤ ሰዎችም ባሻቸው ጊዜ በማሕፀን የያዝዋቸውን ሽሎች ያስወጡ ነበር፤ አሁን ደግሞ አብዛኛው ሕዝብ ውርጃን እየጠላ ስለመጣ፣ ፕሬዚዳንት ቡሽ ውርጃ እንዳይካሄድ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው፤ እንዲያውም አንዳንድ የውርጃ ዐይነቶች ተግባራዊ እንዳይሆኑ ጥብቅ ትእዛዝ አስተላልፈዋል:: ይህም ለዳግም ምርጫ ብዙ ደጋፊ እንደሚያስገኝላቸው፣ በርካታ የፖለቲካ ተንታኞች ያስረዳሉ:: ከዚህ የምንረዳው ነገር በአንድ ወቅት ኅብረተሰቡ ትክክል ነው ብሎ የተቀበለው ነገር፣ በሌላ ጊዜ ይኰነናል:: በአጠቃላይ አንድ ማኅበረሰብ ይበጀኛል ያለው ነገር ትክክል ሲሆን፣ አልፈልገውም ያለው ነገር ደግሞ እኩይ ይሆናል:: የግብረገብን እኩይነትና ሠናይነት የሚወስነው የሰዎች ስምምነት እስከ ሆነ ድረስ፣ ግብረገባዊ ሕግጋት አይሻሬ ናቸው ማለት አይቻልም:: አብዛኛው ሕዝባችን ውርጃን ማካሄድ እየፈለገ አታካሂድ ማለት ደግሞ ትክክል አይደለም::

## 7. በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የምትገኝ የአንዲት ቤተ ክርስቲያን ወንጌላዊ

(እኝህ የወንጌል ሰባኪ፣ *"የሸርቹ ፅንሰ ሐሳብ"* የተባለውን የሥነ ምግባር መርሐ የሚከተሉ ናቸው)

እኔ በመጠኑም ቢሆን ከአብዛኞቹ ተናጋሪዎች የተለየ አቋም ያለኝ ይመስለኛል:: ለእኔ ግድ የሚለኝ ጉዳይ የባሕርይ ለውጥ እንጂ፣ ግብረገባዊ ውሳኔ መወሰን አይደለም:: በእንዲህ መሰሉ ውይይታችን ወቅት መዘንጋት የሌለብን ጉዳይ፣ የግለሰቦችን ባሕርይ ወይም ጸባይ የመመርመሩን ጉዳይ ነው:: በእኔ እምነት መሠረታዊ የሚባለው ግብረገባዊ ጥያቄ እስካሁን የተጠየቀ አይመስለኝም:: ይኸውም ውርጃን ይካሄድልኝ የምትለው እናት ስላላት የባሕርይ ለውጥና ፍላጎት ምን እንማራለን? ውርጃን የሚደግፉም ሆኑ ውርጃን የሚቃወሙ ሰዎች ለኅብረተሰባችን የሚያስቴላልፉት መልእክት ምንድን ነው? ክቡር የሆነውን የሰው ሕይወት እንግደል ወይም አንግደል በሚለው ጉዳይ ላይ ለምን መወሰን አቃተን? የሰው ሕይወት ክቡር መሆኑ እንዴት ጠፋብን? ስለዚህ ቁሎም ነገሩ ያለው በርእሰ ጉዳዩ ላይ ሳይሆን፣ በርእሰ ጉዳዩ ላይ በሚወያዩት ሰዎች የባሕርይ ቀረጻ ላይ ነው:: ለዚህም ነው ከምንወያይበት ጉዳይ ይልቅ ትልቅ ትኵረት መስጠት ያለብን በባሕርይ ለውጥ ወይም ቀረጻ ላይ ነው የምለው:: ልዩነታችን የሰማይና የምድር ያህል መራራቁ የርእሰ ጉዳዩን ውስብስብነት የሚያመለክት ሳይሆን፣ የተወያዮቹን ግብረገብ መራራቅ አመላካች ነው::



በዚህ የመድረክ ውይይት ላይ የቀረቡት ተናጋሪዎች፣ የተለያየ ዐይነት የግብረገብ መርሐ በመጠቀም ሙግታቸውን ሲያዋቅሩ ይስተዋላል:: እያንዳንዱ ተናጋሪ የትኛውን የግብረገብ መርሐ እንደሚከተል በሙግታቸው መጀመሪያ ላይ ተጠቅሶአል:: በርካታ ሰዎች የሥነ ምግባር ውይይት የሚያካሂዱት ከዚህ አንደኛውን መርሐ መሠረት በማድረግ ነው:: በተለያዩ አጋጣሚዎች የምናያቸው ግብረገባዊ ክርክሮች ይህን መሰል ገጽታ አላቸው:: ማንኛውም ሰው አንዱን ግብረገብ ሲቀበልና ሌላኛውን ግብረገብ ሲያወግዝ፣ የተወሰነ መርሐ ተከትሎ እንጂ (የቱን መርሐ እንደሚከተል ላያውቀው ግን ይችላል) በወና አእምሮ አይደለም ርእሰ ጉዳዮቹ የሚመለከተው:: ተናጋሪዎቹ መሠረት ያደረጉበትን ግብረገባዊ መርሖች ጥንካሬያቸውንና ድካማቸውን እንመልከት::

## ሥነ ምግባራዊ እኔነት

*"ሥነ ምግባራዊ እኔነት"* በመባል የሚታወቀው የሥነ ምግባር መርሐ፣ ምግባሮች በአንድ ሰው የግል ፍላጎት የሚበየኑ ናቸው የሚል አመለካከት ነው:: የግለሰብን ፍላጎት የሚያረካው ምግባር ትክክለኛ ምግባር ነው፤ የግለሰብን ፍላጎት የማያረካው ደግሞ ኢግብረገባዊ ነው::

የመጀመሪያዋ ተናጋሪ ለግብረገባዊ ብያኔያቸው መሠረት ያደረጉት የግል ፍላጎታቸውን ነው:: ሥነ ምግባራዊ እኔነትን መሠረት ያደረጉ በርካታ የግብረገብ ብያኔዎችን በአስረጅነት ማቅረብ ይቻላል:: ለምሳሌ በርካታ ሐኪሞች ሙያዊ ውሳኔያቸውን መሠረት የሚያደርጉት፣ የበሽተኞቻቸውን ፍላጎት በማርካቱ ላይ ነው:: በግለሰቦች ድርጅት ውስጥ የሚሠሩ ሰዎች፣ የድርጅቱን ማለትም የቀጣሪያቸውን ፍላጎት ማርካት ትክክል ሲሆን፣ የዚህ ተቃራኒው ደግሞ ስሕተት ነው:: ለምሳሌ ቀጣሪው፣ ተቀጣሪው ስሕተት ነው የሚለውን ነገር እንዲያደርግ ቢጠይቀው፣ አለቃው የተጠየቀውን ነገር ማድረግ ይኖርበታል (ለምሳሌ የተሳሳተ መረጃ በማቅረብ፣ ደንበኞችን እንዲያታልል):: ሠራተኞቹ ሥራቸውን እንዳያጡ ስለሚፈልጉ የታዘዙትን ነገር ይፈጽማሉ፤ ይህ ሁኔታም ሠራተኛው ጥቅሙን ለማስጠበቅ ሲል ሥነ ምግባራዊ እኔነት የሚባለውን የሥነ ምግባር አካሄድ ይከተላል::

በመጽሐፍ ቅዱስ፣ ሰዎች ለእግዚአብሔር ታዛዥ ይሆኑ ዘንድ "ሥነ ምግባራዊ እኔነትን" እንደ መቀስቀሻ ሲጠቀም ይስተዋላል:: ለምሳሌ:- ለእግዚአብሔር ኪዳን ታማኝ መሆን የሚያመጣው በረከትና ተማኝ ያለመሆን ደግሞ የሚያስከትለው ርግማን ዘዳ 27-30:: በዚህ ስፍራ የእስራኤል የግብርናዋ ብልጽግናና የአገሪቱ ሰላም የሚወሰነው ኪዳኑን በመታዘዝ ሲሆን፣ ጣዖታትን በማምለክ ትእዛዙን ያለመታዘዝ ደግሞ በግብርናዋና በሰላሟ ላይ ታላቅ ጥላ እንደሚጥልበት ያስረዳል:: ከዚህ የምንማረው

ቀኑም ነገር፣ የአገሪቱን ፍላጎት ማርካት መልካሙን ነገር ለማድረግ መቀስቀሻ ሆኖ ቀርቦአል:: ክርስቲያን በመሆን የዘላለም ሕይወት ይገኛል የሚለው አስተምህሮ የግለሰቦችን ፍላጎት የሚያረካ ነው:: የዚህ አመለካከት ደጋፊዎች፣ ለሌሎች ሰዎች ጥቅም ብሎ መልካም ነገር ማድረግ፣ የአድራጊውን ፍላጎት ስለሚያረካ የሌሎች ሰዎችን ፍላጎት ለማርካት ሲባል የሚካሄደው ድርጊት በሥነ ምግባራዊ እኔነት ውስጥ ሊመደብ ይገባዋል ባይ ናቸው:: እንዲያውም አንዳንዶች መጽሐፍ ቅዱስ የሰዎችን ፍላጎት በማርካት ላይ መሠረት ስለሚያደርግ፣ የሚከተለው የሥነ ምግባር አካሄድ፣ የሥነ ምግባራዊ እኔነትን ነው ሲሉ ይሞግታሉ::

መጽሐፍ ቅዱስ ግን የሰዎችን ፍላጎት ባይኮንንም እንኳ፣ የግል ፍላጎት የሌሎችንም ሰዎች ፍላጎት በሚያረካ መልኩ መካሄድ እንዳለበት ያስጠነቅቃል (ፊልጵ 2÷4):: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያደርገው የሰዎችን ፍላጎት ማርካት አስፈላጊ ቢሆንም፣ ሥነ ምግባራዊ እኔነት ራሱን የቻለ የሥነ ምግባር መርሐ ነው አይልም::

በሥነ ምግባራዊ እኔነት ሠናይ የሆነው ሥነ ምግባር የአድራጊውን ፍላጎት የሚያረካው ድርጊት ብቻ ነው:: የአመለካከቱ ደጋፊዎች እንደሚያስረዱት፣ የአንድ ሰው ፍላጎት የሌላውን ሰው ፍላጎት ማርካቱ የሚያረካው ከሆነ፣ ይህን ማድረጉ ክፋት የለውም:: የሌሎችን ሰዎች ፍላጎት ማርካት የራሱን ፍላጎት ለማርካት ምክንያት ሊሆነው ይችላል:: የአመለካከቱ ቀዳማይ ጠንሳሽ እንደ ሆነ የሚነገርለት ቶማስ ሆብስ እንደሚያስረዳው፣ የግል ፍላጎታችንን ማርካታችን የማኅበረሰባችንን ህልውና የሚገዳደር ከሆነ፣ ግለሰቦች በፈቃደኝነት አንዳንድ ፍላጎታቸውን ሊተው ይገባል፤ ይህን በማድረጋቸውም የማኅበረሰቡ የረጅም ጊዜ ፍላጎት እንዲጠበቅ ያደርጋሉ ሲል ያስረዳል::

## የሥነ ምግባራዊ እኔነት ሙግቶች

ሥነ ምግባራዊ እኔነትን ለመደገፍ የሚቀርቡ ሙግቶች የሚከተሉት ናቸው::

1. ከራስ በላይ ለሌሎች ማሰብ በፍጹም አይቻልም::

ሀ) ከራሳችን አልፈን የሌሎችን ሰዎች ፍላጎት መርካት አንችልም፤ ለዚህም ምክንያቱ የሰዎችን ፍላጎት አለማወቅና ፍላጎታቸውንም ለማርካት ዐቅም ማጣት ዋነኛው ነው::
ለ) ለሌሎች ሰዎች ፍላጎት መጨነቅ የግል ፍላጎትን ክፉኛ ሊጋፋ ይችላል::



2. ሥነ ምግባራዊ እኔነት የሰዎችን እውነተኛ የግል ፍላጎት የሚያረካ የሥነ ምግባር መርሐ ነው:: በዚህ ርእስ ሥር አምስት ንዑሳን ነጥቦች አሉ:: ይኸውም፣

ሀ) ሰው በዚህች ምድር የሚኖረው አንድ ጊዜ ብቻ ነው:: በዐጸደ ሥጋ የምንኖረው አንድ ጊዜ ብቻ ከሆነ ደግሞ፣ ይህ ሕይወት ልንኖርለት የሚገባን ውድ ሕይወት ነው::
ለ) ከራስ ፍላጎት ይልቅ ለሌሎች ሰዎች ፍላጎት የሚኖር ሰው፣ ውድ ሕይወቱን ለሌሎች ሰዎች ፍላጎት መሥዋዕት እንዲያደርግ ያደርገዋል::
ሐ) ከራስ ፍላጎት ይልቅ ለሌሎች ሰዎች ፍላጎት መኖርን የሚደግፍ ሥነ ምግባር፣ የሰውን ክቡርነት ያገናዘበ አይደለም::
መ) ሥነ ምግባራዊ እኔነት ሰዎች ሁሉ ሕይወታቸውን ፈጹም ክቡር አድርገው እንዲቈጥሩት የሚያበረታታ ሥነ ምግባራዊ መርሐ ነው::

ስለዚህ ሥነ ምግባራዊ እኔነት ልንቀበለው የሚገባን የሥነ ምግባር መርሐ ነው::

3. ሥነ ምግባራዊ እኔነት ሰዎች ሁሉ የሚቀበሉትን ግብረገባዊ አካሄድ፣ መሠረት ያደረገ ነው::

ሰዎችን መጕዳት ትክክል ያልሆነው፣ ሰዎች እኛን እንዲጐዱን ባለመፈለጋችን ነው:: እውነትን መነጋገር እንፈልጋለን፤ ይህ የሆነበት ምክንያት ሰዎች እንዲያምኑንና እኛም ሰዎችን ማመን ስለምንፈልግ ነው:: ልክ እንደዚሁ ሁሉ ለሁለት ሰዎች እኩል ጥቅም ሊያመጣ በሚችል ኮንትራት ወይም ኪዳን ውስጥ መሳተፍ እንፈልጋለን:: ከዚህ የምንማረው ነገር ሥነ ምግባራዊ እኔነት ሰዎች እርስ በርሳቸው እንዳይጐዳዱ (እንዳይበዳደሉ)፣ እንዳይወሻሹ፣ ኪዳናቸውን ወይም ስምምነታቸውን እንዳያፈርሱ የሚያደርግ የሥነ ምግባር መርሐ ነው:: ይህ ደግሞ እውነት ከሆነ፣ በሥነ ምግባራዊ እኔነት ውስጥ መጠቃቃት ወይም መበዳደል ቦታ አይኖረውም:: አንድ ሰው የእኛን ፍላጎት መሥዋዕት አድርገን ለሌሎች ሰዎች ፍላጎት ማደራችን ፍላጎታችንን የሚያረካ መስሎ ከታየን ለግለሰቡ ያሰብነውን መልካም ነገር ማድረግ እንችላለን፤ ይህ ሁኔታ ደግሞ በአብዛኛው ሰዎችም እንደኛው መልካም ነገር እንዲያደርጉልን መንገድ ይጠርጋል::

## የሥነ ምግባራዊ እኔነት የሚታዩበት ችግሮች

የሥነ ምግባራዊ እኔነት በርካታ ችግሮች ያሉበት የሥነ ምግባር መርሖ ነው:: ከታች የተዘረዘሩትን የሙግት ነጥቦች ብቻ ሳይሆን፣ ተጨማሪ እንከኖችንም ነቅሶ ማውጣት ይቻላል::

1. ሥነ ምግባራዊ እኔነት በራሱ ሌላ የሥነ ምግባር መርሖ ሳይጠቀም በግለሰቦች ወይም በተለያዩ ቡድኖች መኻል የሚከሠተውን የፍላጎት ተቃርኖ መፍታት አይችልም:: የእኔ ፍላጎት ከሌላው ሰው ጋር ቢቃረን፣ ቅራኔውን እንዴት መፍታት ይቻላል? ሥነ ምግባራዊ እኔነትን የሚደግፉ ሰዎች፣ ይህን መሰሉን ቅራኔ ለመፍታት መሠረት የሚያደርጉት ራሱን የሰዎችን ፍላጎት ነው:: ነገር ግን የግለሰቦች ፍላጎት እርስ በርሱ አይቃረንም ብሎ ማሰብ ቂልነት ነው:: እንግዲያው ሥነ ምግባራዊ እኔነት የግበረገብ መርሖ ሆኖ እንዲዘልቅ ይህን መሰሉን መሠረታዊ ጥያቄ መመለስ የግድ ይኖርበታል::

2. ሥነ ምግባራዊ እኔነት ላይ የሚታየው ሌላው ችግር (እንከን) ሥርዐት አልበኝነት (ararchy) ነው:: ሰዎች ሁሉ ሥርዐት ያላቸው ሰዎች ሆነው ይቀጥላሉ ብሎ ማሰብ እጅግ አስቸጋሪ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች/ በኀጢአት የተበላሹ፣ ምግባራቸውም የዘቀጠ በመሆኑ፣ ስግብግብነታቸው፣ ዐመፀኝነታቸው አደብ ይገዛል ብሎ ማሰብ አሰቸጋሪ መሆኑን የገልጻል:: የሰዎች ክፉ ፍላጎት ሊገራ የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ሲገራው ብቻ ነው::

3. ሥነ ምግባራዊ እኔነት በዘፈቀደ የሚንቀሳቀስ የሥነ ምግባር መርሖ ነው:: በሁለት ጉሦች መኻል የፍላጎት ለዩነት ቢፈጠር፣ አንዱን ሊኰንንና ሌላውን ሊያደድቀ የሚችልበት አንዳችም መስፈርት ስለማይኖረው የአንዱ ጕሣ (ፍላጎት) ይብለጥ የማይባልበት አንዳችም ምክንየት የለም:: በዘር፣ በቈዳ በባህል ወዘተ መካከል የሚፈጠሩት እኔ እበልጥ እኔ እበልጦችን በዚህ ቦታ በአስረጅነት ልንጠቅሳቸው እንችላለን:: በዘረኝነትና (racism) በኢሴማዊነት (anti-semitism) ርዕዮተ ዓለሞች (ideologies) ሥር ያሉ ሰዎች፣ እነርሱ የሚደግፉት ቡድን ከሚጠሉት ቡድን ፍላጎት እንደሚበልጥ ይገልጻሉ:: በአጠቃላይ ሥነ ምግባራዊ እኔነት፣ ሰዎችን ቢያንስ በሁለት ተቃራኒ ጐራዎች የሚመድብ ሥነ ምግባራዊ ሥርዐት ነው::

4. ሥነ ምግባራዊ እኔነት ግለሰቦች የራሳቸውን ፍላጎት በማርካት በአንጻሩ ደግሞ የሌሎችን ሰዎች ፍላጎት በማክበር ይኖራሉ በሚል የተሳሳተ ግንዛቤ ላይ



መሠረት ያደረገ እምነት ነው፤ እንዲሁም እውነተኛ የሆነ ለሌሎች ሰዎች ፍላጎት የመኖር (altruism) ሕይወት የለም ብሎ ማሰብ ስሕተት ነው::
ይህ ጕዳይ ሁለት መሠረታዊ ችግሮች አሉበት:-
ሀ) አንዳንዴ ስለሌሎች ሰዎች ግድ ሳይለን የሌሎችን ሰዎች ፍላጎት
የሚቃረን ነገር በግብታዊነት የምናደርግበት ጊዜ ብዙ ነው::
ለ) ለሌላው በማኅበራዊ ኑሮአችን ውስጥ እንደ ባልንጀርነት፣ ጋብቻ፣ ቤተሰብነት ሕይወት ውስጥ፣ የራሳችንን ጥቅምና ፍላጎት፣ ለሌላው ሰው ስንል መሥዋዕት እናደርጋለን:: ምናልባት ሥነ ምግባራዊ እኔነትን የሚደግፉ ሰዎች፣ ፈቅደህ እስካደረግኸው ድረስ ፍላጎትህን ያረካል፤ ይህም ሥነ ምግባራዊ እኔነት ነው ሊሉ ይችላሉ:: ነገር ግን ይህ ሁኔታ ከራስ ፍላጎትና ጥቅም በፊት የሌሎችን ሰዎች ፍላጎት ማርካት (altruism) እንጂ፣ ሥነ ምግባራዊ እኔነትን መሠረት ያደረገ አይደለም:: ይህ ጕዳይ ሥነ ምግባራዊ እኔነት ራሱን የቻለ የሥነ ምግባር መርሖ እንዳልሆነና አባብቂኝ ሲገጥመው በሌሎቹ የሥነ ምግባር አካሄዶች ላይ እንደሚንጠላጠል አመላካች ነው::

5. የሥነ ምግባራዊ እኔነት ደጋፊዎች፣ ቃለ እግዚአብሔር ክርስቲያኖች በግል ፍላጎታቸውና ለሌላው ጥቅም በመኖር ሚዛናዊ ሕይወት እንዲኖራቸው እንደሚያስተምር ሊያውቁ ይገባል:: ሰዎች እንደኛው ሰዎች ስለሆኑ ፍላጎታቸውን ማርካት እንዳለብንና የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት በመሆናችን የእርሱን ፋና በመከተል ለሌሎች ፍላጎት ማደር እንዳለብን እናውቃለን:: ክርስቲተያኖች ሌሎችን እንዲያገለግሉ የተጠሩ ሰዎች ናቸው፤ ይህም ከራሳቸው ፍላጎት በበለጠ የሌሎችን ፍላጎት እንዲያሟሉ ይጠበቅባቸዋል:: መጽሐፍ ቅዱስ ለራስና ለሌላው ፍላጎት በመኖር ዙሪያ ሚዛናዊ የሆነ ትምህርት አለው::

## የበለጠ መልካምነት ለበለጠ ቊጥር

"የበለጠ መልካምነት ለበለጠ ቊጥር" የተባለው የሥነ ምግባር አካሄድ፣ ውጤት ተኰር ሥነ ምግባር ነው፤ ይኸውም የግብረገብ እኩይነትና ሠናይነት የሚበየነው በሚያስከትለው ውጤት ነው:: እንዲያውም አንዳንዴ ውጤት ተኰር ሥነ ምግባር ከውጤት ተኰር ሥነ ምግባር ጋር በተለዋዋጭነት ሥራ ላይ ሲውል ይታያል:: ይህ ሊሆን የቻለበት አንዱ ምክንያት፣ "የበለጠ መልካምነት ለበለጠ ቊጥር የሚለው" የግብረገብ አካሄድ ለውጤት ትልቅ ትኩረት ስለሚሰጥ ነው::

የዚህ ሥነ ምግባር ጠንሳሽ የሚባለው ጀርሚ ቤንትሃም (1748-1832) የተባለው ሰው ሲሆን፣ ጥንስሱን በማጕልበት ቀዳሚው ን ስፍራ የያዘው ሰው ደግሞ

ጆን ስትዋርት ሚል (1806-1873) የተባለው ሰው ነው:: ቤንትሃም ይህንን የሥነ ምግባር አካሄድ የሰዎችን ደስታ ከመፍጠርና ሕመምን ከመቀነስ አኳያ ሲያብራራው (ይህ በእንግሊዝኛው Hedonistic Utilitarianism ይባላል፤ ይህ ማለት ትክክለኛ የሚባለው ግብረገብ ደስታን የበለጠ የሚያሳድገውና ሕመምን የበለጠ የሚቀንሰው ግብረገብ ነው)፣ ጆን ስትዋርት ሚል ደግሞ ይህን መርሖ፣ ደስታን ከመሻትና ሕመምን ከመቀነስ አኳያ ብቻ ሳይሆን ርእሰ ጉዳዩን ሰፋ በማድረግ፣ "የበለጠ መልካምነት ለበለጠ ቊጥር" ወደሚል አጠቃላይ መርሖ ቀየረው:: በአጠቃላይ የበለጠ መልካምነት ለበለጠ ቊጥር የሚለው የሥነ ምግባር አካሄድ፣ በመርሖ ላይ መሠረት ያደረገ ቋሚ መመሪያ ሳይሆን፣ እንደ ሁኔታው የሚቀያየር የሥነ ምግባር መመሪያ ነው::

በአሁኑ ጊዜ በሚካሄዱ የሥነ ምግባር ውይይቶች ላይ በጒልሕ የሚታየው አካሄድ ይህ ሥነ ምግባር አካሄድ ነው:: በምዕራቡ ዓለም ሥነ ምግባርን አስመልክቶ የሚተላለፉ ውሳኔዎች ይህን መርሖ መሠረት ያደረጉ ናቸው:: በቊጥር ሦስት ላይ የቀረቡት ሰው፣ ይህን መርሖ መሠረት አድርገው ነው ውርጃ እንዲፈቀድ የሚጠይቁት:: ውርጃ ለበርካታ ሰዎች የተሻለ ወጤት ያመጣል፣ ስለዚህ የዚህ መርሖ ተከታዮች ውርጃ መፈቀዱ ትክክለኛ የሆነ የሥነ ምግባር ወሳኔ ነው ብለው ያምናሉ::

## የመለጠ መልካምነት ለበለጠ ቊጥር በርካታ ተከታዮች ሊያፈራ እንዴት ቻለ?

ይህ የሥነ ምግባር አካሄድ በርካታ ደቀ መዛሙርት ያፈራባቸው የተወሰኑ ምክንያቶች አሉ:: አንደኛ:- በአንጻራዊነት ሲታይ ይህን መርሖ ተግባራዊ ማድረግ (ወደ ሥራ መቀየር) ከሌሎቹ ይልቅ ቀላል ነው:: የዚህ መርሖ ተከታይ የሆነ ሰው እንዲያደርግ የሚጠበቅበት ነገር፣ ሊሆን ይችላል ብሎ የሚያስበውን አዎንታዊ ውጤት ሊከሠት ከሚችለው አሉታዊ ውጤት ጋር በማነጻጸር፣ አወንታዊው ውጤት ከበለጠ ድርጊቱ ሠናይ ሲሆን፣ የሚያንስ ከሆነ ግን ድርጊቱ እኩይ ነው:: ሁለተኛ:- ይህ የሥነ ምግባር አካሄድ፣ የመርሖ ተኰርን "ግትርነት" በማስወገድ፣ መርሖ ላይ የሙጥኝ ብሎ መርሖውን ተከትለው የሚመጡትን አሉታዊ ውጤቶች እንድንቀበላቸው ያደርጉናል:: ይህ ደግሞ የሰዎችን ጥቅም በመርሖ መሰዊያ ላይ እንደ መሰዋት የሚቈጠር ነው:: ሦስተኛ:- ይህ የሥነ ምግባር አካሄድ ግብረገባዊ ሕግጋትን ከመለኮት መገለጥ ጋር አያያይዛቸውም:: ይህ ደግሞ ሃይማኖት እየተወገዘ ዓለማዊነት እየተወደሰ በመጣበት ዓለም የዘመናዊነት መለያ ባሕርይ እንዲሆን አድርጎታል:: አራተኛ:- ማንኛውም ሰው በተፈጥሮ ዕውቀቱ (*በጭልታ ዕውቀቱ*) ሠናይነት እንደሚያሸልም እኩይነት እንደሚያስቀጣ ያውቃል:: ስለዚህ መርሖ ተኰር የሆነውን የሥነ ምግባር አካሄድ



ከመከተል ይልቅ፣ ይህንን መርሖ መከተል ሰዎች ለእኩይ ምግባራቸው ከለላ ያገኙ ስለሚመስላቸው ነው::

## የበለጠ መልካምነት ለበለጠ ቊጥር የሚታዩበት ችግሮች

የበለጠ መልካምነት ለበለጠ ቊጥር የሚባለው የሥነ ምግባር አካሄድ ከሚታዩበት ችግሮች መኻል ጥቂቶቹን እንደሚከተለው አቅርበናቸዋል:- አንደኛ:- አንድ ድርጊት የሚያስከትለው አወንታዊና አሉታዊ ጐኖችን መገመት በራሱ አስቸጋሪ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ አንዱን ሰው ይጠቅመዋል የተባለው ነገር ሌላውን ሰው ሊጐዳው ይችላል:: ሁለተኛ:- የበለጠ መልካምነት ለበለጠ ቊጥር የሚለው የሥነ ምግባር አካሄድ በቡድኖች ወይም በሰዎች መካከል ያለውን የጥቅም ሥርጭት የሚገልጽ መመሪያ የለውም:: ሦስተኛ:- የበለጠ መልካምነት ለበለጠ ቊጥር ለግለሰቦች ወይም ለውኊዳን (minorities) ጥበቃ አያደርግም፤ እንዲያውም አንዳንዴ የበለጠ መልካምነት እናመጣለን በሚል ኢፍትሓዊነት እንዲሠለጥን ያደርጋል:: ለምሳሌ:- አንድ ሠራተኛ የሚሠራበትን መሥሪያ ቤት ችግር ለሕዝብ ቢያሳውቅ የተቀሩትን ሠራተኞች ጥቅም ስላላስከበረ የግለሰቡ አካሄድ እኩይ ነው:: በአንዳንድ አገሮች የነበረው የባሪያ ፍንገላ፣ የባሪያ ፈንጋዮቹንና የባሪያ አሳዳሪዎቹን ፍላጎት ማርካቱ ብቻ ሳይሆን፣ ከፍተኛ የሆነ የአገር ልማት ያመጣላቸውም አገሮች አሉ:: ከአሜሪካን ሰሜናዊው ክፍል ይልቅ የደቡባዊው ክፍል ከፍተኛ የሆነ ብልጽገና የታየው በባሮች ጒልበት ነው:: ይህን የግብረገብ አካሄድ የሚከተል ሰው ጨምሮ አንድም ሰው ባርነት ወይም የባሪያ ፍንገላ በምንም ዐይነት መልኩ ትክክል ነው ብሎ መሞገት አይችልም:: ባርነት ለአንድ አገር የተትረፈረፈ ሀብት ቢያመጣም በጥቂት ባሮች ላይ ይደርስባቸው የነበረውን ግፍ ግን ሊያጸድቅ አይችልም:: ይህ ብቻ አይደለም ባርነት የሰዎችን ክቡርነትና መብት ክፉኛ የሚጋፋ ሥርዐት ነው::

የበለጠ መልካምነት ለበለጠ ቊጥር የሚባለው የሥነ ምግባር አካሄድ፣ ውኊዳንን መጨቈኑና ብዙኃኑን መጥቀሙ ብቻ ሳይሆን፣ ይህንን ማድረግ ግብረገባዊ ግዴታ ነው::

## ስሜታዊነት

በርካታ የሥነ ምግባር ርእሰ ጉዳዮች ላይ የሚካሄዱ ክርክሮች፣ በግብረገብ ብያኔ ላይና በግል ምርጫ (ፍላጎት) ላይ የሚካሄዱ ክርክሮች ናቸው:: አንዳንድ ሰዎች ውርጃ ትክክል አይደለም ሲሉ፣ ውርጃ ኢግብረገባዊ ድርጊት ነው ማለታቸው ሳይሆን፣ እኔ በግሌ አልወደውም ማለታቸው ነው (አልወደውም እንደሚባለው የምግብ ዐይነት ማለት ነው):: ስለዚህ ግብረገብ እንደ ምግብ ጣዕም በሰዎች ፍላጎት ላይ መሠረት ያደረገ ነው የሚሉ ሰዎች፣ አንድ የተወሰነ ግብረገብ ትክክል አይደለም ሲሉ፣

ድርጊቱን እወደዋለሁ ከማለት ያለፈ አይደለም። እንደዚህ የግብረገብ አካሄድ፣ የግብረገብ መስፈርት ያለው በተመልካቹ ዐይን ላይ ነው። በግብረገባዊ አንጻራዊነት ላይ የሚታዩት ችግሮች ሁሉ (በተለይም *ግላዊ ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት፤ ሥነ ምግባራዊ ኅሊናዊነት*) በዚህም የግብረገብ አካሄድ ላይ ይታያሉ። በተጨማሪም ሙግቶቹን ለማጽናት *በዲበ አካላዊ ሥነ ምግባርም* ላይ መሠረት ያደርጋል።

እንደ ስሜታዊነት አስተሳሰብ፣ ግብረገባዊ ቋንቋዎች አንድ ሰው በግብረገብ ላይ ያለውን ስሜት ከመግለጽ ያለፈ ትርጒም የላቸውም። ግብረገብን በተመለከተ ትክክልና ስሕተት የሚባል ነገር የለምና።

ስሜታዊነት እንደ ግብረገብ ንድፈ ሐሳብ መሠረቱን የጣለው በዴቪድ ሒዩም (David Hume) ፍልስፍና ላይ ነው። ለዴቪድ ሒዩም ግብረገብ እውነታ ያለው ነገር ሳይሆን ስሜት ነው።

በግላዊ ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነትና በስሜታዊነት መኻል ያለው ጕልሕ ልዩነት የሚከተለው ነው:- ለስሜታዊነት ግብረገባዊ ብያኔዎች እውነታን መሠረት ያደረጉ ሳይሆን፣ ስሜታዊ ገለጻዎች ብቻ ናቸው። ለግላዊ ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት ግን አንድ ምግባር ስሕተት ነው ሲባል፣ እኔ በግሌ ያንን ምግባር አውግዤዋለሁ (ጠልቼዋለሁ) ማለት ነው። ስለዚህ ስሜታዊነት ከግላዊ ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት ይልቅ የተወሳሰበ ፅንሰ ሐሳብ ነው። የጋራ ነጥባቸው ግብረገባዊ እውነታዎች ነባራዊ ሳይሆኑ ኅሊናዊ ናቸው፤ ነባራዊም የሆነ የግብረገብ እውነት የለም የሚለው ነው።

## አርኤቲክ ሥነ ምግባር

አርኤቲክ የሚለው ስያሜ የተወሰደው ከግሪክ ቃል ሲሆን የእንግሊዝኛ አቻ ቃል (Virtue) የሚለው ቃል ነው። የአርኤቲክ ሥነ ምግባር ትልቅ ትኩረት የሚያደርገው በድርጊት ላይ ሳይሆን ድርጊቱ በሚያከናውነው ሰው ላይ ነው። አርኤቲክ ሥነ ምግባር ከአፍላጦንና ከአርስጣጣሊስ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በርካታ ደጋፊዎች አሉት። ኤፊቆሮሳችና ኢስጦኢኮችን ጨምሮ ወንጌላትና ቶማስ አክዊናስ ለአርኤቲክ ሥነ ምግባር ሰፊ ትኩረት ይሰጡ ነበር።

አንዳንድ የሥነ ምግባር ምሁራን አርኤቲክ ሥነ ምግባር ራሱን ችሎ የሚቆም የሥነ ምግባር መርሖ ነው ሲሉ፣ አንዳንድ ምሁራን ግን አርኤቲክ ሥነ ምግባር (የባሕርይ ቀረጻና) ግብረገባዊ መርሖች እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚሄዱ ናቸው ይላሉ። ከመለኮት ትእዛዝና ከተፈጥሮ ሕግ መርሖ ተኰር ሥነ ምግባር ትክክል መሆኑ



የምንረዳው ያህል አርኤቲክ ሥነ ምግባርንም ችላ ልንለው አንችልም። ምክንያቱም የባሕርይ ቀረጻ በሐዲሳት ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት ስለሚገኝ።

በአርኤቲክ ሥነ ምግባርና በምግባረ ተኰር ሥነ ምግባር መካከል ያለው ትልቅ ልዩነት፣ አርኤቲክ ሥነ ምግባር መሆን ላይ ትኩረት ሲያደርግ ምግባረ ተኰር ሥነ ምግባር ግን፣ በማድረግ ላይ ትኩረት ያደርጋል[2]። በአርኤቲክ ሥነ ምግባር ከድርጊቱ ይልቅ አድራጊው ትልቅ ቦታ ተሰጥቶታል። አርኤቲክ ሥነ ምግባር የባሕርይ ተኰር ሥነ ምግባር እንጂ ምግባረ ተኰር ሥነ ምግባር አይደለም። የአርኤቲክ ሥነ ምግባር ደጋፊዎች ምግባረ ተኰር ሥነ ምግባር በሥነ ምግባር የታነጹ ሰዎችን ሊያፈራ አይችልም በሚለው ነጥብ ላይ አጥብቀው ይሞግታሉ። አንድ ሰው ግብረገባዊ ሕግጋትን ተከትሎ ነገር ግን ሕግጋቱን የተከተለው በጠማማ ልብ ሊሆን ይችላል።

## አርኤቲክ ሥነ ምግባርና ምግባረ ተኰር ሥነ ምግባር

የአርኤቲክ ሥነ ምግባር ደጋፊዎች፣ በምግባር ተኰር ሥነ ምግባር ይታያል የሚሉት ችግሮች የሚከተሉት ናቸው። አንደኛ:- ምግባረ ተኰር ሥነ ምግባር ምናልባትም ሰዎች በሕይወታቸው ዘመን ሊገጥማቸው በማይችሏቸው ግብረገባዊ ግራመጋባቶች ላይ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል። በዚህም ምክንያት በዕለት ተዕለት የሚያጋጥሙ ግብረገባዊ ጕዳዮች ተዘንግተዋል። ሁለተኛ:- ግብረገብ ምግባርንና ቅን ልቡናን ያካተተ ነው። በምግባረ ተኰር ሥነ ምግባር አንድ ሰው ማድረግ ያለበትን ነገር አድርጎ ነገር ግን ማድረግ ያለበትን ነገር ያደረገው ጠማማ በሆነ ልቡና ከሆነ ሊወደስ ነው ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ገንዘባችን እንድናደርጋቸው የተሰጡን በርካታ የመልካምነት ዐይነተኛ ባሕርያት አሉ (ገላ 5፥22-33)። ሦስተኛው:- ምግባረ ተኰር ሥነ ምግባር ሰዎች መልካሙን እንዲያደርጉ ብዙ የሚያነሣሣ አይደለም[3]። አራተኛ:- ምግባረ ተኰር ሥነ ምግባር አድርግና አታድርግ ላይ ትኩረት ስለሚያደርግ ሰዎች ማንነታቸውን እንዲደብቁና በሰው ዘንድ ብቻ ቅቡል ነው የሚሉትን ባሕርይ እንዲያንጸባርቁ ያደርጋቸዋል።

---

[2] በአርኤቲክ ሥነ ምግባር ትልቅ ቦታ ያለቸው ምሁራን የሚከተሉት ናቸው፤ Alasdair MacIntyre (*After Virtue*), Edmund Pincoffs (*Quandaries and Virtues,* University of Kansas Press, 1986), Richard Taylor (*Ethics, Faith and Reason,* New York: Prentice-Hall, 1985), Philippa Foot (*Virtues and Vices,* Blackwell, 1978), James Wallace (*Virtues and Vices,* Ithaca, New York: Cornell University Press, 1978).

[3] Pojman, *Ethics: Descovering Right and Wrong,* 116.

## በአርኤቲክ ሥነ ምግባር የሚያዩ ችግሮች

አርኤቲክ ሥነ ምግባር ከመርሖ ተኩር ሥነ ምግባር ጋር የማይቀናጅ ከሆነ የሚከተሉት ችግሮች ይታይበታል:: አንደኛ:- አርኤቲክ ሥነ ምግባር ግብረገባዊ ግራ መጋባቶችን በመፍታት አቅጣጫን የመጠቆም ዐቅም አይኖረውም:: ሁለተኛ:- አርኤቲክ ሥነ ምግባር በባሕርይ ቀረጻ ላይ ትኩረት ስለሚያደርግ፣ አንድ ሰው በግብረገብ የታነጸ ነው ለማለት ምንም መስፈርት የለውም፤ በሥራ ካልታየ በምን ይታወቃል? ሦስተኛ:- በመርሖ ላይ ሳይሆን በባሕርይ ቀረጻ ላይ ብቻ ትኩረት ካደረግን የኅብረተሰቡን ማኅበራዊ አወቃቀር መጠበቅ አንችልም::

## አርኤቲክ ሥነ ምግባርና መርሖ ተኩር ሥነ ምግባር

በርካታ የሥነ ምግባር ምሁራን፣ አርኤቲክ ሥነ ምግባር ከመርሖ ተኩር ሥነ ምግባር ጋር ሲቀናጅ ጠንካራ የሥነ ምግባር ውጤት ሊያስገኝ እንደሚችል ያስረዳሉ:: የባሕርይ ቀረጻ ያለ መርሖ ዕውር ነው፤ መርሖም ያለ ባሕርይ ቀረጻ ሰዎችን ለሠናይ ሥነ ምግባር ሊያነሣሣ አይችልም:: ነገር ግን ምሁራን አርኤቲክ ሥነ ምግባር ከመርሖ ተኩር ጋር የሚቀናጀው እንዴት ነው በሚለው ርእሰ ጉዳይ ላይ ጠንካራ ክርክር ያደርጋሉ፤ ይኸውም አርኤቲክ ሥነ ምግባር ከመርሖ የሚቀዳ ነው ወይስ ከመርሖ ጋር መሳ ለመሳ የሚቀናጅ:: የመጀመሪያው ስብጥራዊ ምልከታ (Correspondence view) ሲባል፣ ሁለተኛው ደግሞ ሙሊታዊ ምልከታ (Complementary view) በመባል ይታወቃል:: ስብጥራዊ ምልከታ ግብረገባዊ ሕግጋት አንድ ምግባር እንዲደረግ የሚያዙ ወይም የሚያስገድዱ ስለሆነ፣ በአንጻሩ ደግሞ አርኤቲክ ሥነ ምግባር በባሕርይ ቀረጻ ላይ ትኩረት ስለሚያደርግ፣ መርሖ በቀዳሚነት አርኤቲክ ደግሞ በተከታይነት ተያይዘው መሄድ አለባቸው ባይ ነው:: ሠናይ ባሕርዮች (virtues) ሕግ እንዲከበር ወይም አንድ ድርጊቱ እንዲከናወን የሚያበረታቱ ከሆነ፣ እያንዳንዱ ሠናይ ምግባር ከግብረገባዊ ሕግጋት ጋር የሚቀናጁና ግብረገባዊ ሕግጋቱ መልካሙ ባሕርይ እንዲታይ የሚያደርጉ ናቸው:: ስለዚህ ሠናይ ምግባሮች መልካሙ እንዲተገበር እኩዩ ደግሞ እንዲወገድ የሚያደርጉ መሣሪያዎች ናቸው:: እንደ ሙሊታዊ ምልከታ ደግሞ አንዳንድ ግብረገቦች መልካም ሥራን አንዳንዶቹ ደግሞ ሠናይ ባሕርይን ወይም ቅን ልቡናን የሚፈልጉ ናቸው:: ትክክለኛ የሆነውን ምግባር ትክክለኛ በሆነ መንገድና ልቡና ማድረግ አስፈላጊ ከሆነ፣ ሠናይ ባሕርይ መልካም ነገር እንዲደረግ የሚያበረታታ ጉዳይ ተደርጎ መወሰዱ ስሕተት ነው::

ግብረገባዊ አንጻራዊነትን በሚቀጥለው ምዕራፍ በስፋት የምንመለከተው ጉዳይ ስለሚሆን ርእሰ ጉዳዩን በዚህ ቦታ አናነሣውም::

# 4

# ግብረገባዊ አንጻራዊነት

## "በሌላው ላይ የምትፈርድ አንተ ማነህ!"[1]

ሥነ ምግባርን አስመልክቶ አንድ ታላቅ ውይይት ይካሄዳል:: በፕሮግራሙ ላይ በርካታ ሰዎች ታድመዋል:: ለመድረክ ውይይት የተጋበዙት ግለሰቦች የዳበረ የሕይወት ተሞክሮ ያላቸው፣ በቀለሙም ትምህርት አንቱታን ያተረፉ፣ አንዳንዶቹም ስመ ጥር ናቸው በሚባሉት ታላላቅ የትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚያስተምሩ፣ አንዳንዶቹም ጉባኤው በከተመበት ርእሰ ጉዳይ ላይ የመማሪያ መጻሕፍት የጻፉ ናቸው::

የመድረኩ መሪ የተለያዩ ጥያቄዎችን ለውይይት የተጋበዙትን እነዚህን ምሁራን ይጠይቃል፤ እነርሱም እንደ አተያያቸው የተለያየ መልስ ይሰጣሉ:: መልስ ከሰጡት ምሁራን መኻል አንዱ እየተናገሩ ያሉበት ርእሰ ጉዳይ፣ ወሲብን አስመልክቶ የሚታተሙትን ሥዕሎች፣ ፎቶ ግራፎች፣ ቪዲዮ ካሴቶች ወዘተ በተመለከተ መንግሥት ጥብቅ ቊጥጥር ማድረግ እንዳለበት፣ እንዲህ ዐይነት ዝንባሌ ባላቸውም መጽሔቶችና መጻሕፍት ላይ ገደብ መጣል እንደሚገባው የሚያስጠነቅቅ ነበር::

ምሁሩ ይህን ጉዳይ እያስረዱ፣ የሚያመጣውን መዘዝ በማስረጃ እያጕለበቱ ሳለ፣ በጉባኤው ከታደሙት ሰዎች መካከል አንዲት ሴት እጃቸውን ያወጣሉ፤ እጅ አወጣጣቸው ጥያቄ ለመጠየቅ ወይም አስተያየት ለመስጠት የሚወጣው ዐይነት ሳይሆን የብስጭት ቢጤ ነበር:: የመድረኩ መሪ ሴትየዋ ጥያቄአቸውን እንዲያቀርቡ ዕድል ይሰጣቸዋል:: ሴቲቱም በቊጣ፣ "በሌላው ላይ የሚፈርዱ እርስዎ ማንነዎት?" ሲሉ የወሲብ ሥዕሎች፣ ቪዲዮ ካሴቶችና መጣጥፎች ላይ ምሁራዊ አስተያየት ሲሰጡ የነበሩትን ሰው ይጠይቃሉ::

የሴትየዋ ጥያቄ መልስ ፈላጊ ጥያቄ አልነበረም፤ መልስ በማይፈልግ ፈሊጣዊ አነጋገር አስተያየታቸውን የሚያስረዳ እንጂ:: ተናጋሪዋ እያሉ ያሉት፣ "ምሁሩ በግለሰብም ሆነ በማኅበረ ሰብ ላይ፣ ግብረገባዊ ብያኔ ለመስጠት መብት የላቸውም" የሚል ነው:: ጥያቄው መልስ ፈላጊ ባይሆንም ፕሮፌሰሩ ለሴትየዋ ተገቢ ነው ያሉትን መልስ ለመስጠት ጉሮሮአቸውን ጠራረጉ፣ "ግብረገባዊ ብያኔ ለመስጠት ሙሉ መብት

---

[1] Francis J. Beckwith and Gregory Koukl, *Relativism* (Grand Rapids: Baker, 1998), 11.

አለኝ:: ምክንያቱም እኔ እንደ ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር አእምሮ አለኝ፤ ይህም ግብረገባዊና *አመክንዮአዊ* የሆኑትን ግብረገባዊ *መርሖዎች* ጠንቅቄ እንዳውቃቸው አስችለውኛል:: ስለማውቃቸውም ግብረገባዊ ብያኔ ለመስጠት ብቁ እሆናለሁ":: ይህ መልስ ጠያቂዋን ይበልጥ ቢያስቈጣቸውም ምሁሩ ንግግራቸውን በመቀጠል፣ "እርስዎ እኔን 'በሌላው ላይ የምትፈርድ አንተ ማነህ?' እያሉ እየፈረዱብኝስ አይደል? ይህ የእርስዎ አነጋገር እርስ በርሱ ይቃረናል እኮ!" አሏቸው::

ይህ የሴትየዋ ጥያቄ በበርካታ ሰዎች የሚነገር፣ በልባቸውም የሚታመን ነው:: ይህ አደገኛ ነገር ነው፤ ምክንያቱም ***ግብረገባዊ አንጻራዊነት*** ነውና:: ግብረገባዊ አንጻራዊነት ግብረገብን በተመለከተ ዓለም ዐቀፋዊ የሆነ፣ በየትኛውም ጊዜ፣ ቦታና ግለሰብ ዘንድ ተግባራዊ መሆን የሚገባው እንዲሁም ምክንያታዊ የሆነ ሠናይም ሆነ እኩይ ግብረገባዊ መሠረት የለም የሚል ነው:: ስለዚህ ግብረገባዊ አንጻራውያን፣ እውን መሆን ያለባቸው ግብረገባዊ መስፈርቶች ሳይሆኑ፣ የግለሰቦች አመለካከት ወይም ስምምነት ነው ባዮች ናቸው፤ ይኸውም እወደዋለሁ እንደሚባለው የእግር ኳስ ቡድን፣ ጸሓፊ ተውኔት፣ የፊልም ተዋናይ ወይም የመጠጥ ዐይነት ማለት ነው::

በጉባኤው የነበሩት ሴት ግብረገባዊ አንጻራዊነትን ደግፈው መናገራቸውን ልብ አይሉት ይሆናል፤ ይሁን እንጂ፣ አስተሳሰባቸው ግብረገባዊ አንጻራዊነትን መሠረት ያደረገ ነበር:: ተማሩ ተመራመሩ የምንላቸው አብዛኞቹ ምሁራን፣ "መቻቻል"፣ "የተከፈተ አእምሮ" እንዲሁም "ፈራጅ አለመሆን" በሚለው የግብረገባዊ አንጻራዊነት መንጠቆ ብዙዎችን አጥምደዋል:: እነርሱም ቢሆኑ የነገሩን *ምክኑያዊነት* በቅጡ ያጤኑት አይመስልም::

አንጻራዊነት እንደ አውሮፓና አሜሪካ ባሉ አንዳንድ ሕዝቦች ዘንድ ስውር *አንቀጸ ሃይማኖት (creed)* ነው ቢባል፣ እብለትም ሆነ ግነት አይሆንም[2]:: በተለይ ደግሞ በትምህርትና በሕገ መንግሥት ውስጥ አንጻራዊነት ደምቆ ይታያል:: እጅግ ብዙ ሰዎች በማናቸውም ጊዜ፣ በየትኛውም ቦታና ለማንኛውም ሰው የሚሆን፣ ነባራዊ የሆነ ግብረገባዊ ፋይዳ የለም የሚል፣ የጸና እምነት አላቸው:: ከዚህም የተነሣ በማኅበረ ሰብ ውስጥ ያለውን ግብረገባዊ ብያኔ በተመለከተ፣ "ይህ የኔ፣ የግሌ አመለካከት ነው" ወይም፣ "በማንኛውም ሰው ባሕርይ ላይ ልበይን አልችልም" አልያም፣ "አንተ ነገሩን ትክክል ነው የምትል ከሆነ ትችላለህ፤ ነገር ግን እኔ በግሌ ከዚህ ተቃራኒውን አመለካከት እደግፋለሁ" የሚል አቋም አላቸው[3]::

[2] Allan Bloom, *The Closing of the American Mind* (New York: Simon and Schuser, 1987), 25.

[3] ዝኒ ከማሁ::



ፕሮፌሰር አለን ብሉም የተባሉ ሊቅ፣ "ዘ ክሎዚንግ ኦፍ አሜሪካን ማይንድ" በተባለው ስመ ጥር መጽሐፋቸው፣ "ግብረገባዊ አንጻራዊነት የኮሌጅ ተማሪ በሆኑ አሜሪካውያን ዘንድ፣ *ንድፈ ሐሳባዊ (ትውርታዊ)* እይታ ሳይሆን፣ ግብረገባዊ አቋም ወይም የነጻ ሕዝብ ትክክለኛና ዐይነተኛ ባሕርይ ተደርጎ ይታሰባል:: ከዚህም የተነሣ ስሕተትን ለማረም መፈለግ እንደ ትክክለኛ ርምጃ ተደርጎ አይወሰድም" ብለዋል[4]::

በጕዳዩ ላይ ብርሃን ሊፈነጥቅበት የሚችል በአንድ ያከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ፣ በአንድ አስተማሪና በተማሪዎች መካከል የሚካሄድ አንድ የውይይት ናሙና እናቅርብ[5]:-

መምህር:- ጤና ይስጥልኝ ተማሪዎች፤ እንደምን ናችሁ:: ይህ የትምህርታችን የመጀመሪያው ክፍለ ጊዜ ነው፤ ስለዚህ ለዚህ መንፈቀ ዓመት መመሪያ የሚሆነንን፣ አንዳንድ መሠረታዊ መርሖችን ማስቀመጥ እፈልጋለሁ፤ አንደኛ ማንኛውም ሰው እውነት እኔ ዘንድ ነች ማለት ስለማይችል፣ የባልንጀሮቹን አመለካከት በተከፈተ ልብ ሊሰማ ይገባዋል፤ ሁለተኛ እእእ... ኤልሳቤጥ ጥያቄ ያለሽ ትመስያለሽ...

ኤልሳቤጥ:- አዎን መምህር ጥያቄ አለኝ:: ሰዎች ሁሉ እውነታ ከሌላቸው፣ ባልንጀሮቼን መስማት ያለብኝ ምክንያት ምንድን ነው? በሰዎች ሁሉ ዘንድ እውነት ከሌለ የሰዎችን እውነት አልባ አመለካከት በማድመጥ፣ ጊዜዬን የማቃጥልበት ምክንያት ምንድን ነው?

መምህር:- ኤልሳቤጥ እውነትን ማወቅ እችላለሁ እያልሽኝ ነው? እውነትን ማወቅ እችላለሁ ብሎ ማሰብ ግትርነት ምናልባትም ብልግና አይሆንምን?

ኤልሳቤጥ:- አይሆንም! እንዲያውም በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ እውነትን አያውቁም ማለት ግትርነት ምናልባትም ብልግና ነው ባይ ነኝ:: ኧረ ለመሆኑ በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ እውነት እንደሌላቸው ተፈትሾአል? ካልሆነ ይህን ልንል እንዴት እንችላለን:: ለማምንበት ነገር ምክኑያዊ መልስ መስጠት ከቻልሁ፣ እውነትን መጨበጤ እሙን ነው:: ይህንንም እውነት ለእናንተ አካፍላለሁ:: ይህን ካሟላሁ እናንተ እኔን የማትሰሙበት ምክንያት የለም:: እውነት እንዳለኝ ሳይረጋገጥ፣ "እውነት ማወቅ እችላለሁ እያልሽ ነው?" መባሉ ትክክል

[4] ዝኒ ከማሁ::

[5] Francis J. Beckwith and Gregory Koukl, *Relativism* (Grand Rapids: Baker, 1998), 74.

አይመስለኝም:: በዚህ መንገድ ከሆነ፣ አንዱ የሌላውን አመለካከት ማድመጥ እንደሚገባው እምናለሁ::

መምህር:- በርግጥ ይህ መንፈቀ ዓመት አስደሳች እንደሚሆን ባለ ሙሉ ተስፋ ነኝ::

ሌላ ተማሪ:- "በርግጥ ይህ መንፈቀ ዓመት አስደሳች እንደሚሆን ባለ ሙሉ ተስፋ ነኝ" የሚለው አነጋገር ራሱ እውነት ነውን? (ተማሪዎቹ ሁሉ ከት ከት ብለው ሳቁ)::

ከዚህ ናሙናዊ ቅኝት የምንማረው፣ አንጻራዊነት የምዕራቡን ዓለም ባህል ከፉኛ ተቈጣጥሮት እንደሚገኝ ነው::

ይህ የአንጻራዊነት አመለካከት በአገራችን በኢትዮጵያም መሠረቱን ከጣለ ውሎ አድሮአል:: ይህን ርእሰ ጕዳይ በስፋት እንድንመለከተው የፈለግንበትም ምክንያት ይኸው ነው::

*ግንዛቤያዊ (cognitive)* እንዲሁም ግብረገባዊ የሚባሉ የአንጻራዊነት ጐራዎች ቢኖሩም፣ እኛ የምንቃኘው፣ የመጽሐፉ ርእሰ ጕዳይ በሆነው በግብረገባዊ አንጻራዊነት ላይ ነው::

# 41

## ግብረገባዊ አንጻራዊነት ምንድን ነው?[1]

የግብረገባዊ አንጻራዊነትን *ግላጼ* ከማየታችን በፊት፣ *ግብረገባዊ እውነታና ምክኑያዊ እውነታ* እንዲሁም *ኅሊናዊ እውነታና ነባራዊ እውነታ* ምን እንደ ሆኑ በአጭሩ እንመልከት:: ይህም ግላጼውን በትክክል እንድንረዳው ጥሩ ጅማሮ ይሆናል::

### ግብረገባዊ እውነታና ምክኑያዊ እውነታ

ግብረገባዊ እውነታንና ምክኑያዊ እውነታን ሊያስረዱ የሚችሉ፣ ሁለት ዐረፍተ ነገሮችን እንመልከት:- 1. "አንድ ሰው በደል አልባ የሆነውን ሰው ሊገድል አይገባውም" 2. "አንድ ሰው ጅማ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚገኝ ሊያምን ይገባዋል":: እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች የተለያዩ ናቸው:: ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ትክክል ናቸው:: የመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ግብረገባዊ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ምክኑያዊ ነው:: የመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ግብረገባዊ ግዴታን ሲያመለክት፣ ሁለተኛው ዐረፍተ ነገር ደግሞ ምክኑያዊነትን መሠረት ያደረገ ነው::

በአንድ ርእሰ ጕዳይ ላይ ሁለት ዐይነት ስሕተት ልንፈጽም እንችላለን:: ምክኑያዊ ባለመሆን ልንሳሳት እንችላለን አልያም፣ ኢግብረገባዊ በመሆን አግባብ ያልሆነ ነገር ልንፈጽም እንችላለን:: ግብረገብ ትኩረት የሚያደርገው በሁለተኛው ነጥብ ላይ ነው::

ምክኑያዊ ስሕተት ከግብረገባዊ ስሕተት የሚለየውም በዚህ መልኩ ነው::

### ኅሊናዊ እውነትና ነባራዊ እውነት

ግብረገባዊ እውነትና ምክኑያዊ እውነት እንዳለ ሁሉ፣ *ኅሊናዊ (Subjective) እውነትና ነባራዊ (objective) እውነትም* አለ:: አንድ ሰው፣ "የጎመን ወጥ እወዳለሁ" ቢል፣ ግለሰቡ በምግቡ ላይ ያለውን የራሱን አስተያየት (ጣዕም) እየተናገረ እንጂ፣ ስለ ጎመን ወጥ እየተናገረ አይደለም:: ይህ ኅሊናዊ እውነት ይባላል:: አንድ ሰው ይህ

[1] Francis J. Beckwith and Gregory Koukl, *Relativism* (Grand Rapids: Baker, 1998), 26-35.

ምግብ ይጣፍጠኛል፣ ያ ምግብ ደግሞ አይጣፍጠኝም ቢል፣ "እንዴት ሊጣፍጥህ ወይም ላይጣፍጥህ ቻለ? ይህ ትክክል አይደለም" ልንለው አንችልም::

ነገር ግን "የጣዕምን" ጉዳይ ወደ ጐን ትተን፣ ስለ ቊጥር እንነጋገር:: አንድ ሰው ሁለት ሲደመር ሁለት ይሆናል አራት ቢል፣ እየተናገረ ያለው የግሉን "ጣዕም" ሳይሆን ከግለሰቡ ውጪ ስላለው ነባራዊ እውነታ ነው::

ሁለት ሲደመር ሁለት ይሆናል አምስት ቢባል ስሕተት ነው:: ነገር ግን ስሕተት ነው ስንል፣ ግብረገብን ታሳቢ አድርገን አይደለም:: የሒሳብ ስሌቶች ሁለት መልስ ብቻ ይኖራቸዋል፤ እውነት ወይም ሐሰት:: የሒሳብ ስሌቶች በግለሰቦች "ጣዕም" የሚወሰን በርካታ (የተለያዩ) "እውነቶች" የሏቸውም:: በስሌቱ ውጤት ላይ የማንግባባ ከሆነ፣ ልዩነቱን የምንፈታው፣ በቀመሩ መሠረት ሒሳቡን እንደ ገና በማስላት ነው:: ይህን የምናደርገው ተመሳሳይ ስሜት ለመጋራት ሳይሆን፣ ትክክለኛውን መልስ ለማግኘት ነው:: የስሌቱ እውነታ ያለው ግለሰቡ ዘንድ ሳይሆን፣ ነባራዊ በሆነው ድምር ላይ ነው::

ኅሊናዊ እውነቶች መሠረት ያደረጉት በግለሰቦች ምርጫ ላይ ነው፤ ይህም ምርጫ ስሕተት ነው ወይስ ትክክል ነው የሚለውን *በአመክንዩ መመርመር* የሚቻል አይደለም:: በአንጻሩ ነባራዊ እውነታዎች በሰዎች ውስጣዊ ስሜት ላይ መሠረት ያደረጉ ስላልሆነ፣ በሁኔታዎች የሚለወጡ አይደሉም::

## የአንጻራዊነትና የፍጹማዊነት ግላጼ

ከላይ ስለ ኅሊናዊ እውነታና ስለ ነባራዊ እውነታ በተመለከትነው መሠረት፣ ግብረገባዊ እውነታዎች እንደ ምግብ ጣዕም በግለሰቦች ኅሊናዊ ብያኔ ይወሰናሉ የሚለው አመለካከት፣ ግብረገባዊ አንጻራዊነት ይባላል:: እንደ ግብረገባዊ አንጻራዊነት፣ ግብረገባዊ ፋይዳዎች በሰዎች ፍላጎት (ስሜት ወይም ጣዕም) ላይ ሙሉ ለሙሉ መሠረት ስለሚያደርጉ ግለሰቡ፣ "ይህ ለእኔ (Subject) እውነት ነው" እያለ ፋይዳዎቹን ኅሊናዊ (Subjective) ያደርጋቸዋል::

• ግብረገባዊ አንጻራዊነት፣ ግብረገባዊ ፋይዳዎች በሰዎች ወይም በግለሰቦች ፍላጎት ላይ መሠረት ያደረጉ ናቸው የሚል አመለካከት ነው:: ግብረገባዊ አንጻራዊነት ሰዎች ሁሉ ተመሳሳይ በሆኑ ግብረገባዊ ሁኔታዎች ውስጥ ሲሆኑ፣ የተወሰነን ግብረገብ ብቻ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል አይልም::



ለሁለት ሰዎች ተመሳሳይ የሆነ ግብረገባዊ ምርጫ ሲቀርብላቸው፣ አንደኛው የመረጠውን ተቃራኒ ሌላው ሊመርጥ ይችላል:: በሁሉም ሰው ላይ ተግባራዊ የሚሆን ግብረገባዊ መመሪያ የለምና:: እንዲያውም አንድ ሰው ትላንት ያደረገውን ነገር ተቃራኒ ዛሬ ቢያደርግ፣ ተሳስተሓል ማለት አይቻልም (አንዳንድ አንጻራውያን፣ ወጥነት ያለው ሕይወት ለመኖር፣ ተመሳሳይ የሆነ አካሄድ ሊኖረን ይገባል ባዮች ናቸው)::

ግብረገባዊ አንጻራዊነትን ከግብረገባዊ ፍጹማዊነት ጋር እናነጻጽረው ካልን፣ እጅጉን ለየቅል ይሆንብናል:: ቢያንስ ግብረገባዊ ፍጹማዊነት፣ ግብረገባዊ መርሖዎችን አንድ ግለሰብ ወይም የተወሰኑ ሰዎች ቢቀበሏቸውም ሆነ ባይቀበሏቸው፣ እውነትነታቸው እውነት ሆኖ እስከ መጨረሻው ይዘልቃል (ይቀጥላል) የሚል አቋም ነው:: ግብረገባዊ ሕግጋት በሰዎች ፍላጎት የሚፈጠሩ አልያም የተወሰኑ ሰዎች ወይም ባሕል የሚሽሩአቸው አይደሉም:: ቢያደርጉት እንኳ፣ ዓለም ዐቀፋዊነታቸውና ዘላለማዊነታቸው ጸንቶ ይኖራል[2]::

ግብረገባዊ ፍጹማውያን ግብረገባዊ መርሖዎች እንደ ሒሳብ ሕግጋት፣ ራሳቸውን የሚገልጡ ናቸው የሚል አቋም አላቸው:: ግብረገብን አንፈጥረውም፤ የሒሳብን ቀመር እንደምናገኘው ግብረገብንም እናገኘዋለን እንጂ::

## አንጻራዊነት ቀድሞ የነበረውን ግብረገባዊ ትንተና አይቀበልም

ግብረገባዊ አንጻራዊነት ቀድሞ የነበረውን ግብረገባዊ ሥርዐት በአዲስ መስፈርት መዝኖ፣ ከቀድሞው ፍጹም የተለየ ትርጕም የሚሰጥ ግብረገባዊ ሥርዐት ነው::

ማንኛውም ዐይነት ግብረገባዊ ሥርዐት የራሱ የሆኑ፣ ቢያንስ ሦስት መለያ ጠባዮች አሉት[3]፡- 1. ግብረገብ የሰዎችን ኀልዩ፣ ነቢብና ገቢር (አስተሳሰብ፣ አነጋገርና ምግባር) የሚወስን፣ ሥልጣናዊ መመሪያ ነው፤ ይህም የሰዎችን ምርጫ፣ ልማድ፣

---

[2] አንዳንድ ሰዎች አልበርት ኤንስታይን ማናቸውም ነገሮች አንጻራዊ ናቸው ብሎአል ይላሉ፤ ይህ ግን ስሕተት ነው:: የኤንስታይን አንጻራዊነት ትውርት (ንድፈ ሐሳብ) መሠረት ያደረገው በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ነው:: ከእነዚህም መካከል "the problems of absolute simultaneity" እንዲሁም "the idea of absolute motion" ይገኙበታል:: እነዚህም የአንጻራዊነት ንድፈ ሐሳቦች መሠረት ያደረጉት (ቢያንስ በከፊል) አንጻራዊ ባልሆኑ ነገሮች ላይ ነው፤ ይኸውም ውሱን (fixed, constant) በሆነው የብርሃን ፍጥነት ላይ ነው:: ነገር ግን እነዚህ ትውርቶችም ቢሆኑ፣ ከግብረገባዊ አንጻራዊነት ጋራ የሚገናኙ አይደሉም::
[3] ለተጨማሪ ማብራሪያ Tom L. Beauchamp, *Philosophical Ethics: An Introduction to Moral Philosohy* (New York: McGraw-Hill, 1991), 16-19 ይመለከቷል::

ፍላጎት፣ ምግባር ወዘተ ያጠቃልላል:: ስለዚህም ግብረገባዊ ጥያቄዎች በዐጸደ ሥጋ ስንኖር ከምንጠይቃቸው ጥያቄዎች ሁሉ የመጀመሪያውን ደረጃ የሚይዙ ናቸው:: 2. ግብረገብ *ተገላጭ (prescriptive) ገዕዛንን* ብቻ ሳይሆን፣ *ገላጭ (describitive) ገዕዛንንም* ያካተተ ነው::

መሆን ያለባቸውን ግብረገባዊ ግዕዛን ብቻ ሳይሆን፣ ግዕዛኑ እንዴት ተግባራዊ መሆን እንዳለባቸውም የሚያስተምር ነው:: ግብረገባዊ ግዕዛን ምግባረ ተኮር በመሆናቸው፣ ግዴታን ማዕከል ያደረጉ ናቸው:: ይህ ግዴታም ምግባርን ብቻ ሳይሆን ኀሊናን፣ *አመለካከትንና (attitudes)፣ መነሣሣትን (motives)* ይመለከታል:: 3. ግብረገብ ዓለም ዐቀፋዊ ነው:: ግብረገባዊ ሕግጋት ሙሉ ለሙሉ ተፈጻሚ የሚሆኑት በሰዎች ሁሉ ላይ፣ በማናቸውም ጊዜና ሁኔታ ነው:: አንድ የተወሰነ ምግባር ለአንድ ሰው ስሕተት ከሆነ፣ ለሌላውም ሰው ስሕተት ነው::

## አንጻራዊነት ሥነ ምግባራዊ ሥርዐት አይደለም

አንጻራዊነት፣ ከፍጹማዊነት የተለየ ራሱን የቻለ ሥነ ምግባራዊ ሥርዐት አይደለም:: በግብረገባዊ አንጻራውያንና አንዳችም ግብረገባዊ መስፈርት የለም በሚል ሰው መኻል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ቅንጣት ታህል ልዩነት የለም:: አንጻራውያን ግብረገባዊ ውሳኔዎችን የሚወስኑት እንዴት ነው? በፊታቸው መልካም መስሎ የታያቸውን:: አንድ ሰው ያላንዳች ግብረገባዊ መስፈርት ማድረግ ያለበትን ነገር እንዴት መሥራት ይችላል? በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን:: እንግዲያው አንዳችም ግብረገብ የሌለውን፣ እንደ ግብረገባዊ ሥርዐት ልንመለከተው እንዴት እንችላለን? አንድ ነገር ተቃራኒው ከሆነው ጋር አንድ ከሆነ፣ በመካከላቸው ልዩነት ሊኖር እንዴት ይችላል::

ግብረገባዊ አንጻራዊነት አንዳችም ግብረገብ የለም ከሚለው ጋር አንድ ዐይነት ስለሆነ፣ ራሱን የቻለ የግብረገብ መስፈርት ተደርጎ መወሰድ አይችልም::

## አንጻራዊነት የሚያስከትለው መዘዝ

የአንጻራዊነትን ሰንካላነት የምንፈትሽበት ሌላው መስፈርት፣ አንጻራዊነት ምን ዐይነት ሰዎችን ነው የሚያፈራው፣ በሚለው ሚዛን ነው:: አንድ ሰው ግብረገባዊ ነው የሚባለው፣ የተወሰነን ግብረገባዊ መስፈርት ተቀብሎ፣ ወጥነት ባለው መልኩ ተግባራዊ ሲያደርገው ነው::



*ግዕዝና (መርሖና)* ተግባር የተቀናጁበትን አንድ ግብረገባዊ መርሖ ለአብነት እንመልከት "ጐረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ"፤ ይህን ግብረገብ በወጥነት የተገበሩት እማሆይ ቴሬሳ፣ ሕይወታቸውን ለሌሎች አፍሰው ዐልፈዋል:: አንድ ግብረገባዊ ሥርዐት ምን ያህል ያዛልቃል የሚለውን ለመመልከት፣ ግብረገቡን የተቀበሉትን ሰዎችና የግብረገቡን "ጀግኖች" መመልከቱ አንዱ መስፈርት ነው::

"ዐመፃ ያልተቀላቀለበት ሰላማዊ ተቃውሞ" የሚለው ፖለቲካዊ አካሄድ፣ ማህታማ ጋንዲ የሕዝቤ ባላንጣዎች ናቸው ያላቸውን እንግሊዛውያንን፣ በሰላማዊ መንገድ እንዲቃወማቸው (እንዲታገላቸው) አድርጎታል:: ለብሉይ ኪዳን ንባባት ፍጹም መገዛት፣ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ያሉ ምግባረ ሠናይ ሰዎችን ያስገኛል::

ግብረገባዊ አንጻራዊነት የሚያፈራው ምን ዐይነት የሥነ ምግባር "ጀግኖችን" ይሆን? አንጻራዊነት ለሰው ልጆች ሊያስገኝ የሚችለው ነገር ምን ይሆን? የአንጻራዊነትን መርሖ በመከተል ለሌሎች አስተሳሰብ ወይም ግብረገባዊ መስፈርት ቅንጣት ያህል ግድ የማይላቸው፣ ይልቁንም የግላቸውን የግብረገብ አታሞ የሚደልቁትን ምን እንላቸው ይሆን? ምናልባት ነፍሰ ገዳይን አልያም በራሱ የቅዠት ዓለም ውስጥ የሚዳክረውን ሰው፣ እንደ ጀግና እንቈጥረው ይሆን?

አንጻራዊነት በማናቸውም የታሪክ ዘመን የተወገዘና የተናቀ ነው:: ቢያንስ ተወድሶ ወይም "ጀግና" አፍርቶ አያውቅም:: በየዘመናቱ የሚጠቀሱት ታላላቅ የግብረገብ መምህራን አንጻራዊነትን ያወገዙ ናቸው፤ ለምሳሌ ሙሴ፣ ኢየሱስ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ አርስጣጣሊስ፣ ጋንዲ፣ ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ እማሆይ ቴሬሳ::

አንዳንድ አንጻራውያን፣ "አንዳችም ግብረገብ የሌለው ሰው ነው" እንዲባሉ አይፈልጉም፤ "እኔ የራሴ የሆነ ግብረገብ አለኝ፤ ያሻኹትንም አደርጋለሁ፤ የእኔ ግብረገብ ይህ ነው" ይላሉ:: ነገር ግን ግብረገብ የሚባለው ትክክለኛ የሆነውን ነገር ማድረግ እንጂ፣ ያሻንን ነገር ማድረግ አይደለም::

4.2

# የአንጻራዊነት ጐራዎች[1]

ሦስት ዐይነት የአንጻራዊነት አመለካከቶች አሉ:: እነርሱም:- *ባህላዊ (ተገላጭ) አንጻራዊነት፣ ዐዋጃዊ (ግዕዛዊ) ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት እንዲሁም ግላዊ ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት (ሥነ ምግባራዊ ኀሊናዊነት)* ይባላሉ:: የመጀመሪያው ጐራ የግብረገብ ሳይሆን *የባህል ወይም የሥነ ሰብ ጥናት* ነው:: የተቀሩት ሁለቱ፣ ግብረገባዊ ብያኔዎችን ኀሊናዊ የሚያደርጉ አመለካከቶች ናቸው:: ይኸውም ግብረገባዊ ድንበሮችን የሚወስነው ማነው በሚለው ላይ መሠረት ያደረጉ ናቸው:: ዐዋጃዊ (ግዕዛዊ) ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት፣ ግብረገባዊ ፋይዳን የሚወስነው ኅብረተሰቡ ነው የሚል አቋም ነው:: ግላዊ ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት ደግሞ፣ ግብረገባዊ ብያኔ መስጠት ያለበት በእያንዳንዱ ግለሰብ ነው የሚል አመለካከት ነው:: እንደዚህ አመለካከት የእያንዳንዱን ግለሰብ ምርጫ የሚወስነው፣ ማኅበረሰቡ ሳይሆን ራሱ ግለሰቡ ነው::

## ባህላዊ ወይም ተገላጭ አንጻራዊነት

በዚህ ጐራ ሥር ያሉ በርካታ ሰዎች፣ ግብረገባዊ አንጻራዊነትን ለማጽናት ሰዎች የተለያየ ባህል አላቸው፣ እነዚህም ባህሎች መሠረታዊ በሆኑት ግብረገባዊ ፋይዳዎች ላይ ይለያያሉ የሚል አቋም አላቸው:: በርካታ የሥነ ሰብና የማኅበረሰብ ምሁራን፣ እያንዳንዱ ኅብረተሰብ የራሱ የሆነ ሥነ ምግባራዊ መስፈርት አለው ይላሉ:: ይህ አመለካከት ባህላዊ ወይም ተገላጭ አንጻራዊነት ይባላል::

እያንዳንዱ ባህል የራሱ የሆነ፣ ከሌላው የተለየ ግብረገብ ስላለው፣ አንዱ ሌላውን የእኔ ግብረገብ ትክክል ነው፣ የአንተ ደግሞ ትክክል አይደለም ማለት አይችልም:: ስለዚህ ነባራዊ የሆነ ግብረገብ ወይም ፍጹማዊ የሆነ ግብረገብ የለም፤ ግብረገብ አንጻራዊ ነው::

[1] Francis J. Beckwith and Gregory Koukl, *Relativism* (Grand Rapids: Baker, 1998), 36-39.



## ዐዋጃዊ ወይም ግዕዛናዊ ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት

ይህ ዐይነቱ አንጻራዊነት ከባህላዊ ወይም ከተገላጭ አንጻራዊነት የሚለይበት፣ በርካታ መሠረታዊ ነጥቦች አሉት:: ባህላዊ (ተገላጭ) አንጻራዊነት፣ ***ገላጭ*** ሳይሆን ***ተገላጭ*** ነው፤ ይህ ማለት ባህል የገለጠውን ነገር (ያፈራውን ፍሬ) የሚናገር እንጂ፣ አንድ ባህል መሠረት ያደረጋቸውን ግብረገባዊ ግዕዛን (መርሖ) የሚተነትን አይደለም:: ምክንያቱም በባሕርይ ወይም በጠባይ ላይ ብያኔ የሚሰጥ ወይም ለግብረገባዊ ምግባር አቅጣጫ የሚጠቁም አይደለም:: በሌላ አነጋገር ነገሮች ምን መሆን እንዳለባቸው (እንደሚገባቸው) የሚገልጽ አይደለም::

ግዕዛናዊ ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት ግን፣ ባህል በገለጠው ላይ (በባህሉ ውስጥ የሚታየው) ሳይሆን፣ ባህሉ መሠረት ባደረገው ግብረገባዊ ግዕዛን ላይ የሚያተኩር ነው:: ሥነ ምግባራዊ ምርመራ እንጂ፣ ሥነ ሰባዊ ጥናት አይደለም:: በግዕዛናዊ ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት አስተሳሰብ፣ እያንዳንዱ ሰው መኖር ያለበት የማኅበረሰቡን ግብረገባዊ ፋይዳ በመጠበቅ ነው:: ለአንድ ኅብረተሰብ ትክክል የሆነው ነገር ለሌላው ኅብረተሰብ ትክክል ላይሆን ይችላል፤ ሰዎች ማድረግ የሚገባቸው፣ "ኅብረተሰባቸው" የበየነውንና የሚያደርገውን ግብረገባዊ ግዕዝ ነው::

የሥነ ምግባር ምሁራን ግዕዛናዊ አንጻራዊነትን በሁለት ይከፍሉታል[2]:: አንደኛው አንድ ሰው ሊያደርግ የሚገባው፣ የራሱ ማኅበረሰብ መልካም ነው ብሎ የወሰነውን ነገር ነው፤ ይህም ማኅበራዊ የሆነ ግዕዛናዊ አንጻራዊነት ይባላል:: ሁለተኛው ደግሞ አንድ ሰው ማድረግ የሚኖርበት፣ ራሱ መልካም ነው ብሎ የሚያምንበትን ብቻ ነው፤ ይህ ግላዊ የሆነ ግዕዛናዊ አንጻራዊነት ይባላል:: ነገር ግን ግላዊ የሆነው ውሳኔ መገራት ያለበት፣ ባህሉ (ማኅበረሰቡ) በተቀበለው ግብረገባዊ መስፈርት ነው የሚለው የሁሉም አቋም ነው::

## ግላዊ ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት
## (ሥነ ምግባራዊ ኀሊናዊነት)

ግላዊ ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት (ሥነ ምግባራዊ ኀሊናዊነት)፣ የግል ምርጫ ለባሕርይ መሠረት ነው የሚል አመለካከት ነው:: ለአንድ ሰው ትክክል የሆነው፣ ለሌላው ሰው ትክክል አይደለምና፤ ይኸውም ባህል አንዳችም ተጽእኖ ሳያስከትልበት ማለት ነው::

[2] Beauchamp, *Philosophical Ethics*, 50.

እያንዳንዱ ሰው መኖር ያለበት የራሱ የሆነውን ግብረገባዊ ግዕዝ (መርሖ) በመጠበቅ፣ ኅሊናው እንደ ፈቀደለት ነው:: ዘመናት በአዲስ እየተተኩ ሲሄዱ፣ ግዕዛኖቹ እየተቀያየሩ፣ ፍላጎት እየተለዋወጠ ቢመጣም፣ ግብረገብ ግላዊና ኅሊናዊ መሆኑ ጸንቶ ይኖራል:: ግላዊ ሥነ ምግባራውያን፣ "እንዴት መኖር እንዳለብኝ ልትነግረኝ አንተ ማነህ?" በሚለው የዘወትር ንግግራቸው ይታወቃሉ::

አንጻራውያን፣ "የአንተን ግብረገባዊ ፋይዳ በእኔ ላይ የምትጭን አንተ ማነህ!" የሚሉት ፍጹማዊ የሆነና ሰዎች ሁሉ በየትኛውም ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ ሊቀበሉት የሚገባ ግብረገባዊ ግዕዝ የለም፣ የሚል እምነት ስላላቸው ነው:: ግብረገብ ግላዊ ነው:: ይህ ዐይነቱ ሁኔታ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ተከሥቶ እንደ ነበር መጽሐፈ መሳፍንት ይነግረናል፣ "ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም የመሰለውን ነገር ያደርግ ነበር" (መሳ 17÷6)::

ከዚህ በመቀጠል የእያንዳንዱን ግብረገባዊ አንጻራዊነት ጉራ አመክንዩአዊ መሠረት ወደ መመርመሩ እንዘልቃለን::

4.3

## ባህላዊ ወይም ተገላጭ አንጻራዊነት[1]

የሥነ ሰብ ምሁሩ ዊሊያም ግርሃም ሰምነር፣ ግብረገብ መታየት ያለበት ከባህል አንጻር ብቻ ነው ባይ ናቸው:: ስለዚህም ግብረገብ በምንም ዐይነት መልኩ ነባራዊ አይደለም:: እንዲያውም ግብረገብ የተወለደው፣ ኅሊናዊ በሆነው የባህል ዐዋጅ ነው:: ሰምነር ወደዚህ ድምዳሜ ያመጣቸውን ሦስት ነጥቦች በሚከተለው መልክ ያቀርባሉ:- አንደኛ፣ ከተለያየ ባህል የምንማረው ቁም ነገር፣ እያንዳንዱ ባህል የራሱ የሆነ፣ ልዩ ግብረገባዊ ፋይዳ እንዳለው ነው:: ሁለተኛ እነዚህ የተለያዩ ግብረገባዊ ፋይዳዎች የተፈጠሩት፣ ሰዎች ተፈጥሮአዊ የሆነውን ፍላጎታቸውን ለማርካት ደፋ ቀና በሚሉበት ጊዜ ከሚያጋጥማቸው ሐዘን፣ ሕመምና ደስታ ነው:: እነዚህም ፋይዳዎች የአግባብነት፣ የምግባር፣ የትክክል፣ የከበሬታ ወዘተ መገለጫ የሆኑትን ሥርዐት ያላቸውን ልምዶች ፈጠሩ፤ ይህንንም በአንድ አቀናጅቶ የሚይዘው ባህል ነው:: ሦስተኛ ማንኛውም ሰው የራሱ ባህል ግብረገባዊ ፋይዳዎች ትክክል እንደ ሆኑ፣ በአንጻሩ ደግሞ በሌላ ባህል ውስጥ የሚገኙት ፋይዳዎች ትክክል እንዳልሆኑ ያስባል::

በአጠቃላይ ሰምነር ግብረገብ የሰዎች ስምምነት ነው፣ "ግብረገባዊ ደመ ነፍስ" የሚባለውም ነገር፣ ከባህል ዝንባሌ (biases) የዘለለ አይደለም ባይ ናቸው:: "ኢግብረገባዊ" የሚባለውም አንድ ኅብረተ ሰብ በተወሰነ ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ ከተቀበለው ነገር ተቃራኒ የሆነ ከማለት ውጪ አይደለም:: "ትክክል" የሚባለውም መሳ ለመሳ ከሆነው ከመስጠትና ከመቀበል ሕግጋት ውጪ የሆነ ነገር አይደለም፤ ስለዚህም "ትክክል" ተፈጥሮአዊ ወይም "ከእግዚአብሔር የተሰጠ" አልያም ደግሞ፣ ፍጹማዊ የሆነ ነገር ነው ብሎ ማሰብ ተላላነት ነው ባይ ናቸው[2]::

የዚህን አመለካከት ስሕተት፣ ጕልሕ በሆነ ሁኔታ የሚያሳዩንን ሦስት ነጥቦች ወደ መቃኘቱ ደግሞ እንመለስ[3]::

---

[1] Francis J. Beckwith and Gregory Koukl, *Relativism* (Grand Rapids: Baker, 1998), 43-48.

[2] ዝኒ ከማሁ፤ 38:: ከ William Graham Sumner, *Folkways* (Chicago: Ginn and Company, 1906), In *Ethical Theory: Classical and Contemporary Readings*, ed. Louis B. Pojman, (Belmont, Calif.: Wadsworth, 1995), 28. ጠቅሰው እንደ ጻፉት::

[3] ባህላዊ ወይም ተገላጭ አንጻራዊነትን አስመልክቶ Hadley Arkes, *First Things* (Princeton: University Press, 1986) በተባለው መጽሐፉ ምዕራፍ 7 ላይ ምሁራዊ አስተያየት እንደ ሰጠ፣ Francis J. Beckwith and Gregory Koukl, *Relativism* (Grand Rapids: Baker, 1998), 44. ላይ ጠቅሰው ጽፈዋል::

ሰምነር ከዘረዘሯቸው ነጥቦች መኻል አንዷና፣ እያንዳንዱ ባህል የራሱ የሆነ ግብረገባዊ ፋይዳ አለው የሚለው የመጀመሪያው ነጥባቸው ነው:: ነገር ግን ይህ ፍጹም ስሕተት ነው::

በተለያዩ ባህሎች ውስጥ ያሉትን ልምዶች በግልቡ ስንመለከታቸው፣ መሠረታዊ በሆኑት ግብረገባዊ ፋይዳዎች ላይ የሚለያዩ ሊመስሉን ይችላል:: በአንድ ባህል ተቀባይነት ያለው ነገር፣ በሌላው ባህል ውስጥ ተቀባይነት ላይኖረው ይችላል:: ለምሳሌ:- በጥንት ሕንዳውያን ባህል፣ ባል የሞተባት መበለት ከባሏ አስክሬን ጋር ተቃጥላ እንድትሞት ይደረግ ነበር፤ በኢትዮጵያኑ ባህል ይህ ኢግብረገባዊ ድርጊት ነው::

ነገር ግን በጥንት ሕንዳውያንና በኢትዮጵያውያን መካከል ያለውን የባህል ልዩነት ቀረብ ብለን ስንመረምረው፣ እውነታው ከላይ ከተጠቀሰው ፍጹም የተለየ ገጽታ ይዞ እናገኘዋለን:: ይኸውም በሕንዳውያኑና በኢትዮጵያውያኑ መካከል ያለው ልዩነት፣ በግብረገባዊ ፋይዳዎች መካከል ያለ ልዩነት ሳይሆን፣ በግንዛቤው ላይ የተፈጠረ ልዩነት ነው:: በሌላ አገላለጽ ልዩነቱ በተገላጩ ላይ እንጂ፣ በገላጩ ላይ አይደለም፤ ገላጩ ግብረገባዊ ፋይዳ፣ ተገላጩ ደግሞ ባህላዊ ሥነ ሰብ ነው::

በደል አልባ የሆኑትን ሰዎች መግደል፣ በየትኛውም የታሪክ ዘመንና ባህል በጽኑ የተወገዘ ድርጊት ነው፤ ልዩነቱ ያለው ግድያን ለማጽደቅ በሚደረገው ፅንሰ ሐሳብ ላይ ነው:: ሂትለር "ዕብራውያኑን ለመግደል ያነሣሣኝ ምክንያት ዕብራውያን ሙሉ ሰብአዊ ፍጡር አይደሉም" የሚል እምነት ስላለው ነው::

ሂንዱይዝም በተባለው የህንዳውያን ሃይማኖት፣ አንድ ሴት የጋብቻ ኪዳን በምትፈጽምበት ጊዜ ከምታገባው ወንድ ጋር በዕድሜዋ ዘመን ሁሉ ለመኖር፣ ሲሞትም አብራው ለመሞት ቃል ኪዳን ትገባለች:: ይህም በሃይማኖቱ አስተምህሮ መሠረት፣ ታላቅ ክብር እንዲያውም ታላቅ ቅድስና ነው:: ባሏ በሚሞትበት ጊዜ አብራው መሞቷ ይህን ታላቅ ክብርና ቅድስና የሚያጐናጽፋት በተጨማሪም በሞቱ ያላትን መሪር ሐዘን የምታሳይበት ነው:: በየትኛውም ባህል ለኪዳን ታማኝ ሆኖ መገኘት ቅድስና እንዲሁም እስከ ሞት ድረስ ክብሮ የሚታይ ጉዳይ ነው::

በሂንዱ ሃይማኖት ተከታዮቹ ሕንዳውያንና በኢትዮጲያውያን መካከል በታማኝነትና በቅድስና ላይ ተመሳሳይ አቋም አለ:: ይህ በግብረገባዊ ፋይዳዎች ላይ ተመሳሳይ አቋም እንዲይዙ ያደርጋቸዋል:: ይህ ደግሞ ግብረገባዊ አንድነት ነው:: ሕንዳውያኑና ኢየትዮጵያውያኑ የሚለያዩት፣ በትዳር መካከል ያለው ታማኝነትና ቅድስና የሚገለጸው፣ ሴቶችን ከባሎቻቸው ጋር በማቃጠል ነው ወይስ አይደለም በሚለው ነጥብ ላይ ነው:: ይህ ልዩነት የባህል ወይም የተገላጭ ልዩነት ነው::



ውርጃን በተመለከተ የሚካሄደው ክርክር፣ በግብረገባዊ *ፋይዳዎች (ወይም በገላጩ)* ላይ የሚደረግ ክርክር ሳይሆን፣ ***በተገላጩ*** ላይ የሚካሄድ ክርክር ነው:: ውርጃን የሚደግፉ ሰዎች፣ የሰው ሕይወት ታላቅ ክበሬታ ያለው ቢሆንም፣ ሽሉ ሰው ስላልሆነ መግደል ይቻላል ባዮች ናቸው:: ውርጃን የሚቃወሙ ሰዎች ደግሞ፣ የግብረገባዊ ፋይዳዎች መለያየት ሳይሆን፣ በእውነታዎች ላይ ያለ ግንዛቤ ነው ይላሉ::

ከላይ በተወሰኑ ባህሎች የተመለከትናቸው የባህል ናሙናዎች የምንማረው ነገር፣ በእነዚህ ባህሎች መካከል የተፈጠሩት ልዩነቶች ምክንያታቸው የግብረገባዊ ፋይዳ ልዩነት ያለመሆኑን ነው:: ልዩነቱ የመጣው ግብረገባዊ ፋይዳዎችን መሠረት ባደረጉት የሰብአውያን ግንዛቤ ላይ ነው:: ክሊቭ ስታፕላስ ልዊስ የተባሉት እንግሊዛዊ ሊቅ፣ "አንድ ሰው ግብረገባዊ ፋይዳዎችን ማነጻጸር ከከበደው፣ የጥንት ግብፃውያንን፣ ባቢሎናውያንን፣ ሕንዳውያንን፣ ቻይናውያንን፣ ግሪካውያንንና ሮማውያንን የግብረገብ አስተምህሮ ማነጻጸር ይችላል፤ የሚደንቅበትም ጉዳይ፣ በእነዚህ ባህሎች መካከል አንድነት መኖሩና ይህም ከእኛ ጋር ስምሙ መሆኑ ነው"[4]:: ክሊቭ ስታፕላስ ሊዊስ "ዚ አቦልሽን ኦፍ ማን" በተባለው መጽሐፋቸው፣ ግብረገባዊ ፋይዳዎች በሰብአውያን ባህል ውስጥ ሁሉ እውን እንደ ሆኑ በግልጽ አሳይተዋል::

በተለያዩ ባህሎች ውስጥ የግብረገባዊ ፋይዳ ልዩነት አለ የሚሉ ሰዎች፣ አለ የሚሉትን የግብረገባዊ ፋይዳ ልዩነት በማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል:: ከዚህ የምንማረው ቁም ነገር፣ የባህላዊ (የተገላጭ) አንጻራዊነት አስተምህሮ ስሕተት መሆኑን ነው:: በተለያዩ ባህሎች ውስጥ ያለው ልዩነት፣ የግብረገባዊ ፋይዳ ልዩነት ሳይሆን የባህል ልዩነት ነው::

## ሥነ ሰብ ከግብረገብ ጥናት ይለያል

ባህላዊ (ተገላጭ) አንጻራውያን እንደሚሉት፣ የተለያዩ ባህሎች መሠረታዊ በሆኑት ግብረገባዊ ፋይዳዎች ላይ ቢለያዩ እንኳ፣ ግብረገባዊ ፋይዳዎች አንጻራዊ ናቸው ማለት ይቻላልን?

ፕሮፌሰር ሰምነር የሥነ ሰብ ምሁር ስለሆኑ፣ የሥነ ሰብ አተያያቸውን በተረዱበት መልኩ መግለጻቸው ክፋት የለውም:: በተለያዩ ባህሎች መካከል የግብረገባዊ ፋይዳ ልዩነት ቢኖር እንኳ፣ የግብረገብን እውነተኛ ገጽታ አመላካች ሊሆን አይችልም::

---

[4] C. S. Lewis, *Mere Christianity* (New York: Collier Macmillan, 1960), 5.

አንድ ማኅበረሰብ እኔ ልክ ነኝ ሌላው ደግሞ ተሳስቶአል የሚል ግምት ቢኖረው እንኳ፣ የተቀረውን ማኅበረሰብ ሐሰተኛ ያደርገዋልን? ሰዎች በግብረገባዊ ፋይዳዎች ላይ አለመግባባታቸው፣ ግብረገባዊ እውነት የለም እንድንል አያደርገንም። አንድ ነገር አይታወቅም (አላግባባም) ማለት የለም ማለት አይደለምና።

ሰዎች በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ላይ አንድ ዐይነት አቋም (ስምምነት) የላቸውም፤ ለምሳሌ፦ ግብረ ሰዶም፣ ውርጃ፣ ከሞት በኋላ ሕይወት መኖሩን ወዘተ በተመለከተ ሰዎች የተለያየ አመለካከት አላቸው። ነገር ግን በርእሰ ጉዳዩ ላይ አልተግባቡም ማለት፣ ትክክለኛ የሆነ አመለካከት የለም ማለት አይደለም። ተግባብተዋል ማለትም ስሕተት የለም ማለት አይደለም።

ከላይ ለማየት እንደ ሞከርነው ባህላዊ (ተገላጭ) አንጻራዊነት፣ የሥነ ሰብ ጥናት እንጂ የግብረገብ ጥናት አይደለም። አንድ ሰው ከሥነ ሰብ ጥናት የሚማረው እውነት፣ ሰዎች የተለያየ ባህል እንዳላቸው ብቻ ነው።

ስምነር ነባራዊ የሆነ ግብረገባዊ እውነት የለም፤ ምክንያቱም ሁላችንም የባህላችን እስረኞች ነንና፣ ከዚህም የተነሣ ከክልላችን በመውጣት፣ ከአዘንብሎታችን (biases) በመላቀቅ የነገሩን ትክክለኛ ገጽታ ማየት ዐቅም የለንም፤ ይህም ግብረገባዊ እውነታዎች እንደየ ባህሉ አንጻራዊ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፣ የሚለው አባባላቸው ስሕተት ነው። ምክንያቱም ይህ አባባላቸው እርስ በርሱ ስለሚቃረን። ሰዎች የባህላቸው እስረኞች ከሆኑና ከክልላቸውና ከአዘንብሎታቸው በመላቀቅ የነገሩን ትክክለኛ ገጽታ የማየት ዐቅም ከሌላቸው፣ ስምነር ይህን ዐቅም ከየት አመጡት?

የስምነር ትንተና ሁሉም ሃይማኖት ትክክል ነው እንደሚሉት *ብዝኃ ሃይማኖታውያን*፣ ተመሳሳይ ችግር አለበት። ብዝኃ ሃይማኖታውያን አዘውትረው የሚጠቅሱት፣ አንድ የቡድሃ ሃይማኖት ተረት አለ፤ ተረቱ፣ "ማየት የተሳናቸውና ዝሆኑ" በመባል ይታወቃል። ስድስት ማየት የተሳናቸው ሰዎች፣ ለመጀመሪያ ጊዜ "ራጃ" በተባለው ንጉሥ ይዞታ ሥር ባለው ስፍራ ላይ አንድ ዝሆን ያገኛሉ፤ ስድስቱም ዝሆኑን በእጃቸው እየዳሰሱ ስለዝሆኑ የተረዱትን ነገር ይናገራሉ።

ማየት የተሳነው የመጀመሪያው ሰው እጁን በመዘርጋት የዝሆኑን ጐን ይዳስስና፣ "ዝሆን እንደ ግድግዳ የተገደገደ ፍጥረት ነው!" ይላል። ሁለተኛው ሰው እጁን በመዘርጋት የዝሆኑን ኩንቢ ይዳስስና፣ "ዝሆን እባብ መሰል ፍጥረት ነው!" ይላል። ሦስተኛው ሰው የዝሆኑን እግር ይዳስስና፣ "ዝሆን እንደ ቀስት የሾለ ፍጥረት ነው!" ይላል። አራተኛው ሰው የዝሆኑን እግር ይዳስስና፣ "ዝሆን እንደ ባሕር ዛፍ ረዥም ፍጥረት ነው!" ይላል። አምስተኛው ሰው፣ የዝሆኑን ጆሮ በመዳሰስ፣ "ዝሆን



እንደ ማራገቢያ ያለ ፍጥረት ነው!" ይላል። ስድስተኛው ሰው እጁን በመዘርጋት የዝሆኑን ጭራ ይዳስስና፣ "ዝሆን ገመድ መሰል ፍጥረት ነው!" ይላል። እያንዳንዱም ሰው ስለ ዝሆኑ የራሱን ግኝት ተናገረ። በዚህ ጭቅጭቅ ምክንያት "ራጃ" የተባለው ንጉሥ ከእንቅልፉ ይነቃና ወደ ሰገነቱ በመሄድ፣ "ዝሆን በጣም ትልቅ እንስሳ ነው፤ እያንዳንዱ ሰው የዳሰሰው የዝሆኑን የተወሰነ ክፍል ነው፤ ዝሆን ምን ይመስላል የሚለውን በትክክል ለማወቅ፣ እያንዳንዱን አካል በጥምረት መዳሰስ ይፈልጋል" ይላቸዋል።

ማየት የተሳናቸው ሰዎች በራጃ ጥበብ በመደነቅ፣ "እያንዳንዳችን የምናውቀው የእውነታውን አንድ ክፍል ብቻ ነው፤ ሁሉንም እውነት ለማወቅ እያንዳንዱን ክፍል በአንድ ላይ ማቀናጀት ያስፈልጋል" ወደሚለው ስምምነት ላይ ይደርሳሉ[5]።

ይህ ተረት የሚተረተው ሁለት ነገሮችን ለማስጨበጥ ነው። አንደኛው በብዝኃ ሃይማኖታውያን የሚሉትን ዐዋጅ ለማዋዛት ነው፤ ይኸውም የእያንዳንዱ ሃይማኖት ዕይታ፣ የትልቁ እውነት አንድ ክፍል ብቻ ነው፤ ነገር ግን እውነታዎች ሁሉ አንድ ላይ ሲደመሩ፣ ወደ እግዚአብሔር ያደርሳሉ የሚል ነው። ሁለተኛው *በጥርጣራውያን* ***(Skeptics)*** የሚጠቀሰው ነው፤ ይኸውም የእያንዳንዱን ነገር ትክክለኛ ገጽታ እንዳናውቅ፣ ባህላችን አሳውሮናል የሚለው ነው። የስምነር ትንተና ከዚህ ጋር የሚገጥም ነው። ይኸውም ግብረገባዊ ንግግሮች (ዐዋጆች) ሁሉ፣ ቅዠቶች ናቸው የሚለው ነው። እውነቱ እርሳቸው እንደሚሉት ከሆነ፣ እርሳቸውስ ከዚህ "ቅዠት" እንዴት ሊያመልጡ ቻሉ? ራጃ የተባለው ንጉሥ ዝሆኑን ሙሉ ለሙሉ አጥርቶ ማየት በመቻሉ ማየት የተሳናቸውን ሰዎች ከስሕተት ታደጋቸው። "ራጃ" እውነትን የማወቅ ችሎታ (ዐቅም) ነበረው፤ ማየት ለተሳናቸውም ሰዎች እውነቱን የገለጠላቸው ለዚሁ ነው። እንግዲያው ስምነር ያላቸው ሌላው ሰው የታወረበት ነገር ምን ይሆን?

ባህላዊ (ተገላጭ) አንጻራዊነት ሦስት መሠረታዊ ችግሮች ይታዩበታል። እያንዳንዱ ባህል የራሱ የሆነ ግብረገባዊ ፋይዳ አለው የሚለው አንዱ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የተለያዩ ባህሎች መሠረታዊ በሆኑት ግብረገባዊ ፋይዳዎች ላይ ቢለያዩ እንኳ፣ የተለያየ አመለካከት እንዳለ የሚያስተምር እንጂ፣ አንዳችም እውነት የለም የሚለውን የሚያሳይ አይደለም። ጉዳዩ ፍጹማዊ የሆነ ግብረገባዊ መስፈርት አለ ወይስ የለም የሚለውን ጥያቄ የሚዳስስ አይደለም። ሦስተኛው፣ በባህላችን ማነቆ ውስጥ ነን ማለት፣ ነባራዊ የሆነ ወይም ከአዘንብሎ የጠራ አመለካከት የለም ማለት አይደለም።

---

5 ዝኒ ከማሁ፡ 47። ከ Lillian Quigley, *The Blind Men and the Elephant* (New York: Charles Scribner's, 1959) ጠቅሰው እንደ ጻፉት።

# ዐዋጃዊ ወይም ግዕዛናዊ ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት[1]

ዐዋጃዊ ወይም ግዕዛናዊ ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት ሥነ ምግባራዊ ምርምር
እንጂ፣ እንደ ባህላዊ ወይም ተገላጭ አንጻራዊነት ሥነ ሰባዊ ጥናት አይደለም::
በተለያዩ ባህሎች ውስጥ ያሉትን እምነቶች የሚተርክ ሳይሆን፣ አንድ ሰው ምን
ዐይነት ግብረገብ ሊኖረው እንደሚገባ የሚያስተምር ሥነ ምግባራዊ ትንተና ነው::
ይኸውም ሰዎች ማድረግ የሚገባቸው፣ ማኅበረሰባቸው እንዲያደርጉ የሚጠብቀውን
ብቻ ነው[2]::

እንደ ዐዋጃዊ (ግዕዛናዊ) ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት አስተምህሮ፣ "ነባራዊ
የሆነ ሥነ ምግባራዊ መርሖ የለም፤ ነገር ግን ተገቢ የሆኑትን ግብረገባዊ መርሖዎች
የሚበይነው (የሚያጸድቀው) ባህል ነው"[3]፤ ስለዚህ ግብረገብ እንደ ባህሉ ስምምነት
የሚወሰን፣ በሕግ፣ በልማድና በባህል የሚገለጽ ነው::

## አንዳችም ማኅበረ ሰብ ኢግብረገባዊ አይደለም

ዐዋጃዊ (ግዕዛናዊ) ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት መሠረታዊ የሆኑ ችግሮች
አሉበት:: ባህል ግብረገብ ጠንሳሽና አጽዳቂ ከሆነ፣ ባህል ከሌለ ግብረገብ የለም ማለት
ነው:: በተለያዩ አካባቢዎች ተራርቀው በሚኖሩ ሰዎች መካከል አንድ ዐይነት ባህል
ከሌለ፣ አንድ ሰው ያሳንዳች ምክንያት አመር ብሎ ሌላውን ሰው ቢገድል፣ ገዳዩ
አንዳችም ግብረገባዊ ሕግ አልተጻረረም ማለት ነው::

ዐዋጃዊ (ግዕዛናዊ) ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት በማኅበረሰብ መካከል ያለውን
እኩይ ምግባር ሊተች (ሊያወግዝ) አይችልም:: ከማኅበረሰብ በላይ የሆነ ሕግ ከሌለ፣
ማኅበረሰብ በእኩይ ምግባሩ ሊኰነን፣ በሠናይ ምግባሩ ሊወደስ አይችልም ማለት
ነው::

[1] Francis J. Beckwith and Gregory Koukl, *Relativism* (Grand Rapids: Baker, 1998), 49-60.
[2] አንዳንድ ሰዎች ይህን አመለካከት ባህላዊ አንጻራዊነት ይሉታል፤ ይህ ግን ስሕተት ነው::
[3] Louis P. Pojman, *Ethics: Discovering Right and Wrong* (Belmont, Calif.: Wadsworth, 1990), 23.



ይህ አመለካከት በዘመነ ደርግ የነበረውን ግፍ፣ የናዚን የጭቈና አገዛዝ፣
የዘረኞችን መሰሪነት መኰነን አይችልም:: ምናልባት ይህ ሁኔታ (ፖሊሲ) የአብዛኛው
ሕዝብ ፈቃድ ሳይሆን፣ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ፈቃድ ነው ሊባል ይችላል፤
ነገር ግን ይህ ቢያንስ ሁለት መሠረታዊ ችግሮች አሉበት፤ አንደኛው:- ግብረገብን
የሚወስነው በሥልጣን ላይ ያለው አካል ሳይሆን፣ አብዛኛው ማኅበረሰብ ይሁን
የተባለበት ምክንያት ምንድን ነው? አንድ ሰው ለማኅበረሰቡ ሕግጋት የመታዘዝ
ግዴታ ካለበት፣ መታዘዝ ያለበት በሥልጣን ላይ ላለው አካል ወይስ ለተቀረው
ኅብረተሰብ? ይህ የዐዋጃዊ (ግዕዛናዊ) ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት አንዱ ድካም ነው::

ባህል ውስብስብ የሆነ ነገር ነው:: አንዱ ማኅበረሰብ የራሱ ሕግጋት
እንዲከበርለት የሚፈልገውን ያህል ሌላውም ማኅበረሰብ ይፈልጋል:: እንግዲያው
ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ባህል የቱ ነው?

ሁለተኛ:- በአንድ የተወሰነ አገር (ሕዝብ መካከል) የሚፈጸም ኢፍትሓዊነት፣
የአብዛኛው ሕዝብ ፍላጎት ላይሆን ይችላል፤ ነገር ግን ይህ ቢሆን በየትኛው ግብረገባዊ
መስፈርት ሊመዘን ይችላል? የጀርመን ናዚዎች በኅብረተሰቡ ዘንድ ትልቅ የሆነ
ተቀባይነት ነበራቸው፤ ነገር ግን በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘታቸው፣
ምግባራቸውን ኢግብረገባዊ ከመሆን ይታደገዋልን?

ዐዋጃዊ (ግዕዛናዊ) ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት ትክክል ቢሆን ኖሮ፣ መንግሥት
የደገፈው (ያጸደቀው) የዘር ጭርጨፋ እኩይ ባልተባለ፣ ሊቃወሙትም ባልተገባ ነበር::

## አንዳችም ሕግ ኢግብረገባዊ መሆን አይችልም

በዐዋጃዊ (ግዕዛናዊ) ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት ዕይታ፣ ኢግብረገባዊ የሆነ
አንዳችም ሕግ የለም:: ማኅበረሰብ፣ ግብረገብን የሚጠነስስ፣ የሚያዘጋጅና የሚያጸድቅ
ከሆነ፣ ማኅበረሰብ የበየነው ብያኔ ሁሉ ሠናይ ግብረገብ ነው ማለት ነው:: ይህ ደግሞ
በትክክለኛው ሥነ ምግባርና መንግሥት ባጸደቀው ሕግ መካከል ልዩነት አያደርግም::
በአንድ የተወሰነ አገር፣ ሕገ መንግሥት ያጸደቀው ነገር ሕጋዊ ይሆናል፤ ሕጋዊ ሆነ
ማለት ግን ትክክለኛ ሆነ ማለት አይደለም:: ዐዋጃዊ ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት
እነዚህን ሁለት መሠረታዊ ልዩነቶች፣ አሳዛኝ በሆነ ሁኔታ ይደባልቃቸዋል::
የሰብአውያን ሸንጎ (የመንግሥት ኀይል ወይም የሕዝብ ኀይል) ግብረገብን የሚወስን
የመጨረሻ ባለሥልጣን ከሆነ፣ ግብረገብ የኀይል ጉዳይ ብቻ ይሆናል:: ትክክል መሆን
ያለበትን ነገር የሚወስነው ሕግ ወይም ሸንጎ ከሆነ፣ ሕግም ሆነ ሸንጎ ኢግብረገባዊ
ሊሆን አይችልም ማለት ነው::

# ግብረገባዊ ተሐድሶ የሚባል አንዳችም ነገር የለም

በዐዋጃዊ ወይም በግዕዛናዊ ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት ዘንድ፣ የማኅበረሰብን ግብረገብ ማደስ የሚባለው ነገር ትርጒም የለሽ ነው:: ይህ የሆነበት ሁለት ምክንያት አለ፤ አንደኛው የተሐድሶ መሪዎች ግራ መጋባት ነው::

የግብረገብ ሐዳስያን ማኅበረሰቡ ላይ የሚፈርዱት በማኅበረሰቡ ውስጥ ሆነው ነው:: በማኅበረሰቡ ውስጥ ሆነው የማኅበረሰቡን የግብረገብ ዝቅጠት ይኰንናሉ፤ የለውጥ እንቅስቃሴ ያደርጋሉ:: ነገር ግን የግብረገብ ሠናይነት የሚወሰነው አንድ ማኅበረሰብ ባለበት የአሁን ጊዜ ሁኔታ ከሆነ፣ የማኅበረሰቡን መስፈርት ለመለወጥ መጣር ኢግብረገባዊ ይሆናል:: የግብረገብም ሐዳስያን በግብረገብ ደረጃ የተናቁ (የተወገዙ) ሰዎች ይሆናሉ፤ ኅብረተሰቡ የተቀበለውን ግብረገብ ተቃውመውታልና::

እንደ ኮሪ ቴን ቡም ያሉ ሰዎች፣ በዕብራውያን ላይ በተካሄደው የዘር ጭፍጨፋ ወቅት ሕይወታቸውን አጣብቂኝ ውስጥ በመክተት፣ ዕብራውያንን ከግፈኞች ጭፍጨፋ ለመታደግ ተነሥተው ነበር:: በዐሥራ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ፣ ዊልያም ዊልበርፎርስ የተባለው ሰው፣ በእንግሊዝ አገር የነበረውን የባሪያ ንግድ ተቃውሞ ነበር:: ማርቲን ሉተር ኪንግ በዐሥራ ዘጠኝ ሃምሳዎቹና ስልሳዎቹ ላይ በአሜሪካን አገር የነበረውን የዘር ልዩነት ክፉኛ አውግዞአል:: በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ማርቲን ኒሙለርና ዲትሪች ቦንሆፈር የተባሉት ጀርመናውያን ክርስቲያኖች ሂትለርን ይቃወሙ ዘንድ ከፍተኛ ቅስቀሳ አድርገዋል:: እንደ ኔልሰን ማንዴላ ያሉ አፍሪካውያን አፓርታይድን ክፉኛ ተቃውመዋል::

እነዚህን የታሪክ ሰዎች፣ የግብረገብ ጀግኖች እንላቸዋለን፤ ምክንያቱም ግብረገባዊ ተሐድሶ ይካሄድ ዘንድ ሕይወታቸውን ለሞት አሳልፎ እስከ መስጠት ድረስ እጅግ ታላቅ ዋጋ ከፍለዋልና:: ነገር ግን ዐዋጃዊ ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት እነዚህን የታሪክ ጀግኖች፣ የግብረገብ ቀበኞች አድርጎ ይቈጥራቸዋል::

ይህ አመለካከት የማኅበረሰብን ግብረገባዊ ችግር በተመለከተ ሌላም ችግር ይስተዋልበታል:: የኅብረተሰብ ሕግና ባህል፣ ባሕርይን የሚወስን የመጨረሻው መስፈርት ከሆነ፣ በሕግና በባህል ዙሪያ ያለው ግብረገባዊ ሕግ ይሻሻል ማለት ትርጒም አይኖረውም:: እንደዚህ አመለካከት የኅብረተሰብ ሕግ አይሻሻልም፤ ይለወጣል እንጂ::

"ማሻሻል" የሚለው ቃል፣ የሚወክለውን ርእሰ ጒዳይ ለጥቂት ጊዜ ያስቡ:: "ማሻሻል" ማለት የአንድን ነገር የጥራት ደረጃ ወይም ሁኔታ ከፍ ማድረግ ማለት ነው:: እንግዲያው ይህ እውነት ከሆነ፣ የአንድ ነገር ጥራት መሻሻሉን እንዴት ማወቅ



እንችላለን? ፍጽምና የሚለካበት ፍጹም የሆነ ውጫዊና የተወሰነ መስፈርት ከሌለ፣ ማሻሻል የሚለው ጒዳይ አንዳችም ትርጒም አይኖረውም::

የማኅበረሰቡን ግብረገብ ማሻሻል ማለት የማኅበረሰቡን ሕግና ፋይዳ፣ ፍጹማዊ ወደ ሆነው ግብረገባዊ ሕግጋት ማስጠጋት (ማቅረብ) ማለት ነው:: ይህ ውጫዊ የሆነ ፍጹማዊ መስፈርት ከሌለ፣ ባህልና ወግ መጨረሻው ሥልጣናዊ ሕግ ስለሚሆን፣ ተሐድሶ የሚባለው ነገር ትርጒም አይኖረውም:: የአንድ ኅብረተሰብ ሕግ ከሌላቸው ኅብረተሰብ ሕግ የተለየ ይሆናል እንጂ፣ የተሻለ አይሆንም::

ከላይ ለማየት እንደ ሞከርነው ከባህል ጋር የተቈራኙ የአንጻራዊነት እይታዎች ሁሉ መሠረታዊ ችግር አለባቸው:: ባህላዊ (ተገላጭ) አንጻራዊነት የግብረገብ ምርምር ሳይሆን፣ የሥነ ሰብ ጥናት እንዲሁም የምሁራኑ ግላዊ አመለካከት ነው:: ዐዋጃዊ (ግዕዛናዊ) ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት ደግሞ፣ አሁን ያለው ባህል (ሁኔታ) ግብረገባዊ ነው የሚል አስተምህሮ ስላለው፣ ማናቸውንም ባህል በተመለከተ ሒስ መሰንዘር በፍጹም አይቻልም:: በዚህ አመለካከት ግብረገብን የሚያድሱ ሰዎች፣ ሥነ ምግባር የጐደላቸው ሰዎች ናቸው::

45

# ግብረገባዊ ፋይዳዎችን "በሌላው ላይ መጫን" ተገቢ ነው?[1]

ግብረገባዊ መስፈርቶችን በሌላው ላይ መጫን አይቀሬ ነው:: ብዙ ሰዎች ግብረገባዊ መስፈርቶችን በሌላው ላይ መጫን ተገቢ አይደለም ይላሉ:: ይህ አነጋገራቸው እርስ በርሱ የሚጋጭ ነው:: ዐዋጃቸውን በሌላ መልኩ ከገለጽነው፣ "ግብረገባዊ ፋይዳዎችን በሌላው ላይ መጫን ኢግብረገባዊ ነው--ግብረገባዊ አይደለም?" እንደ ማለት ነው:: ሕግ ይረቅ ዘንድ የሚቃወሙ ሰዎች፣ "ሕግ አይርቀቅ" የሚለውን ግብረገባዊ አቋማቸውን በሌላው ላይ እየጫኑ ነው:: ለዚህም ነው፣ "ግብረገባዊ መስፈርቶችን በሌላው ላይ መጫን ግብረገባዊ አይደለም" የሚለው አቋም እርስ በርሱ ይጋጫል ያልነው::

እነዚህ ሰዎች የሚቃወሙት ሁሉንም ግብረገባዊ መስፈርቶች አይደለም:: የሚቃወሙት እነርሱ የማይደግፉትን አቋም ብቻ ነው:: ይህም አቋማቸው ወጥነት እንደሌለው የሚያሳይ ነው:: እነዚህ ሰዎች ሁሉንም ግብረገባዊ መስፈርቶች ፈጽመው የሚቃወሙ አይደሉም (በመሠረቱ ሁሉንም ግብረገባዊ መስፈርቶች መቃወም በፍጹም አይቻልም)፤ ነገር ግን ዕቅዳቸው እኛ የምንከተላቸውን ግብረገባዊ መስፈርቶች፣ እነርሱ በሚፈቅዷቸው ግብረገቦች መተካት ነው::

እስካሁን በተነጋገርንባቸው ነገሮች ላይ ብርሃን ሊፈነጥቁባቸው የሚችሉትን አንዳንድ ምሳ ሌዎች እንመልከት:-

ኢትዮጵያ የምትተዳደርበት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሆን ብለው የዋሃንን የገደሉ ሰዎች፣ በሠሩት ወንጀል እነርሱም እንዲሞቱ ያዛል:: ነገር ግን ይህን መሰል ጥፋት ያጠፉ ሰዎች መሞት የለባቸውም የሚሉ ሰዎች፣ የራሳቸውን ግብረገባዊ መስፈርት የችግሩ ሰለባ በሆነው ሰውና በማኅበረሰቡ ላይ እየጫኑ ነው:: በጥፋተኞች ላይ የሚበየነውን ከፍተኛ ቅጣት መቃወማቸው፣ የጥፋቱ ሰለባ የሆነው ሰው ከፍተኛ ፍትሕ እንዳያገኝ መከልከላቸው እንዲሁም ለኅብረተሰቡ እንከን አልባ የሆነ ሰው

[1] Norman L. Geisler and Frank S. Turek III, *Legislating Morality* (Minneapolise: Bethany House, 1998), 41-45.



እንዳይገደል፣ የሕግ ጥበቃ አያስፈልገውም ማለታቸው ነው:: ስለዚህ አንድ ሰው ከፍተኛ ቅጣትን ቢቃወም ወይም ቢደግፍ፣ የሚደግፈውን ግብረገባዊ ፋይዳ በሌላው ላይ እየጫነ ነው ማለት ነው::

በአጠቃላይ ማናቸውንም ዐይነት ግብረገባዊ ፋይዳዎች መቃወም አይቻልም:: ባይሆን ሊጠየቅ የሚገባው መሠረታዊ ጥያቄ፣ "ሰዎች፣ ሁሉ ሊቀበሉት የሚገባቸው ትክክለኛ የሆኑ ግብረገባዊ ፋይዳዎች የትኞቹ ናቸው?" የሚለው ነው::

"ግብረገባዊ ፋይዳዎችን ልትጭንብኝ አይገባም" ለሚሉት ሰዎች ሌላ አንድ ምሳሌ ብጨምርስ? ውርጃን የሚደግፉ ሰዎች፣ "ውርጃን የሚከለክለውን ሕግ አንሡልን" ሲሉ እንዲሁም የውርጃ ተቃዋሚዎች፣ "ውርጃን የሚከለክለው ሕግ መነሣት የለበትም" ማለታቸው፣ ሁለቱም ወገኖች የራሳቸውን ግብረገባዊ መስፈርት በሌላው ላይ መጫናቸው ነው::

ውርጃን የሚቃወሙ ሰዎች፣ "እናቲቱ እርግዝናዋን ማቋረጥ የለባትም" የሚለው አቋማቸው፣ እናትየው እርግዝናዋን እንዳታቋርጥ የሚያስገድድ ሲሆን፣ ውርጃን የሚደግፉ ሰዎች ደግሞ፣ እናቲቱ ፅንሱን ለማቋረጥ የምታደርገውን ምርጫ (ውሳኔ) በፅንሱና (ባልተወለደው ልጅና) በአባትየው ላይ የሚጭን ነው፤ አባትየው የልጁ አባት እንዳይሆን፣ የሟች አባት እንዲሆንና የአብራኩን ክፋይ የመጠበቅ መብት እንዳይኖረው የሚያደርግ ነው::

በአጭሩ ውርጃን የሚቃወሙ ሰዎች ግብረገባዊ ፋይዳቸውን በእናቲቱ ላይ ሲጭኑ፣ ውርጃን የሚደግፉ ሰዎች ደግሞ ግብረገባዊ ፋይዳቸውን ባልተወለደው ልጅና በአባትየው ላይ ይጭናሉ:: በሌላ አገላለጽ ሁለቱም ጐራዎች፣ የራሳቸውን ግብረገባዊ ፋይዳ በሌላው ላይ መጫን ፍላጎታቸው ነው:: ስለዚህ መጠየቅ የሚገባን ቍልፍና መሠረታዊ ጥያቄ፣ "ልንከተለው (ልንቀበለው) የሚገባን ትክክለኛ ግብረገባዊ ፋይዳ የማን ነው? ወይም የቱ ነው?" የሚለውን ጥያቄ ነው::

ምናልባት እዚህ ጋ፣ "*የነጻዊነት አመለካከት* (እሳቦት) [Libertarian] የት ቦታ ነው የምናስቀምጠው?" የሚለውን ጥያቄ እንጠይቅ ይሆናል:: ይህን ጥያቄ የምንጠይቅበት ምክንያት፣ በዚህ ጐራ ሥር ያሉ ወይም ይህን አመለካከት የተቀበሉ ሰዎች፣ የራሳችንን ግብረገባዊ ሕግጋት በሌላው ላይ መጫን አንፈልግም የሚለውን ዐዋጃቸውን ስለተቀበልን ነው:: እውነቱ ግን እነርሱ እንደሚሉት አይደለም:: በአብዛኛው የእዚህ አመለካከት ደቀ መዛሙርት ፓለቲከኞች ናቸው:: ነጻነት የሚለውም አመለካከታቸው የቆመው "ነጻነት" [Liberty or Freedom] ገደብ የለሽና ፍጹም ነው በሚለው ወለል (መሠረት) ላይ ነው:: ለዚህም ነው ሰዎች ያሻቸውን ነገር

የመምረጥ፣ የፈለጉትን ነገር (ፍላጎታቸውን) የመግለጽ፣ የፈለጉትን ሥራ የመሥራት፣ ውርጃን የማካሄድ ወዘተ "መብት" አላቸው የሚሉት::

ከስድስት ቢሊዮን ያላነሰ ሰው በሚኖርባት በዚህች ምድር፣ የነጻዊነት አስተሳሰብ ብዙ የሚያላውስ (የሚያስሄድ) አይደለም:: ነጻነት ገደብ ካልተበጀለት ሌላውን ይጐዳል:: የፈለግኸውን የመናገር ነጻነት አለህ ያልነው አንድ ሰው፣ ሲኒማ ቤት ውስጥ "እሳት!" እያለ ቢጮኽስ? አስቸጋሪ ነው:: የፈለግኸውን የመጠጣት ነጻነት አለህ ያልነው ሰው፣ አደንዛዥ ዕፆችን ቢወስድስ? አስቸጋሪ ነው:: እንግዲህ እውነታው እንደዚህ ነው:- "ለሰው ልጆች ከፍተኛ የሆነ ነጻነት መስጠት፣ እንዳችም ነጻነት ያለመስጠት ያህል አደገኛ ነው":: ይህ የሚሆንበት ምክንያት፣ የነጻነቱ አሉታዊ ጉን፣ ሌሎችን ሰዎች ስለሚጐዳ ነው::

ግብረገባዊ መስፈርቶች በያንዳንዱ ሰው ላይ የማንጭን ከሆነ፣ ወንጀለኞች ኢግብረገባዊ የሆነው ፋይዳቸውን (መስፈርታቸውን) በእንከን አልባ ሰዎች ላይ መጫናቸው ነው::

## "ሌላውን ሰው እስካልጐዳው ድረስ"

የነጻዊነትን አመለካከት የተቀበሉም ሰዎች አስገድዶ መድፈርን፣ ግድያን፣ ስርቆትን፣ ወዘተ በተመለከተ ሕግ እንደሚያስፈልግ ያምናሉ:: ነገር ግን ሌላውን ሰው የማይጐዳ፣ በተጠቃሚው ወይም በአድራጊው ላይ ብቻ አሉታዊ ውጤት የሚያስከትለውንስ (ለምሳሌ:- ዝሙት አደንዛዥ ዕፅ) እንዴት እንመለከተዋለን? የነጻዊነት አራማጆች፣ "ሌላውን ሰው እስካልጐዳህ ድረስ የፈለግኸውን ማድረግ ትችላለህ" የሚለው አነጋገራቸው ትክክል ነውን? ይህ አነጋገር ምክንያታዊ ቢመስልም ብዙ ችግሮች አሉበት::

1. ይህን አመለካከት የሚከተሉ ሰዎች፣ "እስካልጐዳህ ድረስ" ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? አንድ ሰው የሌላውን ሰው አካል ሳይነካ፣ የሥነ ልቡና ወይም የስሜት ጉዳት ቢያስከትልበት ጉዳው አይባልምን?

2. አብዛኞቹ ነገሮች በቀጥታም ይሆን በተዘዋዋሪ ሌላውን ሰው የሚጐዱ ናቸው:: ለምሳሌ:- ዝሙትን ሕጋዊ ብናደርግ ብዙ ሰዎች ከፈለጉት ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ያደርጋሉ:: ይህም ኤድስን ጨምሮ በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉትን የአባለዘር በሽታዎችን በኅብረተ ሰቡ ውስጥ የሚያዛምት፣ አገርንና ሕዝብን የሚጐዳ ድርጊት ነው:: አደንዛዥ ዕፅን መውሰድ ተጠቃሚውን (ወሳጁን) በሱስ፣ በህመም እንዲያውም በሞት



መቅጣቱ ብቻ ሳይሆን፣ በግለሰቡ ቤተ ሰቦች ላይ የሚያስከትለው ምጣኔ ሀብታዊ፣ አካላዊና ሥነ ልቡናዊ ቀውስ በቀላል የሚገመት አይደለም::

ሰዎች ሊቀበሉትና ሊኖሩበት የሚገባቸው እውነታ፣ ሰው ባዶ በሆነ ነገር ውስጥ መኖር ያለመቻሉን ነው:: ማንኛውም ሰው ራሱን የቻለ፣ ከሌላው የተገለለ ደሴት አይደለም:: ስለዚህ ቍልፍ የሆነው ነገር፣ "የነጻዊነት ተከታዮች ለሰዎች ተጨማሪ ነጻነት እንሰጣለን ማለታቸው [ቀድሞ ሕገወጥ የሆነውን ነገር በመሻር]፣ የራሳችሁን ፋይዳ በሌላው ላይ አትጫኑ እያሉ፣ ሌሎችን ሲከሱበት የነበረውን ጉዳይ ራሳቸው እያደረጉት ነው:: የራሳቸውን ፋይዳና የሚያስከትለውን ውጤት ይህንን ሕግጋት በማይቀበሉ ሰዎች ላይ እያጫኑ ነው"::

ምንም ዐይነት ግብረገባዊ ሕግ አልፈልግም የሚሉ ሰዎች፣ የራሳቸውን ግብረገባዊ ፋይዳ በማይፈልገው ሰው ላይ እየጫኑ ነው:: 2+2=4 የሚለውን ስሌት ወይም $H_2O$=ውሃ የሚለውን እውነት የማይቀበል ሰው፣ ከእነዚህ እውነታዎች ተቃራኒ የሆነውን ነገር መቀበሉ አይቀሬ ነው:: ማናቸውም ዐይነት ሕጎች፣ (መጥፎም ይሁን ጥሩ) በሌላው ላይ ግብረገባዊ ፋይዳዎችን መጫናቸው የግድ ነው:: ትክክለኛ የሆነ ግብረገብ የሰዎችን ነጻነት በመወሰን፣ ጥፋት አልባ ለሆኑት ሰዎች ጥበቃ ያደርጋል:: በአጠቃላይ ሕግን ማርቀቅ ግብረገባዊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ልንሸሸው የማንችለው እንዲሁም ለአንድ ኅብረተሰብ ህልውና እጅግ አስፈላጊ የሆነ ነገር ነው:: ሕግን አርቅቆ ተፈጻሚ ያለማድረግ ፍጹም የሚቻል ነገር አይደለም::

## ማጠቃለያ

ግብረገባዊ መስፈርቶችን ሕጋዊ ማድረግ፣ ሥነ ምግባራዊ ነው ወይስ አይደለም በሚለው ርእስ ዙሪያ፣ ግብረገብን ሕጋዊ ማድረግ የሚቃወሙ ሰዎች የራሳቸውን ግብረገባዊ ሕግጋት ሕጋዊ ለማድረግ እንደሚሞክሩ አይተናል:: "ግብረገባዊ መስፈርቶችን በሰው ላይ መጫን ኢግብረገባዊ ነው" የሚሉ ሰዎች፣ የራሳቸውን ግብረገብ ለማቆም እንደሚውተረተሩ ተገንዝበናል:: ሕግጋቶች ሁሉ አንድን ባሕርይ ወይም ግብር ትክክልና (ሠናይ) ስሕተት (እኵይ) እስካሉ ድረስ፣ ግብረገብን ሕጋዊ ማድረግ ሥነ ምግባራዊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን አይቀሬ ነው::

4.6

# ግብረገባዊ አንጻራዊነትን የማንቀበለው ለምንድን ነው?

"ግብረገባዊ አንጻራዊነት ምንድን ነው?" በሚለው ርእስ ሥር፣ የአንጻራዊነትን ትንታኔ በስፋት ለማየት ሞክረናል:: ግብረገባዊ አንጻራዊነት፣ ግብረገባዊ እውነታዎች እንደ ምግብ ጣዕም በግለሰቦች ኀሊናዊ ብያኔ ይወሰናሉ የሚል አመለካከት ነው:: ስለዚህም ግብረገባዊ ፋይዳዎች በሰዎች ፍላጎት (ስሜት ወይም ጣዕም) ላይ ሙሉ ለሙሉ መሠረት ስለሚያደርጉ ግለሰቡ፣ "ይህ ለእኔ (Subject) እውነት ነው" እያለ ፋይዳዎቹን ኀሊናዊ (Subjective) ያደርጋቸዋል::

ሁለት ሰዎች ተመሳሳይ የሆነ ግብረገባዊ ምርጫ ሲቀርብላቸው፣ አንደኛው የመረጠውን ተቃራኒ፣ ሌላው ሊመርጥ ይችላል:: በሁሉም ሰው ላይ ተግባራዊ የሚሆን ግብረገባዊ መመሪያ የለምና:: አንድ ሰው ትናንት ያደረገውን ተቃራኒ ነገር ዛሬ ቢያደርግ፣ ስሕተት ነው ማለት አይቻልም::

ግብረገባዊ ሕግጋት ፍጹማዊ ናቸው ሲባል፣ ሕግጋቶቹ ነባራዊ እንጂ ኀሊናዊ ስላልሆኑ፣ ለማንኛውም ሰው፣ በየትኛውም ጊዜና በማናቸውም ቦታ የማይሻር ወይም የማይለዋወጡ ናቸው ማለት ነው:: በርካታ ኢትዮጵያውያን፣ ግብረገባዊ አንጻራዊነትን የሚደግፉ አይደሉም:: ነገር ግን አውሮፓና አሜሪካ ተምረው የሚመጡ ብዙ ሰዎች፣ ግብረገባዊ ሕግጋት አንጻራዊ እንጂ ፍጹማዊ አይደሉም፣ የሚለውን አቋም ይዘው ይታያሉ:: ነገር ግን ይህን አቋም የያዙ ሰዎች በቀለም ዕውቀት "ዘልቀው ሄደዋል" ማለት፣ አቋማቸው ችግር የለበትም ማለት አይደለም:: ቢያንስ እስካሁን ያየናቸው እውነታዎች፣ አንጻራዊነት ስሕተት ለመሆኑ በቂ እማኞች ናቸው:: ከዚህ በመቀጠል እስካሁን ያየናቸውን የአንጻራዊነት መሠረታዊ ችግሮች በአጭሩ እንከልሳቸዋልን፤ ይህም አንጻራዊነትን መቀበል የሌለብንን ምክንያት አመላካች ነው[1]::

[1] Norman L. Geisler and Frank S. Turek III, *Legislating Morality* (Minneapolise: Bethany House, 1998), 51-54.



## 1. አንጻራዊነት እርስ በርሱ ይቃረናል

አንጻራዊነት የቆመባቸው ሁለት መሠረቶች:-

ሀ. ፍጹማዊ የሆነ እውነት የለም እንዲሁም፣
ለ. ፍጹማዊ የሆነ ፋይዳ የለም የሚሉት ናቸው::

የመጀመሪያውን ዐዋጅ እንመልከት:: እውነት ፍጹም ካልሆነ፣ "ፍጹማዊ የሆነ እውነት የለም" የሚለው አነጋገር እንዴት ፍጹም እውነት ሊሆን ይችላል? ዐረፍተ ነገሩ እርስ በርሱ ይቃረናል:: አንጻራዊነትን የተቀበሉ ሰዎች፣ "ይህ ለአንተ እውነት ነው፤ ለእኔ ግን አይደለም" ወይም "እውነት የሚባል ነገር የለም" ሲሉ ይደመጣል:: አንጻራውያን አነጋገራቸው ኢምክንያታዊ መሆኑን ለማሳየት፣ "ይህ አነጋገራችሁ እውነት ነው?" ብላችሁ ብትጠይቁአቸው፣ ከአቋማቸው ጋር የተቃረነ መልስ እንደሚሰጡ እሙን ነው:: ፍጹማዊ እውነት ከሌለ፣ የአንጻራዊነት አራማጆች ፍጹማዊ እውነት ላለመኖሩ ፍጹም እርግጠኞች ናቸውን?

ፍጹም የሆነ እውነት መኖሩን እንደማንክድ ሁሉ፣ ፍጹማዊ ፋይዳን መካድ አንችልም:: ነገሩን ግልጽ ለማድረግ እርስዎ በእዚሁ ርእስ ጕዳይ ላይ ከወዳጆች ጋር ይወያያሉ እንበል:: እርሶ ፍጹም የሆነ ግብረገባዊ ፋይዳ አለ የሚሉ ሲሆን፣ ባልንጀራዎ ደግሞ ይህንን ነገር በመቃወም፣ "ሰዎች የተለያየ ፋይዳ አላቸው፤ ስለዚህ ይህ ሰው ትክክል ነው ያ ደግሞ ተሳስቶአል ለማለት ምንም ዐይነት መሠረት የለም..." እያሉ ሳለ፣ ንግግራቸውን ሳይጨርሱ፣ "ዝም በል አሳብህን የመግለጽ ምንም ዐይነት መሠረት የለህም!" ቢሏቸው፣ ባልንጀራዎ በአነጋርዎ ክፉኛ ማዘናቸው ቅቡል ነው:: ምክንያቱም ማንኛውም ሰው እውነት ነው ብሎ የተቀበለውን መብት (ሐሳብን የመግለጽ)፣ እርሶ ተቃውመዋልና ነው:: ልክ ነው ጓደኛዎ ሐሳባቸውን የመግለጽ መብት አላቸው::

ከብዙ ዓመት በፊት አንድ አዛውንት በትምህርታቸው ገፍተው የሄዱ ወጣቶች ዘንድ፣ በዚህ ርእሰ ጕዳይ ዙሪያ ንግግር ያደርጋሉ[2]:: አንዲት ወጣት እጇን በማውጣት ጥያቄ እንዳላት ከገለጸች በኋላ፣ አዛውንቱ ጥያቄዋን እንድትጠይቅ ፈቃድ ይሰጧታል:: ልጅቱም ቆማ፣ "ፍጹማዊ የሆነ ፋይዳ ስለሌለ እያንዳንዱ ሰው እንደ መሰለውና እንደ ተረዳው ይወስደዋል" ትላቸዋለች:: አዛውንቱም ጮኽ ብለው፣ "አፍሺን ዘግተሽ ተቀመጪ! ድንጋይ ራስ!፤ የአንቺን አመለካከት የሚሰማ ያበደ ሰው አለ?" ይሏታል:: ልጅቱም፣ "ሐሳቤን የመግለጽ መብቴን ነፍገውኛል" ስትል በአዛውንቱ ላይ እጅግ አዘነች:: አዛውንቱ ጠንከር ያለ፣ ሊያሳዝናት የሚችል ቃል

[2] እኚህ ሰው Professor Norman L. Geisler ናቸው::

የተናገሩት፣ ለሚመልሱት መልስ መደላድል እንዲሆናቸው ነበር፡ "እንዲህ ዐይነት መብት የለሽም፤ ይህ ዐይነት መብት እንደ ሌለ የነገርሽኝ አንቺው ነሽ" አሏት።

ቁም ነገሩ እዚህ ጋ ነው። የልጅቷ ቅሬታ "ፍጹማዊ ፋይዳ የለም" የሚለውን አስተያየት (ጥያቄ) የሠነዘረችው የመናገር መብቷን ተጠቅማ እንዲሁም ይህ መብት እንዳለ ታሳቢ አድርጋ ነው። በሌላ አገላለጽ ፍጹማዊ ፋይዳዎችን በሙሉ የሚክዱ ሰዎች፣ ቢያንስ መብታችን መጠበቅ አለበት (የመናገር መብት) የሚለውን ፋይዳ እንደ ተቀበሉት የሚያሳይ ነው። ይህም አቋማቸው ወጥነት እንደ ጐደለው የሚያመለክት ነው። ግብረገባዊ ፋይዳዎች መኖራቸውን ልንክድ አንችልም። ይህም መኖራቸውን ፍንትው አድርጐ ያሳያል።

በሺካጎ ዩኒቨርስቲ መምህር የነበሩት ፕሮፌሰር አለን ብሉም፣ አንጻራዊነትን ለተቀበሉ ተማሪዎቻቸው ግብረገባዊ ሕግጋትን በተመለከተ እንዲህ ይሏቸዋል፤ "በሕንዳውያን ባህል አንድ ሰው ሲሞት በሕይወት ያለች ሚስቱ ከሟች ባሏ ጋር ተቃጥላ እንድትገደል ይፈረድባታል"። ፕሮፌሰር ይህ ተግባር ፍጹም ስሕተት መሆኑን ተማሪዎቻቸው መቀበላቸውን ካረጋገጡ በኋላ፣ "እናንተ በሕንድ አገር የምትኖሩ፣ በእንግሊዝ መንግሥት የተወከላችሁ የሕንድ አስተዳዳሪ ናችሁ እንበል፤ እንግሊዛዊ የሆነች ሴት ሕንዳዊ ባሏ ስለሞተባት ከሬሳው ጋር ትቃጠል ብትባል ትስማማላችሁ?" ሲሉ ተማሪዎቹን ይጠይቃሉ[3]።

ሕያዋንን ከሙታን ዘመዶቻቸው ጋር ማቃጠል ፍጹም ስሕተት ነው። ስለዚህም በሕንድ የሚገኘው እንግሊዛዊ አስተዳዳሪ፣ ሕጉን በመቃወም ሴትየዋን መታደግ እንዳለበት እሙን ነው። ነገር ግን ይህ ጒዳይ ለፕሮፌሰር ብሉም ተማሪዎች የምጥ ጣር ነው የሆነባቸው። ትገደል የሚሉ ከሆነ (ግድያውን የሚፈቅዱ ከሆነ) እንከን አልባ የሆነቸውን ሴት ግድያ ሊደግፉ ሆነ፤ ቢቃወሙ የተቀበሉትን የአንጻራዊነት አመለካከት ሊክዱ ሆነ[4]።

## 2. ፍጹማዊ የሆነ የፍትሕ መስፈርት ከሌለ ኢፍትሓዊነትን ማወቅ አንችልም

ከብዙ ዓመታት በፊት በአንድ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ሥነ ምግባርን ያስተምሩ የነበሩ አንድ መምህር፣ ለተማሪዎቻቸው ከፍተኛ ነጥብ የሚይዝ የጥናት ጽሑፍ እንዲጽፉ ይነግሩአቸዋል። የሚጽፉበትን ርእስ የሚመርጡት ተማሪዎቹ ራሳቸው ናቸው፡

[3] Allan Bloom, *The Closing of the American Mind* (New York: Simon and Schuster, 1987), 26

[4] ዝኒ ከማሁ።



ነገር ግን መምህሩ ጽሑፋቸው በሥርዐቱ ተጠርዞና ምንጩ በትክክል ሰፍሮ መቅረብ እንዳለበት ለተማሪዎቹ ይገልጻሉ። የአንጻራዊነትን አስተሳሰብ የሚቀበል አንድ ተማሪ ግብረገብ አንጻራዊ ነው በሚል ርእስ፣ "ግብረገቦች ሁሉ አንጻራዊ መሆናቸውን፤ ሁሉም የአመለካከት ጒዳይ እንደ ሆነ፤ አንዱ ኮካኮላ ቢወድ ሌላው ፋንታ ቶኒክ እንደሚመርጥ" በመግለጽ፣ አሳማኝ ጽሑፍ በአንጻራዊነት ላይ ያቀርባል። የተማሪው ጽሑፍ በቆንጆ የእጅ ጽሕፈት የተከተበ፣ በማስረጃ የተጠናከረ፣ መረጃ የወሰደባቸውን ምንጮች ሥርዐቱን ጠብቆ የጠቀሰ፣ በተፈለገው መጠን የተጻፈ፣ ወቅቱን ጠብቆ (በማስረከቢያው ትክክለኛ ጊዜ) ለመምህሩ የተሰጠ እንዲሁም ማራኪ በሆነ ሁኔታ የቀረበና በሰማያዊ ሽፋን የተጠረዘ ነበር። ፕሮፌሰሩ ጽሑፉን ካነበቡ በኋላ፣ በመጀመሪያው ገጽ ላይ፣ "እኔኮ ሰማያዊ ሽፋን አልወድም፤ ስለዚህ ኤፍ ሰጥቼሃለሁ" የሚል ጽሑፍ ይጽፋሉ[5]።

ተማሪው ጽሑፉ ተመልሶለት ውጤቱን እያየ፣ ሲቃ እየተናነቀው እንደ ብራቅ ይጮኻል። ወደ ፕሮፌሰሩ ቢሮ ሮጦ በመሄድ ዐይኑን እያጒረጠረጠ፣ እጁን ወዲያና ወዲህ እያወራጨ፣ "ሰማያዊ ሽፋን ስለማልወድ 'F' ሰጥቼሃለሁ ይሉኛል እንዴ? በርግጥ ይህ አግባብ አይደለም! በፍጹም ትክክል አይደለም! ይህ እንዴት ፍትሓዊ ይሆናል! አንድ ጽሑፍ በይዘቱ አንጂ በተጠረዘበት (በተሸፈነበት) ወረቀት እንዴት ይመዘናል?"[6]።

ከብዙ ጸጥታ በኋላ ፕሮፌሰሩ፣ "ቆይ እስቲ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ፤ _አግባብ_፣ _ትክክል_፣ _ፍትሕ_ ስትል ምን ማለትህ ነው? ማንኛውም ነገር የአመለካከት ጒዳይ ነው፤ አንዱ ኮካኮላ ቢወድ ሌላው ፋንታ ቶኒክ ይወዳል አላልክም እንዴ?" በማለት ተማሪውን ይጠይቁታል[7]።

ተማሪውም፣ "ልክ ነው! ይህ የእኔ አቋም ነው" ይላል። ፕሮፌሰሩም፣ "መልካም፤ እኔም ሰማያዊ ሽፋን አልወድም ስለዚህ 'F' አግኝተሃል"[8]።

እዚህ ጋ ሲደርሱ ነው የፕሮፌሰሩ አካሄድ ለተማሪው የገባው። የተማሪው ሁኔታ ፍጹም የሆነ ግብረገባዊ ፋይዳ እንዳለ የሚያሳይ ነበር። ቢያንስ አግባብ፣ ትክክልና ፍትሕ እንዳሉ ያምናል። ተማሪው መምህሩን ፍትሓዊ አይደሉም ሲል የከሰሰው፣ ፍትሕን በተመለከተ ፍጹማዊ የሆነ መስፈርት እንዳለ በማመኑ (መስፈርቶቹን ታሳቢ

[5] Allan Bloom, *The Closing of the American Mind*, 26.

[6] ዝኒ ከማሁ።

[7] ዝኒ ከማሁ።

[8] ዝኒ ከማሁ።

አድርጎ) ነው:: ይህ ቀላል እውነት ነበር፣ ተማሪው ለወራት ሲያዋቅር የቆየውን የአንጻራዊነት ማስረጃ ዶግ ዐመድ ያደረገው::

ይህ ታሪክ ፍጹም የሆነ ግብረገባዊ ፋይዳ እንዳለ የሚገልጽ ነው:: ግብረገባዊ ሕግ በሰዎች ልብና አእምሮ ውስጥ የተቀረጸ ጉዳይ እንደ ሆነ ነው:: ተማሪው የአስተማሪውን ድርጊት የኰነነበት ሁኔታ፣ ፍጹማዊ የሆነ ትክክልና ስሕተት እንዳለ የሚያሳይ ነው:: ሰዎች ኢፍትሐዊ የሆነ ሁኔታ ሲያደርሱብን ምን ይሰማናል? ከተሞክአሮችን የምንማረው እውነት፣ ግብረገባዊ ሕጋጋት ከፀሓይ እንኳ ይልቅ ብሩኅ ሆነው እንደሚታዩ ነው::

## 3. አንድን ነገር መለካት የሚቻለው፣ ፍጹማዊ መስፈርት ሲኖር ብቻ ነው

እውነታዎች ሁሉ አንጻራዊ ናቸው ሲባል፣ "አንጻራዊ የሆኑት ከምን አንጻር ነው?" የሚለው ጥያቄ አእምሮአችንን ይሞላዋል::

የትራፊክ መብራት እርሶ መኪናዎን በሚያሽከረክሩበት አቅጣጫ ያሉትን መኪናዎች አስቆሞአል እንበል:: ከእርሶ ጐን የቆመው መኪና እየሄደ ነው:: አሁን እየሄደ ያለው እርስዎኖት ወይስ ሌላኛው መኪና? እርሶም ሆኑ ሌላኛው መኪና መሄድ ብትጀምሩ፣ በተጨማሪም ልክ እንደናንተው ዛፎች፣ ሕንጻዎች፣ የኤሌክትሪክ ምሰሶዎች፣ ራሱ መንገዱ እንዲሁም ማናቸውም ነገሮች እናንተ በምትሄዱበት አቅጣጫ ቢሄዱ፣ እንቅስቃሴ መኖሩን መለካት (ማወቅ) አይቻልም:: ማን እየተንቀሳቀሰ እንዳለ፣ ማን ደግሞ እንደ ቆመ መለካት የሚቻለው፣ ቋሚና ፍጹም የሆነ መስፈርት ሲኖር ብቻ ነው::

እንደ እንቅስቃሴው ሁሉ ግብረገብ ሊለካ የሚችለው ቋሚና ፍጹም የሆነ መስፈርት ሲኖር ብቻ ነው:: ቋሚና ፍጹም የሆነ ግብረገባዊ መስፈርት ከሌለ፣ "ሂትለር መጥፎ ሰው ነው"፣ "የዘር ጥላቻ ትክክለኛ ነገር አይደለም" ወዘተ የሚባሉት ነገሮች ትርጉም አይኖራቸውም:: ነገር ግን ሂትለር ጥፋተኛ እንደ ሆነ፣ የዘር ጥላቻ መጥፎ መሆኑን እናውቃለን:: ምክንያቱም ፍጹም የሆነ ግብረገባዊ መስፈርት ስላለ ነው::

እንዲያውም ፍጹም የሆነ ግብረገባዊ መስፈርት ከሌለ፣ ፋይዳን የሚያመለክቱ ቃላት ለምሳሌ:- "ጥሩ"፣ "መጥፎ"፣ "የተበላሸ"፣ "የከፋ"፣ "እኩይ"፣ "ሠናይ"፣ "ዋልጌ"፣ "ጨዋ" ወዘተ የሚሉት ቃላት ቅንጣት ታህል ትርጉም አይኖራቸውም:: ነገር ግን ትርጉም አላቸው:: ይህ የሆነበትም ምክንያት፣ ፍጹም የሆነ ግብረገባዊ



መስፈርት ስላለ ነው:: "የኅብረተሰባችን ግብረገብ እየተበላሸ ነው" ስንል፣ ኅብረተሰባችንን ከቋሚ መስፈርት ጋር አነጻጽረነው ነው:: እማሆይ ቴሬሳ፣ "መልካም ሴት" ሂትለር ደግሞ፣ "መጥፎ ሰው" ነው የምንለው፣ ከእነርሱ በላይ ካለ ግብረገባዊ መስፈርት ጋር አነጻጽረናቸው ነው:: እማሆይ ቴሬሳ መልካም ሰው ነበሩ የምንለው የታረዘን በማልበስ፣ የተራበን በማብላት፣ የታመመን በማስታመም ሁላችንም ወደ ተቀበልነው ፍጹም ወደ ሆነ ግብረገባዊ መስፈርት ስለተጠጉ ነው:: ሂትለር መጥፎ ሰው ነው ያልንበት ምክንያት፣ ምግባሩ ፍጹማዊ ከሆነው ግብረገባዊ መስፈርት ጋር ስለሚቃረን ነው:: ሂትለር ሰዎች እንዲያደርጉለት የሚፈልገውን ነገር፣ እርሱ ለሰዎች ማድረግ ያለመፈለጉ ነው እኩይ የሚያሰኘው::

## 4. ፍጹማዊ የሆነ ግብረገባዊ መስፈርት ከሌለ፣ ግብረገባዊ መግባባት ሊኖር አይችልም

በቅርቡ ከባልንጀራዎ ጋር የተከራከሩበትን ነገር ያስታውሱ:: ለምንድን ነው የተከራከራችሁት? እርሶ የሚደግፉት ነገር ትክክል፣ የተቃረኑት ነገር ደግሞ ስሕተት ስለሆነ ነው:: ትክክልና ስሕተት ትርጉም የሚኖረው ትክክልን ትክክል፣ ስሕተትን ደግሞ ስሕተት የሚል መስፈርት ሲኖር ብቻ ነው:: በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ላይ በሚከራከሩበት ጊዜ ሁሉ፣ በውስጥ ታዋቂነት ቋሚ የሆነ መስፈርት መኖሩን እንደ ተቀበሉ የሚገልጽ ነው:: ሙግቱም ማእከል ያደረገው፣ ፍጹም ወደ ሆነው መስፈርት መጠጋትን ነው::

ፍጹማዊ የሆነ ግብረገባዊ መስፈርት ከሌለ፣ ግብረገባዊ ውይይቶች ትርጉም አይኖራቸውም:: አንድ ሰው ከማሆይ ቴሬሳ ይልቅ ሂትለር "ጥሩ ሰው" ነበር ማለት ይችላል:: ሰዎች ሊሠሩአቸው ከሚችሏአቸው ነገሮች ሁሉ ግድያ "ጥሩ ነገር ነው" የሚል ሰው "ትክክል" ነው ማለት ይቻላል:: የባሪያ ንግድም ሆነ አስገድዶ መድፈር ጥሩ እንዲሁም ሊደፋፈር የሚገባው ነገር ነው ማለት ነው:: የታረዘን ማልበስ፣ የተራበን ማብላት፣ የታመመን ማስታመም ወንጀል ሊሆን ይችላል ማለት ነው:: ሰብአዊነታችን የተቀበለው ግብረገባዊ መስፈርት፣ እነዚህ ነገሮች ሁሉ ትርጉም የለሽ መሆናቸውን የሚገልጽ ነው:- ከላይ ያየነውም ሁሉ ፍጹም ስሕተት ነው:: እንግዲያው እነዚህ ነገሮች ስሕተት ከሆኑ፣ አንጻራዊነት ስሕተት ነው ማለት ነው::

በሌላ አገላለጽ ከግብረገባዊ መስፈርቶች የምንማረው ነገር፣ ግድያንና አስገድዶ መድፈርን የመሳሰሉት ነገሮች፣ ፍጹም ስሕተት መሆናቸውን ነው:: ይህ እውነት ከሆነ አንጻራዊነት ስሕተት ነው:: አንጻራዊነትን ማመን ማለት፣ በእማሆይ ቴሬሳና በሂትለር፣ በባርነትና በነጻነት፣ በእኩልነትና በአድልዎ፣ በፍቅርና በጥላቻ፣

በሕይወትና በሞት ወዘተ መካከል ምንም ዐይነት ግብረገባዊ ልዩነት የለም ማለት ነው።

ይህ ርእሰ ጉዳይ የሚሽከረከርበት ሌላው ነጥብ፣ ሰዎች ትክክልና ስሕተትን ይወስናሉ ወይስ ያገኛሉ የሚለው ነው። የሰው ልጆች ትክክልና ስሕተትን የሚወስኑ ከሆነ፣ ከላይ የጠቀስናቸውን ነገሮች ጨምሮ፣ ማናቸውንም ነገሮች ቢያደርጉ «ትክክል» ናቸው ማለት ነው። ነገር ግን የእውነት ፈጣሪዎች የሰው ልጆች አይደሉም፤ የሚያገኙ እንጂ። የመሬትን ስበት የወሰነው ኒውተን አይደለም፤ ያገኘው እንጂ። እንደዚሁም ግድያ ስሕተት ነው የሚለውን ጉዳይ የሚወስነው ሰው አይደለም፤ ነገር ግን በውስጣችን ያለው ግብረገባዊ መስፈርት ነው እንጂ።

በውስጣችን የሚገኘውን ግብረገባዊ መስፈርት ያኖረው፣ የግብረገብ ጠንሳሽ የሆነ፣ ከእኛ በላይ ያለ አካል ነው። ከግብረገብ የምንማረው ነገር፣ እግዚአብሔር ትክክልና ስሕተትን በተመለከተ ያለውን ሕግጋት ነው። ይህም የግብረገብ ጠንሳሽ፣ ራሱ እግዚአብሔር ነው እንድንል ያደርገናል። ግብረገባዊ መስፈርቶችን እግዚአብሔር [ከእኛ ኀላይ የሆነ አካል] ባያቆመው ኖሮ፣ ፍጹማዊ መስፈርት (ሥልጣናዊ መስፈርት) ሳይሆን፣ የሰዎች አመለካከት ይሆን ነበር። በሌላ አገላለጽ ፍጹማዊ የሆኑ ግብረገባዊ መስፈርቶች ፍጹም የሆኑት፣ ሁሉ ነገር የሚመዘንባቸው የመጨረሻ መስፈርት ስለሆኑ ነው።

ሃይማኖቶች የተጀመሩት ግብረገባዊ ሕግጋትን ለማቆም ነው የሚለው የአንዳንድ ግለሰቦች አነጋገር፣ ኢምክንያታዊ የሚሆነው ከዚህ የተነሣ ነው። አንድ ሰው ሕግ ሰጪውን ባያውቅም እንኳ ግብረገባዊ ሕግጋትን ግን መካድ አይችልም።

## 5. አንጻራዊነት እኵይ ምግባርን አይኰንንም

ግላዊ ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት (ሥነ ምግባራዊ ኀሊናዊነት) የግለሰቦችን እኵይ ባሕርይ አይኰንንም፤ እኵይ የሚባል ግብረገብ አለ የሚል እምነት ስለሌለው። ግብረገብ ኀሊናዊ ከሆነ (በሰዎች ፍላጐት ["ጣዕም"] የሚወሰን ከሆነ)፣ ሰዎች የቱንም ያህል ጸያፍ ሥራ ቢሠሩ፣ ምግባራችሁ ስሕተት ነው የሚል ዐቅም የለውም (ቢያደርገው እንኳ እየገለጸ ያለው ስሜት፣ ጣዕም ወይም ግለሰቡ ያሻው ነገር እንጂ፣ መሆን ያለበት ነገር አይደለም)። ተሳስተሃል ማለት አይቻልም![9]

ሰዎችን መተቸት፣ እውነትን ማሳመን፣ መኰነንም ሆነ ማወደስ አይቻልም። ይህም ሕግ በሌለበት ጨዋታ (ለምሳሌ እግር ኳስ)፣ ተጫውቶ ማሸነፍ ወይም ሕግ በሌለበት ቦታ ወንጀለኛን ፍርድ ቤት ይዞ መሄድ እንደ ማለት ነው። በሌላ አገላለጽ

[9] Francis J. Beckwith and Gregory Koukl, *Relctivism* (Grand Rapids: Baker, 1998), 61.



አንጻራዊነት አስገድዶ መድፈርን፣ ዘረኝነትን፣ ሙስናን፣ ሌብነትን፣ ግድያን የመኰነን እንዲሁም የዚህን ተቃራኒ ወገን የማወደስ ዐቅም (መሠረት) የለውም፤ በምን መስፈርት ይኰነናሉ? በምንስ መስፈርት ይወደሳሉ? ችግሩን ለመፍታት በምንስ መስፈርት ጣልቃ መግባት ይቻላል? ምክንያቱም ፍጹማዊ የሆነ አንዳችም እውነት ወይም ሐሰት የለም[10]።

በርካታ አንጻራውያን ውርጃን ሲደግፉ ይስተዋላል። ለዚህ ምክንያታቸው ለሰዎች ምርጫ ከፍተኛ ቦታ ስለሚሰጡ ነው። አንጻራውያን ዘረኝነትን፣ አስገድዶ መድፈርን፣ ሌብነትን ወዘተ እንቃወማለን ማለት አይችሉም፤ አቋማቸው እርስ በርሱ ይቃረናልና።

በአንጻራውያን ዘንድ ውሸትን በመናገር፣ በደል አልባ ሰዎችን መኰነን እንዲሁም ወንጀለኞችን መሸለም ተቀባይነት ሊያገኝ ይችላል። በአንጻራዊነት አስተምሮ፣ ወንጀለኝነትና ወንጀል አልባነት ልዩነት የለውምና።

እንደ አንጻራዊነት አመለካከት በሰዎች መካከል የሚካሄዱ ኪዳኖች፣ ትርጒም የለሽ ናቸው። የጋብቻ ኪዳኖችን ጨምሮ፣ ትዳርን የሚያጸኑና ታማኝነትን መሠረት ያደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ፣ ግብረገባዊ ኀይል የላቸውም። ቃል ኪዳን ተራ ዕቅድ ሳይሆን፣ በግብረገባዊ ግዴታዎች የታሰረ፣ ትርጒም የሞላበት የኑሮ ዘይቤ ነው[11]።

ትክክልና ስሕተት የግል ምርጫ ("ጣዕም") ከሆነ፣ በሌሎች ግብረገብ ላይ ለመፍረድ አንዳችም ዐቅም የለንም። አንዳንድ ነገሮች ስሕተት አንዳንዶችም ትክክል ናቸው የምንል ከሆነ፣ አንጻራዊነት ስሕተት ነው ማለታችን ነው[12]።

## 6. አንጻራዊነት እኵይን እኵይ የማለት ዐቅም የለውም

አንዳንድ ኢአማንያን እግዚአብሔር የለም ለሚለው አቋማቸው ማስደገፊያ ይሆን ዘንድ፣ የመከራከሪያ ነጥብ አድርገው የሚወስዱት፣ «በምንኖርባት ዓለም ውስጥ እኵይ ለምን ተከሠተ» የሚለውን ነጥብ ነው። እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ እንዲሁም ቅዱስ ከሆነ፣ እርሱ በፈጠራትና በበላይነት በሚቈጣጠራት ዓለም ውስጥ፣ እኵይ መከሠት አልነበረበትም፤ ነገር ግን እኵይ የዕለት ተዕለት እውነታ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ራሱን ይቃረናል አልያም እኵይን የመገደብ ዐቅም የለውም ወደሚለው ድምዳሜ ይወስዳል ባዮች ናቸው[13]።

[10] ዝኒ ከማሁ፤ 62።
[11] ዝኒ ከማሁ።
[12] ዝኒ ከማሁ።

ይህ የኢአማንያኑ ሙግት፣ በምንኖርበት ዓለም ውስጥ እኩይ እንዳለ ታሳቢ ያደረገ ነው፤ ይኸውም አንዳንድ ነገሮች ነባራዊ በሆነ መልኩ ስሕተት ናቸው የሚል:: ግብረገብ አንጻራዊ ከሆነ እኩይ አለ የሚለው የሙግት ጅማሮ ትክክል አይሆንም[14]::

ይህን ጉዳይ በተመለከተ ሲ. ኤስ ልዊስ የተባሉት እንግሊዛዊ ሊቅ፣ "እግዚአብሔር የለም ለሚለው ሙግቴ የማቀርበው ማስረጃ፣ በዓለማችን ውስጥ እኩይና ኢፍትሓዊነት አለ የሚለውን ነጥብ ነው፤ ነገር ግን ፍትሓዊና ኢፍትሓዊ የሚለውን ሐሳብ ከየት አገኘሁት? አንድ ሰው አንድን መስመር ጠማማነው ማለት የሚችለው፣ ስለ ቀጥተኛ መስመር የተወሰነ ግንዛቤ ሲኖረው ነው:: ነገር ግን ኢፍትሓዊ በምልበት ጊዜ ይህቺን ዓለም ከምን ጋር እያወዳደርኳት ይሆን?...በርግጥ ፍትሕ የሚባለው ሐሳብ የግሌ ሐሳብ ብቻ ከሆነ ደግሞ፣ እግዚአብሔር የለም የሚለው ሙጉቴ ዶግ ዐመድ ይሆንብኛል:: ነገር ግን በዓለማችን ኢፍተሓዊነት አለ ስል፣ የግሌን አመለካከት ለመደገፍ ያልተከሠተ ነገር ተከሠተ እያልሁ አይደለም"[15]::

አንጻራዊነትን እውነት ከሆነ፣ እኩይን የመነሻ ነጥብ አድርጎ እግዚአብሔር የለም ማለት ስሕተት ነው[16]::

## 7. አንጻራዊነት ወንጀለኞችን የመቅጣት፣ መልካሞችን የመሸለም ዐቅም የለውም

እንደ አንጻራዊነት አስተሳሰብ በመቀጣትና በመሸለም መኻል፣ ቅንጣት ታህል ልዩነት የለም:: ማን ይቀጣ፣ ማንስ ይሸለም ለሚለው ብያኔ መሠረት የሚሆን አንዳችም ውጫዊ መስፈርት የለምና[17]::

ፍጹማዊ መስፈርት ከሌለ ክፉ፣ መልካም ወዘተ የሚባል ነገር አይኖርም:: የሚገርመው ግን፣ አንጻራውያን መኩነንን ይቃወሙ እንጂ፣ መሸለምን ይፈልጋሉ:: ታላቁ ምሁር ሲ. ኤስ ልዊስ፣ "በባሕርያችን ሙገሳንና ሽልማትን መሻታችን እንዲሁም ይቅርታን መጠየቅ መፈለጋችን፣ ግብረገብ ነባራዊ እንደ ሆነ ከልብ እንደ ተቀበልነው አመላካች ነው"[18] ባይ ናቸው::

---

[13] ዝኒ ከማሁ፤ 63::
[14] ዝኒ ከማሁ::
[15] C. S. Lewis, *Mere Christianity* (New York: Macmillan, 1960) 31.
[16] ዝኒ ከማሁ::
[17] ዝኒ ከማሁ፤ 65::
[18] ዝኒ ከማሁ፤ 6-7::



እንግዲያው ለአንጻራውያን ክፉ፣ መልካም ወዘተ የሚሉት ቃላት ትርጒም የለሽ ከሆኑ፣ ከመድብለ ቃላታቸው ውስጥ ሊሰርዙአቸው ይገባል፤ ነገር ግን ነቀፋና ሙገሳ ትርጒም ያላቸው ቃላት ከሆኑ፣ አንጻራዊነት ስሕተት ነው[19]::

## 8. አንጻራዊነት ኢፍትሓዊነትንና ስሕተትን መኰነን አይችልም

በአንጻራዊነት አስተሳሰብ መልካም፣ ጨዋ፣ ሠናይ ወዘተ የሚሉት ቃላት ብቻ ሳይሆኑ፣ ኢፍትሓዊነት፣ ኢግብረገባዊነት፣ ዘረኝነት፣ አስገድዶ መድፈር ወዘተ የሚሉትም ቃላት ትርጒም የለሾች ናቸው:: ይህ የአንጻራዊነት እሳቦት፣ በእነዚህ ተቃራኒ ቃላት መካከል አንዳችም የትርጒም ልዩነት የለም የሚል ነው:: በዚህ አካሄድ፣ በደል አልባ የሆነውን ሰው መቅጣት፣ ወንጀለኛውን መሸለም፣ ስሕተት ላይሆን ይችላል[20]::

አንጻራዊነት ትክክል ከሆነ፣ ፍትሕ፣ አግባብ ወዘተ የሚል ነገር አይኖርም፤ ምክንያቱም ፍትሕና አግባብ ነባራዊ የሆኑ የእውነት መለኪያዎች ናቸው:: ፍትሕ፣ አግባብ ወዘተ የሚሉት ቃላት ትርጒም ያላቸው ከሆኑ፣ አንጻራዊነት ስሕተት ነው[21]::

## 9. አንጻራዊነት የሰዎችን ግብረገብ ማሻሻል አይችልም

በአንጻራዊነት እሳቦት ግብረገባዊ መሻሻል ወይም ተሐድሶ በፍጹም የሚታሰብ ነገር አይደለም:: አንጻራውያን ምግባራቸውን ሊለውጡ ይችሉ ይሆናል፤ ነገር ግን ሊያሻሽሉ፣ የተሻለም ሰው ሊሆኑ አይችሉም[22]::

"መሻሻል" የሚለው ርእሰ ጉዳይ ትርጒም ሊኖረው የሚችለው ነባራዊ የሆነ መስፈርት ሲኖር ብቻ ነው:: የተሻለ መንገድ ከሌለ፣ መሻሻል የሚባል ነገር ሊኖር አይችልም:: ግብረገብ ይለወጣል እንጂ አይሻሻልም:: ግብረገብ የመሻሻሉ ጉዳይ እውነት ከሆነ፣ አንጻራዊነት ስሕተት ነው[23]::

---

[19] ዝኒ ከማሁ::
[20] ዝኒ ከማሁ፤ 65-66::
[21] ዝኒ ከማሁ፤ 66::
[22] ዝኒ ከማሁ::
[23] ዝኒ ከማሁ::

## 10. ግብረገባዊ አንጻራዊነት ግብረገባዊ ውይይት አያውቅም

ትርጒም ያለው የግብረገብ ውይይት ማካሄድ የሚቻለው፣ ግብረገባዊ መርሖዎች ዓለም ዐቀፋዊነታቸው በግልጽ ሲታይ ብቻ ነው::

ማናቸውም ዐይነት ውይይቶች (ሙግቶች) መሠረት ያደረጉት የትኛው አመለካከት እውነት፣ የትኛው ደግሞ ስሕተት ነው፣ የትኛው ደካማ፣ የትኛው ደግሞ ጠንካራ ነው የሚለውን ፋይዳ ነው:: ግብረገብ አንጻራዊ ከሆነና ሁሉም አመለካከት እኩል ክብደት ካለው፣ አንዱ ከሌላው ይበልጣል (ይሻላል) ማለት አይቻልም[24]::

ምሁራን፣ "ግብረገባዊ ርእሰ ጕዳዮችን አስመልክቶ መወያየት የሚቻለው፣ የተወሰኑ መስፈርቶችን፣ ቅድመ ግንዛቤ ውስጥ ስናስገባ ብቻ ነው" የሚሉትም ለዚሁ ነው[25]::

ሲ. ኤስ. ልዊስ፣ "ክርክር ማለት፣ ተቃራኒው ወገን ያለው አመለካከት ስሕተት መሆኑን ለማሳየት የሚካሄድ ውይይት ነው:: በሁለቱም ወገኖች መኻል እውነትና ስሕተት ምንድን ነው በሚለው ነጥብ ላይ ተመሳሳይ አቋም ከሌለ፣ ውይይት ትርጒም አይኖረውም:: አንድ የእግር ኳስ ተጫዋች ስሕተት ፈጸመ የምንለው፣ እግር ኳስን በተመለከተ አንድ ዐይነት ደንብ ሲኖር ብቻ ነው"[26] ይላሉ::

ሥነ ምግባራዊ ክርክር (ውይይት) ትርጒም ሊኖረው የሚችለው፣ ግብረገብ ፋይዳዎች ፍጹማን ሲሆኑ ብቻ ነው:: ይህ እውነት ከሆነ፣ አንጻራዊነት ውይይትን ይጻረራል[27]::

---

[24] ዝኒ ከማሁ፣ 67::

[25] Francis J. Beckwith and Gregory Koukl, *Relativism* (Grand Rapids: Baker, 1998), 61. ከ A. J. Ayer, "Emotivism," ላይ Louis P. Pojman, ed. *Ethical Theory: Classical and Contemporary Readings* (Belmont, Calif.: Wadsworth, 1995), 416. ጠቅሶ ከጻፈው፣ ጠቅሰው እንደ ጻፉት::

[26] Lewis, *Mere Christianity*, 3,4.

[27] ዝኒ ከማሁ፣ 68.

[26] ዝኒ ከማሁ፣ 3,4.

[27] ዝኒ ከማሁ፣ 68.



## 11. አንጻራዊነት ትዕግሥትን አያውቅም

ትዕግሥት ግብረገባዊ ፋይዳ ከሆነ፣ በአንጻራዊነት ዘንድ ትዕግሥት ሊኖር አይችልም:: አንጻራውያን፣ "መቻቻል" (ግብረገብ ፍጹም ነው በሚል በመርሖች ላይ ግትር አቋም በመያዝ፣ ሰው ሁሉ ግብረገባዊ ፋይዳዎችን እንዲቀበል ከመፈለግ፣ ሰው ሁሉ ያሻውን መንገድ እንዲከተል በማድረግ መቻቻልን ማስፈን አለብን) የሚለው ንግግራቸው ከአቋማቸው ጋር የሚቃረን ነው[28]::

## አንጻራዊነት ከፍጹማዊነት ጋር የሚቃረን ከሆነ፣ ያለመግባባታችን ምክንያት ምንድን ነው?[29]

ከላይ ለማየት እንደ ሞከርነው፣ ፍጹማዊ የሆኑ ግብረገባዊ ፋይዳዎች ካሉ፣ ብዙ ሰዎች ግብረገብ አንጻራዊ ነው ለምን ይላሉ? የችግሩ ዐቢይ ምክንያት፣ ልዩነቱን በውል ያለመረዳት ነው:: ልዩነታቸውን አጥርተን ማየት እንችል ዘንድ፣ አደናጋሪ ናቸው የሚባሉትን ነጥቦች በአጭሩ እንቃኝ:-

### 1. ፍጹማዊ ፋይዳን ከባሕርይ ለውጥ ጋር ማቀላቀል የለብንም

የአንጻራዊነት አራማጆች የጋራ ችግር፣ ባሕርይንና ፋይዳን መቀላቀላቸው ነው:: ባሕርይ ማለት የሆነው ነገር ሲሆን፣ ፋይዳ ደግሞ መሆን ያለበት ነገር ነው:: ልዩነቱ በማኅበረ ሰብ ጥናትና በግብረገብ መካከል ያለ ልዩነት ነው:: ባሕርይ ***ገላጭ*** (descriptive) ሲሆን፣ ፋይዳ ደግሞ ***ተገላጭ*** (prescriptive) ነው::

በሌላ አገላለጽ የአንጻራዊነት ተከታዮች ሁነኛ ችግር፣ የባሕርይ ለውጥን ከማይለወጠው ግብረገባዊ ግብር ጋር ማደባለቃቸው ነው:: ለምሳሌ:- ከጋብቻ በፊት የሚደረግን የግብረ ሥጋ ግንኙነት፣ "ይህ የሠለጠነውና ዘመናዊው ዓለም ስለሆነ ይቻላል» ሲሉ ይደመጣሉ:: የአሁኑ ሁኔታ (ዘመናዊነት) ስሕተትንና ትክክልን የሚወስን ይመስላቸዋል:: የአንጻራዊነትን አስተሳሰብ ኢምክንያታዊ እንደ ሆነ አጥርቶ ለማየት፣ እንደ ግድያ ያሉ እጅግ ጠንካራ ርእሰ ጕዳዮችን ማየት ይበጃል:: የትኛው የአንጻራዊነት ደቀ መዝሙር ነው ግድያን፣ "ይህ የሠለጠነውና ዘመናዊው ዓለም

---

[28] ዝኒ ከማሁ::

[29] Norman L. Geisler and Frank S. Turek III, *Legislating Morality* (Minneapolise: Bethany House, 1998), 51.

ስለሆነ ይቻላል" የሚለው? ለዚህም ነው ሰዎች የሚሠሩአቸው ሥራዎችና መሥራት ያለባቸውን ጉዳዮች ሲቀላቅሉ የሚታዩት።

## 2. ፍጹማዊ ፋይዳን ተለዋዋጭ ከሆነው ከሰዎች ዕውቀት ጋር ማቀላቀል የለብንም

ፍጹማን በሆኑት ግብረገባዊ ፋይዳዎችና ተለዋዋጭ በሆነው በሰዎች ዕውቀት መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። ለምሳሌ:- በአንዳንድ ባህል፣ ከብዙ ዓመታት በፊት ጠንቋዮች እንደ ነፍስ ገዳዮች ይታዩ ነበር፤ አሁን ግን በዚያ መልኩ አይታይም፤ አንጻራዊነትን የተቀበሉ ሰዎች፣ "ጠንቋዮችን ለመግደል ያለመፈለጋችን፣ ግብረገባዊ ፋይዳዎቻችን እየተለወጡ እንዳሉ የሚያመላክት ነው፤ ግብረገብ ከጊዜ ጊዜ፣ ከባህል ባህል የሚለዋወጥ ጉዳይ ነው" ይሉ ይሆናል። ነገር ግን ይህ ትክክል አይደለም። የተለወጠው ግድያ ስሕተት ነው የሚለው ግብረገባዊ መስፈርት ሳይሆን፣ ሰዎች "ጠንቋዮች መግደል ይችላሉ ወይስ አይችሉም" የሚለው እምነታቸው ነው። በሌላ አገላለጽ ግብረገባዊ ሁኔታዎችን መረዳት አንጻራዊ ነው (በርግጥ ጠንቋዮች ሰዎችን በርግማን መግደል ይችላሉ?) ነገር ግን በሁኔታው ለውጥ የተከሠተው ግብረገባዊ ፋይዳ ፍጹማዊ ነው (ግድያ በማናቸውም ጊዜ ስሕተት ነው)።

ብዙ ሰዎች ይህንን ልዩነት መረዳት ያለመቻላቸው፣ የባህል ልዩነቶች መሠረታዊ የሆኑትን የግብረገብ ፋይዳ ልዩነቶች ያመጣሉ ብለው ያምናሉ። ለምሳሌ:- አንዳንዶች፣ የሂንዱ እምነት ተከታዮች ላሞችን ያመልካሉ፣ ኢትዮጵያውያን ደግሞ ላሞችን ዐርደው ይበላሉ፤ ይህ የሚያሳየን በሂንዱ እምነት ተከታዮችና በኢትዮጵያውያን መካከል የግብረገባዊ ፋይዳ ልዩነት መኖሩን ነው ይላሉ። ነገር ግን በሕንድ አገር የሚገኙ የእምነቱ ተከታዮች ላሞችን ቅዱስ ፍጥረቶች ናቸው ብለው ማመናቸው፣ ከግብረገባዊ ፋይዳዎች ጋር የሚቀላቀል ጉዳይ አይደለም፤ ነገር ግን አንድ እንስሳ (ሰውን ጨምሮ) ከሞተ በኋላ ወደ ሌላ ዐይነት ፍጥረት ይለወጣል ብለው የማመናቸው ውጤት ነው። ላሞችን የማይበሉበት ምክንያት፣ ላሞች የሞቱ ሰዎችን ነፍስ ይዘው ሊሆን ይችላል፣ ብለው በማመናቸው ነው። ነገር ግን በኢትዮጵያ የምንገኘው እኛ፣ የሞቱ ዘመዶቻችን፣ ምናልባት በላሞቹ ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ የሚል እምነት ስለሌለን፣ በነጻነት ላሞችን ዐርደን እንበላለን።

በሐመሮች ባህል አንድ ሕፃን እየጠባ ሌላኛው ከተረገዘ፣ የተረገዘው ሕፃን ከሰይጣን እንደ ተረገዘ ስለሚቈጠር ልክ እንደ ተወለደ፣ እናቲቱ ሕፃኑ ላይ ተቀምጣበት እንድትገድለው ይደረጋል። ይህ ሁኔታ የሚያመለክተው፣ በአዲስ አበባ ነዋሪዎችና በሐመሮች መካከል፣ የግብረገባዊ ፋይዳ ልዩነት መኖሩን ሳይሆን፣ ሐመሮች



ይህን የሚያደርጉት ከሰይጣን ተወለደ ያሉት ልጅ፣ ሰው ሳይሆን ሰይጣን ነው ብለው በማመናቸው ነው።

ልዩነቱን የፈጠረው እኛም ሆንን ከዚህ በላይ የጠቀስናቸው ሰዎች የምናምነው ተመሳሳይ አቋም ነው። በሁለቱም (በሐመርም ሆነ ሐመር ባልሆነ) ባህል ውስጥ ባሉ ሰዎች ዘንድ ያለው መሠረታዊ አንድነት፣ የሞቱ ወገኖቻችንን መብላት የለብንም የሚለው ነው። የምንለያየው ደግሞ የሞቱ ወገኖቻችን ነፍስ መኖሪያው የት ነው፣ በሚለው ነጥብ ላይ ነው። ልዩነቱን የፈጠሩት፣ ከግብረገባዊ ፋይዳዎች ጋር ተቈራኝተው በሚገኙት እውነታዎች ላይ ያሉን ልዩነቶች ናቸው።

አንዳንድ ሰዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ባህል ፍጹም ለየቅል ስለሆነ፣ ከዚህም የተነሣ የተለያዩ ግብረገባዊ ፋይዳዎች ስላሉን፣ ተመሳሳይ የሆነ ግብረገባዊ ፋይዳን ማጽደቅ በፍጹም አንችልም ይላሉ። ነገር ግን እስካሁን ያየነው እውነት ይህ ትክክል እንዳልሆነ የሚገልጽ ነው። መሠረታዊ የሆኑት ግብረገባዊ ፋይዳዎች በአንድ ባህል ውስጥ ብቻ የታሰሩ አይደሉም፤ ነገር ግን 2+2=4 እንደሚለው የሒሳብ ስሌት፣ በየትኛውም ባህል ውስጥ ዘልቀው የሚሄዱ ሕግጋት ናቸው። ግብረገባዊ ፋይዳዎችን ሕጋዊ ማድረግ፣ ለአንድ ኅብረተሰብ ሕልውና መሠረታዊ ጉዳይ ነው።

## 3. ፍጹማዊ የሆኑ ፋይዳዎችን፣ አንጻራዊ ከሆኑት ባህላዊ ሥርዐቶች ጋር ማቀላቀል የለብንም

ግብረገባዊ ፋይዳዎች አንጻራዊ ናቸው የሚሉ ሰዎች፣ መገንዘብ ያለባቸው ሌላው እውነት፣ ግብረገባዊ ፋይዳዎች ፍጹማዊ መሆናቸውንና እነዚህ ፋይዳዎች በተለያዩ ባህሎች ውስጥ በተለያየ መልክ መገለጣቸውን ነው። ለምሳሌ:- በተለያዩ ባህሎች ውስጥ ያሉ ሰዎች፣ በተለያዩ መንገዶች ሰላምታ ይለዋወጣሉ። የሰላምታዎቹም መልእክት ፍጹም ለየቅል ነው (በተለያዩ ባህሎች ሰዎች ሰላምታ የሚለዋወጡት በመሳሳም፣ በመተቃቀፍ፣ በመጨባበጥ፣ እጅ በመንሣት ነው)። የጋራ ባሕርያቶቻቸው ምንድን ነው የሚለውንና እንዴትስ ይለያያሉ የሚሉትን ነጥቦች መገንዘብ ያስፈልጋል። አንዳንድ ሰዎች ይህንን ባለመገንዘባቸው፣ በተለያየ ባህል ውስጥ የተለያየ ሥርዐት መኖሩ፣ ሰዎች የተለያዩ ፋይዳዎች ስላሉአቸው ነው ብለው ያስባሉ። ነገር ግን ይህ ስሕተት ነው። ግብረገባዊ ፋይዳዎች ፍጹማዊ ናቸው፤ ነገር ግን የሚገለጡት አንጻራዊ በሆነ (በተለያየ) መንገድ ነው።

## 4. የአቋም ልዩነቶችን ፍጹማዊ ከሆኑት ፋይዳዎች ጋር ማቀላቀል የለብንም

ሰዎች በአመለካከት ይለያያሉ ማለት፣ ግብረገባዊ ፋይዳዎች አንጻራዊ ናቸው ማለት አይደለም:: አንጻራውያን የተለያየ ዐይነት ግብረገባዊ ፋይዳዎች እንዳሉ ለማሳየት፣ የውርጃን ጉዳይ በአብነት ያቀርባሉ:: አንዳንዶች ውርጃን ሲቀበሉ ሌሎች ደግሞ፣ ውርጃን እንደ ግድያ ይመለከቱታል:: ነገር ግን ይህ ጉዳይ ከላይ ስለሂንዱ ላሞችና ስለ ሐመር ሕፃናት ከተወያየንባቸው ናሙናዎች ጋር ተቀራራቢ ነው:: ልዩነቱን የሚፈጥረው እውነትን የአቀባበል መንገዳችን እንጂ፣ ግብረገባዊ ፋይዳዎች አንጻራዊ ስለሆኑ አይደለም::

ከአንጻራዊነት አመለካከት ጋር በተቃረነ መልኩ፣ ውርጃን የሚደግፉ አብዛኞቹ ሰዎች፣ በደል አልባ የሆኑ ሰዎች ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል፣ የሚለውን ፍጹማዊ የሆነውን ግብረገባዊ ፋይዳ ይቀበላሉ:: ነገር ግን የሙግታቸው ጭብጥ የሚሽከረከረው፣ ያልተወለደው ሕፃን ሰው አይደለም በሚለው ርእስ ዙሪያ ነው:: የውርጃ ደጋፊዎች የውርጃን ርእስ ጉዳይ ልዩ በሆነ (ለየት ባለ) ግብረገባዊ ሕግ ማየት አለብን ባዮች ናቸው፤ ይኸውም እናቲቱ አካሏን የመቈጣጠር ግላዊ መብት አላት::

በመሠረቱ ግብረገባዊ ፋይዳዎች አንጻራዊ ቢሆኑ ኖሮ፣ በውርጃ ደጋፊዎችና በውርጃ ተቃዋሚዎች መካከል ውይይት መካሄድ ባላስፈለገው ነበር፤ ምክንያቱም በመካከላቸው የጋራ ነጥብ የለም (በደል አልባ ሰዎች ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል፣ የሚለው የጋራ ነጥባቸው ነው):: ስለዚህ ክርክሩ የሚያጠነጥነው፣ ሽሉ ሰው ነው ወይስ አይደለም በሚለው አልያም የሰው ሕይወት (የሽሉ ሕይወት) ይበልጣል ወይስ የናቲቱ ምርጫ በሚለው ነጥብ ዙርያ ነው::

## 5. ፍጹማዊ ፋይዳዎችን ወደ ፋይዳዎቹ ከሚወስዱ አቅጣጫዎች ጋር ማቀላቀል የለብንም

አብዛኛውን ጊዜ ግብረገባዊ አንጻራውያን፣ ውጤቱን ወደ ውጤቱ ከሚደረስበት መንገድ ጋር ያቀላቅሉታል:: ብዙ የፖለቲካ ክርክሮች ይህን ዐይነት መልክ አላቸው:: በብዙ ርእስ ጉዳዮች ዙሪያ ውጤትን በተመለከተ አንጻራውያንም ሆኑ ፍጹማውያን ተመሳሳይ አቋም አላቸው:: ነገር ግን ወደዚያ ያደርሳል የሚሉት መንገድ ግን ለየቅል ነው::

ሁሉም የፖለቲካ ሰዎች (ቢያንስ አብዛኞዎቹ) ፍትሕ መስፈን አለበት የሚል አቋም አላቸው:: ነገር ግን የማን መንገድ ነው ወደዚያ የሚያደርሰን በሚለው ፅንሰ



ሐሳብ ላይ አይግባቡም:: ለምሳሌ የጦር ኀይልን ቅነሳ የሚያምኑና የጦር ኀይልን ማጐልበት የሚያምኑ ሰዎች የሚፈልጉት የጋራ ውጤት ሰላም ሲሆን፣ ወደዚያ በሚደረስበት መንገድ ግን ይለያያሉ (የጦር ኀይልን መቀነስ—የጦር ኀይልን ማጐልበት):: ፍጹማዊ በሆነው ውጤት ሁለቱም ወገኖች ቢስማሙም፣ አንጻራዊ በሆነው አካሄድ ላይ ግን አይግባቡም::

## ማጠቃለያ

ግብረገባዊ አንጻራዊነትን የማንቀበለው፣ ቅንጣት ታህል እውነት ስለሌለበት ነው:: መሠረታዊ የሆኑት ግብረገባዊ ፋይዳዎች ፍጹማዊና ከባህል የዘለሉ ናቸው:: እንዲያውም የሚቃወሙት እንኳ የሚጠቀሙበት፣ ፍጹም ልንሸሸው የማንችለው ጉዳይ ነው:: ሰዎች ግብረገባዊ ፍጹማዊነትን የሚቃወሙበት ምክንያት፣ ስለግብረገባዊ ፍጹምነት የተሳሳተ ግንዛቤና የተሳሳተ አጠቃቀም ስላላቸው እንጂ፣ እውናዊ ምክንያት ኖሮአቸው አይደለም:: አንጻራዊነት እውንት ከሆነ፣ ሊኖረን የሚችለው ዓለም ምን ይመስል ይሆን? እንዳችም ስሕተት፣ ትክክል፣ ውዳሴ፣ ኩነኔ፣ መቻቻል ወዘተ የሌለበት ዓለም ይፈጠራል:: ፍትሕ ትርጕም የለሽ ቃል ይሆናል:: ኀላፊነት፣ የግብረገብ መሻሻል እንዲሁም ግብረገባዊ ውይይት የሚባል ነገር አይኖርም::

ስለግብረገባዊ ፍጹምነት ያለን መረዳት ፍጹም (ሙሉዕ) ባይሆንም፣ ግብረገባዊ ፋይዳዎች ግን ፍጹማን ናቸው::

# 5

## ግብረገባዊ የወል ስሜት[1]

አንጻራዊነት ኪሳራ የሞላበት ግብረገባዊ አቋም ነው:: ("ግብረገባዊ አንጻራዊነትን የማንቀበለው ለምንድን ነው?" የሚለውን ክፍል ይመለከቷል)::

ነፍሰ ገዳዮች ለፍርድ ይቅረቡ፣ አስገድዶ መድፈር ወንጀል ነው...የምንለው፣ ፖለቲከኞቻችን የሰብአውያንን መብት በተመለከተ በየስብሰባው ቦታ የሚከራከሩት (የሚወያዩት) ወዘተ በምንኖርባት ዓለም እነዚህ ነገሮች እውነት ስለመሆናቸው ተመሳሳይ አቋም ስላለ ነው:: እውነት መሆናቸውን ጤነኛ የሆነ ሰው ሁሉ ሊክዳቸው ስለማይችል ነው:: ይህ እውነት ከሆነ፣ ግላዊ ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት *(ሥነ ምግባራዊ ጎሊናዊነት)* ስሕተት ነው::

ግብረገባዊ ውይይት ሊካሄድ የሚችለው፣ እኵይ ምግባርን መኰነን፣ ሠናይ ምግባርን ማወደስ፣ ወንጀለኞችን መቅጣት፣ መልካሞችን መሸለም፣ የሰዎችን ግብረገብ ማሻሻል ወዘተ የምንሞክረው፣ ነባራዊ የሆነ የሥነ ምግባር መስፈርት ሲኖረን ብቻ ነው:: አንጻራዊነት ይህ ዐይነቱ መስፈርት የለም የሚል ግብረገባዊ ዕይታ ነው::

## እውነትን ከስሕተት መለየት እንዴት እንችላለን?

እውነትን ከስሕተት የምንለይባቸው ሦስት መንገዶች፣ የሚከተሉት ናቸው::

### 1. ተሞክሮአዊ ዕውቀት

በቁሳዊው ዓለም የአንዳንድ ነገሮችን ማንነት (እውነትነትና ሐሰትነት) ማወቅ የምንችለው፣ በስሜት ሕዋሳቶቻችን ረዳትነት ***በተሞክሮ*** *(empiricaly)* ነው:: መረጃዎችን ከሰበሰብን በኋላ ድምዳሜ ላይ እንደርሳለን፤ የምናምነውም ነገር በማስረጃ የተደገፈ ይሆናል:: ፈላስፎች ይህ ዐይነቱን ዕውቀት ***ተሞክሮአዊ ዕውቀት***

[1] Francis J. Beckwith and Gregory Koukl, *Relativism* (Grand Rapids: Baker, 1998), 54.



*(a posteriori knowledge)* ይሉታል:: ሳይንስ መሠረት ያደረገው ይህ ዐይነቱን ተሞክሮአዊ ዕውቀት ነው[2]::

### 2. ምክኑያዊ ዕውቀት

የአንዳንድ ነገሮችን እውነትነት የምናውቀው፣ ***ምክንዩን*** (reason) በመጠቀም ነው:: ***ከመንሥኤና*** (cause) ***ከተገብሮት*** (effect) በመነሣት ወይም ***የሥነ አመክንዩን*** (Logic) ሕግጋት በመጠቀም፣ ድምዳሜ ላይ እንደርሳለን:: ለምሳሌ አንድ ሰው አራት ማዕዘን-ክብ ሣጥን ሠራሁ ቢል፣ የገለሰቡ ንግግር ስሕተት ነው፤ ምክንያቱም የግለሰቡ ንግግር እርስ በርሱ ይቃረናል (አራት ማዕዘን-ክብ የሚባል ነገር የለም):: አራት ማዕዘን ሣጥን አለ፤ ክብ ሣጥንም አለ፤ ነገር ግን በአንድ ጊዜ አራት ማዕዘን-ክብ ሣጥን ሊኖር አይችልም:: ዐረፍተ ነገሩ እርስ በርሱ ይቃረናል::

አራት ማዕዘን-ክብ የሚባል ነገር ላለመኖሩ መስረጃ አድርገን የምናቀርበው፣ ***ቅራኔ አልባ*** (Law of noncontradiction) የሚባለውን የሥነ አመክንዩ ሕግ ነው:: የአንድን ሙግት እውነትነት የምንመረምረው፣ ወደ ድምዳሜ የደረስንበትን የሥነ አመክንዩ አካሄዶቹን በመመርመር ነው፤ ይኸውም ሙግቶቹ ለይ ***ተፋልሶ*** (fallacy) ያለመኖሩንና ሙግቶቹ እውነትን መሠረት ያደረጉ ከሆነ (valid)፣ ድምዳሜያችን ***ርቱዕ*** (sound) ውጤታችንም ትክክለኛ ይሆናል::

### 3. ጭልታዊ ዕውቀት

የነገሮችን እውነታነት የምናውቅበት ሦስተኛ መንገድ ***ጭልታዊ ዕውቀት*** *(Intuition)* ይባላል:: ጭልታዊ ዕውቀት መረጃ የሚፈልግ አይደለም:: የጭልታ ዕውቀት በመረጃዎች ላይ ያልተደገፈ፣ የሥነ አመክንዩን ሕግጋት በእማኝነት የማይፈልግ፣ ደመ ነፍሳዊ የሆነ የሰው ልጆች ዕውቀት ነው:: የጭልታ ዕውቀት ሰዎች በተፈጥሮ ያላቸው ዕውቀት ነው::

የጭልታ ዕውቀት አለን ስንል፣ እንደ ፓሊስ ውሻ ነገሮችን አነፍንፈን እናውቃለን ማለት አይደለም:: እንዲህ ዐይነቱን ዕውቀት፣ የምናገኘው ተሞክሮአዊና ምክኑያዊ ከሆነ ማስረጃ ነው:: ነገር ግን የተፈጥሮ ዕውቀት፣ «የአንድን ነገር እውነታነት፣ ያለአንዳች ማስረጃ እንዲያው ማወቅ» ማለት ነው:: ፈላስፎች ይህ ዐይነቱን ዕውቀት ***ተሞክሮአዊ ያልሆነ ዕውቀት*** *(a priori knowledge)* ይሉታል::

[2] ዝኒ ከማሁ፤ 56:: ከ Paul Edwards, ed., *The Encyclopedia of Philosophy*, vol. 4 (New York: Macmillan, 1967), 204. ላይ ጠቅሰው እንደ ጻፉት::

የሥነ ምግባር መሁሩ ሊዊስ ፓጃማን፣ ስለ ተፈጥሮ ዕውቀት ሲያስረዳ፣ "ዮሐንስ ከማርታ ይልቅ ረዥም ነው፤ ቶማስ ደግሞ ከዮሐንስ ይበልጣል፤ ስለዚህ ቶማስ ከማርታ ይበልጣል"። ይህ ትክክለኛ ዐረፍተ ነገር ነው። "ዮሐንስ፣ ቶማስ፣ ማርታ እነማን ናቸው? በሕይወት አሉ ወይስ ሞተዋል? አንዱ ከሌላው የሚበልጠው ምን ያህል ነው? ወዘተርፈ የሚሉ ጥያቄዎች፣ የድምዳሜውን እውነት ለመመርመር አስፈላጊዎች አይደሉም። መነሻችን፣ "ማን ከማን ይበልጣል?" የሚለውን ጥያቄ መመለስ ስለሆነ። ስለዚህ የድምዳሜውን ዐረፍተ ነገር ትክክል ነው ብለን የምንቀበለው፣ በስሜት ሕዋሳቶቻችን ላይ መሠረት አድርገን አይደለም[5]።

ጭልታዊ ዕውቀት ማስረጃ አይፈልግም። ለማንኛውም ጤነኛ ሰው በግልጥ የሚታየው ዕውነት ነውና። እንዲያውም ሰዎች ዕውቀት እንዲገበዩ ምክንያት የሚሆናቸው፣ ጭልታዊ ዕውቀት ነው። ሲ. ኤስ. ሊዊስ፣ "አንዳንድ ነገሮች እውነትነታቸው ግልጥ ሆኖ የማይታይ ከሆነ፣ የማንኛውንም ነገር እውነትነት ማረጋገጥ አይቻልም" ይላል። አንዳንድ ነገሮችን ያለአንዳች ዕገዛ በቀጥታ እንረዳቸዋለን (እናውቃቸዋለን)፤ እነዚህም ዕውቀቶች (እውነታዎች) ሌላውን ነገር ለማወቅ መሣሪያ ይሆኑናል[6]።

ታላቁ ፈላስፋ አርስጣጣሊስ፣ "በርግጥ የአንዳንድ ነገሮችን እውነትነት እናረጋግጣለን...ነገር ግን፣ ለሁሉ ነገር ማረጋገጫ ማቅረብ መፍጹም እንችልም። ማረጋገጫ እናቅርብ ካልን መቋጫ ወደሌለው *(ሕልቆቢስ [infinty])* ትብታብ ውስጥ እንገባለን፤ ስለዚህም ማስረጃ ሊኖረን አይችልም"[7]።

እንደ አርስጣጣሊስ ትምህርት፣ የጭልታ ዕውቀቶች፣ ለሌሎች ዕውቀቶች ሁሉ መልሕቅ (መሠረት) ናቸው። ለምሳሌ፣ "ይህን እውነት እንዴት ዐወቅኸው" ብዬ ብጠይቅዎ፣ ለጥያቄዬ መልስ ቢሰጡኝ፣ በመቀጠልም፣ "የሰጠኸኝ ማስረጃ እውነት መሆኑን በምን ታውቃለህ?" ብዬ ብጠይቅዎ፣ ተጨማሪ መልስ እንደሚሰጡኝ እሙን ነው፤ ነገር ግን የሰጡኝን በልሶች ሁሉ፣ "ይህን እንዴት ልታውቀው ቻልህ?" እያልሁ ብጠይቅዎ፣ መልስ ወደማይገኝለት ሕለቆቢስ ውይይት መሄዳችን አይቀሬ ነው።

ለምናውቃቸው ነገሮች ሁሉ ማስረጃ እናቅርብ ካልን፣ ዕውቀትን መገብየት አንችልም፤ ምክንያቱም ጥያቄውን ተከትለው ለሚመጡት መቋጫ አልባ

[5] Pojman, *What Can We Knwo?* 196.
[6] C. S. Lewis, The Abolition of Man (New York: Macmillan, 1955), 53.
[7] Francis J. Beckwith and Gregory Koukl, *Relativism* (Grand Rapids: Baker, 1998), 56. ከ Aristotle, *Metaphysics,* 1006a. ላይ ጠቅሰው እንደ ጻፉት።



ጥያቄዎች ሁሉ፣ መልስ መስጠት አንችልም። ስለዚህ ለጭልታዊ እውቀቶች ሁሉ ማስረጃ መፈለግ አይኖርብንም፤ ለጥያቄዎችም ሁሉ መልስ ልናገኝ አንችልም።

የሚከተለውን ቃለ ምልልስ (ተዋስኦ) ይመለከቷል፤

- ማሜ፡- እጄን አሞኛል
- ፋሲል፡- እጅሽን እንዳመመሽ እንዴት ልታውቂ ቻልሽ?
- እንዴ! የሕመም ስሜት እየተሰማኝ ነዋ!
- የሕመም ስሜት እንደ ተሰማሽ እንዴት ዐወቅሽ?
- አመመኝ እኮ ነው የምልህ!
- እያልኩሽ ያለሁት፣ የሕመም ስሜት እንደ ተሰማሽ እንዴት ልታውቂ ቻልሽ?

ማሜ ከዚህ በላይ መሄድ አትችልም። ማሜ ሕመም እንደ ተሰማት ማስረጃ መቅረብ አትችልም። ስለሕመሟ ያላት ዕውቀት የተመሠረተው፣ በቀጥታ በውስጣዊ ስሜቷ ላይ ነውና። እንዲህ ዐይነት ዕውቀቶች ግላዊና ማስረጃ የማይሹ ናቸው። ልንሳሳትባቸውም አንችልም። እንዳመመኝ ማወቅ እችላለሁ፤ ሕመሜን ግን ማስረዳት አልችልም።

ብዙ ነገሮችን የምናውቀው በጭልታ ዕውቀት ነው። የጭልታ ዕውቀት፣ ወዲያውኑ ያለአንዳች ማስረጃ የሚታወቅ፣ በራሱ ብቁና እውነት የሆነ ዕውቀት ነው። የሥነ ምግባር ሊቃውንት፣ "ግልጥ ግብረገባዊ እውነታዎች" እንዲሁም፣ *"ግብረገባዊ የወል ስሜት (moral common sens)"* የሚሉት ለዚሁ ነው።

# 6

## ግብረገብ ከየት መጣ?[1]

ግብረገብ የመጣው ከየት ነው? ግብረገብ ሰዎችን ብቻ የሚመለከተው ለምንድን ነው? ግብረገብ የአጋጣሚ ክሥተት ነውን? ግብረገብ ትርጒም የሚገኝበት ***ንጽሮተ ዓለም*** የትኛው ነው?

የግብረገብን ተፈጥሮአዊ አካሄድ በመመርመር፣ እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ እንሞክራለን:: የግብረገብን ***ተገብሮ*** *(effect)* በመመልከት ***መንሥኤውና*** *(cause)* ጠባዩ ምንድን ነው ለሚለው ጥያቄ መልስ ማፈላለግ ይቻላል::

## አራት ዕይታዎች

ከግብረገብ ሕግጋት የምንማረው መሠረታዊ እውነታ፣ ግብረገብ ቁሳዊ ነገር እንዳልሆነ ነው፤ ምክንያቱም ቁሳዊ አካል፣ ክብደት፣ ኬሚካላዊ ውኅደት ወዘተ የለውም:: በአጠቃላይ ግብረገብ ቁሳዊ ነገር ስላልሆነ በአምስቱ የስሜት ሕዋሳቶቻችን ልንረዳው አንችልም፤ በትክክለኛው ***እሳቦታዊ ሂደት*** እንጂ:: ይህ እሳቦታዊ ሂደት ደግሞ ተአማኒነት ያለው ጒዳይ ነው:: ነገር ግን ይህን እውነት በሳይንሳዊ ሕግጋት ወይም በዕለት ተዕለት ተሞክሮ ልንገነዘበው አንችልም:: ከዚህ የምንማረው፣ ግብረገብ ቁሳዊ ያልሆነ፣ ነገር ግን በቁሳዊው ዓለም ውስጥ ታላቅ ሚና የሚጫወት ዐቢይ ጒዳይ መሆኑን ነው:: በምንኖርበት ዓለም እንደ ግብረገባዊ ሕግጋት ያሉ፣ ቁሳዊ ያልሆኑ ነገሮች እውን ከሆኑ፣ ***የቁስ አካልነት ንጽሮተ ዓለም*** ስሕተት ነው ማለት ነው::

በቁሳዊው ዓለም የሚኖሩ ቁሳዊ ያልሆኑ በርካታ እውነታዎች (ነገሮች) አሉ፤ ለምሳሌ:- ቊጥሮች፣ የሥነ አመክንዮ ሕግጋቶች፣ ደስታ፣ ባልንጀርነትና ታማኝነት ስምና ትርጒም ተሰጥቶአቸው በምንኖርባት ዓለም ውስጥ አብረውን ይኖራሉ:: ከዚህ የምንማረው እውነት፣ ሳይንስ የማይደርስባቸውና በቀመሩ ውስጥ የሌሉ ነገሮች መኖራቸውን ነው:: አንዳንድ ነገሮች ለሳይንሳዊ ሕግጋት አይገዙም፤ ይህ ደግሞ ስለምንኖርባት ዓለም ትክክለኛ መረጃ የሚሰጠን ሳይንስ ብቻ እንዳልሆነ የሚያስረዳ ነው:: ይህ እውነት ከሆነ ***የተፈጥሮአዊነት ንጽሮተ ዓለም*** ስሕተት ነው::

[1] Francis J. Beckwith and Gregory Koukl, *Relativism* (Grand Rapids: Baker, 1998), 165-170.



ቁስ አካላዊነትም ሆነ ተፈጥሮአዊነት ስሕተት አይደለም የሚል ሰው፣ ቢያንስ ነባራዊ የሆኑ ግብረገባዊ ፋይዳዎች መኖራቸውን እንዲሁም እስካሁን ለተነጋገርንባቸው የአንጻራዊነት ችግሮች መልስ መስጠት ይኖርበታል::

ግብረገባዊ ፋይዳዎች የመኖራቸው እውነታ፣ ከቁሳዊ ነገሮች ውጪ እውነትም እንዳለ የሚያመለክት፣ ልባችንንም እንድናሰፋ የሚያደርገን ነው:: ከዚህ የምንማረው ሌላው ቁም ነገር፣ ግብረገባዊ ሕግጋት ***ተግባቦትን*** ማዕከል ያደረጉ መሆናቸውን ነው:: ይህ ማለት ከአንድ አእምሮ ወደ ሌላው አእምሮ የሚሸጋገሩና የአእምሮ ውጤት የሆኑ ዐረፍተ ነገሮች ናቸው:: እነዚህ ትእዛዛዊ አንቀጾች የሚተላለፉት በትእዛዝ ነው:: ትእዛዝ ትርጒም ሊኖረው የሚችለው በሁለት አእምሮዎች መካከል ብቻ ነው፤ አንዱ ያዛል፤ ሌላው ትእዛዝ ይቀበላል::

ግብረገብን በተመለከተ የሚነሣው ሦስተኛው ነጥብ፣ ግብረገብ የባሕርይ ለውጥ ከማስከተሉ በፊት የሚሰማን ኀይል መኖሩ ነው:: ፈቃዳችንንም በመቈጣጠር የተወሰኑ ባሕርያት እንዲኖሩን ያደርጋል:: ለኀይሉ ታዛዦች ባለመሆን፣ ሕግጋቱን ብንተላለፍ፡ እንኳ ማለት ነው::

አራተኛውና የመጨረሻው ነጥብ ግልጽና ከባድ የሚባሉትን ግብረገባዊ ሕግጋት ስንተላለፍ ከፍተኛ የሆነ የበደለኝነት ስሜት ይሰማናል:: ይህ የበደለኝነት ስሜት ስሕተት መፈጸማችንና ቅጣት የሚገባን ሰዎች መሆናችንን የሚያስረዳ ነው:: የበደለኝነት ስሜት ምቾት እንዳይሰማን የሚያደርግ ብቻ ሳይሆን፣ ፍርሓት በማሳደር ጥፋታችንን እንድንናዘዝ የሚያደርገን ነው:: ክሕደት ለችግሩ ጊዜያዊ መፍትሔ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ችግሩን ሙሉ ለሙሉ የሚያስወግድ አይደለም::

## መሠረታዊ ጥያቄዎች

ግብረገብ እውን ያልሆነ ነገር ግን እውን የሚመስል ምትሐት ነውን? ግብረገባዊ ሕግጋት እውን የሚሆኑት በአጋጣሚ ነውን? ወይስ የአጋጣሚ ውጤቶች ናቸውን? ስለ ግብረገብ ትርጒም የሚሰጠው አመለካከት የቱ ነው?

አንዳንዶች ነባራዊ የሆኑ ግብረገባዊ ሕግጋት እንዳሉ ቢያምኑም፣ እነዚህ ግብረገባዊ ሕግጋት በአጋጣሚ እንደ ተከሠቱ ይገልጻሉ:: የጽንፈ ዓለም አንድ እውነታ ሆነው ድንገት እንደ ተከሠቱ እንጂ፣ ከየት እንደ መጡ ማብራሪያ መስጠት አይቻልም ባዮች ናቸው::

ነገር ግን "አይቻልም" የሚለው ጥሩ ምክንያት አይደለም:: ግብረገባዊ ሕግጋት መሠረት አልባ ከሆኑ ወይም ትክክለኛነታቸው ካልተረጋገጠ ልንታዘዛቸው አንችልም:: ትእዛዝ አእምሮ ባላቸው ሁለት አካላት መካከል የሚካሄድ ተግባቦት ነው:: የሚያዝ ከሌለ ትእዛዝ የለም::

መንታ መንገድ ላይ ቆሜ ግራና ቀኝ የሚሄዱትን መኪኖች እንዲቆሙ ባዝ፣ ሰሚ ላጣ እችላለሁ፤ ምክንያቱም ትራፊክ ስላልሆንሁ፤ የትራፊክንም ልብስ ስላልለበስሁ:: እንግዲያው በትራፊክና በእኔ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? መልሱ እኔ ተቀባይነት ያለው ሥልጣን ስለሌለኝ ነው:: ነገር ግን ፖሊስ መንግሥትን ይወክላል፤ ስለዚህም ሥልጣኑ የተረጋገጠ ሥልጣን ነው:: የመንግሥትን ፈቃድ እንዲፈጽም የተሾመ ሕጋዊ ባለሥልጣን ነውና::

ሕግ ግብረገባዊ ኀይል የሚኖረው፣ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሕጋዊ በሆነ መልኩ ሲተገብረው ብቻ ነው:: ሰዎች ይህን ሕግ የሚጣረሱ (የሚቃረኑ) ከሆነ ይቀጣሉ:: ይህ ለግብረገባዊ ሕግጋትም እውነት ነው:: ግብረገባዊ ሕግጋት ኀይል የሚኖራቸው፣ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ከጐናቸው ሲቆም ብቻ ነው:: ግብረገባዊ ሕግጋት በአጋጣሚ የተከሠቱ ከሆነ፣ ይህ ዐይነቱ እውነታ መሠረት ሊኖረው አይችልም ነበር::

ግብረገብ የአጋጣሚ ክሥተት ከሆነ፣ ግብረገብ በሁለት አእምሮዎች መካከል የሚደረግ ተግባቦት መሆኑ እንዲሁም ግብረገብ የትእዛዝ አንቀጽ መሆኑ ይቀራል:: እንዲሁም በግብረገባዊ ሕግጋት የሰብአውያን መስፈርት ባልሆነ፣ ስሕተት ሲሠራ የበደለኝነት መንፈስ፣ እንዲሁም ቅጣትን የመጠበቅ ስሜት በሰዎች ውስጥ ባልተፈጠረ ነበር::

የግብረገብ ጠንሳሽ ማነው ለሚለው ጥያቄ አማራጭ መልስ ሊሆን የሚችለው አንድ ብቻ ነው:: ግብረገብ ምትሐት ወይም የአጋጣሚ ክሥተት ካልሆነ፣ ግብረገብ አእምሮ ያለው አካል የቀረጸው የአእምሮ ውጤት ነው ማለት ነው፤ ምክንያቱም አትግደል፣ አታመንዝር፣ አትስረቅ፣ በሐሰት አትመስክር ወዘተ የሚሉት ግብረገባዊ ሕግጋት በዘፈቀደ የተደረደሩ ትርጒም የለሽ ሆሀያት አይደሉምና:: ጽንፈ ዓለማዊ የሆኑት ግብረገባዊ ሕግጋት እውነተኛ ሊሆኑ ያቻሉት ፈጣሪ ስላላቸው፣ እርሱም ጽንፈ ዓለምን የመቈጣጠር ሥልጣን እንዳለው፣ በመጨረሻም ፍጹም ፍትሕ ማስፈን እንደሚችል አመላካች ነው::

ግብረገባዊ ሕግጋት እውን መሆናቸውን በተመለከተ ያለው ብቸኛ ትንተና፣ ፍጹም የሆነ ግብረገባዊ መስፈርት ባለቤት የሆነ አምላክ እንዳለ የሚገልጽ ነው:: የሥነ



ምግባር ጠንሳሽ ግዑዝ የሆነ ኀይል ቢሆን ኖሮ፣ ትርጒም ያለውና ፍጹም አእምሮአዊ የሆነ ትእዛዝ ማስተላለፍ ባልቻለ ነበር::

ይህ ቊሳዊውንም ሆነ መንፈሳዊውን ዓለም የፈጠረ አምላክ እንዳለ በግልጽ የሚያሳይ ነው:: ግብረገባዊ ሕግጋት፣ *የግብረገብ ሕግጋት ሰጪ* (Moral law giver) እንዳለ የሚያስተምሩ ናቸው:: ይኸውም ፈቃዱን በሕግጋቱ አማካይነት የሚገልጽ፣ ሰብአውያን ትእዛዙን እንዲታዘዙት የሚፈልግ::

አንዳንድ ሰዎች ግብረገብ እውን መሆኑን ብቀበልም እንኳ፣ መንሥኤውን ማወቅ አይጠበቅብኝም ይላሉ:: እንደዚህ ዐይነቶቹ ሰዎች ራት ለመብላት በማዕድ ዙሪያ ቊጭ ብለው ገበሬው፣ ዓሣ አጥማጁ፣ አብሳይዋ፣ ምግብ አቅራቢዋ ወዘተ መኖራቸውን ማወቅ አያስፈልገኝም እንደ ማለት ነው፤ ይኸውም ምግቡ ምትሐታዊ በሆነ መንገድ የምግብ ጠረጴዛው ላይ የተከሠተ፣ ምንም ዐይነት የትመጣህ ትንታኔና መንሥኤ እንደማያስፈልገው የሚያምን፤ ይህ ሞኝነት ነው[2]::

እስካሁን ለማየት የሞከርነው እውነታነት ያለው ነገር ከሆነ፣ የግብረገብ አመንጪ ማን እንደ ሆነ መነጋገር አግባብነት ይኖረዋል:: ለዚህም የእግዚአብሔር *አልሆት* (መኖር) ትክክለኛ መፍትሔ ነው::

ግብረገባዊ አንጻራዊነት ስሕተት ከሆነ፣ ግብረገባዊ ፍጹማዊነት ትክክል ነው:: ፍጹማዊ የሆነ ግብረገብ ካለ ይህን ግብረገባዊ መርሖ የሚተነትነው ንጽሮተ ዓለም የትኛው ነው፣ የሚለው ጥያቄ ይነሣ ዘንድ የግድ ነው::

የኢአማኒነት ንጽሮተ ዓለም ይህን የሚያሟላ አይደለም:: የምሥራቃውያንም ሃይማኖት ለዚህ ብቁ አይደለም:: የምሥራቃውያን ሃይማኖት እንደሚያስረዳው እውነት *ምታሕት (illusion)*ከሆነ፣ እኩይና ሠናይ ትርጒም ሊኖረው አይችልም::

በእግዚአብሔር ላይ መሠረት ያደረገው ግብረገብ፣ የሰው ልጆች ለፍትሕ ያላቸውን ረሓብ የሚያጠግብ ነው:: ይኸውም የሰው ልጆች በመጻኢው ዘመን የሚጠብቁት፣ ክፉዎች የሚቀጡበትና ንጹሓን የሚሸለሙበት ዘመን::

ይህ ትንተና ለሰብአውያን ፍርሓት መልስ የሚሰጥ ነው:: የበደለኝነት ስሜት የሚሰማን በደለኞች ስለሆንን ነው:: ይህ የሆነው ፍጹም የሆነና ለመቅጣት ሕጋዊ

---

[2] ዝኒ ከማሁ፣ 169:: ከ Philip Yancey, "the Other Great Commission" *Christianity Today*, 7 October 1996, 136. ጠቅሰው እንደ ጻፉት::

ሥልጣን ያለው አካል ይቀጣናል በሚል እሳቦት ነው:: ላደረግነውም ወንጀል ሁሉ በእግዚአብሔር መጠየቃችን አይቀሬ ነው::

ግብረገባዊ አንጻራዊነት ብዙዎችን መሳብ የቻለበትን ምክንያት ያውቃሉ? ሰዎች ግብረገብንና እግዚአብሔርን እንዳያስቡ ከተደረገ፣ የበደለኝነት መንፈስና ፍርድ አብረው ይጠፋሉ በሚል ነው:: ይህ አባባል ዶክተሮችና ሆስፒታሎች ቢጠፉ፣ በሽታና ሥቃይ አብሮአቸው ይጠፋል እንደ ማለት ነው፤ ይህ ተላላነት ነው::

ያም ሆነ ይህ ከሁለቱ አማራጮች መኻል አንዱን መምረጣችን የግድ ይላል:: ግብረገባዊ አንጻራዊነትን፣ አልያም ግብረገባዊ ፍጹማዊነትን:: ሌላ አማራጭ መንገድ (ሊሆን ይችላል ላይሆንም ይችላል) የሚባል አማራጭ የለም:: አንዱ ስሕተት ከሆነ ሌላው ደግሞ በርግጠኝነት ትክክል ነው[3]::

[3] ዝኒ ከማሁ፣ 170:: ከ Francis Schaeffer, *He Is There and He Is Not Silent*, vol. 1 of *The Complete Works of Francis Schaeffer* (Wheaton, Ill.: Crossway, 1982), 303. ጠቅሰው እንደ ጻፉት::

# 7

# ግብረገባዊ ፍጹማዊነት

## ግብረገባዊ ግጭቶች[1]

ኮሪ ቴን ቡም ***ግብረገባዊ ግጭቶች*** ውስጥ የገቡ ሰው ናቸው:: እኚህ ሴት፣ በናዚ ዘመነ መንግሥት እስራኤላውያንን እቤታቸው በመሸሸግ፣ ብዙዎችን ከናዚዎች የግፍ ግድያ ታድገዋል:: "ክርስቲያኖች በደል አልባ የሆኑትን እስራኤላውያን ሕይወት ለመታደግ፣ የናዚን ወታደሮች መዋሸት ነበረባቸው ወይስ አልነበረባቸውም?"፤ ይህ ሁኔታ በኀጢአት በተበላሸው በዚህ ዓለም ስንኖር፣ ሊገጥሙን የሚችሉትን ግብረገባዊ ግጭቶች ለማመልከት፣ በናሙናነት ልንወስደው የምንችለው ጉዳይ ነው:: ክፍት የሥራ ቦታ ለመወዳደር የማመልከቻ ደብዳቤዬን በምጽፍበት ጊዜ፣ ቀድሞ አደገኛ ሌባ የነበሩ ሰዎች የሥራውን ዕድል እንደማያገኙ በግልጽ እያወቅሁ፣ ቀድሞ አደገኛ ሌባ እንደ ነበርሁ በማመልከቻዬ ላይ መግለጽ አለብኝ? እንዲያ በማድረጌ ጥሩ ክፍያ ያለውን ይህን የሥራ ዕድል ባጣስ? የተበደርሁትንስ ዕዳ እንዴት መክፈል እችላለሁ? ልጆቼስ ከራብና ከጕስቍልና እንዴት መውጣት ይችላሉ? የሰባት ዓመት ሥራ የማጣት እንቆቅልሼስ እንዴት ይፈታል? በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ፣ በእዚህ ችግር ውስጥ እያለን ባለቤቴ ስምንተኛ ልጅ ለመጨመር ዕንስ ቋጥራለች፤ ይህንንስ ሽል ማስወጣት የለብንም?

ትክክልኛ የሆኑ ሥነ ምግረባራዊ ዕንስ ሐሳቦች እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ሥነ ምግባራዊ ውሳኔዎችን፣ ትክክለኛ በሆነ መልኩ የመፍታት ዐቅም አላቸው::

በሥነ ምግባር ላይ የሠሩ ምሁራን፣ እነዚህን መሰል ጕዳዮች ግብረገባዊ ግጭቶች ይሏቸዋል:: ግብረገባዊ ግጭት ማለት፣ እግዚአብሔር የሰጠን ግብረገባዊ ***ግዕዛን*** (ሕግጋት) በአንድ ሁኔታ ውስጥ እርስ በርሳቸው ሲጋጩ፣ ግብረገባዊ ግጭት ብለን እንጠራቸዋለን:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ ለአንዱ ግብረገባዊ ***ግዕዝ*** ስንታዘዝ፣ ሌላውን መቃረናችን አይቀሬ ነው፤ በዚህ ጊዜ ግብረገባዊ ፋይዳዎች እርስ በርሳቸው መጋጨታቸው የግድ የሆናል:: ግብረገባዊ ግጭቶች እንዳሉ የሚቀበሉ ***የሥነ ምግባር***

[1] *Readings in Christian Ethics Volume 1: Theory and Method*, eds. David K. Clark and Robert V. Rakestraw, (Grand Rapids: Baker, 1994), 113-117.

*ምሁራን*፣ ኮሪ ቴን ቡም በደል አልባ የሆኑትን ሰዎች ነፍስ በመታደግና እውነቱን ለገዳዮቻቸው በመናገር አጣብቂኝ ውስጥ እንደ ገቡ ያምናሉ:: የእስራኤላውያኑን ሕይወት ለመታደግ ሲባል፣ "በቤታችን ውስጥ አልተሸሸጉም" በማለት፣ የናዚን ወታደሮች መዋሸት ነበረባቸው:: ለተጠየቁት ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ቢሰጡ፣ እነዚያን በደል አልባ ሰዎች ለሞት አሳልፈው ይሰጡአቸው እንደ ነበር ልብ ይሏል::

በዕለት ኑሮአችን የምናገኛቸው ግብረገባዊ ውሳኔዎች፣ የእዚህን ያህል በግጭት የተሞሉ ናቸው ማለት ግን አይደለም:: የዕውቀት ማነስ ችግሮችና የኀሊና ውጥረቶች ሁሉ የግብረገብ ግጭቶች አይደሉም:: የዕውቀት ማነስ ችግሮችና የኀሊና ውጥረት ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ ግልጽ ለማድረግ አንዳንድ ምሳሌዎችን እንመልከት:- አቶ ነጋሳ በከተማ ልማት ቢሮ ውስጥ በዋና ሥራ አስኪያጅነት የሚሠራ፣ ፈሪሓ እግዚአብሔር ያለው ክርስቲያን ወንድም ነው:: አቶ ነጋሳ የሚሠራበት የከተማ ልማት ቢሮ በማደግ ላይ ላሉ አንዳንድ ከተሞች የከተማቸውን ዕድገት በተመለከተ የሚነድፉትን ዕቅድ የሚያግዝ የገንዘብ፣ የምክርም ሆነ የቴሳቀኑስ ርዳታ መስጠት ሲኖርበት፣ ለአንዳንድ ከተሞች ይህን አያደርግም:: ይህ አሠራር አዱሎአዊ፣ ኢፍትሐዊና ሕገ ወጥ ነው:: አቶ ነጋሳ ሁለት ምርጫ አለው፣ አሁን ባለው ሁኔታ ሥራውን እየሠራ የድርጅቱን ኢፍትሓዊ አሠራር መደገፍ ወይም ሥራውን በማቆም (በመልቀቅ) መጽሐፍ ቅዱስ ቤተ ሰብህን አስተዳድር የሚለውን ሕግ መሻር:: አቶ ነጋሳ የሚያስተዳድረው መሥሪያ ቤት እየተጓዘበት ያለው መንገድ ስሕተት መሆኑ ከገባው፣ የመሥሪያ ቤቱን ስሕተት ማረም እስከ ቻለ ድረስ ከላይ ያየናቸውን አማራጮች ሊከተል አይገባውም:: ይህን የአቶ ነጋሳን ጉዳይ ግብረገባዊ ግጭት ልንለው አንችልም፤ የዕውቀት (የብልኀት) ማነስ ችግር እንጂ::

እንደዚሁ ሁሉ የኀሊና ጦርነት፣ ግብረገባዊ ግጭት አይደለም:: ሂዋን ጭር ባለ ቦታ ላይ በብር የታጨቀ ቦርሳ መንገድ ላይ ወድቆ ብታገኝ፣ ገንዘቡ የጠፋበትን ሰው (ግለሰብ) ሳፈላልግ አልያም የጠፋበትን ሰው ፈልጎ ለሚያስረክብ ሕጋዊ አካል (ፖሊስ፣ ቀበሌ) ልስጥ ወይስ ገንዘቡን ወስጄ ፀናቴ ላይ የሚያናጥረውን የሁለት ዓመት ውዝፍ የቤት ክራይ ዕዳ ልክፈል፣ በሚሉት ሁለት ሐሳቦች ኀሊናዋ ጦርነት ሊገጥም ይችላል:: ይህ ግን ግብረገባዊ ግጭት አይደለም:: ግብረገባዊ ግጭት የሚባለው፣ ትክክለኛ የሆነው ግብረገባዊ ውሳኔ (ምርጫ) የትኛው እንደ ሆነ ዐውቀን፣ አንዱን ግብረገባዊ ሕግ ስንከተል ሊላውን ግብረገባዊ ሕግ የምናፈርስበት ሁኔታ ሲፈጠር ነው:: የአቶ ነጋሳ ችግር ብልኀት የማጣት ችግር ነው:: የሂዋን ችግር ደግሞ፣ ትክክል የሆነውን ነገር በማድረግና በጊዜው ያፈጠጠባትን ችግር በመፍታት ላይ የሚያጠነጥን ነው::

ሁሉም የሥነ ምግባር ምሁራን፣ የግብረገብ ግጭት አለ የሚል እምነት የላቸውም:: *ኢተጣራሽ ፍጹማውያን* እግዚአብሔር ፍጹማዊ የሆኑ በርካታ *ግብረገባዊ*



*ግዕዛንን* (*መርሖችን*) ለሰው ልጆች ቢሰጥም፣ እነዚህ ግዕዛን ግን በዕለት ኑሮአችን ውስጥ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ (የሚጣረሱ) አይደሉም የሚል እምነት አላቸው:: ኢተጣራሽ ፍጹማውያን ፍጹማዊ በሆኑ በሁለት ትእዛዛት መካከል ግጭት ሊኖር አይችልም፤ ያለ ቢመስል እንኳ እውነታው ግን ግጭት ያለመኖሩ ነው:: እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ሁለት መለኮታዊ ትእዛዛት እርስ በርሳቸው በሚቃረኑበት ሁኔታ ውስጥ አያሳልፋቸውም:: በሌላ አገላለጽ ግብረገባዊ ግጭቶች የዕውቀት ማነስና የኀሊና ጦርነት ችግሮች ብቻ ናቸው ባዮች ናቸው:: ኮሪ ቴን ቡም ግራ በመጋባት ውስጥ የገቡት፣ ውሸት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለተኰነነ ነው፤ ነገር ግን ሰዎችን ከአካላዊ ሞት ስለመታደግ ቃለ እግዚአብሔር በግልጽ የሚያስተምረው ትምህርት (የደነገገው ሕግ) የለም፤ ስለዚህ ግብረገባዊ ውጥረት ውስጥ የሚያስገባቸው አንዳችም ምክንያት አልነበረም::

የኢተጣራሽ ፍጹማዊነት አመለካከት፣ በብዙ ክርስቲያኖች ዘንድ ተቀባይነት ያለው አመለካከት ነው:: የተጣራሽ ፍጹማዊነትን አመለካከት የሚከተሉ ሰዎች ግን፣ ግብረገባዊ ትእዛዛት እርስ በርሳቸው ሊቃረኑ እንደሚችሉ ያምናሉ:: ተጣራሽ ፍጹማውያንና ተዋረዳዊ ፍጹማውያን በዚህ አቋማቸው አንድ ቢሆኑም፣ አንዱ ግብረገባዊ ሕግ ተግባራዊ ሲያደረግ ሌላኛው ሕግ ተግባራዊ የማይደረግ ከሆነ፣ ተግባራዊ ባልተደረገው ሕግ ላይ ንስሓ መግባት ያስፈልጋል ወይስ አያስፈልግም በሚለው ነጥብ ላይ ግን ይለያያሉ:: ተጣራሽ ፍጹማውያን ባልተከበረው ሕግ ላይ ንስሓ መግባት ያስፈልጋል ሲሉ፣ ተዋረዳዊ ፍጹማውያን ግን ይህን አይቀበሉም::

***ተጣራሽ ፍጹማውያን*** እግዚአብሔር በርካታ የሆኑ ፍጹማዊ ግዕዛንን ለሰው ልጆች መስጠቱን፣ እነዚህም ግብረገባዊ ግዕዛን በተፈጥሮአቸው ሊቃረኑ እንደማይችሉ ይገልጻሉ:: ነገር ግን ከኀጢአት የተነሣ፣ በምንኖርባት በዚህች ዓለም እነዚህ ግብረገባዊ ግዕዛን እርስ በርሳቸው ሲጋጩ (ሲጣረሱ) ይስተዋላል:: ሁለት የእግዚአብሔር ግብረገባዊ ሕግጋት በሚከቡን ጊዜ፣ ለአንደኛው ሕግ ስንታዘዝ ሌላኛውን ሕግ በመጣስ ኀጢአት ልናደርግ እንችላለን:: በዚህ ዐይነቱ አጣብቂኝ ሰዓት ኀጢአት አይቀሬ ጉዳይ ከሆነ፣ የከፋ ውጤት የማያስከትለውን ኀጢአት መምረጥ ይኖርብናል:: ለምሳሌ:- አንድ ክርስቲያን ውሸትን ተናግሮ በደል የሌለበትን የሌላውን ሰው ሕይወት መታደግ ከቻለ መዋሸት ይኖርበታል፤ ምክንያቱም የሰው ሕይወት ውሸትን ከመናገር ይበልጣልና:: ነገር ግን ይህ ሥራ ከኀጢአት የጠራ ነው ማለት በፍጹም አንችልም:: ስለዚህም አንዱን ግብረገባዊ ሕግ መታዘዛችን መልካም ቢሆንም፣ በአንጻሩ ያለውን ሕግ በመተላለፋችን ንስሓ ልንገባ ያስፈልጋል::

***ተዋረዳዊ ፍጹማውያን*** ከላይ እንዳየናቸው እንደ ሁለቱ ጉራዎች መጽሐፍ ቅዱስ ፍጹማዊ የሆኑ ግብረገባዊ መስፈርቶች እንዳሉት ያምናል:: በሁለት ግብረገባዊ

ሕግጋት ስንያዝ፣ የተሻለ ውጤት የሚያመጣውን ሕግ መከተል አስፈላጊ ነው ከሚለው ከተጣራሽ ፍጹማዊነት አመለካከት ጋር ተመሳሳይ አቋም ይጋራል:: ነገር ግን ይህን አመለካከት ከተጣራሽ ፍጹማዊነት የሚለየው፣ በሁለት ሕግጋት ስንከበብ (ስንያዝ) ለከፍተኛው ሕግ በመታዘዝ ዝቅተኛውን ሕግ ማፍረሳችን መልካም ማድረጋችን እንጂ፣ መለስተኛ ክፋት (ኀጢአት) ማድረጋችን አይደለም፤ እግዚአብሔር የሰጠን ግብረገባዊ ሕግጋት ተዋረዳዊ ስለሆኑ፣ በማይወገዱ በግብረገባዊ ግጭቶች ውስጥ በምንወጠርበት ጊዜ፣ ከፍተኛውን ሕግ መታዘዝ ይኖርብናል የሚል ነው:: የንጹሓንን ሕይወት ለመታደግ መዋሸት ክፋት የለውም፤ ይህም ንስሓ የሚያስገባን ጕዳይ (ኀጢአት) አይደለም የሚል አቋም ነው:: ሁለት መኪኖች ከተለያዩ አቅጣጫዎች ወደ አንድ መገናኛ መንገድ የሚሄዱ ከሆነ፣ ለአንደኛው መኪና ቅድሚያ የሚሰጥ እንዲሁም ሌላኛውን መኪና የሚያዘገይ ሕግ ከሌለ፣ ሁለቱም መኪናዎች አደጋ ውስጥ መውደቃቸው አይቀሬ ነው:: ለዚህም ነው የትራፊክ ፖሊስ አንደኛውን የሚያስቆምና ለሌላኛው ቅድሚያ የሚሰጥ ሕግ በእንዲህ ዐይነቶቹ መንገዶች ዳር ላይ የሚተከለው:: ሁለቱም መኪኖች በመገናኛው መንገድ ላይ የመሄድ መብት ቢኖራቸውም፣ ሕጉ ይህን ተግባራዊ የሚያደርገው ተዋረዳዊ ሕግ በማኖር ነው (አንዱ ከሄደ በኋላ ሌላው ይከተል)::

ሁሉም የሥነ ምግባር ምሁራን፣ ከላይ ባየናቸው ሦስት ጐራዎች ብቻ ይከፈላሉ ማለት አይደለም:: ቢያንስ ቢያንስ *ጥቅላሌነትንና ትራኪያዊ ሥነ ምግባርን* በዚህ ቦታ ልንዘክራቸው ይገባል::

ጥቅላሌነት ዓለም ዐቀፍ ወይም ፍጹም የሆኑ ሕግጋት የሉም፤ ነገር ግን አንዳንድ ሥነ ምግባራዊ ሕግጋት ሁሉን ዐቅፈው የሚይዙ ናቸው:: እንደዚህ አመለካከት ውሸትን መናገር በሁሉ ዘንድ ስሕተት ነው፤ በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ (ለምሳሌ:- የሰውን ሕይወት ማዳን) ግን ውሸትን መናገር ትክክል ይሆናል እንደዚህ አመለካከት ሁሉ ዐቀፍ የሆኑት የእግዚአብሔር ሕግጋት (ለምሳሌ:- አትስረቅ፣ አትዋሽ ወይም አትግደል የሚሉት) ዐልፎ ዐልፎ በሚከሠቱ አንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ በፍጹም ተፈጻሚ ሊሆኑ አይችሉም::

ትራኪያዊ ሥነ ምግባርን የሚከተሉ ምሁራን፣ ታሪክን መተረክ ነገረ መለኮትን ለማስተማር ዐይነተኛ መንገድ ነው የሚል እምነት አላቸው:: ትራኪያዊ ሥነ ምግባር ዐላማ ያደረገው፣ እጅግ ውስብስብና "የማይጨበጡ" ሥነ ምግባራዊ ችግሮችን መፍታት ሳይሆን፣ የሰዎችን ግብረገብ ማሳደግ ነው::



# ኢተጣራሽ ፍጹማዊነት[1]

ሥነ ምግባርን በተመለከተ ያሉት ሁለቱ ዐበይት አመለካከቶች፣ ግብረገባዊ ፍጹማዊነትና ግብረገባዊ አንጻራዊነት ናቸው::

ግብረገባዊ ፍጹማውያን ግብረገባዊ ግዕዛን (መርሖች) በቦታ፣ በሁኔታና በጊዜ አይወሰኑም (ኃባራዊ ናቸው) ሲሉ፣ ግብረገባዊ አንጻራውያን ግን የዚህን ተቃራኒ አመለካከት ይከተላሉ (ግብረገባዊ ግዕዛን ኀሊናዊ ናቸው ይላሉ፤ ግብረገባዊ አንጻራዊነት የሚለውን ክፍል ይመለከቷል):: ከዚህ በመቀጠል የምንመለከተው፣ በግብረገባዊ ፍጹማውያን መካከል ስላሉት ሦስት አመለካከቶች ይሆናል:: እነዚህም ኢተጣራሽ ፍጹማውያን፣ ተጣራሽ ፍጹማውያንና ተዋረዳዊ ፍጹማውያን በመባል የሚታወቁ ናቸው::

በብዙ ክርስቲያኖች ዘንድ ተቀባይነት ያለው አመለካከት፣ የኢተጣራሽ ፍጹማዊነት አመለካከት ነው (ብዙዎች ይህን አመለካከት የሚከተሉት አማራጮቹን አመለካከቶች ዐውቀዋቸው አይደለም):: እንደ ኢተጣራሽ ፍጹማውያን አመለካከት፣ ግብረገባዊ ግጭት የሚባል ነገር የለም:: ኀጢአት ዘወትር ልናስወግደው የምንችለው ጕዳይ ነው:: ግብረገባዊ ግዕዛን (መርሖች) በማናቸውም ሁኔታ እንዲሁም ጊዜና ቦታ፣ እርስ በርሳቸው የማይጣረሱ (የማይቃረኑ) ናቸው:: በመካከላቸውም መብለጥና መበላለጥ፣ መቅደምና መቀዳደም የለም:: ከዚህ ቀጥሎ ለኢተጣራሽ ፍጹማዊነት መሠረት የሆኑትን ነጥቦች እንመልከት::

## ፍጹማን የሆኑ በርካታ መለኮታዊ ግዕዛን አሉ

ኢተጣራሽ ፍጹማዊነት የተዋቀረው፣ እግዚአብሔር ፍጹማን የሆኑ በርካታ ግብረገባዊ ግዕዛንን (መርሖችን) ሰጥቶአል በሚለው መሠረት ላይ ነው:: "አትግደል"፣ "አታመንዝር"፣ "አትስረቅ" ወዘተ የሚሉት ግብረገባዊ ግዕዛን፣ ሳይበላለጡና ሳይቀዳደሙ በማንኛውም ሰውና በየትኛውም ጊዜ ተግባራዊ መሆን አለባቸው ይላሉ::

---

[1] Robert V. Rakestraw, "Ethical Choices: A Case for Non-Conflicting Absolutism," *Criswell Theological Review* (Spring 1988) 239-267. ይህ አመለካከት በብዙ ክርስቲያኖች ዘንድ ተቀባይነት ይኑረው እንጂ፣ አመለካከቱን በመደገፍ የተጻፈ ጽሑፍ የለም፤ ምናልባት ይህን አመለካከት ከሐያስን ለመጠበቅ የተጻፈ ብቸኛ ጽሑፍ በግርጌ ማስታወሻው ላይ የተጠቀሰው ጽሑፍ ብቻ ነው::

እንደ አመለካከቱ መምህራን፣ ይህ አስተምህሮ የተቀዳው ከቃለ እግዚአብሔር ሲሆን፣ ወደዚህ መረዳት የሚደርሰውም፣ ትክክለኛ የሆነውን የቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥበብ በመጠቀም ነው:: እነዚህ ግብረገባዊ ግዕዛን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሰጣቸውና በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጡ፣ ትክክለኛ የሆነ የአፈታት ሥልት በመከተል ቃለ እግዚአብሔርን በማጥናት ብቻ የምንረዳቸው ናቸው::

## ግብረገባዊ ግዕዛንን እርስ በርስ የሚያስተሳስር አንድ ፍጹማዊ ግዕዝ አለ

እንደ ኢተጣራሽ ፍጹማውያን አመለካከት፣ ግብረገባዊ ግዕዛንን እርስ በርስ የሚያስተሳስረው ፍጹማዊ ሕግ፣ "ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም፣ በፍጹም አሳብህም ውደድ:: ታላቂቱና ፊተኛዪቱ ትእዛዝ ይህቺ ናት:: ሁለተኛዪቱም ይህችን ትመስላለች፤ እርስዋም:- ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ" የሚለው ነው (ማቴ 22÷34-40):: የሥነ ምግባር መሠረቱ ይህ ነው::

እግዚአብሔርን ውደድ የምትለዋ "ቀዳማዪቱ" እንዲሁም ባልንጀራህን ውደድ የምትለው "ሁለተኛዪቱ" (ተከታይዋ) ትእዛዝ አይደለችምን? ይህስ በትእዛዛቱ መካከል ተዋረድ (መብለጥና መበላለጥ መቅደምና መቀዳደም) እንዳለ አያመለክትምን? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል:: "ፊተኛዪቱና" "ሁለተኛዪቱ" የሚሉት ቃላት፣ በግብረገባዊ ትእዛዛት መካከል ተዋረድ መኖሩን የሚያመለክቱ ሳይሆን፣ "ባልንጀራን እንደ ነፍስ" ለመውደድ "እግዚአብሔርን በፍጹም ልብ" መውደድ ቅድመ ሁኔታ መሆኑን የሚያመለክት ነው እንጂ፣ ግብረገባዊ ትእዛዛት እርስ በርሳቸው ይጋጫሉ፣ አንዱም ከሌላው የበለጠ ነው የሚለውን ትምህርት የሚያጸና አይደለም:: በክፍሉ ኢየሱስ አጽንዖት ሰጥቶ የሚገልጸው ጉዳይ፣ ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር ምግባራችንን እንደሚወስነው ነው:: እግዚአብሔርን ስንወድድ ነው ጐረቤቶቻችንን ትክክለኛ በሆነ መልኩ መውደድ የምንችለው፤ ምክንያቱም ጐረቤቶቻችሁን ውደዱ የሚለው ሕግ አምላክ የሰጠን ትእዛዝ ነው (ዮሐ 14÷15):: ይህ ማለት ግን ለጐረቤቶቻችን ያለን ፍቅር ለእግዚአብሔር ባለን ፍቅር የተወሰነ ነው ማለት አይደለም:: ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅርና ለተገለጠው እውነት ያለን ታዛዥነት መሠረታዊ ጉዳይ ነው፤ አልያ ለጐረቤቶቻችን ያለን ፍቅር ስሜታዊ፣ ሥጋዊ እንዲሁም ኀላፊነት የጐደለው እንዲሆን ያደርገዋል::



## ግብረገባዊ ግዕዛን እርስ በርሳቸው አይጣረሱም

ግብረገባዊ ግዕዛን እርስ በርሳቸው የሚጣረሱ (የሚጋጩ) ቢመስለን እንኳ፣ እውነታው ግን በፍጹም ያለመጣረሳቸው ነው:: አንዱን ግብረገባዊ ግዕዝ (ሕግ) ስንከተል ሌላውን የምናፈርስበት አንዳችም ምክንያት የለም:: በደል አልባ የሆነውን ሰው ከሞት አድናለሁ በሚል መዋሸት የለብንም:: ከእኛ የሚጠበቀው ማዳን ሳይሆን አለመዋሸት ነው:: እውነትን መናገር ሊሻር የማይችል ፍጹማዊ ትእዛዝ ነውና (ኤፌ 4÷15):: ቃለ እግዚአብሔር በግልጽ ያዘዘን እውነትን እንድንናገር እንጂ፣ ውሸት እየተናገርን በደል አልባ የሆኑ ሰዎችን ከሞት መታደግ አይደለም:: መጽሐፍ ቅዱስ

ጐረቤቶቻችንን መውደድ እንዳለብን ያስተምረናል፤ ነገር ግን ፍቅራችንን መግለጽ የሚኖርብን ከውሸት በጠራ መንገድ ብቻ ነው::

## ግብረገባዊ ግዕዛን ፍጹማን ናቸው ብለን በአንጻሩ ደግሞ ይጣረሳሉ ማለት ስሕተት ነው

ግብረገባዊ ግዕዛን ፍጹማን ናቸው ብለን በአንጻሩ ደግሞ ይጣረሳሉ ማለት እንዴት እንችላለን? ለምሳሌ:- ልጆች ለወላጆቻቸው ይታዘዙ የሚለው ትእዛዝ ፍጹም ነው:: ይህ ፍጹም ሕግ ልጆች ለወላጆቻቸው መታዘዝ ያለባቸው፣ የወላጆች ትእዛዝ እንደ ቃለ እግዚአብሔር ሲሆን ብቻ ነው የሚል ቅድመ ሁኔታ ስላልተበጀለት፣ ልጆች የወላጆቻቸውን ትእዛዝ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ መታዘዝ ይጠበቅባቸዋል:: ወላጆች ልጆቻቸው እንዲሰርቁ፣ እንዲዋሹ ወዘተ ትእዛዝ ቢሰጡ እንኳ፣ ልጆች የመታዘዝ ግዴታ አለባቸው፤ ምክንያቱም ቃለ እግዚአብሔር፣ ልጆች ለወላጆቻቸው መታዘዝ ያለባቸው፣ የወላጆች ትእዛዝ ከቃለ እግዚአብሔር ጋር ሲጣጣም ብቻ ነው አይልምና::

## ግብረገባዊ ግዕዛንን ለመተላለፍ አንዳችም ምክንያት የለንም

አንድ ሰው ግብረገባዊ ግዕዛንን እስካከበረ ድረስ፣ ለሚከተለው ውጤት ተጠያቂ ሊሆን አይችልም:: "የሂትለር ወታደሮች እቤቴ መጥተው፣ እስራኤላውያንን ደብቀሃል?" የሚል ጥያቄ ቢያቀርቡልኝ ደብቄያቸው ከሆነ መደበቄን እናገራለሁ፤ ነገር ግን የሂትለር ወታደሮች ለሚወስዱት ርምጃ እኔ ተጠያቂ ልሆን አልችልም:: ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሊከተል ይገባዋል፤ መታዘዙ የሚያስከትለውን ውጤት ግን ለእግዚአብሔር የምንተወው ጉዳይ ነው:: ያለመስረቅና ሐሰትን ያለመናገር ሊያስገድል ይችላል፤ ነገር ግን ይህ የእኛ ሳይሆን የእግዚአብሔር ጉዳይ

ነው:: ሐሰት ባለመናገራችን ወዘተርፈ የተገደልነው፣ እርሱ እንድንታዘዘው የሚፈልገውን ነገር ፈጽመን በመገኘታችን ነውና::

## ውጤቱ መልካም ነው ማለት መንገዱ መልካም ነው ማለት አይደለም

ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር፣ ሰናይም ሆነ እኩይ ምግባራት የሚመዘኑት፣ ፍጹማዊ በሆኑ ግብረገባዊ ግዕዛን እንጂ፣ ምግባሩ በሚያስከትለው ውጤት አይደለም የሚል የጸና አቋም አለው:: "የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው"[2] የሚለው ብሂል፣ ክርስትና መሠረት ባደረገው ሥነ ምግባራዊ መርሕ ውስጥ ስፍራ የለውም:: የሚፈጭበት ቦታና መንገድ ከእኩይነት ፍጹም የጠራ መሆን አለበት:: ኢተጣራሽ ፍጹማዊነት ምግባርን እንጂ ውጤትን ማእከል ያደረገ አይደለም:: ግብረገባዊ ግዕዛንን የምንከተለው፣ መከተላችን በራሱ ትክክል ስለሆነ እንጂ፣ መልካም ውጤት ያስከትላል በሚል ሐሳብ አይደለም:: ይህ ማለት ግን ኢተጣራሽ ፍጹማዊነት የውጤት ጉዳይ ግድ አይለውም ማለት አይደለም:: ከኩርንችት በለስ አይለቀምምና መልካም ዛፍ መልካም ፍሬ፣ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ማፍራቱ አይቀሬ ነው:: ኢተጣራሽ ፍጹማዊነት ለውጤት ስሙርነት ግድ የሚለው ቢሆንም፣ ግብረገባዊ የሆኑትን ፍጹማዊ ግዕዛን እየሠዋን፣ ውጤታችንን አናሳምርም:: አጠቃላይ ውጤቱ ሠመረ ማለት፣ ወደ ውጤት የደረስንበት መንገድ ትክክል ነበር ማለት ላይሆን ይችላል::

## ትክክለኛ ሥራ ሲሠራ ያልተጠበቀ ውጤት ሊገኝ ይችላል

ፍጹማን የሆኑትን ግብረገባዊ ግዕዛን ለመተግበር በምንውተረተርበት ጊዜ፣ ያልተጠበቀ ውጤት ሊከተል ይችላል:: ይህን ጣምራ ውጤት ብለን እንጠራዋለን፤ ይኸውም ተፈላጊው ውጤትና ሳይፈልግ የተከሠተው ውጤት ናቸው:: ያልተፈለገው ውጤት ሆን ተብሎ እስካልታቀደ ድረስ፣ ተፈላጊውን ውጤት ተግባራዊ ማድረግ እንችላለን:: ለምሳሌ:- ራሳችንን ለመከላከል ብለን ሰው ብንገድል፣ ቀዶ ጥገና በሚካሄድበት ወቅት የበሽተኛው ወይም የፅንሱ ሕይወት ቢያልፍ ወዘተ እንደ ማለት ነው:: እነዚህ ውጤቶች አሳዛኝ ቢሆኑም፣ ሆን ተብለው እስካልተሠሩ ድረስ፣ እንደ ኀጢአት ሊቈጠሩ አይገባም:: ይህ የጣምራ ውጤት ጉዳይ ነውና::

ነገር ግን ክፋትን ያስከተለው ሥራ እንደ ሠናይ ሊቈጠር የሚችለው ቢያንስ የተከናወነው ምግባር፣ አራት ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት ሲችል ነው (1) ክፋትን

[2] ይህ ብሂል "The end justifies the means" የሚለውን የእንግሊዝኛ ብሂል ሊተካው ይችላል ስላልን፣ በዚህ ስፍራ ተጠቅመንልታል::



ያስከተለው ምግባር፣ በሥነ ምግባር መስፈርት ተመዝኖ የግድ ሠናይ ሆኖ መገኘት ይኖርበታል:: (2) ድርጊቱ የተካሄደበት ዐላማ (ልባዊ ፍላጎት) ከክፋት ፍጹም የጠራ እንዲሁም የሚያስከትለው ውጤት መጥፎ ሳይሆን ጥሩ ሊሆን ይገባዋል:: (3) መልካሙ ምግባር ሊቀድም አልያም ከእኩይ ውጤት ጋር መሳ ለመሳ ሊሄድ ይገባዋል:: (4) መልካሙ ውጤት ከተከተለው ክፉ ውጤት ጋር እቻ ሊሆን ይገባዋል::

ኢተጣራሽ ፍጹማዊነት ግብረገባዊ ምግባሮች ሁሉ፣ በጣምራ ውጤት የተሞሉ ናቸው የሚል እምነት የለውም:: የምንሠራቸውን እኩይ ሥራዎች ሁሉ

በጣምራ ውጤት ልናመሃኝ አንችልም:: ለምሳሌ:- ክርስትናን በጦርነት ለማስፋፋት መሞከር:: እስራኤላውያን የተስፋዪቱን ምድር ለመውረስ ባደረጉት ጦርነት፣ እግዚአብሔር ራሱ የምድሪቱ ቀደምት ነዋሪዎች እንዲገደሉ (ሕፃናትን ይጨምራል) ሲያዝ እንመለከታለን (ዘዳ 20÷16-18፤ ኢሱ 6÷21፤ 8÷2: 24-27፤ 11÷6-20):: ይህ መቼም የሚፈለግ ጉዳይ አይደለም፤ እንዲያውም አሰቃቂ ሂደት እንጂ:: ነገር ግን ይህ አሰቃቂ ሁኔታ የተፈጸመው ትክክል በሆነው በእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው:: ይኸውም "ይጥፉ" የተባሉት እነዚህ ሰዎች፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ እግዚአብሔርን ከማምለክ እንዲመለስ ስለሚያደርጉትና የጣዖት አምልኮም ጥፋትን ማስከተሉ አይቀሬ ስለሆነ ነው (ዘዳ 20÷16-18)::

እስራኤላውያን በአምላክ ትእዛዝ እነዚህን ሰዎች ማጥፋታቸው ተገቢ ነበር:: ዛሬ አንድም ሰው ይህን ኀብረት ሰብ በአምላክ ትእዛዝ አጠፋለሁ ማለት ግን አይችልም:: እግዚአብሔር ለእስራኤል ከሰጣት ከዚህ ትእዛዝ የምንማረው ነገር፣ የአምላክ ትእዛዝ ጣምራ ውጤት ሊያስከትል መቻሉ ነው::

## ማጠቃለያ

ኢተጣራሽ ፍጹማውያን እግዚአብሔር በራሱ ርዳታ ተግባራዊ ይሆናሉ ብሎ በሰጠን ፍጹማዊ ትእዛዛት መኻል፣ ግጭት አለ ብሎ ማሰብ ስሕተት ነው ባዮች ናቸው:: እግዚአብሔር ተግባራዊ ሊሆኑ የማይችሉ ወይም የሚቃረኑ ግብረገባዊ ግዕዛንን እንዴት ይሰጠናል? ተጣራሽ ፍጹማውያን መለኮታዊ የሆኑት ፍጹማዊ ግዕዛን በመሠረቱ እርስ በርሳቸው አይቃረኑም:: ነገር ግን ዓለማችን በኀጢአት ስለተበላሸች እነዚህ ግዕዛን የሚጣረሱ መስሎ ሊታየን ይችላል ባዮች ናቸው:: ነገር ግን እንዲያ ከሆነ ከውድቀት በኋላ ግብረገባዊ ግዕዛን በሕይወታችን እውን ሊሆኑ አይችሉም ማለት ነው? ፍጹማን የሆኑትስ የእግዚአብሔር ባሕርያት (ሕግጋት) ጊዜ ሊወስናቸው ነው ማለት ነው:: ፍጹማን የሆኑት ግብረገባዊ ግዕዛን በምንም መልኩ ሊቃረኑ አይችሉም:: እግዚአብሔር (ኢየሱስ) እውነት ነው (ዮሐ 1÷14፤ 14÷6፤ 2ዮሐ 1-3) የእግዚአብሔር

ልጆችም በእውነት እንዲሄዱ ታዘዋል (ኤፌ 4፥15)፤ በእውነትም ሄደዋል (2ዮሐ 4፤ 3ዮሐ 3-4)። ስለዚህ በግብረገባዊ ባሕርያት መካከል ተዋረድ አለ፣ የበላይ የሆነውንም ሕግ እንድንከተል ታዘናል የሚለው የተዋረዳዊ ፍጹማውያን ትምህርት ትክክል አይሆንም። ይህ እንግዲህ፣ የኢተጣራሽ ፍጹማውያን አስተምህሮ ነው።

# 7.2

## ተጣራሽ ፍጹማዊነት[1]

ግብረገባዊ ግጭቶችን አስመልክቶ፣ ግብረገባዊ ፍጹማውያን በሦስት ጐራ እንደሚከፈሉ ከላይ ለማየት ሞክረናል። ኢተጣራሽ ፍጹማዊያን በግብረገባዊ ግዕዛን መካከል ቅራኔ የለም፤ ያለ ቢመስለን እንኳ፣ እውነታው ግን ግጭት ያለመኖሩ ነው ባዮች ናቸው። ተጣራሽ ፍጹማውያን ደግሞ በግብረገባዊ ግዕዛን መካከል ግጭት ሊኖር (ሊከሠት) ይችላል፤ ነገር ግን ለተላለፍነው ግብረገባዊ ግዕዝ፣ ንስሓ መግባት አለብን ባዮች ናቸው። ተዋረዳዊ ፍጹማውያን ደግሞ፣ በግብረገባዊ ግዕዛን መካከል ዐልፎ ዐልፎ ቅራኔዎች ሊከሡቱ ይችላሉ፤ ነገር ግን አንድ ሰው በደለኛ የሚሆነው የበለጠውን (ከፍ ያለውን) ግዕዝ በመታዘዝ፣ የበለጠውን መልካም ነገር ሳያደርግ ሲቀር ነው የሚል አቋም አላቸው። ይህ ክፍል የተጣራሽ ፍጹማዊነትን አመለካከት ይተነትናል።

### የተጣራሽ ፍጹማዊነት መሠረታዊ ነጥቦች

ተጣራሽ ፍጹማውያን በኀጢአት በተበላሸ ዓለም ስለምንኖር ግብረገባዊ ግጭቶች ይከሠታሉ የሚል አቋም አላቸው። ግብረገባዊ ግጭቶች በሚከሠቱበት ጊዜ፣ ሰዎች ለተጋጩት ግብረገባዊ ግዕዛን የመጠየቅ ኀላፊነት አለባቸው። የእግዚአብሔርን ሕግጋት የምናፈርሰው በኀጢአት ጐዳና ስንሄድ ብቻ ነውና ሰዎች ግብረገባዊ ግጭቶች በሚገጥሟቸው ጊዜ፣ ጥቂት እርኩሰት (ጥፋት) የሚያስከትለውን በመከተል፣ የእግዚአብሔርን ይቅርታ መጠየቅ ይኖርባቸዋል። የተጣራሽ ፍጹማዊነትን አመለካከት በስፋት የሚያራምዱት የሉተራን የነገረ መለኮት ምሁራን ናቸው። ከመራሕያነ ተሐድሶ መኻል ማርቲን ሉተርና የነገረ መለኮት ምሁሩ ሔልሙት ቴሊክ በዚህ አመለካከት ሥር ያሉ ናቸው።

ማርቲን ሉተር፣ ክርስቲያን በእግዚአብሔር መንግሥትና በዚህች ዓለም መንግሥት ውስጥ በእኩል ስለሚኖር፣ ለሁለቱም መንግሥት ኀላፊነት አለበት። በዚህም ምክንያት በግብረገብ ግዕዛን መካከል ግጭት መኖሩ የማይቀር ጉዳይ ነው። የሉተራን የነገረ መለኮት ምሁሩ ቴሊክ፣ "ኀጢአተኛ ሁን፤ በድፍረትም ኀጢአትን ሥራ፤ ነገር ግን በኀጢአት፣ በሞትና በዓለም ላይ ሥልጣን ባለው በክርስቶስ ታመን

[1] ይህ ክፍል የተወሰደው Norman L. Geisler, *Chriatian Ethics: Options and Issues* (Grand Rapids: Baker, 1989), 116-122 ከ Helmut Thielicke, *Theological Ethics*, ed. William H. Lazareth, vol. 1 (Philadelphia: Fortress, 1966), 504-602. ጠቅሶ ከጻፈው ላይ ነው።

(ሐሴት አድርግ)" የሚለውን የሉተርን አባባል አስመልክቶ፣ "(ይህ ማለት) ለመጽደቅ ቅድመ ሁኔታ አለው ማለት አይደለም...እውነታው ግን ክርስቶስ ዓለምን ስላሸነፈ እንዲህ ብሎ በድፍረት መናገር ስለሚያስፈልግ ነው":: ኀጢአት የምናስወግደው ሳይሆን፣ የምናሸንፈው ጉዳይ ነው ይላል::

በኀጢአት በወደቀችው ዓለም ሲኖር፣ ኀጢአት አይቀሬ ጉዳይ ነው፤ ነገር ግን ዓለም ከኀጢአት ስለ ተቤዠች፣ በዓለም ሲኖር በክርስቶስ ወጀአዊ ሥራ፣ የኀጢአት ይቅርታ ዘወትር የሚገኝ ነገር ነው::

ቴሊክ፣ "ግብረገባዊ ግጭቶች መኖራቸውን መካድ የውሳኔን ሕልውና መካድ ነው" ባይ ነው:: ግብረገባዊ ግጭቶች በሚከሠቱበት ጊዜ ኀጢአት አይቀሬ ጉዳይ ነው:: ሰዎች በኀጢአት የወደቀ ፍጡራን ስለሆኑ፣ ይህ ዐይነቱ ግብረገባዊ ግጭት የሚጠበቅ ነው:: ይህ ብቻ አይደለም ነገር ግን የእዚህ ዓለም መልክ፣ ከሰብአውያን ልብ የተሻለ ጽድቅ እንዲገኝ የሚያግዝ (የሚያበረታታ) አይደለም:: ስለዚህ ለእዚህ ምድር አኗኗር በሚጠቅሙና አምላካዊ በሆኑ ግዕዛን መካከል ግጭት ሊከሠት የሚችል ጉዳይ ነው::

ሙሉ ለሙሉ በኀጢአት መውደቃችን ለግብረገባዊ ግጭቶች ምክንያት ናቸው:: ስለዚህ በኀጢአት በተበላሸችው በዚህች ዓለም ስንኖር ግብረገባዊ ግጭቶችን ልንጋፈጣቸው እንችላለን::

እርስ በርስ በሚጣረሱ ግብረገባዊ ግጭቶች ውስጥ ስንሆን፣ መለስተኛ እርኩሰት ያለበትን ነገር ብቻ ማድረግ ይጠበቅብናል፤ ምክንያቱም ቀላልና ከባድ ኀጢ አቶች ስላሉ:: ነገር ግን እኩል ክብደት ባይኖራቸውም እንኳ፣ ሁሉም ኀጢአቶች ናቸው:: ማወቅ የሚኖርብን መሠረታዊው ነጥብ ጥቃቅን የሆኑትን ኀጢአቶች እንኳ ማድረግ እንደሌለብን ነው:: ግብረገባዊ ግጭቶች በሚፈጠሩበት ጊዜ፣ ሁለቱንም ግብረገባዊ ግዕዛን የመተግበር ኀላፊነት ቢኖርብንም፣ አንዱን ስንከተል ሌላውን መተላለፋችን የግድ ይሆናል:: በዚህ ጊዜ ክርስቲያን መለስተኛ ኀጢአት (እርኩሰት) የሆነውን ነገር በማድረግ፣ በእግዚአብሔር ይቅር ባይነት ላይ ሊታመን ይገባዋል:: ክርስቲያን ማወቅ የሚኖርበት ጉዳይ፣ "ፍጹም ጽድቅ (ቅድስና) በዚህች ምድር እንደ ሌለ ነው...ነገር ግን ሰፊ ጥፋት የሚያስከትል እርኩሰት እንዳለ ሁሉ መልካምና እጅግ መልካም የሆነ እውነታ አለ"::



# የተጣራሽ ፍጹማዊነት አስተምህሮዎች

የተጣራሽ ፍጹማዊነት አስተምህሮ በአራት መሠረታዊ ነጥቦች ላይ መሠረት ያደረገ ነው:: አንደኛ:- የእግዚአብሔር ሕግጋት ፍጹማን እንዲሁም በፍጹም ልንተላለፋቸው የማይገቡ ናቸው:: ሁለተኛ:- በኀጢአት በተበላሸው በዚህ ዓለም ስንኖር፣ በእግዚአብሔር ትእዛዛት መካከል ግጭት ሊፈጠር ይችላል:: ሦስተኛ:- ግብረገባዊ ግጭቶች በሚከሠቱበት ጊዜ፣ መለስተኛ እርኩሰት ያለበትን ነገር ልናደርግ ይገባል:: አራተኛ:- ኀጢአታችንን ከተናዘዝን፣ እግዚአብሔር ከበደላችን ያነጻናል::

## 1. የእግዚአብሔር ግብረገባዊ ሕግጋት ፍጹማን ናቸው

"የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው" (መዝ 19÷7):: ዘማሪው፣ "የቃልህ መጀመሪያ እውነት ነው፤ የጽድቅህም ፍርድ ሁሉ ለዘላለም ነው" (መዝ 119÷160) ይላል:: እግዚአብሔር ሕግጋቱን ያቆመው እንተላለፋቸው ዘንድ አይደለም:: ዘማሪው ይህንኑ እውነት ሲገልጽ፣ "ትእዛዛትህን እጅግ እንጠብቅ ዘንድ አንተ አዘዝህ" (መዝ 119÷4) ስለዚህም፣ "ባሪያህ ደግሞ ይጠብቀዋል፤ በመጠበቁም እጅግ ይጠቀማል" (መዝ 19÷11) ይላል::

እግዚአብሔር ፍጹም ነው፤ ሕግጋቶቹም የባሕርይው ነጸብራቅ ናቸው፣ "እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ፣ እናንተ ፍጹማን ሁኑ" (ማቴ 5÷48):: የእግዚአብሔርን ሕግጋት በተላለፍን ቍጥር ሁሉ ኀጢአትን እናደርጋለን፣ "ኀጢአትን የሚያደርግ ሁሉ ዐመፅን ደግሞ ያደርጋል፤ ኀጢአትም ዐመፃ ነው" (1ዮሐ 3÷4):: እግዚአብሔር አይለወጥም (ሚል 3÷9)፤ ባሕርያቱን የሚገልጹ ግብረገባዊ ሕግጋትም እንደዚሁ (ዕብ 6÷18)::

## 2. ግብረገባዊ ግጭቶችን ማስወገድ አይቻልም

ተጣራሽ ፍጹማዊነት መሠረት ያደረገበት ሌላው ነጥብ፣ ሰዎች በኀጢአት መውደቃቸውን ነው:: የሰው ልጅ በኀጢአት በመውደቁ፣ ሊወጣው በማይችልበት የኀጢአት ማነቄ ውስጥ ገብቶአል:: ከውድቀት በፊት አዳም ኀጢአት ያለማድረግ ችሎታ ነበረው፤ ነገር ግን ከውድቀት በኋላ የሰው ልጅ ሁሉ ኀጢአትን ሊያስወግድ አልቻለም:: ሰው ኀጢአትን ማስወገድ ብቻ አይደለም ያቃተው፤ ነገር ግን ግብረገባዊ ግጭቶች ውስጥ በመግባት ሊወጣው በማይችለው አሳዛኝ አጣብቂኝ ውስጥ ገብቶአል:: ይህ በኀጢአት የወደቀችው ዓለም

እውነተኛ ገጽታ ነው:: ስለዚህ ሰዎች በግብረገባዊ ግጭቶች ውስጥ በሚገቡበት ጊዜ መለስተኛ እርኩሰት ያለበት ነገር በማድረግ፣ በእግዚአብሔር ምሕረት ሊደገፉ ይገባል::

## 3. ትልቅ ኀጢአትና ትንሽ ኀጢአት አለ

ኀጢአቶች ሁሉ እኩል አይደሉም:: ኢየሱስ ለጲላጦስ፣ "...ለአንተ አሳልፎ የሰጠኝ ኀጢአቱ የከፋ ነው" ሲል በኀጢአት መካከል ደረጃ እንዳለ አመላካች ነው:: መንፈስ ቅዱስን መሳደብ ስርየት እንደ ሌለው ልብ ይሏል (ማቴ 12÷32):: ይህ ከከፋው ኀጢአት ይልቅ መለስተኛውን ኀጢአት እንድናደርግ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚመክረን ነው:: ግብረገባዊ ግጭት በሚከሠትበት ጊዜ ለበለጠው ግብረገባዊ ግዕዝ በመታዘዝ መለስተኛውን ሕግ እናፈርሳለን::

## 4. ለኀጢአት ይቅርታ አለው

ኀጢአትን ሙሉ ለሙሉ መሸሽ የማንችል ከሆነ፣ የእግዚአብሔር ይቅርታ በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በኩል ዘወትር እንዲሚያገኘን መዘንጋት የለብንም:: ኀጢ አትን የምንሸሸው ሳይሆን፣ በንስሓ የምናስወግደው ጉዳይ ነው::

# ተዋረዳዊ ፍጹማዊነት[1]

ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ግብረገባዊ አንጻራዊነትን በብርቱ ይቃወማል:: እግዚአብሔር አምላክ ገንዘቡ ያደረጋቸው ባሕርያት የማይለወጡ ስላልሆኑ፣ ሕግጋቱ ይህንኑ የሚያንጸባርቁ ናቸው::

## የተዋረዳዊ ፍጹማዊነት ታሪካዊ መሠረት

ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የሚቀበሉት ሥነ ምግባራዊ ፍጹማዊነት በሦስት ጐራ ይከፈላል:: ከመጥምቃውያን ትውፊት ጋር ተዛማጅ እንደ ሆነ የሚነገርለት ኢተጣራሽ ፍጹማዊነት፣ ከሉተራውያን ትውፊት ጋር የሚዛመደው ተጣራሽ ፍጹማዊነትና የተሐድሶአውያን ትውፊት የሆነው ተዋረዳዊ ፍጹማዊነት ናቸው:: የተዋረዳዊ ፍጹማዊነት አስተምህሮ ከመመልከታችን በፊት ታሪካዊ ዳራውን በአጭሩ እንቃኝ::

## ቅዱስ አውግስጢኖስ ዘሂጶ

አብዛኛውን ጊዜ የተሐድሶአውያን ትውፊት የሚጀምረው ከቅዱስ አውግስጢ ኖስ ዘሂጶ ነው:: እንደ ተዋረዳዊ ፍጹማውያን ሁሉ አውግስጢኖስም በኀጢአት መካከል ልዩነት አለ፣ አንዱ ኀጢአት ከሌላው ኀጢአት ይከፋል አልያም ይቀላል ባይ ነው:: የአውግስጢኖስ ሥነ ምግባር ማእከል ያደረገው ፍቅርን በመሆኑ፣ የነገሩ ክብደትና ቀለት የሚወሰነውም ባለን ፍቅር መጠን ነው:: ከሰው ይልቅ ሊወደድ የሚገባው እግዚአብሔር ነው፤ ከነገሮችም (ከቁሶችም) ባላይ ሊፈቀር የሚገባው የሰው ልጅ ነው[2]:: ስለዚህ በፋይዳ ተዋረድ ውስጥ እግዚአብሔር የበላይ የተቀሩት ነገሮች ደግሞ የበታች ናቸው:: በልጦና ልቆ ላገኘነው ነገር መታዘዝ ወሳኝ ነው፤ ከምድራውያን የሚጠበቀውም ይኸው ነው::

---

[1] Norman L. Geisler, *Christian Ethics: Options and Issues* (Grand Rapids: Baker, 1989), 116-122. ጸሐፊው ይህን አመለካከት ከሚያራምዱት ሰዎች መኻል፣ ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዝ ነውና፣ ምናልባትም ጸሐፊው የአመለካከቱ ብቸኛ ጸሐፊ ነው::

[2] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 114:: ከ Saint Augustine, *Christian Doctrine, in A Select Liberary of the Nicene and Post-Nicene Fathers of the Christion Church*, ed. Philip Schaff, Vol. 2 (Grand Rapids: Eerdmans, 1956), 530. ላይ ጠቅሶ እንደ ጻፈው::

አውግስጢኖስ አንዳንዱ ግብረገባዊ ውሳኔዎች እርስ በርሳቸው ይጋጫሉ የሚል አቋም አለው:: ለምሳሌ:- በግብረገባዊ ፋይዳ ውስጥ መግደል ትክክል ባይሆንም አውግስጢኖስ የሶምሶንን ግድያ በተመለከተ፣ "በእግዚአብሔር በራሱ ሕግ ውስጥ አንዳንድ ልዩ ምክንያቶች በመለኮታዊ ሥልጣን ተበይነዋል:: ይህ ልዩ ምክንያት ሁለት ፈርጅ አለው፡ ይኸውም በአጠቃላይ ሕግ ሕያው የሚሆን አልያም ለተወሰነ ጊዜ ለአንዳንድ ግለሰቦች የተሰጠ ልዩ ተልእኮ ነው"[3]:: አውግስጢኖስ በሁለተኛው ጐራ ውስጥ የመደባቸው አብርሃም፣ ዮፍታሔና ሶምሶን ናቸው፡ እነዚህ ሰዎች ሆን ብለው ሰዎችን እንዲገድሉ መለኮታዊ ትእዛዝ ተሰጥቶአቸዋል::

አውግስጢኖስ ሁለት ግብረገባዊ አማብቂኞች በሚገጥሙን ጊዜ፣ የበለጠውን ግብረገባዊ ጉዳይ በማክበር ትንሹን ማፍረስ፣ ጥቂት ኀጢአት ማድረግ ሳይሆን፣ እጅግ መልካም ነገር ማከናወን ነው የሚል እምነት አለው:: ለምሳሌ አብርሃምና ሶምሶን አምላክ እንዲገድሉ ትእዛዝ ሰጥቶአቸዋል:: በተመሳሳይ ጊዜና ሁኔታ ውስጥ ሁለት ግብረገባዊ ጥያቄዎች በሚቀርቡልን ጊዜ ከፍተኛውን በማክበር ዝቅተኛውን መጣስ (መተላለፍ) እንችላለን::

## ቻርልስ ሆጅ

ቻርልስ ሆጅ በትምህርተ መለኮት መጽሐፉ፣ ተዋረዳዊ ፍጹማዊነትን እንደሚከተል ይፋ አድርጎአል:: ሆጅ እውነት በእግዚአብሔር ባሕርይ ላይ መሠረት ስላደረገ ፍጹም ነው የሚል አቋም ቢኖረውም፣ አንዳንዴ ልዩ በሆነ ትእዛዝ እውነት የሆነው ነገር ስሕተት፣ ስሕተት የሆነውም ነገር እውነት ሊሆን ይችላል ባይ ነው[4]:: ሆጅ የዕብራውያኑን አዋላጆችና (ዘፀ 1) የሳሙኤልን ውሸት በአስረጅነት ያቀርባል:: ሳሙኤል እንዲዋሽ በአምላክ መታዘዙን ልብ ይሏል:: ሁኔታዎች በዚህ መልኩ ተቀናጅተው በሚመጡበት ጊዜ፣ የበለጠውን ለማክበር እውነቱን ያለመናገር ክፋት የለውም[5]:: ለምሳሌ፣ "አንዲት እናት በደል አልባ ልጇን ለመግደል የመጣውን ነፍሰ ገዳይ፣ ከሁኔታው እንዲታቀብ የሚቻላትን ሁሉ በማድረግ ገዳዩን ማሳሳት ትችላለች፤ ምክንያቱም በዚህ አጋጣሚ ከፍተኛውን ግዴታ ለማክበር እውነታውን የመናገሩ ግዴታ

[3] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 114:: ከ Saint Augustine, *Christian Doctrine, in A Select Liberary of the Nicene and Post-Nicene Fathers of the Christion Church,* ed. Philip Schaff, Vol. 2 (Grand Rapids: Eerdmans, 1956), 15. ላይ ጠቅሶ እንደ ጻፈው::

[4] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 114:: ከ Charles Hodge, *Systematic Thelogy* (reprint ed, Grand Rapids: Eardmans, 1952), 437. ላይ ጠቅሶ እንደ ጻፈው::

[5] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 114:: ከ Charles Hodge, *Systematic Thelogy* 440 ላይ ጠቅሶ እንደ ጻፈው::



ጠፍቶአል"[6]:: ሆጅ፣ "ለታላላቅ ግዴታዎች መታዘዝ፣ ታናናሾቹ ጸንተው እንዲቆሙ ማድረግ ነው"[7] ባይ ነው::

ሆጅ ተዋረዳዊ ፍጹማዊነት፣ "ከኅሊና ጋር እንኳ የተጣጣመ ነው" ይላል:: ለምሳሌ፣ የአንድን ሰው ሕይወት ለማዳን በሚደረገው ሂደት ውስጥ፣ ሰውየውን ልናሳምመው እንችላለን::

## የተዋረዳዊ ፍጹማዊነት አስተምህሮዎች

ሥልጣን ተዋረዳዊ ፍጹማዊነት መሠረቱን የጣለው ዋና ዋና በሆኑ ሦስት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቶች ላይ ነው::

### 1. ታላላቅና ታናናሽ የሆኑ ግብረገባዊ ፋይዳዎች አሉ

ሁሉም ግብረገባዊ ሕግጋት እኩል የሆነ ክብደት ያላቸውም:: ኢየሱስ ክርስቶስ፣ "በሕግ ያለውን ዋና ነገር" (ማቴ 23÷23)፣ "ከሁሉ ካነሱት ትእዛዛት" (ማቴ 5÷19)፣ "ማናቸዪቱ ትእዛዝ ታላቅ ናት?" (ማቴ 22÷36) በማለት ታላላቅና ታናናሽ የሆኑ ግብረገባዊ ፋይዳዎች እንዳሉ አሳይቶአል:: ኢየሱስ የይሁዳ ኀጢአት ታላቅ ("የባሰ") ለመሆኑ ለጲላጦስ ነግሮታል (ዮሐ 19÷11):: ትክክለኛ ከሆኑ ነገሮች (ፋይዳዎች) መካከል እንኳ፣ አንዱ ከሌላው የሚበልጥ ከሆነ (1ቆሮ 13÷13) እንዲያውም አንድ ዐይነት ከሆኑት መካከል እንኳ አንዱ ከሌላው እጅግ የሚሻል ከሆነ፣ በኀጢአት መካከል መበላለጥ (ልዩነት) እንዴት ላይኖር ይቻላል (ዮሐ 15÷13)?

እንደ ሥልጣን ተዋረዳዊ ፍጹማውያን፣ ሁሉም ኀጢአቶች እኩል ክብደት አላቸው የሚለው ትምህርት የመጣው ያዕቆብ 2÷10 ላይ ያለውን ትምህርት፣ ትክክል ባልሆነ መልኩ በመረዳት ነው "ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ፣ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል በሁሉ በደለኛ ይሆናል":: ክፍሉ ሁሉም ሕግ እኩል ክብደት ስላለው፣ ሁሉም ኀጢአት እኩል ነው የሚል ትምህርት የለውም:: የክፍሉ ትምህርት ትልቅም ሆነ ትንሽ ኀጢ አት፣ ሰዎችን ኀጢአተኛ በማድረግ ይኰንናቸዋል የሚል ነው::

በልብ መመኘት ከማመንዘር ጋር እኩል ነው (ማቴ 5÷28)፣ የሚለው አመለካከት የችግሩ ሌላ ምክንያት ነው:: ነገር ግን ጌታ በዚያው ስብከት ውስጥ (በተራራው ስብከት) ኀጢአት ሁሉ እኩል ነው የሚለውን አመለካከት ሲቃወም

[6] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 114:: ከ Charles Hodge, *Systematic Thelogy* 442 ላይ ጠቅሶ እንደ ጻፈው::

[7] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 114:: ከ Charles Hodge, *Systematic Thelogy* 441 ላይ ጠቅሶ እንደ ጻፈው::

እናያለን፤ እንዲያውም ኀጢአት ሦስት የተለያየ ደረጃ እንዳለው ይገልጻል (5÷22)። በገሐነብ የሚቀጣ ኀጢ አትና (ማቴ 5÷22፤ ሮሜ 2÷6፤ ራእ 20÷12) በሰማይ በተለያየ ደረጃ የሚያሽልምን (1ቆሮ 3÷11-12) እንዴት እኩል እናየዋለን? ይህ ኀጢ አት በተለያየ መጠን እንደሚቀጣ የሚያስተምር ነው። የአንዳንድ ክርስቲያኖች ኀጢ አት፣ ከማኅበር ምዕመናን ኅብረት ያስገልላል (1ቆሮ 5)፤ አንዳንዱ ኀጢአት ደግሞ በሞት ያስቀጣል (1ቆሮ 11÷30)፤ ይህ ኀጢአት ሁሉ እኩል ክብደት እንደሌላው የሚገልጽ ነው። እንዲያውም ይቅርታ ሊደረግለት የማይችል ኀጢአት እንዳለም ልብ ይሏል (ማር 3÷29)።

ኢየሱስ፣ ሕግ ዐዋቂው፣ "ከሕግ ማናቸዪቱ ትእዛዝ ታላቅ ናት?" ብሎ ሲጠይቀው (ማቴ 22÷34-35) የሰጠው ምላሽ፣ በግብረገባዊ ሕግጋት ውስጥ መበላለጥ እንዳለ የሚገልጽ ነው። ኢየሱስ፣ "ታላቂቱና ፊተኛዪቱ"፣ ከ"ሁለተኛዪቱ" እንደምትበልጥ የሳያል። ይህ የኢየሱስ ትምህርት በሌላም ስፍራ ተደግሞ እናነባለን፣ "ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤ ከእኔ ይልቅም ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ፣ ለእኔ ሊሆን አይገባውም" (ማቴ 10÷37)። ይህን እውነት ከተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችም ውስጥ ማግኘት ይቻላል (ምሳ 6÷16፤ 1ጢሞ 1÷15፤ 1ዮሐ 5÷16፤ ማቴ 5÷55)።

እንደ ሥልጣን ተዋረዳዊ ፍጹማውያን አቋም ሁሉም ኀጢአት እኩል አይደሉም፤ በግብረገባዊ ሕግጋትም መካከል ታላቅና ታናሽ ሕግ አለ።

## 2. ልናስወግዳቸው የማንችላቸው ግብረገባዊ ግጭቶች አሉ

ልናስወግዳቸው የማንችላቸው ግብረገባዊ ግጭቶች ስላሉ፣ ሁለት ሕግጋትን በአንዴ ልንታዘዝ አንችልም። የእዚህ አመለካከት ደጋፊዎች ለእዚህ አስተምህሮ አስረጅ ናቸው የተባሉትን ውስጣዊና (መጽሐፍ ቅዱሳዊና) መጫዊ ማስረጃዎችን እንመልከት።

የአብርሃምና የይስሐቅ ታሪክ (ዘፍ 22) ግብረገባዊ ግጭት በውል ይታይበታል። "አትግደል" የሚለው፣ አምላካዊ የሆነ ግብረገባዊ ሕግ ነው (ዘፀ 20÷13)፤ ነገር ግን አብርሃም ልጁን ይስሐቅን እንዲገድል በእግዚአብሔር ሲታዘዝ እንመለከታለን። አብርሃምም በትእዛዙ መሠረት ልጁን ለመግደል እንደ ቈረጠ፣ ከዐውዱ እንማራለን (እንዲያውም የዕብራውያን ጸሓፊ ይስሐቅ ቢሞት እንኳ፣ እግዚአብሔር ዳግም ሊያስነሣው እንደሚችል አብርሃም አምኖ እንደ ነበር ይገልጻል (ዕብ 11÷19)። ከዚህ ታሪክ የምንማረው በተመሳሳይ ጊዜና ሁኔታ ሁለት ሕግጋት



በአምላክ ልዩ ትእዛዝ ተጻርረው እንደ ቀረቡ እንዲሁም ታላቅ የሆነው ግብረገባዊ ትእዛዝ ከትንሹ ትእዛዝ ይልቅ ሲከበር እናያለን።

ይህ እውነት በሶምሶን ታሪክ ውስጥም በግልጥ የሚታይ ጒዳይ ነው። ምንም እንኳ ግድያ ወንጀል ቢሆንም፣ ሶምሶን ራሱን ለማጥፋት ያቀረበውን ጥያቄ እግዚአብሔር ሲቀበል እንመለከታለን (መሳ 16÷30)። "አትግደል" የሚለውን ሕግ የሰጠ አምላክ፣ ሶምሶን ራሱንም ሆነ ሌሎችን እንዲገድል ሲፈቅድለት (ጒልበት ሲሰጠው) እናያለን። ይህ ግጭት (ቅራኔ) ነው።

ዮፍታሔ በእግዚአብሔር ፊት የተሳለውን ስእለት ይሞላ ዘንድ (ሊተላለፈው የማይችለውን) በደል አልባ የሆነችውን ልጁን መሥዋዕት አድርጎ ማቅረቡ፣ ታላቅ የሆነውን ሕግ በመታዘዝ መለስተኛ የሆነውን ሕግ ሲጥስ እናያለን (መሳ 11)። ይህ

ግጭት (ቅራኔ) ነው። እንደ ተዋረዳዊ ፍጹማውያን ዮፍታሔ ለታላቂቱ ሕግ ተገዛ እንጂ፣ በደል አልባ የሆነችውን ሴት ልጁን በመግደል ኀጢአት አላደረገም።

ኢተጠራሽ ፍጹማውያን ኀጢአት ሊያመጣ (ሊያስከትል) የሚችለውን ስእለት የመፈጸም ግዴታ የለብንም፤ ስለዚህ ዮፍታሔ ልጁን በመግደል ስእለቱን መጠበቅ አልነበረበትም ባዮች ናቸው። ነገር ግን ቃለ እግዚአብሔር ዮፍታሔ ልጁን በመግደል ስእለቱን መፈጸሙ፣ ትክክል እንደ ነበር ይገልጻል። አንዳንዶች ዮፍታሔ መሥዋዕት ያደረገው ቊሳዊ አካሏን ሳይሆን፣ የጋብቻ ሕይወቷን ነው (ዘመኗን ሁሉ በድንግልናዋ እንድትኖር ነው) ባዮች ናቸው። ነገር ግን ይህን ትንተና ከቍጥር 31 አኳያ ሲታይ የሚያስሄድ አይመስልም "...ሊገናኘኝ ከቤቴ ደጅ የሚወጣው ማንኛውም ለእግዚአብሔር ይሆናል፤ ለሚቃጠልም መሥዋዕት አቀርበዋለሁ ብሎ ለእግዚአብሔር ስእለት ተሳለ"። የሚቃጠል መሥዋዕት ማቅረብ ሳያገቡ መኖር ሳይሆን፣ ተዘወትሮ ይደረግ እንደ ነበረው መግደል ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በመዋሸት ሰዎችን ከሞት ስላዳኑ ግለሰቦች ይናገራል። ዕብራውያን አዋላጆችንና (ዘፀ 1) ረዓብን (ኢሱ 2) በዚህ ስፍራ ልንዘክራቸው እንችላለን። እውነቱን ሳይናገሩ በዝምታ ማለፍ ሦስተኛ አማራጭ ሊሆን አይችልም፤ ዝምታ በጠያቂዎቹ (በገዳዮቹ) ዘንድ አዎንታዊ ምላሽ ስለማያገኝ፤ በሌሎች የፈሩት ግድያ በእነርሱም ላይ ሊደርስ ስለሚችል ነው። ነገር ግን የዕብራውያን አዋላጆችም ሆኑ ረዓብ፣ መለስተኛውን ኀጢአት (ውሸትን) በመምረጥ ከፍተኛውን ኀጢአት (ግድያን) አስቀርተዋል።

ተዋረዳዊ ፍጹማውያን መስቀል ላይ በተከናወነው የደኅንነት ሥራ ላይ እንኳ፣ ግብረገባዊ ቅራኔ ነበር ባዮች ናቸው። አንድ ሰው ባልሠራው ኀጢአት መቀጣት የለበትም፤ ነገር ግን ክርስቶስ ለኀጢአታችን ዋጋ ከፍሎአል (ተቀጥቶአል) (ኢሳ 53፤ 1ጴጥ 2÷24፤ 3÷15፤ 2ቆሮ 5÷21)። አንዳንዶች ኢየሱስ ለኀጢታችን ዋጋ የከፈለው ወዶና ፈቅዶ ነው በማለት ቅራኔውን ለማስታረቅ ይሞክራሉ። ነገር ግን አንድ ሰው ሌላውን ግለሰብ ራሱን እንዲያጠፋ ቢያስተምረው፣ ተማሪው ሰው ደግሞ እንደ ተማረው ራሱን ቢያጠፋ፣ ራሱን እንዲገድል ያስተማረው ሰው ከደሙ ንጹሕ ነው ማለት ነው። ምክንያቱም ራሱን የገደለው ሰው ራሱን ያጠፋው ወዶና ፈቅዶ ነውና!

በቃለ እግዚአብሔር ለመንግሥት በመታዘዝና ለእግዚአብሔር ሕግ በመገዛት መካከል ለበርካታ ጊዜያት የተነሣውን ግብረገባዊ ግጭት በስፋት ይገልጻል። ለምሳሌ ዕብራውያን አዋላጆች "ሕፃናት ወንዶችን ግደሉ» የሚለውን የፈርዖንን ትእዛዝ ተላልፈዋል (ዘፀ 1)፤ ወደ ባቢሎን የተወሰዱት የአይሁድ ምርኮኞች፣ ናቡከደነፆር ላቆመው ምስል አንሰግድም በማለት የንጉሡን ትእዛዝ ተላልፈዋል (ዳን 6)። ከላይ ባየናቸው ሁኔታዎች ውስጥ መፍትሔ ይሆን ዘንድ በሦስተኛነት ሊቀርብ የሚችል ሌላ አማራጭ የለም፤ የእግዚአብሔርን አልያም የነገሥታቱን ቃል ማክበር። "ለበላይ ባለ ሥልጣናት ታዘዙ" ያለው እግዚአብሔር "አምላክህን እግዚአብሔርን ብቻ አምልክ፤ ለእርሱም ስገድ" የሚል ትእዛዝ ሰጥቶናል። ከላይ ባየናቸው ግለሰቦች ሕይወት የታየው፣ ሁለት መለኮታዊ ትእዛዛት በአንድ ጊዜ ተግባራዊ ይሆኑ ዘንድ መከሠታቸው ነው።

## 3. ሊወገዱ ለማይችሉ አጣብቂኞች ተጠያቂ ልንሆን አይገባም

እግዚአብሔር ፍጹም ሊወገዱ ለማይችሉ ግብረገባዊ ቅራኔዎች ሰዎችን ተጠያቂ አያደርግም፤ ከፍተኛውን ሕግ (የሚበልጠውን ሕግ) እንዲከተሉ (እንዲተባበሩ) ያግዛቸዋል እንጂ። ይህን እውነት ለማስረዳት የሚያግዙ አመክንዮአዊ ማስረጃዎችን እንመልከት። አንደኛ እግዚአብሔር ለሰዎች የማይቻለውን ነገር እንዲያደርጉ እንዴት ትእዛዝ ይሰጣቸዋል (ባለማድረጋቸው እንዴት ተጠያቂ ያደርጋቸዋል)። መወገድ የማይችለውን ነገር ማስወገድ እንዴት ይቻላል? ሁለት ተቃራኒ ምግባሮችን በተመሳሳይ ጊዜ መከወን አይቻልም።

ሁለተኛ ግብረገባዊ ቅራኔዎች ውስጥ የገባ ሰው፣ ለታላቁ ሕግ መታዘዝ የሚችለው ታናሹን ሕግ ሲያፈርስ ብቻ ነው። ከላይ ያየናቸው ምሳሌዎች ሁሉ ይህን እውነት የሚያጠናክሩ ናቸው። ከወዳጁ ጋር በዐሥር ሰዓት ተገናኝቶ ለመጫወት ቀጠሮ ያበጀ ሰው፣ በምጥ ትሠቃይ የነበረችውን ጐረቤቱን ሆስፒታል ይዞ በመሄድ



የሴትየዋን ሕይወት ቢታደግ፣ ቀጠሮ ባለማክበሩ ሊኰነን አይችልም። ታላቁን ሕግ አክብ ሮአልና።

ሦስተኛ በመጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ተጻራሪ ግብረገባዊ ጥያቄዎች የቀረበላቸው ሰዎች፣ ትልቁን ሕግ በመከተላቸው በእግዚአብሔር ተሞግሰዋል። እግዚአብሔር ለአብርሃም አንድያ ልጁን እንዲሠዋለት በጠየቀው ጊዜ መታዘዙ (ዘፍ 22፤ ዕብ 11) እንደዚሁም ዳንኤልና (ዳን 6) ሦስቱ ዕብራውያን ወጣቶች፣ ለመንግሥት ሳይሆን ለእግዚአብሔር እንታዘዛለን ማለታቸው እግዚአብሔርን አስደስቶታል። እንዲያውም እግዚአብሔር በመረጡት ምርጫ ሲተባበራቸው ይታያል። የዕብራውያን አዋላጆች የንጉሡን ሕግ በመተላለፋቸው እግዚአብሔር ባርኮአቸዋል (ዘፀ 1)። ዳዊት እንዲሁም እርሱን ይከተሉ የነበሩ ሰዎች ቤተ መቅደሱ ውስጥ በመግባት የተቀደሰውን የመባ ኅብስት ቢሰርቁም (1ሳሙ 21÷1-6)፣ ክርስቶስ ኀጢአት ያለማድረጋቸውን ገልጾአል (ማቴ 12÷3-4)። እነዚህ ሰዎች ባልጠበቁአቸው (ተግባራዊ ባላደረጉአቸው) ግብረገባዊ ሕጋጋት ምክንያት፣ በአምላክ ሲኰነኑ ሳይሆን ሲደገፉ (ሲበረታቱ) ይታያል። ይህ እውነት ከዚህ ጋር ተዛማጅ በሆኑ ጕዳዮችም ላይ ተግባራዊ መሆን የሚችል ነው። ወላጆችም (ሉቃ 2÷41-42) ሆኑ እግዚአብሔር የሾማቸው ሹማምንት (ዘፀ 12፣ ሐሥ 4-5፣ ራእ 13) ይህንኑ እውነት ሊከተሉ ይገባል።

## ተዋረዳዊ ፍጹማዊነት ትክክል ነው

እንደ ተዋረዳዊ ፍጹማውያን አመለካከት፣ ተዋረዳዊ ፍጹማዊነት ፍጹም ትክክል ነው። ሊወገዱ የማይችሉ ግብረገባዊ ግጭቶች በሚከሠቱበት ጊዜ፣ አንድ ሰው ትልቁን ትእዛዝ ተግባራዊ እስካደረገ ድረስ፣ ትንሹን ትእዛዝ ለምን አልታዘዝህም (ተግባራዊ) አላደረግህም በሚል፣ በእግዚአብሔር ሊኰነን አይችልም። ሁለት መኪኖች በመገናኛ መንገድ ላይ እኩል ቢደርሱ፣ ትራፊኩ ቅድሚያ የሰጠው መኪና ቀድሞ የመሄድ ዕድል ያገኛል። ሁለቱም መኪናዎች እኩል መሄድ በፍጹም አይችሉም፤ አንዱ መቆም ሌላው ደግሞ ማለፍ አለበት። ልክ እንደዚሁ ሁሉ፣ አንድ ሰው በሁለት ሕጋጋት ምርጫ ውስጥ ቢሆን፣ ለታላቁ ሕግ (ከፍ ላለው ሕግ) በመገዛት ከአጣብቂኙ በድል ሊወጣ ይችላል።

## የተዋረዳዊ ፍጹማዊነት አካሄድ

እንደ ተዋረዳዊ ፍጹማውያን እግዚአብሔርን ውደድ የሚለው ቀዳማይ ሕግ ሲሆን፣ ጐረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ የሚለው ደግሞ የቀዳማዪቱ ሕግ ተከታይ ነው። ሁልጊዜ የመጀመሪያው ሕግ የሁለተኛው ሕግ የበላይ ነው።

## 1. እግዚአብሔርን መውደድ፣ ሰውን ከመውደድ ይበልጣል

ጌታ በግልጥ እንዳስተማረው እግዚአብሔርን ውደድ የሚለው ሕግ፣ "የመጀመሪያውና ከሁሉ የሚበልጠው" ሕግ ነው (ማቴ 22÷36-38)፡፡

## 2. እግዚአብሔርን መታዘዝ፣ መንግሥትን ከመታዘዝ በልጣል

ሹማምንት የሚሾሙት፣ ነገሥታት ነጋሢነታቸው የሚጸናው በእግዚአብሔር ነው (ነገሥታትን የሚሽመው እግዚአብሔር ነው)፡፡ ክርስቲያኖች ለበላይ ባለሥልጣን "ይገዙና" "ይታዘዙ" ዘንድ ታዘዋል፤ ክርስቲያኖች ለበላይ ባለ ሥልጣናት መታዘዝ የሚኖርባቸው ሹማምንቱ ክፉዎች ቢሆኑ እንኳ ነው (ሮሜ 13÷1-2፤ ቲቶ 3÷1)፡፡ እንዲያውም ጴጥሮስ መታዘዝ የሚኖርብን ለጌታ ስንል እንደ ሆነ ይገልጻል፣ "ስለ ጌታ ብላችሁ ለምድራዊ ባለ ሥልጣን ሁሉ ተገዙ" (1ጴጥ 2÷13)፡፡

ነገር ግን ለባለ ሥልጣናት የማንገዛባቸውና የማንታዘዝባቸው በርካታ ሁኔታዎች አሉ፡፡ እግዚአብሔርን ማምለክ ከማናቸውም ዐይነት የነገሥታት ሕግ ይበልጣል (ዳን 3)፡፡ ለእግዚአብሔር ያለንን የግል የጽሞና (የጸሎት) ጊዜ የሚገፋ ማናቸውም ዐይነት የመንግሥት ሕግጋት፣ በክርስቲያኖች ላይ ተግባራዊ መሆን አይችሉም (ዳን 6)፡፡ የወንጌልን ስብከት የሚከለክለውን የመንግሥት ሕግ አናከብርም (ሐሥ 4-5)፡፡ የጣዖት አምልኮን የሚያበረታታውን የበላይ ባለሥልጣናት ሕግ አንታዘዝም (ዳን 3)፡፡ በደል አልባ የሆኑ ሰዎች ይገደሉ የሚለንን ሕግ አንቀበልም (ዘፀ 1)፡፡ ጸልይ፣ እግዚአብሔርን አምልክ፣ ወንጌልን ስበክ ወዘተ የሚሉት ሕግጋት፣ ለበላይ ባለ ሥልጣናት ተገዛ ከሚለው ሕግ የሚበልጡ ናቸው፡፡

## 3. ምሕረት እውነትን ከመናገር ይበልጣል

ቃለ እግዚአብሔር፣ "በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር" (ዘፀ 20÷16) "...ውሸትን አስወግዳችሁ፣ እያንዳንዳችሁ ከባልንጀራችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ" (ኤፌ 4÷25) ይላል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ውሸት መናገርን ደጋግሞ ኰንኖታል (ምሳ 12÷22፤ 19÷5)፡፡ አንዳንዴ ሆን ተብሎ የተነገረ ውሸት፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተቀባይነትን አግኝቶ እናያለን፡፡

ረዓብ የእስራኤለን ሰላዮች ነፍስ መታደጓ፣ ከእምነት አበው ጐራ እንድትሰለፍ አድርጓታል (ዕብ 11)፡፡ አንደኛ ረዓብ ይህን ሥራ በመሥራቷ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በአንዳችም ስፍራ ሲኰንናት አንመለከትም፡፡ ሁለተኛ የሰላዮችን ሕይወት



ለማዳን መፈለጓ፣ እውነትን ከመናገር ይልቅ ለምሕረት ከፍተኛ ስፍራ መስጠቷን የሚያመለክት ነው፡፡ ሦስተኛ መጽሐፍ ቅዱስ፣ "...የላክናቸውን መልእክተኞች ስለሸሸገች፣ ጋለሞታዪቱ ረዓብ ከእርሷዋም ጋር በቤትዋ ውስጥ ያሉ ሁሉ ብቻ በሕይወት ይኖራሉ" (ኢሳ 6÷17) ይላል፤ ይህ ወሮታ የመጣው ባለሥልጣናቱን በማታለሏ ነው፡፡ ከዚህ የተነሣም እግዚአብሔር እንደ ባረካት እናያለን፡፡ የረዓብ ውሸት በእግዚአብሔር ላይ ያላትን እምነት ይፋ የምታደርግበት ሁኔታ ነው (ዕብ 1÷31፤ ያዕ 2÷25)፡፡

የዕብራውያን አዋላጆች የሕፃናቱን ሕይወት ለመታደግ ሲሉ የተናገሩት ውሸት፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ማግኘቱ ብቻ ሳይሆን፣ አዋላጆቹ ይህን በማድረጋቸው እግዚአብሔር ውለታቸውን እንደ ከፈለ እናያለን፣ "እግዚአብሔርም ለአዋላጆች መልካም አደረገላቸው፤ ሕዝቡም በዛ፤ እጅግም ጸና፡፡ እንዲህም ሆነ፤ አዋላጆች እግዚአብሔርን ስለፈሩ ቤቶችን አደረገላቸው" (ዘፀ 1÷20-21)፡፡ እግዚአብሔር የባረካቸው ስላሳዩት ምሕረት ነው፡፡

ምሕረት ከእውነት መብለጧ ብዙ ሊያስደንቀን አይገባም፡፡ ኮሪ ቴም ቡም በቤታቸው የተሸሸጉትን አይሁዶች ነፍስ የታደጉት፣ የናዚ የወታደሮችን በመዋሸት ነበር፡፡ ይህም መልካም እንጂ መጥፎ አልነበረም፤ የሰው ሕይወት ከማናቸውም ነገር በላይ ነውና፡፡

# 8

# ሥነ ምግባርን አስመልክቶ ውሳኔ ላይ የሚደረሰው እንዴት ነው?[1]

አንድ የሃያ ዓመት ኢትዮጵያዊ ማጅራት መቺዎች በተኰሱበት ጥይት ኸዱ ላይ ክፉኛ ቈስሎ ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ድንገተኛ ክፍል ይወሰዳል። ይህ ወጣት የሕክምና ኢንሹራንስ የለውም፤ እንዲሁም የሚሠራበት መሥሪያ ቤት ለሠራተኞቹ አንዳችም የሕክምና ክፍያ አይከፍልም። የሚኖርበት ቀበሌ ደግሞ ሥራ ላላቸው ሰዎች ነጻ ሕክምና እንዲያገኙ የትብብር ደብዳቤ አልጽፍም ባይ ነው። ይህ ወጣት በሆስፒታሉ ሆኖ ሕክምናውን የሚከታተልበት አንዳችም ገንዘብ ስላልነበረው የመጀመሪያ ርዳታ ከተደረገለት በኋላ፣ ሐኪሙ እቤቱ ሆኖ ሕክምናውን መከታተል ይችላል ስላሉ፣ ወደ ቤቱ ተወስዶ ሕክምናውን እዚያው ቤቱ ሆኖ እንዲከታተል ይደረጋል።

ይህ ወጣት በሆስፒታል በነበረበት ጊዜ የደም ምርመራ ወስዶ ኖሮ፣ በደሙ ውስጥ የኤድስ አማጪው ቫይረስ እንዳለበት ይረጋገጣል። ሐኪሙ ከሆስፒታል ወጥቶ ወደ ቤቱ ከመወሰዱ በፊት፣ ቊስሉ እየመረቀዘ መመረዝ (infection) እንዳያስከትል፣ ሥልጡን ነርስ እቤቱ ድረስ እየሄደች ቊስሉን እንድትቀይርለትና የጤናውን ሁኔታ እንድትከታተል ሐሳብ ያቀርባሉ። አሁን አገሪቱ ባለችበት ሁኔታ መንግሥት ወደየ ግለሰቦች ቤት የጤና ባለሙያዎችን በመላክ ነጻ ሕክምና አይሰጥም። ወጣቱም ሆነ የወጣቱ ቤተሰቦች፣ በሽተኛው ያለበ ስፍራ ድረስ እየሄደች እንዲህ ዐይነት ርዳታ ለምታደርግለት ነርስ የሚከፍሉት ገንዘብ የላቸውም።

ነገር ግን የ22 ዓምት ዕድሜ ያላት የሕመምተኛው ታላቅ እኅት፣ ወንድሟ ድኖ ከዐልጋው እስከሚነሣ ጊዜ ድረስ፣ የሚያስፈልገውን ርዳታ በማድረግና ቊስሉን በመቀየር ልታስታምመው ፈቃደኛ ትሆናለች። የእነዚህ ወጣቶች እናት ከአንድ ዓመት በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። አባትየው ደግሞ ሥራ የላቸውም። ይህቺ ወጣት፣ አባትዋን ጨምሮ ከሥሯ ያሉትን ወንድሞችዋንና እኅቶችዋን ታስተዳድራለች።

---

[1] ልዩ መግለጫ ካልተሰጠ በስተቀር ይህ ክፊል በአብዛኛው የተወሰደው ከ Scott B. Rae, *Moral Choices: An Introduction To Ethics* (Grand Rapids: Zondervan, 1985), 99-116 ላይ ነው። ለውይይት የቀረበውን ርእሰ ጒዳይ ጨምሮ አንዳንድ ሐሳቦች ተቀይረዋል።

ሕመምተኛው እኅትህ ትርዳህ በመባሉ ተቃውሞ ባይኖረውም፣ ኤች. አይ. ቪ. በደሙ ውስጥ እንደተገኘበት ግን እኅቱ እንድታውቅበት በፍጹም አይፈልግም። ከጋብቻ በፊትም የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደ ጀመረ ቤተሰቡ እንዲያውቅበት አይሻም፤ በተለይ አባትየው ይህን እንዲያውቁ በፍጹም አይፈልግም። ቤተ ሰቡ መጽሐፍ ቅዱስን የኑሮው መመሪያው አድርጎ የሚከተል ቤተሰብ ስለሆነ፣ እንዲህ ዐይነቱ ሁኔታ በቤተሰቡ ውስጥ መከሠቱ፣ ለቤተሰቡ ትልቅ ተስፋ መቊረጥ ሊያስከትል ይችላል።

ወጣቱ ለሐኪሙ ኤች. አይ. ቪ. በደሙ ውስጥ እንደ ተገኘበት የሚገልጽ አንዳች መረጃ፣ ለማንኛውም ሰው እንዳይሰጥ ጥብቅ ማሳሰቢያ ሰጥቶአል። ሐኪሙም ቢሆን፣ "የበሽተኞች ምስጢር መጠበቅ አለበት" ለሚለው የሕክምና ሥነ ምግባር ያደረ ሰው ነው። በተለይ ደግሞ ኤች. አይ. ቪ./ኤድስን በተመለከተ ያለው የምስጢር አጠባበቅ ጉዳይ፣ እጅግ ጠንካራ ኀላፊነት የሚሻ መሆኑን ብዙዎችን የሚያግባባ ጉዳይ ነው። በተለይ ይህ ቤተሰብ ጥብቅ የሆነ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር መከተሉ ወጣቱ ያለውን ሁኔታ ይፋ ባደርግ የቤተሰቤ ልብ ክፉኛ ይሰበራል የሚል ግምት እንዲያድርበት አድርጎታል። በአንጻሩ ደግሞ የታማሚው እኅት ወንድሟን በዐልጋው ላይ ለማስታመም እንዲሁም የቊስሉን ጨርቅ በየጊዜው መቀየር ፈቃደኛ መሆኗ ከቊስሉ ጋር ባላት ንክኪ በኤች. አይ. ቪ. የመጋለጥ ዕድል ሊገጥማት ይችላል። ወንድሟን ለማስታመም ፈቃደኛ መሆኗ በከፍተኛ ጥንቃቄ ካልታገዘ በቀር፣ ሁኔታው የእርሷንም ሕይወት መጠየቁ አይቀርም። ታዲያ ይህች ወጣት ጥንቃቄ ታደርግ ዘንድ ስለ ወንድሟ ሕመም ግንዛቤ ሊኖራት አይገባም?

እርስዎ ሐኪም ቢሆኑ በእንዲህ መሰሉ ሁኔታ ውስጥ ምን ያደርጋሉ? ሕመምተኛው በምስጢር ይያዝልኝ ያለውን ጉዳይ ይፋ በማውጣት፣ አስታማሚዋ ወንድሟን በምታስታምምበት ጊዜ ከፍተኛ ጥንቃቄ በማድረግ ሕይወቷን እንድትጠብቅ ይነግሯታል ወይስ በበሽተኛው ላይ የሚደርስበትን መገለልና መድሎ ለመከላከል እንዲሁም የበሽተኞችን ምስጢር እንዲጠበቅ የሚያዘውን ሥነ ምግባር (በሕክምና ሙያ ውስጥ በተለይ የሕሙማንን ምስጢር መጠበቅ ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል) በማክበር የበሽተኛውን ምስጢር ይጠብቃሉ? በአጠቃላይ ምን መደረግ አለበት የሚለውን ጉዳይ እንዴት ይወሰናሉ? ሥነ ምግባራዊ ውሳኔ ማድረግ አስፈላጊ የሆነውን ያህል ወደ ግብረገባዊ ውሳኔ የሚደረስበትን ሂደት ማወቅ አስፈላጊ ነው። በዐጸደ ሥጋ ስንኖር የሚገጥሙን ግብረገባዊ ውሳኔዎች በርካታ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን አንዳንዶቹ ደግሞ ውስብስቦች ናቸው። ታዲያ ወደ ውሳኔ ከመደረሱ በፊት ርእሰ ጉዳዩን በቅጡ ማጤን ማስፈለጉ የሚያግባባን ጉዳይ ቢሆንም፣ ርእሰ ጉዳዩን በቅጡ መርምሮ ወሳኔ ላይ ለመድረስ፣ መጀመር ያለብን ከየት ነው የሚለው ጉዳይ ግን የብዙ ሰዎች ጥያቄ ነው። ከዚህ በመቀጠል ለውሳኔ የሚረዱ አንዳንድ ነጥቦችን ለማየት እንሞክራለን።



# ግብረገባዊ ወሳኔ ላይ ከመድረሳችን በፊት ልንወስዳቸው የሚገቡ ርምጃዎች

ግብረገባዊ ውሳኔዎችን ከመወሰናችን በፊት፣ ልንወስዳቸው የሚገቡን እርምጃዎች ከዚህ ቀጥለን እንመለከታቸዋለን። አንባቢው ልብ እንዲለው የምንፈልገው ቊም ነገር ግን ይህ አካሄድ ብቸኛ መንገድ ነው የሚል ግምት የለንም። ይህንንም አቅጣጫ የተከተለ ሰው ወደ ትክክለኛው ውሳኔ መድረሱ አይቀሬ ነውም አንልም። ነገር ግን እንዚህ ነጥቦች ግብረገባዊ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ዕገዛ ይኖራቸዋል የሚል ግምት አለን። ይህ ወደ ውሳኔ የሚያደርስ አካሄድ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና ጋር የተጣመረ ቢሆንም፣ ክርስቲያን ያልሆኑም ሰዎች ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

በበርካታ ሥነ ምግባራዊ ጉዳዮች ላይ ቀጥተኛ ወሳኔ መስጠት የሚያስቸግረን፣ መጽሐፍ ቅዱስ እያንዳንዱን ርእሰ ጉዳይ በቀጥታ ስለማይመልስልን ነው። ነገር ግን አጠቃላይ የሆኑትን የመጽሐፍ ቅዱስ መርሖች በመጠቀም ርእሰ ጉዳዮቹን ለመፍታት እንሞክራለን። ነገር ግን የትኛው አጠቃላይ መርሖ የትኛውን ርእሰ ጉዳይ ያወሳል በሚለው ግን፣ አብዛኛውን ጊዜ አለመግባባት ይኖራል። ለምሳሌ ከላይ ያየነውን ርእሰ ጉዳይ በተመለከተ፣ አንድ ሐኪም በሽተኞቹን ከጥቃት ስለመጠበቅና ርኅራኄ ስለማሳየት የሚገልጸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሖ በመጠቀም፣ ኤች. አይ. ቪ. በደሙ ውስጥ የተገኘበትን ሰው ምስጢር መጠበቅ እንዲሁም ያንኑ የርኅራኄ መርሖ በመጠቀም እኅቲቱ በኤች. አይ. ቪ. እንዳትያዝ ጥበቃ ማድረግ ይኖርበታል።

አንዳንዴ ግብረገባዊ ውሳኔዎችን ለመወሰን የሚያስቸግረን አንዱ ምክንያት፣ ***ልዩ መገለጥ*** የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስን *ከአጠቃላይ* ***መገለጥ*** ጋረ አቀናጅተን ያለመመልከታችን ነው። ከዚህ በመቀጠል የምናየው የውሳኔ አካሄድ፣ ልዩ መገለጥንና አጠቃላይ መገለጥን ያጣመረ ስለሆነ፣ ሰዎች ግብረገብን አስመልክቶ የሚገጥማቸውን ግራ መጋባት ሊያቃልል ይችላል።

በመጀመሪያ ለውሳኔ ይጠቅማሉ የምንላቸውን ሰባት ነጥቦች ከተመለከትን በኋላ፣ እነዚህ ነጥቦች ከላይ ያየነውን ርእሰ ጉዳይ እንዴት ሊፈቱልን እንደሚችሉ እንቃኛለን።

## 1. መረጃዎችን መሰብሰብ

አብዛኛውን ጊዜ ግብረገባዊ ርእሰ ጉዳዮችን ለመፍታት ጠቃሚ ከሆኑት ነጥቦች መኻል አንደኛው፣ ርእሰ ጉዳዩን ግልጽ በሆነ ሁኔታ ማብራራት ነው። በተቻለ መጠን አስፈላጊ (ጠቃሚ) የሆኑት መረጃዎች ሁሉ መሰብሰብ ዐይነተኛ ነገር ነው። ርእሰ ጉዳዩን ለመመርመርና ለመመዘን አስፈላጊ ናቸው የምንላቸውን መረጃዎች ሁሉ

ማወቅ ይኖርብናል:: ስለዚህ የበሰለ ሥነ ምግባራዊ ብያኔ ለማካሄድ አንድ ሰው የሚከተሉትን ሁለት መሠረታዊ ጥያቄዎች መጠየቅ ይኖርበታል—የምናውቀው ነገር ምንድን ነው? እንዲሁም ማወቅ የሚኖርብንስ ነገር ምንድን ነው?

## 2. ሥነ ምግባራዊ ርእሰ ጉዳዩን መወሰን

ሥነ ምግባራዊ ርእሰ ጉዳዮች በፍላጎት ወይም በመልካምነት ተነጻጽረው መቀመጣቸው ርእሰ ጉዳዩን ያወሳስቡታል:: ለምሳሌ:- ከላይ የተመለከትነው ኤች. አይ. ቪ. በደሙ የተገኘበት ወጣት፣ ፍላጎት ከእንቱ ፍላጎት ጋር ተነጻጽሮአል:: የእርሱ ምስጢር መጠበቁ እርሷ ከኤች አይ ቪ ኤድስ ያለመያዝ ከመፈለጓ ጋር ተነጻጽሮአል::

## 3. ከርእሰ ጉዳዩ ጋር የሚሄደው መርሖ የትኛው እንደ ሆነ መለየት

የተወሰነ የግብረገብ ሕግ ወይም መርሖ፣ ለተነጻጸሩት ግብረገባዊ ጉዳዮች መሠረት ነው:: ይህን መርሖ በወል መለየቱ እንዲሁም የትኛው መርሖ ከየትኛው መርሖ የበለጠ ነው የሚለውን ማወቁ ትክክል ነው (በግብረገባዊ ፍጹማዊነት ሥር "ተዋረዳዊ ፍጹማዊነት" የሚለውን ክፍል ይመለከቷል):: በተለይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ መርሖች ትልቅ ክብደት ሊሰጣቸው ይገባል፤ ምክንያቱም ርእሰ ጉዳዩን በተመለከተ ያለው መርሖ፣ ከወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ወይም ከተፈጥሮ ሕግ (Natural Law) የተቀዳ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን ክብደት ልንሰጠው የሚገባን ለመጽሐፍ ቅዱሳዊው ሕግ ነው::

## 4. አማራጭ መፍትሔዎችን መዘርዘር

ሥነ ምግባራዊ ርእሰ ጉዳዮችን አስመልክቶ ለምንወስዳቸው እርምጃዎች፣ የመፍትሔ አማራጭ ይሆናሉ ብለን የምንገምታቸውን ነገሮች ሁሉ፣ ዐቅም በፈቀደ መጠን መዘርዘር ያስፈልጋል:: የዝርዝር መጠናችንን ባበራከትን መጠን፣ ወደ እውነታው የበለጠ እንድንቀርብ ይረዳናል::

## 5. አማራጭ መፍትሔዎችን ከመርሖች ጋር ማነጻጸር

በዚህ ስፍራ ማድረግ የሚኖርብን ነገር አማራጭ የሚባሉትን መፍትሔዎች እየቀነሱ በመሄድ፣ የተሻለውን አማራጭ ነቅሶ ማውጣት ነው:: አማራጮቹን የምናወዳድረው ከርእሰ ጉዳዩ ጋር ተዛማጅነት ካላቸው መርሖች ጋር ነው:: በዚህ ጊዜ ከሞላ ጎደል ርእሰ ጉዳዩ መልስ (ውሳኔ) ያገኛል:: ምክንያቱም አማራጭ ናቸው



የተባሉት መፍትሔዎች ሁሉ እየተቀነሱ አንድ ብቸኛ መፍትሔ ይቀራል:: ነገር ግን በዚህ ስፍራ ርእሰ ጉዳዩ መፍትሔ የማያገኝ ከሆነ፣ በተቀሩት ሁለት ነጥቦች ርእሰ ጉዳዩን መመርመር ያስፈልጋል:: ነገር ግን ቢያንስ የተወሰኑት የመፍትሔ አማራጮች እዚህ ስፍራ ላይ ይቀነሳሉ::

## 6. የሚያስከትለውን ውጤት መመርመር

የምንወስዳቸውን እርምጃዎች ወይም የምንወስናቸውን ውሳኔዎች፣ የሚያስከትሉትን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ውጤት መመርመር ይኖርብናል:: አዎንታዊ ውጤት የሚያመጡት አሉታዊ ውጤት ከሚያስከትሉት ይልቅ ጠቀሜታ አላቸው::

## 7. ውሳኔ ላይ መድረስ

ግብረገባዊ ርእሰ ጉዳዮችን ለመወሰን የምንሄድባቸው ጉዞዎች አድካሚ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፣ ውሳኔውን ለማስተላለፍ እንዲሁም የተወሰነውን ውሳኔ ለመቀበል አስቸጋሪ የሚሆንበት ጊዜ አለ:: የዚህ ዋነኛ ምክንያቱ የምንወስናቸው ግብረገባዊ ውሰኔዎች የራሳቸው የሆነ አሉታዊ ውጤት ሊኖራቸው ይችላልና ነው:: ነገር ግን እዚህ ቦታ ስንደርስ መወሰን የግድ ይሆናል::

## እነዚህን መርሖች እንዴት እንጠቀምባቸው?

እነዚህን መርሖች የምንመለከተው በምዕራፉ መግቢያ ላይ ያቀረብነውን ታሪክ መሠረት አድርገን ነው:: በዚህ ሂደት ውስጥ ግልጽ ሳይሆኑ ያለፉት ነጥቦች ግልጽ እየሆኑ ይሄዳሉ::

### 1) መረጃዎችን መሰብሰብ

ከርእሰ ጉዳዩ ጋር ተዛማጅ የሆኑት እውነታዎች የሚከተሉት ናቸው፤

- ወጣቱ የግብረ ሥጋ ግንኙነት አድርጓል፤ ኤች. አይ. ቪ. በደሙ ውስጥ ተገኝቶአል::
- ኸዱን በጥይት ተመትቶ ክፉኛ ቈስሎአል:: የመጀመሪያ ርዳታ ከተደረገለት በኋላ እቤቱ ሆኖ ሕክምናውን እንዲከታተል ተደርጐአል::
- ከጋብቻ በፊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ ለወጣቱ ቤተ ሰብ እጅግ በጣም አስነዋሪ ነገር ነው::

- ወጣቱ ኤች. አይ. ቪ. በደሙ ወስጥ እንደተገኘበት ሐኪሙ ለማንም ሰው እንዳይነግሩበት፣ ጉዳዩ በጥንቃቄ በምስጢር እንዲያዝለት ጠይቆአል።
- ወጣቱ ከጋብቻ በፊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረጉ ቤተሰቦቹ እንዳይሰሙ እንዲሁም ኤች. አይ. ቪ. እንዳለበት ከታወቀ መድሎና መገለል ይደርስብኛል የሚል ፍራቻ አለው።
- ገንዘብ ስለሌለው በሆስፒታል ሆኖ መታከም፣ እንዲሁም በቤቱ ውስጥ የምትከታተለውና ቁስሉን የምትቀይርለት ነርስ መቅጠር አልቻለም።
- መንግሥት የጤና ባለሙያዎችን ግለሰቦች ቤት እየላከ በሽተኞችን እንዲከባከቡ አያደርግም።
- የሕመምተኛው እኅት ወንድሟን በቤት ውስጥ ለማስታመም ፍቃደኛ ነች፤ እንዲሁም ቤተሰቡን በሚያስፈልገው ሁሉ በመርዳት ላይ ትገኛለች።
- ወጣቱ በደሙ ውስጥ ኤች. አይ. ቪ. እንደ ተገኘበት እኅቱ እንደትሰማ አይፈልግም።
- ቁስሉን የምታጥብለትና የቁስሉን ጨርቅ የምትቀይርለት እኅቱ ናት። ከደም ጋር ባላት ንክኪ በኤች. አይ. ቪ. የመያዝ ዕድል ሊያጋጥማት ይችላል።

## 2) ሥነ ምግባራዊ ርእሰ ጉዳዩን መወሰን

በዚህ ቦታ የተነጻጸረው የአስታማሚዋና የሕመምተኛው ፍላጎት ነው። ሁለቱም ችግር እንዳያገኛቸው ይፈልጋሉ። ሕመምተኛው በኤች. አይ. ቪ. መያዙና ከጋብቻ በፊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመጀመሩ ምክንያት፣ ቤተ ሰቦቹም ሆኑ ማኅበረሰቡ የሥነ ልቡና ጉዳት እንዳያመጡብት ይሻል። ይህም ሁኔታ ነው ወጣቱ ጉዳዩ በምስ ጢር እንዲያዝለት ሐኪሙን በመጠየቁ፣ ሐኪሙ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንዲገባ ያደረገው። ይህ ጉዳይ የበሽተኛውን ምስጢር በመጠበቅና አስታማሚዋን የሕይወት ዋጋ ሊያስከፍላት የሚችለውን ሁኔታ በመደበቅ ረገድ ግጭት ተፈጥሮአል።



## 3) ከርእሰ ጉዳዩ ጋር የሚሄደው መርሖ የትኛው እንደ ሆነ መለየት?

በዚህ ስፍራ፣ ሐኪሙ የሕመምተኛውን ፍላጎት ይጠብቅ ወይስ የአስታማሚዋን ሕይወት ይታደግ የሚለው ነጥብ ነው ቅራኔውን የፈጠረው። ሐኪሙ በሁለቱም ላይ ጉዳት እንዳይደርስባቸው የማድረግ ሥነ ምግባራዊ ኀላፊነት አለበት። ሕመምተኛው የጤና ሁኔታውን የሚገልጽ መረጃ ለማንም እንዳይነገርበት የመጠየቅ መብት አለው። በተለይ ደግሞ መጠበቅ ያለበት መረጃ እርሱን የሚያስጠቃው ከሆነ፣ መረጃዎቹ ሁሉ በጥንቃቄ መያዝ አለባቸው። በአንጻሩ ደግሞ ሐኪሙ ከሕመምተኛው ጋር ንክኪ ያላቸውን፣ በተለይም ደግሞ ከበሽተኛው ጋር ካላቸው ንክኪ የተነሣ ሕይወታቸውን አደጋ ውስጥ የሚጥልባቸው ሰዎች መኖራቸውን ካወቀ፣ ሁኔታውን በመግለጽ እነዚህን ሰዎች የማስጠንቀቅ ኀላፊነት አለበት።

ግብረገባዊ ውሳኔዎችን ለማካሄድ ከሚያስቸግሩ ምክንያቶች መኻል፣ ከርእሰ ጉዳዩ ጋር ተዛማጅነት ላላቸው መርሖች የምንሰጠው ክብደት ነው። ለጤና ባለሙያዎች የሕመምተኞቻቸውን ምስጢር መጠበቅ ፍጹም የተቀደሰ ተግባር ነው። በርካታ ሐኪሞች የሕመምተኛውን ምስጢር መጠበቅ፣ ሕመምተኛው በሐኪሙ ላይ እምነት እንዲኖረው ያደርገዋል፤ ይህ ደግሞ ሕክምናውን እስከ መጨረሻው ድረስ እንዲከታተል ያስችለዋል ሲሉ ይሞግታሉ። ነገር ግን ምስጢርን መጠበቅ የሌላውን ሕይወት አደጋ ላይ የሚጥለው ከሆነ፣ ምስጢሩ መጠበቅ አለበት የሚለው ጉዳይ የሰዎችን ሕይወት ከመታደግ ሕግ ያነሰ ስለሆነ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል። ለምሳሌ አንድ የሥነ ልቡና ሐኪም የአእምሮ ሕመም ያለበት አንድ ሕመምተኛ፣ ሚስቱን ሊደበድባት ወይም ሊገላት ይችላል የሚል እምነት ካደረበት፣ ይህን ጉዳይ ለሚስትየው የመግለጽ ሕጋዊም ሆነ ግብረገባዊ ግዴታ አለበት። በእንዲህ ዐይነቱ ሁኔታ ውስጥ፣ የሕመምተኛውን ምስጢር መጠበቅ የሌሎችን ሰዎች ሕይወት አጣብቂኝ ውስጥ የሚጥለው ከሆነ፣ ምስጢሩ ከመጠበቁ ይልቅ ምስጢሩ መገለጡ የሰዎችን ሕይወት ስለሚታደግ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል።

በዚህ ቦታ የተነጻጸሩት መርሖች ምስጢርን መጠበቅና የሌላውን ሕይወት ማዳን የሚሉት ናቸው። ሚዛን ሊደፋ የሚገባው ሕይወትን ማዳን እንጂ ምስጢርን መጠበቅ አይደለም።

## 4) አማራጭ መፍትሔዎችን መዘርዘር

በታሪኩ ውስጥ የተጠቀሰውን ችግር ለመፍታት፣ በርካታ አማራጮች ሊቀርቡ ይችላሉ። ነገር ግን ሊቀርቡ ከሚችሉት አማራጮች ሁሉ፣ ብዙ ሊያከራክር የሚችለው

ምስጢሩ ለአስታማሚዋ ይገለጽ ወይስ ምስጢሩ ለሕመምተኛው ይጠበቅ የሚሉት ናቸው:: የመጀመሪያው አማራጭ የእኅቲቱን ሕይወት መታደግ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ሕመምተኛው መደሉና መገለል እንዳይደርስበት ጥበቃ ማድረግ ነው::

ምናልባት ሐኪሙ አስታማሚዋ ቊስሉን በምትቀይርበት ጊዜ ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ እንድታደርግ በደፈናው ቢገልጽላት ይሻላል የሚል አማራጭ ሊመጣ ይችላል:: ነገር ግን አስታማሚዋ ይህን ዐይነት ጥንቃቄ ለምን ያስፈልጋል በላ ብትጠይቅ የሐኪሙ ምላሽ ምን ሊሆን ይችላል የሚለውን ጥያቄ አይመልስም:: እንደ አማራጭ መቅረብ የሌለበት ሌላው ጒዳይ፣ ሕመምተኛው ራሱ ለእኅቱ ሁኔታውን ይንገራት የሚለው ነው:: ምክንያቱም ወጣቱ ሁኔታው ለእኅቱ እንዲገለጽ በፍጹም አይፈልግም የሚለው ጒዳይ ከመጀመሪያውም ስለተገለጸ::

## 5) አማራጮ መፍትሔዎችን ከመርሖች ጋር ማነጻጸር

አስታማሚዎች የሚያስታምሙትን በሽተኛ በተመለከተ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው የሚለው ጒዳይ እዚህ ቦታ ላይ የቀረበችውን አስታማሚ በተመለከተ ሚዛን የሚደፋ አይደለም:: እንዲያውም ጥንቃቄውን አበራክተንና ለጥንቃቄው ትልቅ ትኲረት እንዲሰጥ በገለጽን ቊጥር አስታማሚዋ የበለጠ ጥያቄ እንድትጠይቅ ሊቀሰቅሳት ይችላል::

## 6) የሚያስከትለውን ውጤት መመርመር

የተለያዩ አማራጮች የሚያስከትሉትን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ውጤት መመርመር:: እንዲሁም አዎንታዊ የሆነው ውጤት ምን ዐይነት ወጤት ያስከትላል የሚለውን ጒዳይ አሉታዊ ውጤቱስ ምን ያህል ጥልቅ ሊሆን ይችላል የሚለውን ማገናዘብ ይኖርብናል::

ለምሳሌ:- የበሽተኛው እኅት ወንደሟ በኤች. አይ. ቪ. መያዙን ብታውቅ የሚከትሉት ሁኔታዎች ሊከሠቱ ይቻላሉ:-

- ○ ወንድሟን በምታስታምምበት ጊዜ ከፍተኛ ጥንቃቄ ስለምታደርግ በኤች. አይ. ቪ./ኤድስ የመያዝ ዕድሏ በከፍተኛ መጠን ይቀንሳል:: ይህም ሁኔታ በገዳይ በሽታ እንዳትያዝ ያደርጋታል::
- ○ ወጣቱ የፈራው መድሉና መገለል ሊገጥመው ይችላል:: የቤተሰቡ ልብ ክፉኛ ይሰበራል:: ወጣቱ ምስጢሩ ስላልተደበቀለት ሐዘን ይሰማዋል:: በዚህም የወጣቱ ሥነ ልቡና ይጐዳል::



- ○ ወጣቱ በሐኪሙ ላይ ያለው ተአማኒነት ይሸረሸራል:: ምናልባትም ከተደረገበት ነገር የተነሣ ለበቀል ሊነሣሣ ይችላል::

አስታማሚዋ የሕመምተኛው ሁኔታ ባይነገራት፣ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሊከሠቱ ይችላሉ:-

- አስታማሚዋ የወንድሟ በሽታ ምን እንደ ሆነ በትክክል ስለማታውቅ፣ ለጒዳዩም የሚገባውን ዐይነት ጥንቃቄ ስለማታደርግ ለበሽታው በመጋለጥ ሕይወቷን ልታጣ ትችላለች:: የመያዝ ዕድሏ ምን ያሕል ነው የሚለው ጒዳይ ሊያከራክር ይችላል፤ ነገር ግን በቫይረሱ በፍጹም መያዝ አትችልም ማለት ግን አይቻልም:: በቫይረሱ ከተያዘች ግን የምትያዘው በገዳይ በሽታ እንደ ሆነ ልብ ይሏል::
- ሕመምተኛው ከጋብቻ በፊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት መጀመሩም ሆነ በኤች. አይ. ቪ. መያዙ አይታወቅም:: ቢያንስ ቫይረሱ ወደ ኤድስ ተለውጦ ጥቃት እስከሚጀምርበት ጊዜ ድረስ ጒዳዩ ምስጢር ሆኖ ሊቆይ ይችላል::
- ምስጢሩ በመደበቁ የበሽተኛውና የሐኪሙ ግንኙነት እንዳማረበት ይዘልቃል::
- ሕመምተኛው ለበቀል የሚያነሣሣው ነገር አይኖርም::

## 7) ውሳኔ ላይ መደረስ

በዚህ ዐይነት ሁኔታ ውስጥ ምን ዐይነት ውሳኔ ይወስናሉ? የትኛው ግብረገባዊ መርሖ ነው ሚዛን ሊደፋ የሚችለው? ሌላ አማራጭ መፍትሔ አልዎት? የትኛው አማራጭ ነው የበለጠ ጒዳት የሚያስከትለው?

# 9

## ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር፣ መጽሐፍ ቅዱስና የትርጓሜ መርሖች*

ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ሲጠየቅ የነበረና ከዚህ ርእሰ ጉዳይ ጋር የሚዛመድ አንድ ጥያቄ አለ:: ይኸውም ሥነ ምግባራዊ መርሖችን መቅረጽ እንችላለን ወይ? ብዙ ከመሄዳችን በፊት ገና ከጠዋቱ መልሳችን ከቶ አይቻልም ነው:: ምክንያቱም ፈጣሪና ፍጡር ወይም አምላክና ሰው ባሉበት ዓለም ውስጥ ምግባራዊ ደንቦች "ራስ ገዝ" ወይም "ሰው ሠራሽ" ሊሆኑ አይችሉም:: በራሳቸው የሚኖሩ ወይም በሰው የሚቀመሩ ምግባራዊ ደንቦች የሉም:: በአንድ የተወሰነ ኅብረተሰብም የሚደነገጉ አይደሉም:: ምግባራዊ ደንቦች አምላክ ገዝ ወይም አምላክ ሠራሽ ናቸው[1]:: ከሰው በፊት ለሰው የሚበጀውን ነገር የተናገረው እግዚአብሔር ነውና (ዘፍ 2÷16-17):: በመሆኑም የእግዚአብሔር ሕግ ከሰው ሕግ በላይ ነው:: ለሰው ሕግ መሠረቱም ሆነ መርሑ የእግዚአብሔር ሕግ ነው:: እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ለእስራኤል ሕዝብ ሕጉን ሲሰጥ፣ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ኪዳን ተጋባ፤ በዚህም እስራኤልም ብሔራዊ ሕይወቷን በእግዚአብሔር ምግባራዊ ሕግ ለመምራት ውል አደረገች:: ወደ አዲስ ኪዳን ስንመጣ ደግሞ ኢየሱስ የአዲሱ መሲሐዊ ኅብረተሰብ ማለትም የቤተ ክርስቲያን ሕግ ሰጪ ሆኖ እናገኘዋለን:: ስለዚህ መሲሐዊቷ ኅብረተሰብ መኖር ያለባት ክርስቶስ እንደኖረው ነው::

### 1. ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርና መጽሐፍ ቅዱስ

እግዚአብሔር ሰውን "በመልኩና በአምሳሉ" ከፈጠረ በኋላ፣ እንዳሻው እንዲኖር አልተወውም:: ይልቁንም በየጊዜው ለሕይወቱ መመሪያ ይሰጠው ነበር:: ከአዳም ጀምሮ በክርስቶስ የመጨረሻውን የሕይወት መርሕ/ዘይቤ እስከ ሰጠን ጊዜ ድረስ በየዘመኑ የሰው ልጆች እምነታቸውን፣ ሕይወታቸውንና እርምጃቸውን የሚቀርጹበት መርሕ/ሕግ ይሰጣቸው ነበር:: እነዚህ መርሖች/ሕጎች ደግሞ በየጊዜው እየተጻፉ ለተከታዩ ትውልድ እንዲተላለፉ ተደርጓል:: አሁን በጥቂቱ ለመወያየት የምንፈልገው፣ ይህ በየጊዜው እየተጻፈ ለመጪው ትውልድ የተላለፈው ቃል

---

* ይህን ክፍል ያዘጋጀው ወንድም ምኒልክ አስፋው ነው::

[1] Arthur F. Holmes, *Ethics: Aproaching Moral Decisions* (Downers Grove: Inter Varsity Press, 1984), 102.

(በመደበኛው አጠራር መገለጥ) ምግባራዊ ደንቦችን በተመለከተ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ምንድን ነው? የሚለውን ይሆናል::

ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን ለመወሰን መጽሐፍ ቅዱስ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው:: ሥነ ምግባር፣ መልካሙ የቱ ነው? ትክክሉ የቱ ነው? ባንጻሩም እኩዩ የቱ ነው? ሐሰቱስ /ስሕተቱስ/ የቱ ነው? ሊሚሉት ጥያቄዎች መልስ የሚፈልግ የነገረ መለኮት ዘርፍ ነው:: እንግዲህ ሥነ ምግባር፣ ለእነዚህ ጥያቄዎች የተሰጡትን አማራጭ አመለካከቶች ይመዝናል፤ ምግባራዊ ዕውቀቶች የምናገኝበትን መንገድ ይተልማል፤ ለምን መልካም ባሕርያትን መላበስ እንዳለብን ጥያቄ ይጠይቃል:: ታዲያ ይህን በሚያደርግበት ጊዜ መልስ ፍለጋ የሚሄደው ወደ ሰዎች አይደለም፤ ወደ እግዚአብሔር እንጂ! ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር መርሖቹን በሙሉ የሚቀዳው ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው:: ምክንያቱም ሌሎች ምንጮች ውሃውን ሊያጨቀዩት ይችላሉ:: ሥነ ምግባራዊ ደንቦችን በምንቀርጽበት ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ቁልፍ ሚና አለው::

አንደኛው፣ ምግባራዊ ደንቦች ነገረ መለኮታዊ መሠረት እንዲኖራቸው ያደርጋል[2]:: የተጠራነው በእግዚአብሔር መንገድ እንድንጓዝ ነው፤ ፈቃዱን እየለየን እንድንኖር ነው:: እርሱ ፈጣሪ ከሆነ፣ (ዘፍ 1÷27-30) ሕግ ሰጭም እርሱ ነው (2÷15-17)፤ ወደ ህልውና የመጣነው በእርሱ ከሆነ፣ መርሕ የሚሰጠንም እርሱ ነው (ማቴ 5÷17-20፤ ዮሐ 15÷12-17፤ 1ዮሐ 2÷1-6):: እንዴት መኖርና እንዴት ማሰብ እንዳለብን ሊነግረን መብት አለውና::

ሁለተኛው፣ እግዚአብሔር ለሥነ ፍጥረቱ ያለውን ዐላማ እንድንገነዘብ ያደርጋል[3]:: ይህ ዓለም ሥርዐተ ቢስ ሆኖ እንዲኖር የተፈጠረ ዓለም አይደለም:: በዚህ ዓለም ውስጥ ሥርዐት አልበኛነት ስፍራ የሌለው፣ ዓለሙ የእግዚአብሔር ዓለም በመሆኑ ነው:: ምክንያቱም ሰዎች በመልኩና በአምሳሉ እግዚአብሔር ለሚፈልገው ዐላማ ተፈጥረዋል:: ክርስቶስ ኢየሱስም አሁን እየመለሰን ያለው ወደዚህ አስቀድሞ ወደ ተፈጠርንበት ዐላማ ነው (ዕብ 2÷6-15):: የሰው ልጆች በኀጢአት በወደቁ ጊዜ የተፈጠሩበትን ዐላማ ስተዋል:: በእግዚአብሔር ጸጋ የጽድቅ ሕይወትን መኖር ስንጀምር፣ ወደ ተፈጠርንበት ዐላማ እየተመለስን ነው::

ሦስተኛው፣ ፍትሕና ፍቅር የእግዚአብሔር ዐይነተኛ ባሕርያት እንደ ሆኑ ሁሉ የእኛም መለያና መርሕ እንዲሆኑ ያስተምረናል[4]:: እግዚአብሔር ከእርሱ እንድንወርስ ከሚፈልጋቸው ባሕርያት መካከል ፍትሕና ፍቅር ዋነኞቹ ናቸው፤ እግዚአብሔር

[2] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 14 እንዲሁም ገጽ 69-78::

[3] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 14 እንዲሁም ገጽ 49-56::

[4] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 14 እንዲሁም ገጽ 115-123::



ውስጣዊ እኛነታችን ማለትም እኛን እኛ የሚያሰኘን ነገር በእነዚህ ሁለት ባሕርያት እንዲቀረጽ ይፈልጋል:: ምክንያቱም ማንኛውም ግብር (ሰናይም ሆነ ጽድቅም) የሚመነጨው ከእነዚሁ ነገሮች ነው:: እግዚአብሔር በእነዚህ መልካም ባሕርያት እንድናድግ የሚሻው፣ የእርሱን መልክ በትክክል የሚያንጸባርቁት እነዚህ ባሕርያት በመሆናቸው ነው (በድኅነት ታሪኩ እንዳየነው):: መልካሙና ሰናዩ በአንጻሩም መጥፎውና እኩዩ የቱ እንደሆነ ማወቅ እምብዛም ላይረዳን ይችላል:: ውስጣዊ እኛነታችን ግን በትክክል ተለይተን እንድንታወቅ ያደርገናል:: ድንገት ተነሥተን ዕብሪተኞችና እኩዮች አንሆንም:: ውስጣዊ እኛነታችን በፍትሕና በፍቅር የተገራ ከሆነ፣ በማንኛውም ነገር ታማኞችና ኀላፊነት የሚሰማን ሰዎች እንሆናለን:: በሌላ አነጋገር ማንም ሰው ስለ እኛ በእርግጠኛነት እርሱ እኮ እንዲህ ዐይነት ሰው ነው ብሎ መናገር ይችላል:: ጳውሎስ ውስጣዊ እኛነታችን ሊገራ የሚገባው በምን እንደ ሆነ በገላ 5÷22-23 ላይ ገልጾአል:: እነርሱም ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት ናቸው:: በአንጻሩም በዚሁ መጽሐፍና ምዕራፍ ውስጥ (ቊጥር 19-21) የእነዚህን ባሕርያት ተቃራኒ ዘርዝሯል::

አራተኛው፣ የእግዚአብሔርን ምግባራዊ ሕግ ያስታውቀናል[5]:: እግዚአብሔር በሕዝቡ ሕይወት ማየት የሚፈልጋቸውን፣ በንጻሩም የሚጠላቸውን ነገሮች በግልጽ አስታውቋል:: ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑን ዐሥርቱ ትእዛዛት ናቸው (ዘፀ 20÷3-17):: እግዚአብሔር በአምሳሉ የፈጠራቸው ሰዎች እርሱን እንዲመስሉ፣ እርሱን እርሱን እንዲሸቱና የእርሱን ባሕርይ/መልክ እንዲያንጸባርቁ ይሻል:: እግዚአብሔርን እጅግ የሚያስቈጣው "የመልኩ መለወጥ" ማለትም በመጥፎ ነገር መመሰል ነው (ሮሜ 1÷18-32):: እግዚአብሔር በመልኩ ሲፈጥረን መልኩን አትሞብናል:: ሥነ ፍጥረት ለእግዚአብሔር ምግባራዊ ሕግ ምስክር ነው:: እርግጥ ነው ኀሊናችን ዘወትር በእግዚአብሔር ጸጋና መንፈስ መለወጥና መታደስ አለበት:: አለበለዚያ ተላልፈን ከተሰጠንበት እስራት ነጻ ለመውጣት አንችልም::

አምስተኛው፣ እንዴት መኖር እንዳለብን ምሳሌ ያኖርልናል[6]:: እግዚአብሔር አንድ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደዚህ ምድር የላከው አንድም ከኀጢአታችን እንዲቤዠን፣ አንድም ደግሞ ለሕይወታችን ምሳሌ እንዲሆነን ነው:: ሌሎች የሕይወት ዘይቤዎች በሙሉ ምሳሌ ሊሆኑን አይችሉም:: ምክንያቱም የሕይወት ግቧም ሆነ ትርጕሟ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው:: መታደስን ያገኘነው በእርሱ ከሆነ፣ በተለወጠ ሕይወት ለመኖር አርአያም የሚሆነን እርሱው ነው::

[5] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 14 እንዲሁም ገጽ 57-67::

[6] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 14፤ እንዲሁም Richard B. Hays, *The Moral Vision of the New Testament : A Contemporary Introduction to the New Testament Ethics* (New York: Harpercollins Publishers, 1996) ገጽ

ለምናምነውና ለምንኖረው ሕይወት ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻው ትልቁ መለኪያችን ከሆነ፣ ይህን መጽሐፍ እንብበን በትክክል የምንረዳውና የምንተረጉመው እንዴት ነው? ወደሚለው ጥያቄ እናልፋለን።

## 2. ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርና የትርጓሜ መርሖቹ

ሥነ ምግባራዊ ርእሰ ጉዳዮችን አንሥተን ስንነጋገር፣ ፈጥኖ ወደ ኅሊናችን የሚመጣ አንድ ጥያቄ አለ። ምናልባት ጥያቄውን ልብ ልንለውም ልብ ሳንለውም እንችላለን። በእኛ እምነት ግን ጥያቄው ወሳኝ ጥያቄ ነው። ይኸውም በልዩ ልዩ ሐዋርያት የተጻፉልንን የአዲስ ኪዳን ምንባቦች የምንተረጉመው/የምንፈታው እንዴት ነው? የሚለው ነው[7]። ይህ ደግሞ የትርጓሜ ጥያቄ ነው። አዲስ ኪዳን ከተጻፈ ወደ 2000 ዓመት ይሆነዋል። ታዲያ ይህ ጥንታዊ መጽሐፍ ዛሬም ለእኛ የሚሆን መልእክት ካለው፣ መልእክቱን በቅጡ ለመረዳት ምን "የትርጓሜ ስልት" መከተል አለብን? ይህ መጽሐፍ ለምንለው ነገር ሁሉ (ለእምነታችን ማለት ነው) እንዲሁም ለምንኖረው ሕይወት ሁሉ (ለምግባራችን ማለት ነው) ሥልጣናዊ ቃልና ፍጹማዊ መርሕ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው? ሥልጣናዊነቱስ በከፊል ነው? ወይስ በሙሉ? እነዚህ ጥያቄዎች ጥንቃቄ የተሞላበት መልስ ስለሚሹ ነገሩን በእርጋታ ለማየት እንሞክራለን።

### 2.1. ሥልጣናዊ ምንጮች

እዚህ ላይ አንድ ነገር መታወቅ ያለበት ይመስለናል። ይኸውም እምነታችንም ሆነ ምግባራችን መመራት ያለበት ፍጹማዊ መርሕ/ሥልጣናዊ ቃል በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ነው የሚል ጽኑ አቋም ቢኖረንም፣ አቋማችን ግን ከመቅድመ ልባዊ የጸዳ ሊሆን አይችልም። እርግጥ ነው እንደ ተሐድሷውያኑ ሁሉ መፈክራችን "ሶላ ስክሪፕቱራ" (ቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ) ነው። ይሁንና የትርጓሜ ስልታችን የሚከናወነው በወና እንጉል (ዓለም) ውስጥ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስን ማለትም ፍጹሙን መርሕ ስናነብ የየራሳችን ዕይታ አለን። ይህን ግን ልብ አንለውም። በመሆኑም መጽሐፍ ቅዱሳችንን ለመፍታት ስንነሣ፣ በቅዱሳት መጻሕፍትና በሌሎች ሥልጣናዊ ምንጮች መካከል ያለውን ልዩነትና ዝምድና በግልጽ መወሰን አለብን[8]። ሌሎቹ

7 ሥነ ምግባራውያን (የሥነ ምግባር ሊቃውንት) ምንም ነገር ከማድረጋቸው ማለትም ወደ ትንተናው ከማረጋቸው በፊት ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ይጥኳራሉ።

8 Richard B. Hays, *The Moral Vision of the New Testament: A Contemporary Introduction to the New Testament Ethics* (New York: Harpercollins Publishers, 1996), 210.



ሥልጣናዊ ምንጮች የቤተ ክርስቲያን ወግ ወይም ትውፊት፣ አመክንዮና ተሞክሮ ናቸው።

ሥነ ምግባራዊ ደንቦች ሲረቀቁ ወይም ድንበሮች ሲካለሉ ነገሩ የሚታየው ከአንድ አቅጣጫ ብቻ አይደለም። ከፍ ሲል እንደ ተመለከትነው ቢያንስ አራት አቅጣጫዎች አሉ፤ (1) መጽሐፍ ቅዱስ (2) የቤተ ክርስቲያን ወግ ወይም ትውፊት (3) አመክንዮ እና (4) ተሞክሮ። ይህ ምን ማለት እንደ ሆነ በጥቀቱ እንወያይ።

**መጽሐፍ ቅዱስ፤** ስለ አንድ ማንኛውም ምግባራዊ ጥያቄ ስንወያይ፣ መልሱን መፈለግ ያለብን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው። ምግባራዊ ደንቦችን፣ መርሖችን፣ ሕጎችን ስንቀርጽ መነሻችን ቅዱሳት መጻሕፍት መሆን አለባቸው። በሌላ አነጋገር ለመቅዳት መውረድ ያለብን ወደ አንዱ ምንጭ ነው---ወደ መጽሐፍ ቅዱስ። ምግባራዊ ጥያቄዎች መመለስም ሆነ መመርመር ያለባቸው ከጌታ ቃል አንጻር ነው። ምክንያቱም ልናምነውም ሆነ ልንኖረው የሚገባንን ነገር ለመናገር መብት ያለው እርሱ ብቻ ነው። እኛ በቀመርነው መርሕ እርሱን ደስ ልናሰኘው አንችልም። ደግሞም እኛ የምንቀምረው መርሕ ከእርሱ ምግባራዊ ደረጃ ጋር ሊደራረስ አይችልም። በመሆኑም ክርስቲያኖች ለሕይወታቸው ምሳሌና መርሕ የሚሆናቸውን ነገር ለመፈለግ መሄድ ያለባቸው ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ነው[9]። እግዚአብሔር ለሕዝቡ የተናገረውን ሐሳብ የምናገኘው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በመሆኑ ሌሎች ምንጮች አይጠቅሙንም። በመሆኑም ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር እውነት፣ መልካምና እኩይ የሆነውን ነገር የሚመዝነው በቅዱሳት መጻሕፍት ነው[10]።

**የቤተ ክርስቲያን ወግ/ትውፊት፤** በዚህ አገባቡ ወግ ስንል የትኛውንም ወግ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ከአንዲት ቀዬ አንሥቶ እስከ አገር ድረስ በየደረጃው አያሌ ወጎች አሉ። በዚህ ስፍራ ለመጥቀስ የፈለግነው ይህን አይደለም። ቤተ ክርስቲያን ባለፈችባቸው ጎዳናዎች ብዙ ነገር አይታለች። ለገጠማት ነገሮችም ብዙ መልስ ሰጥታለች። አምልኮን (ጥምቀትንና የጌታን ራት ጨምሮ)፣ አገልግሎትን፣ አስተምህሮን፣ ወዘተ በተመለከተ ብዙ ውይይቶች ተደርገዋል። በእነዚህና በሌሎችም ጉዳዮች ላይ ግለ ሰቦችም ብዙ አስተምረዋል፤ ጽፈዋልም። የአንዳንዶቹ ጽሑፍ እንዲያውም እስከ ዛሬ ድረስ ጽኑ ስፍራ ይዞ ይገኛል (ለምሳሌ የአውግስጢኖስ፣ የአኩዊናስ፣ የሉተር፣ የካልቪን፣ የዌስሊ)። የተወሰኑ ቤተ እምነቶችና ባህላዊ ቡድኖችም በሂደቱ ውስጥ ያበረከቱት አስተዋጽኦ ይኖራል። በእኛ ዘመን የተነሡ ምግባራዊ ጥያቄዎች በእነርሱም ዘመን ተነሥተው መልስ ተሰጥቶባቸዋል። የተሰጡት መልሶች የሚናቁ

9 Stanley J. Grenz, *The Moral Quest: Foundations of Christian Ethics* (Downers Grove: InterVarsity Press, 1997), 96.

10 Kevin J. Vanhoozer, *First Theology: God, Scripture and Hermeneutics* (Downers Grove: InterVarsity Press, 1997), 160.

ባይሆኑም፣ በክርስቲያናዊ ነገረ መለኮት ውስጥ ግን የቤተ ክርስቲያን ወግ የማይገረሰስና የማይሻር ደንብ ተደርጎ መቈጠር የለበትም[11]:: ጌታ እንዲህ ሲል አስጠ ንቅቋልና:- "...የራሳችሁን ወግና ሥርዐት ለመጠበቅ ስትሉ የእግዚአብሔርን ቃል ትሽራላችሁ" (ማር 7÷13፤ ሕያው ቃል)::

ይህን ስንል ግን ትውፊትን ለማጣጣልና ሚናውንም ለማንኰዋሰስ አንሻም:: እኛ አበክረን ለማስገንዘብ የምንፈልገው መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር መገለጥ እንደ ሆነና ምንጩም እርሱ እንደ ሆነ ነው:: ቤተ ክርስቲያን የመገለጡ ተቀባይ ናት:: እምነትም ሆነ ሕይወት መለካት ያለበት በትውፊት ሳይሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ነው የሚባለው በዚህ ምክንያት ነው:: መንበረ ሥልጣኑ መጽሐፍ ቅዱስ እንጂ ቤተ ክርስቲያን አይደለችም:: የሥልጣኑ ሰንሰለታዊ ትስስር እግዚአብሔር ⇒ ሕዝቡ ⇒ ትውፊት ⇒ መጽሐፍ ቅዱስ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ➡ መገለጡ ➡ መጽሐፍ ቅዱስ ➡ ቤተ ክርስቲያን ነው[12]:: መጽሐፍ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን እጅ ውስጥ እንጂ፣ በቤተ ክርስቲያን ሥልጣን ሥር አይደለም:: ደግሞም ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን የምትተረጕመው በመንፈስ ቅዱስ በመመራት/እየተመራች ነው:: ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ የሚሰጣትን ትቀበላለች:: በሌላ በኩል ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስንና ትውፊትን እንደ ዛፍ ሥርና እንደ ቅርንጫፍ ልናነጻጽራቸው እንችላለን:: ቅርንጫፎች ሁሉ ቀጥ ያሉና ጽኑ አይደሉም:: ይሁንና ለህልውናቸው ሁልጊዜ የሚመኩት ከሥሩ በሚያገኙት ምግብ ነው:: አንዳንድ ትውፊቶች አርቲ ቡርቲና ምናልባትም አደገኛ ሊሆኑ ይችላሉ:: ይህ ማለት ግን ትውፊቶች ሁሉ ከንቱ ናቸው ማለት አይደለም[13]::

**አመክንዮ፤** አመክንዮ ስንል መላለምን (ጽንፈ ዓለምን) ወይም ይህን የምናየውን ግዙፍ ዓለም ለመረዳት ሥርዐታዊ ፍልስፍናና ሳይንሳዊ ምርመራ እንደሚያስፈልግ ሁሉ የመጽሐፍ ቅዱስንም ምክኑያዊነት ለመመዘን አመክንዮ ያስፈልጋል የሚለውን የዘመነ አብርሆት አስተሳሰብ ነው:: ለሌሎች የምናስተላልፈው እኛ የተረዳነውንና የደረስንበትን ነገር ነው:: ከ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወዲህ አመክንዮ ብዙ ዝና አግኝቷል:: ይሁንና አመክንዮ ራሱ ከመቅድመ ልባዌ የጸዳ አይደለም:: እያንዳንዱ ሰው ተወልዶ ያደገበት የየራሱ ቀዬ (ባህል፣ ወግ፣ ትምህርት፣ ፍልስፍና፣ አኗኗር) አለው:: በመሆኑም ማንኛውም ሰው ከየቀዬው ተጽዕኖና ማለትም ***ከመቅድመ ልባዌ*** ነጻ አይደለም:: እርግጥ የተጽዕኖው መጠን እንደየ ሰዉ ንቃትና ምጥቀት ሊለያይ ይችላል:: መጽሐፍ ቅዱስ በርካታ ታላላቅ ሐሳቦች አሉት:: ሐሳቡን

[11] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 210::
[12] Donald G. Bloesch, *Holy Scripture: Revelation, Inspiration, and Interpretation* (Downers Grove: InterVarsity Press, 1994), 146.
[13] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 147-148::



በትክክል ለመጨበጥ አመክንዮ አስፈላጊ ቢሆንም፣ ወሳኝ ግን አይደለም:: ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በቀላሉ ለመረዳት የሚያስቸግሩ ሐሳቦች አሉ:: በዚህ ጊዜ ምን ልናደርግ ነው? ከአመክንዮ ጋር የማይገጥሙ ሐሳቦች ቢያፋጥጡን ምን ልንሆን ነው? ቃሉን ሽረን አመክንዮን ልንሾም ነው? መቼም ይህን ሁሉ ስንል አንድ መሠረታዊ ነገር ረስተን አይደለም:: እግዚአብሔር ምክኑያዊ ማለትም ኀሊናዊ አምላክ እንደ ሆነ ሁሉ፣ በእርሱም አምሳል የተፈጠሩ ሰዎች ምክኑያውያንና ኀሊናውያን ናቸው:: እግዚአብሔር ራሱን የገለጠበት መንገድ ራሱ ኀሊናዊነትን የሚደመስስ አይደለም:: ይልቁንም ኀሊናዊው አምላክ የሰጠን መገለጥ ኀሊናዊ ሰውን ይሻል:: ኀሊናዊው አምላክ "ሐሳቡን አካፈለን"[14]፤ ማለትም መገለጡን ሰጠን:: ይህ መገለጥ ደግሞ የእውነት ሁሉ ምንጭ ነው:: ይህን መገለጥ ለመረዳት ኀሊና አስፈላጊ ነው:: ይኸውም አመክንዮ ያልነው ነገር የእግዚአብሔርን "ታሪክ ድኅነት" ለመረዳትና ምላሽ ለመስጠት እጅግ ያስፈልጋል[15]::

**ተሞክሮ፤** ተሞክሮ ስንል የግለ ሰቦችን ብቻ ሳይሆን የኅብረተሰቡንም ተሞ ክሮ እያሰብን ነው:: ሰዎች በዚህ ምድር ሲኖሩ የሚያካብቱት በርካታ ልምድ ይኖራ ቸዋል:: በተለይ በመንፈሳዊው ዓለም ይህ ትልቅ ስፍራ አለው:: ሰዎች በግል የሚያገኟ ቸው አብርሆቶች በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እስካገኙ ድረስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመፍታት መርሕ ተደርገው የሚወሰዱበት ጊዜ አለ:: እዚህ ላይ ብዙ ጊዜ ምሳሌ ተደርጎ የሚጠቀሰው ማርቲን ሉተር ነው:: ሉተር በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የጸጋንና የይቅርታን ምስጢር በተለየ መንገድ ተረዳ፤ ይህ ግላዊ ተሞክሮ ትልቅ ለሆነ ነገረ መለኮታዊ እሳቤ (ጽድቅ በእምነት) ለሚለው መሠረት ሆነ:: ግላዊ ተሞክሮ የምንባቡን ትርጕም/ፍቺ ከመግለጡም በላይ የቅዱሳት መጻሕፍቱን ምስክርነት በልባችን ወይም በኅብረተሰቡ ሕይወት ውስጥ ያጸናል:: ይሁንና ተሞክሮው ከቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት ጋር የሚጣረስ ቢሆንስ? የቤተ ክርስቲያን ወግም ሆነ አመክንዮ የራሳቸው የሆነ እንከን እንደማይጠፋባቸው ሁሉ፣ ይህም ከእንከን ነጻ ሊሆን አይችልም:: እንግዲህ ነገሩ እንዲህ ከሆነ፣ መቼም መች ቋሚ መለኪያ ሊሆነን የሚችል ነገር ያስፈልገናል ማለት ነው[16]::

*ታዲያ ቋሚ መለኪያ ምንድን ነው?* በእኛ እምነት ሥነ ምግባራዊ ጥያቄዎች በሙሉ መመለስ ያለባቸው፣ መርሖች መቀረጽ ያለባቸው፣ ስልቶች መነደፍ ያለባቸው ሥልጣናዊ ቃል በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ነው:: እንዲህ ስንል ግን የቤተ ክርስቲያን ወግ፣ አመክንዮና ተሞክሮ ምንም ሚና የላቸውም ማለታችን አይደለም:: ነገር ግን ዋናውን (እርሱም መጽሐፍ ቅዱስን) ከተራው (እርሱም ከወግ፣ ከአመክንዮና ከተሞክሮ)

[14] Carl F.H.Henry, *God, Revelation and Authority*. Vol. 1 (Waco: Word,1983), 244.
[15] ዝኒ ከማሁ፤ Vol. 3 ገጽ 457::
[16] Hays, *The Moral Vision of the New Testament*. 209-212.

መለየት እንዳለብን ለማስጠንቀቅ ነው:: የመጀመሪያው ፍጹማዊ ሲሆን፣ ሁለተኛው ግን አንጻራዊ ነው:: ፍጹማዊውን ከአንጻራዊው መለየትና ሁሉንም በየቦታቸው መጠቀም ያስፈልጋል[17]:: ሥነ ምግባራዊ ጥያቄዎችን ስንመልስ ነገራችንን ሁሉ ሊገራው፣ ሊገዛውና ሊመራው የሚገባው የትርጓሜ ስልት የቱ ነው? የሚለው ቁልፍ ጥያቄ ይሆናል::

## 2.2. የአፈታት መርሖች/ስልቶች

ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር በሚቀረጽበት ጊዜ ልዩ ልዩ ስልቶችን የሚከተሉ ሊቃውንት እንዳሉ እሙን ነው:: ይሁንና ከአዲስ ኪዳን ምንባቦች ጋር ብርቱ ውይይት የሚያደርግ ሰው፣ ምንባቦቹን እየመረጠና በእግረ መንገዱ እየተመለከተ ከሚሄድ ሰው ይልቅ የተሻለ ሐሳብ ሊናገር ይችላል[18]:: ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን ለመቅረጽ እውነተኛ ሒታቲ ሆኖ መገኘት ያስፈልጋል:: የምንለው ነገር በሙሉ በጥልቅ ሒቲታዊ ብያኔ ላይ ካልተመሠረተ፣ የምንለው ነገር ከየትም የታፈሰ ሐሳብ ይሆናል:: በእኛ እምነት ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን ለመንደፍ ልንከተላቸው የሚገቡት የአፈታት መርሖች ወይም ስልቶች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው::

### 2.2.1. ሙሉውን ቀኖና (ብሉይና አዲስን) ማገናዘብ

እግዚአብሔር ሕዝቡ ሕይወቱንና እምነቱን ይመዝንበት ዘንድ መገለጡን ማለትም መጽሐፍ ቅዱስን ሰጥቷል:: በመሆኑም ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን ስንቀርጽ፣ ሙሉውን ቀኖና ማገናዘብ ያስፈልጋል:: ስለ አንድ ርእሰ ጒዳይ ለምሳሌ ስለ ጉቦ፣ ውርጃ፣ መፋታት፣ ወዘተ ስንነጋገር፣ በብሉይና በአዲስ ኪዳን ውስጥ እነዚህን አርእስት አስመልክቶ የተጻፉትን ምንባቦች በሙሉ መመልከትና አንድምታዎቻቸውን መመርመር ያሻል:: ሥነ ምግባራዊ መርሖችን በምንቀርጽበትና ሥነ ምግባራዊ ርእሰ ጉዳዮችን በምንመረምርበት ጊዜ ሙሉውን ቀኖና ማገናዘብ የሚያስፈልግበት በርካታ ምክንያቶች አሉ::

አንደኛው፣ መጽሐፍ ቅዱስ ሕገ አምላክ ነው:: ማለትም ልናደርገውና ልንሆነው የሚገባንን ነገር የሚያሳየን፣ ልንከተለውና ልንይዘው የሚገባንን ነገር የሚያሳውቀን አምላካዊ መመሪያ ነው:: ባሕርያችንና አካሄዳችን ምን መምሰል እንዳለበት መመሪያ የምናገኘው ከዚህ መጽሐፍ ነው:: በዚህ ምድር ስንኖር

---

[17] Vern S. Poythress, *God Centered Biblical Interpretation* (New Jersy: P & R Publihing, 1999), 63-68.

[18] Bloesch, *Holy Scripture: Revelation, Inspiration, and Interpretation.* 291.



የምናነሣቸው ወሳኝ ጥያቄዎች አሉ[19]:: ባሕርያችንና አካሄዳችን ምን መምሰል እንዳለበት መመሪያ የምናገኘው ታዲያ ከየትም አይደለም፤ እግዚአብሔር ከሰጠን ከዚህ መራሔ እንጂ::

ሁለተኛው፣ መጽሐፍ ቅዱስ እሙነ መርሕ ነው:: ማለትም በሚለው ነገር ሁሉ የታመነ መጽሐፍ ነው:: በመሆኑም ወደ እውነት ሊያደርሰን የሚችል ታማኝ መሪ ነው[20]:: ፍጹም እውነተኛ ቃል በመሆኑ የእግዚአብሔርን ሐሳብና ፈቃድ እያስታወቀን እርሱን ደስ ወደሚያሰኝ ድምዳሜ ያደርሰናል::

ሦስተኛው፣ መጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣነ ሕይወት ነው:: ማለትም ልንኖረው የሚገባንን ሕይወት የሚነግረን መጽሐፍ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሕዝቦች የሚመሩበት ብቸኛው ባለ ሥልጣን ተደርጎ መታየት አለበት[21]:: ይህ መጽሐፍ ሥልጣኑን ያገኘው ከእግዚአብሔር ነው:: የመጽሐፉ መገኛ እርሱ ነውና:: በመሆኑም እንዴት መኖር እንዳለብን ብቻ ሳይሆን ምን ማመን እንዳለብንም ሊነግረን ይችላል::

### 2.2.2. ሁነኛ ሒቲት ማከናወን

መጽሐፍ ቅዱስ በርካታ ልዩ ባሕርያት አሉት:: ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ደራሲዎች አሉት - መለኮታዊና ሰብአዊ[22]:: ሁለት ዓለሞች አሉት - የጥንቱና የአሁኑ[23]:: እንዲህ ዐይነት ወሳኝ ባሕርያት ያሉት መጽሐፍ ደግሞ ሁነኛ ሒቲት ይሻል[24]::

ልብ እንበል! ሰዎች የሚግባቡት በቋንቋ ነው:: ነባቤ ፍጡራን በመሆናችን ቋንቋ ዐይነተኛ የመግባቢያ መሣሪያችን ነው:: የሰዎች ቋንቋ ደግሞ የራሱ የሆነ

---

[19] David S. Dockery, *Christian Scripture: An Evangelical perspective on Inspiration, Authority and Interpretation* (Nashville: Broadman and Holman Publishers,1996), 63.

[20] ዝኒ ከማሁ:: ገጽ 60::

[21] ዝኒ ከማሁ:: ገጽ 71::

[22] George Eldon Ladd, *The New Testament and Criticism*፤ እንዲሁም Robert H. Stein, *Playing by the Rules: A Basic Guide to Interpreting the Bible* (Grand Rapids: Baker Book House, 1994). John Stott, *Evangelical Truth: A Personal Plea for Unity* (Leicester: InterVarsity Press, 1999). Nicholas Wolterstroff, *Divine Discourse: Philosophical Reflections on the Claim that God Speaks* (Cambridge: Cambridge University Press, 1995). Kevin J. Vanhoozer, *First Theology: God, Scripture and Hermeneutics* (Downers Grove: InterVarsity Press, 2002).

[23] Peter H. Davids, *Authority, Hermeneutics, and Criticism*, in Interpreting the New Testament: Essays on Methods and Issues. Eds. , David Alan Black and David S. Dockery (Nashville: Broadman and Holman Publishers, 2001), 4-5.

[24] Gordon D. Fee and Douglas Stuart, *How to Read the Bible for All its Worth: A Guide to Understanding the Bible* (Grand Rapids: Zondervan Publishing House, 1993), 17-19.

የቋንቋ ሥርዐት አለው:: ሐሳብ ተላለፈ፣ ሰዎችም በቅጡ ተግባቡ የሚባለው ለማስተላለፍ የተፈለገው ሐሳብ በቋንቋው ሥርዐት መሠረት ሲነገር ወይም ሲጻፍ ነው:: የቋንቋውን ሥርዐት ጠብቆ ያልተላለፈ ሐሳብ በቀላሉ ይሳታል:: ቋንቋን ተጠቅመው ሐሳባቸውን የሚያስተላልፉ ሰዎች የራሳቸው የሆነ ባህል፣ ታሪክ፣ ልማድ፣ ቀዬ፣ ርእዮተ ዓለምና ንጽሮተ ዓለም አላቸው:: እነዚህ ሁሉ በድምሩ ዳራ ሊባሉ ይችላሉ[25]::

ለምሳሌ የሐዲስ ዓለማየሁን ፍቅር እስከ መቃብር የተሰኘውን መጽሐፍ እንውሰድ:: መጽሐፉ የተጻፈው ከዛሬ 38 ዓመት በፊት ነው (1958 ዓ.ም) — በአማርኛ ቋንቋ:: ለመጽሐፉ ዝናን ያጐናጸፈው የአገላለጽ ስልቱ (ቋንቋዊ ለዛው ልንለው እንችላለን) ብቻ ሳይሆን ቅድም በድምሩ ዳራ ያልናቸውም ነገሮች ናቸው:: ፍቅር እስከ መቃብርን አንብቦ ለማጣጣም መጽሐፉ የተጻፈበትን ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ልማዳዊ፣ አካባቢያዊ ዳራ ወይም ዐውድ ማወቅ ያስፈልጋል:: መጽሐፉን አንብበን ለማጣጣም እምብዛም ችግር የሌለብን ጊዜው ቅርብ ስለ ሆነ ነው:: ቢያስፈልግም ጸሐፊው በሕይወት ስላሉ፣ ግር ያለን ነገር ካለ ጠይቀን ዝርዝር መረጃ ለማግኘት እንችላለን (ይህ መጽሐፍ እስከ ተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ፣ ጸሓፊው በሕይወት ነበሩ):: ይሁንና ከ2000 ዓመት በኋላ ፍቅር እስከ መቃብርን የሚያነብ ሰው አሁን እኛ ያለንን ዐይነት ዕድል ሊኖረው አይችልም:: የጸሐፊው በሕይወት አለመኖር ብቻ ሳይሆን የጊዜውም ክፍተት ትልቅ ፈተና ይሆንበታል:: ከ2000 ዓመት በኋላ ተነሥቶ መጽሐፉን የሚያነብ ሰው፣ የመጽሐፉን ጭብጥ ለመረዳት ሌሎች የታሪክ ድርሳናትን መመርመር ያስፈልገዋል:: የጊዜውን ክፍተት የሚደፍንለትና የጸሓፊውን በሕይወት አለመኖር የሚያካክስለት መንገድ የግድ ያሻዋል:: ቋንቋዊ አጠቃቀሙም ቢሆን የራሱ የሆነ ፈተና አለው:: ዛሬ ለእኛ ውብና ብሩኅ የሆኑ አገላለጾች (ቃሎች፣ ፈሊጦች፣ ተረቶች፣ ዘይቤያዊ አነጋገሮች፣ ወዘተ) ከ2000 ዓመት በኋላ ለሚመጣው ትውልድ እንግዳ ሊሆኑ ይችላሉ:: መጽሐፍ ቅዱስንም አስመልክቶ የሚገጥመን ፈተና ልክ እንደዚሁ ነው:: ከዛሬ 2000 (አዲስ ኪዳን) እና 3000 (ብሉይ ኪዳን) ዓመት በፊት የተጻፉ መጻሕፍትን አንብበን በትክክል የምንረዳውና የምንተረጒመው እንዴት ነው? የጊዜውንስ ክፍተት የሚደፍንልን፣ የጸሓፊዎቹንም በሕይወት አለመኖር የሚያካክስልን ነገር ምንድን ነው?— ሁነኛ ሐቲት::

ሁነኛ ሐቲት ከጸሎት መጀመር አለበት[26]:: እናስታውስ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ደራሲዎች አሉት ብለን ነበር:: አንደኛው ደራሲ መንፈስ ቅዱስ ነው:: ሁለተኛው ደራሲ የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረባቸው ቅዱሳን ሰዎች (ነቢያትና ሐዋርያት) ናቸው:: በእኛ እምነት መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ ጭብጡን (ቊልፉ ጭብጥ

[25] Gordon D. Fee, *New Testament Exegesis: A Handbook for Students and Pastors* (Louisville, Kentucky: Westminster Press, 1983), 114-123.

[26] Dockery , *Christian Scripture*, 162.



ኢየሱስ ክርስቶስ ነው) ለመረዳት አብርሆተ እግዚአብሔር ያስፈልገናል:: ምክንያቱም ያለ መጽሐፉ ደራሲ መጽሐፉን በትክክል መረዳት አይቻልም:: ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን 6÷17 ላይ ሲናገር:- "የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፤ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው" ይላል:: በሌላ በኩል ደግሞ "ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለ ሆነ ሊያውቀው አይችልም" (1ቆሮ 2÷14) ይላል:: ይህ ምንባብ የሚናገረው ስለ አብርሆተ እግዚአብሔር ከሆነ፣ መንፈስ ቅዱስ የአንባብያንን ልብና ልቡና ከፍቶ ቃሉ በውስጣችን እንዲሠራ ካላደረገ በቀር፣ ማስተዋልም ሆነ ማመን (ዮሐ 20÷31) አይቻልም ማለት ነው[27]:: መንፈስ ቅዱስ "የቃሉ መንፈስ" ማለትም የክርስቶስ መንፈስ ነው (ዮሐ 1÷1-14)፤ የሚያገለግለውም ቃሉን ማለትም ክርስቶስን ነው[28]:: ሁነኛ ሐቲት ከጸሎት መጀመር አለበት ያልነው፣ የእግዚአብሔርን ቃል ሕያውና የሚሠራ (ዕብ 4÷12) የሚያደርገው መንፈስ ቅዱስ በመሆኑ ነው:: መንፈሱ ያለ ቃሉ ድዳ ነው፤ ቃሉ ያለ መንፈሱ ምውት ነው[29]::

ሁነኛ ሐቲት መጽሐፍ ቅዱስ ልዩ ልዩ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጾች እንዳሉት ይገነዘባል:: መጽሐፍ ቅዱስ ከዳር (ዘፍጥረት) እስከ ዳር (ራእየ ዮሐንስ) ድረስ የተጻፈው በአንድ ዐይነት የአጻጻፍ ስልት/ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ አይደለም:: ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ ስንል የጽሑፍ ዐይነት ማለታችን ነው:: ማንም እንደሚያውቀው በአገራችን ኢትዮጵያ በርካታ የሥነ ጽሑፍ ሀብቶች አሉ:: እነዚህን የሥነ ጽሑፍ ሀብቶቻችንን በጥሞና ስንመረምር፣ ሁሉም በአንድ ዐይነት የአጻጻፍ ስልት ተጽፈው አናገኝም:: አንዳንዶቹ በግጥም መልክ የተጻፉ ናቸው:: ሌሎቹ በትረካ መልክ የተጻፉ ናቸው:: አንዳንዶቹ በተውኔት መልክ የተጻፉ ናቸው:: ሌሎቹ በተረትና ምሳሌ መልክ የተጻፉ ናቸው:: አንዳንዶቹ በሕግ መልክ የተጻፉ ናቸው:: ሌሎቹ *በአቡቀለምሲስ* መልክ የተጻፉ ናቸው:: ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ (ወይም የጽሑፍ ዐይነት) የምንለው እንግዲህ እንደ እነዚህ ዐይነት (ግጥምን፣ ትረካን፣ ተውኔትን፣ ተረትና ምሳሌን፣ ሕግን፣ አቡቀለምሲስን) የአጻጻፍ ስልቶችን ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በትንሹ ከዐሥር በላይ ዋና ዋና ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጾችን እናገኛለን[30]::

ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽን እንደ ቋንቋ ጨዋታ ልንመለከተው እንችላለን:: በአገራችን ቊጥራቸው በርካታ የሆነ አገር በቀል ጨዋታዎችና (ለምሳሌ ገበጣ) ድንበር

[27] Kevin J. Vanhoozer, *Is There a Meaning in This Text? The Bible, the Reader, and the Morality of Literary Knowledge* (Grand Rapids: Zondervan, 1998), 428.

[28] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 429::

[29] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 428::

[30] Dan McCartney and Charles Clayton., Let the reader Understand: A Guide to Interpreting and Applying the Bible (Wheaton: Victor Books, 1994). 210-228.

ዘለል ጨዋታዎች (ለምሳሌ እግር ኳስ) እንዳሉ ይታወቃል:: ለጊዜው ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ ያልነውን ነገር በአገራችን ከምናውቃቸው ጨዋታዎች በአንዱ እንመስለው:: የአንድ መጽሐፍ ቅዱስ ሐታቲ ተግባር የትኛው የጨዋታ ዐይነት (ታሪካዊ፣ ትንቢታዊ፣ ደብዳቤያዊ፣ ራእያዊ፣ ወዘተ) እየተከወነ እንዳለ መወሰን ነው:: ምክንያቱም እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ትርጕም የሚኖረው የጨዋታው ዐይነት ሲታወቅ ነው[31]:: በአገራችን ከምናውቃቸው ጨዋታዎች መካከል አንዱን ወስደን እንጫወት ብንል በቅድሚያ የጫወታውን ሕግ ማወቅ አለብን:: አለበለዚያ በጨዋታው ውስጥ የምናሳየው ማንኛውም እንቅስቃሴ ትርጕም ያጣል:: የጨዋታው ዐይነት ብቻ ሳይሆን የጨዋታውም ሕግ ለየቅል ነው::

አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሐታቲ የሚያነበውን መጽሐፍ (እንበልና የዮሐንስ ራእይን) ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ በውል ካላወቀ መጽሐፉን በትክክል መተርጐም፣ ሐሳቡንም በትክክል መጨበጥ አይችልም:: አንድ መጽሐፍ/ምንባብ የተጻፈበትን ስልት ማወቅ የመጽሐፉን/የምንባቡን ሐሳብ ለማወቅ እጅግ ወሳኝ ነው:: የመጽሐፉ መልእክት ወይም የምንባቡ ሐሳብ የተላለፈው በቅርጹ አማካይነት በመሆኑ፣ የቅርጹ ትርጕም ወሳኝ ነው[32]:: ቀደም ሲል ሐታትያንን የሚገዳደሩ ሁለት ፈተናዎች እንዳሉ ጠቅሰን ነበር:: ይኸውም የጊዜውን ክፍተት የሚደፍንልንና የጸሓፊውን በሕይወት አለመኖር የሚያካክስልን ነገር መኖር አለበት:: ጊዜው ሩቅ ቢሆንም፣ ጸሓፊውም በሕይወት ባይኖርም፣ እነዚህን ትርጕም ወሳኝ ነገሮች የሚተካልን ሌላ ትርጕም ወሳኝ ነገር አለን — ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ ዐውድ[33]::

ሁነኛ ሐቲት መጽሐፍ ቅዱስ ታሪካዊና ባህላዊ ዐውዶች እንዳሉት ይገነዘባል:: ከፍ ሲል እንደ ጠቆምነው በመጽሐፍ ቅዱስ የጽሕፈት ሂደት ውስጥ ሰብአውያንም ድርሻ አላቸው:: የብሉይና የአዲስ ኪዳን ጸሓፊዎች የየራሳቸው ማንነት የነበራቸው ሰዎች ናቸው:: የእግዚአብሔር ቃል/መጽሐፍ ቅዱስ ለሰዎች የተሰጠው የራሳቸው ታሪካዊ ዐውድ ወይም ዳራ በነበራቸው ሰዎች አማካይነት ነው[34]:: የእነዚህን ሰዎች ጽሑፍ አንብቦ ለመረዳት ዳራቸውን ወይም መቼታቸውን ማወቅ ያስፈልጋል:: ለምሳሌ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በቀላሉ ለመረዳት እጅግ አስቸጋሪ የሆኑ ሐሳቦች አሉ:: እነዚህን ሐሳቦች በትክክል ለመረዳት ከጥንቱ ዓለም ጋር መተዋወቅ የግድ ያሻል[35]::

---

[31] Vanhoozer, *Is There a Meaning in This Text?* 338.

[32] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 342:: እንዲሁም E.D. Hirsch, Jr., *Validity in Interpretation* (New Haven: Yale University Press, 1967), 79.

[33] Vanhoozer, *Is There a Meaning in This Text?* 338-339.

[34] George Eldon Ladd, *The New Testament and Criticism* (Grand Rapids: Eerdmans, 1967), 72.

[35] David E. Garland, *Background studies and New Testament Internetation*, Ed. David Alan Black and David S. Dockery, *New Testament Criticism and Interpretation* (Grand Rapids: Zondervan, 1991), 350.



ከቀራጮችና ከኀጢአተኞች ጋር መብላት ምን ተአብ አለውና ነው የኢየሱስን ባላጋሮች ይሄን ያህል ያስጨነቃቸው (ሉቃ 5÷30፤ 7÷34፤ 15÷1)? "የተሰቀለው ክርስቶስ" (1ቆሮ 1÷23) የሚለው ቃል ለአይሁዳውያኑ ማሰናከያ፣ ለግሪካውያኑ ሞኝነት የሚሆነው እንዴት ነው? "ሴት በመውለድ ትድናለች" (1ጢሞ 2÷15) ማለት ምን ማለት ነው? ዮሐንስ "አንድም አውሬ ከባሕር ሲወጣ አየሁ" (ራእ 13÷1) ሲል ምን ማለቱ ነው? ከአያሌ አብነቶች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው::

እነዚህንና ሌሎችንም ጠንካራ ጥቅሶች ባነበብን ቁጥር ቆም ብለን ራሳችንን አከክ አከክ ማድረጋችን አይቀርም:: በግለ ሰብ ደረጃ ፍላቪየስ ጆሴፈስ (37-100 ዓ.ም) እና ፊሎ (20 ዓ.ዓ - 50 ዓ.ም) የተባሉ ሁለት አይሁዳውያን በጽሑፍ ያቆዩልን ሰነዶች ትልቅ ታሪካዊና ባህላዊ ዳራ ሊሆኑን ይችላሉ[36]:: ከ1947 እስከ 1960 ዓ.ም ድረስ በሙት ባሕር አካባቢ የተገኙት ጥንታዊ ጽሑፎች ለዳራ ጥናት ከፍተኛ ግምት ይሰጣቸዋል:: የአይሁድ ረበናት የጻፏቸውና ሚሽና፣ ታልሙድ፣ ታርጉምና ገመራ በመባል የሚታወቁት ሥነ ጽሑፎች በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን የነበረውን ሁኔታ ለመረዳት ጠቃሚ ምንጮች ናቸው:: በብሉይና በአዲስ ኪዳን ዘመን መካከል እንደ ተጻፉ የሚገመቱትና መጻሕፍተ አዋልድና (ወደ 15 የሚጠጉ መጻሕፍት) መጻሕፍተ አዋልድ ብሉይ (ወደ 65 የሚጠጉ መጻሕፍት) በመባል የሚታወቁት ሥነ ጽሑፎች ረጅም ዘመን ስለሚሸፍኑ (300 ዓ.ዓ - 300 ዓ.ም) በዳራ ጥናት ጊዜ ቁልፍ ድርሻ አላቸው[37]:: ከዚህም በተጨማሪ በድንጋይ፣ በሸክላ፣ በብረትና በፓፒረስ ላይ ተጽፈው በተለያዩ አጋጣሚዎች በምድር ሆድ ውስጥ ተቀብረው በከርሰ ምድር ጥናት የተገኙ ጥንታዊ ሰነዶች የጥንቱን ዓለም ሕይወት ለማወቅ ግሩም መረጃ ናቸው:: መጽሐፍ ቅዱስን በቅጡ ለመረዳት የሚደረግ ጥረት ብርቱ ትግል ያለበት ቢሆንም፣ ፍሬው ግን ጣፋጭ ነው:: በሐቲት ሂደቱ ወቅት ድቅድቅ ጨለማ በሚሆኑብን ምንባቦች ላይ ብርሃን የሚፈነጥቁልን ልዩ ልዩ ምንጮች አሉን:: በመሠረቱ ከዐይን ምስክር በላይ ምንም ዐይነት አሳማኝ ማስረጃ ሊኖር አይችልም[38]:: የጥንቱን ዓለም ሕይወት ለማወቅ ያሉን ምንጮች እነዚሁ ናቸው ለማለት ሳይሆን፣ ያነሣነውን ሐሳብ ግልጽ ለማድረግ የወሰድናቸው ናሙናዎች ብቻ ናቸው::

ሁነኛ ሐቲት በቀኖናቱ ውስጥ የሚያገኛቸውን እውነተኛ ውጥረቶች (ሒያምአዊ ዐዋጆች) በግልጽ ይቀበላል[39]:: በመጽሐፍ ቅዱስ አሻሚ ግን ደግሞ እውነ

---

[36] ፍላቪየስ ጆሴፈስ (በአገራችን ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን በመባል ይታወቃል) ከጻፋቸው መጻሕፍት መካከል "The Jewish war"፣ "The Antiquities of the Jewish" እና "Against Apion" ትልቁን ስፍራ ይይዛሉ::

[37] በእንግሊዝኛ Apocrypha and Pseudepigrapha / Apocrypha Old Testament ይሰኛሉ::

[38] Garland , *Background Studies and New Testament Interpetation*. 371.

[39] እዚህ ላይ የተከተልነው: Richard B. Hays, "*The Moral Vision of the New Testament: A Contemporary Introduction to New Testament Ethics*" (New York: Harpercollins Publishers

ትነት ያላቸው ሐሳቦች አሉ:: በሳይንሱም ዓለም እንዲህ ዐይነት ባሕርይ ያላቸው ነገሮች አሉ:: ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ብርሃን ነው:: ብርሃን ሁለት ዐበይት ባሕርያት አሉት:: አንደኛው ቅንጣጢት (······) ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ሞገድ (~~~~~~~) ነው:: አንድ ሰው ተነሥቶ ብርሃን በባሕሪው ቅንጣጢት ነው ቢል ያስሄደዋል:: ሌላው ሰው ተነሥቶ ደግሞ ብርሃን ሞገድ ነው ቢል ያስሄደዋል:: ሁለቱም ሰዎች ትክክል ናቸው:: ምክንያቱም ብርሃን በባሕሪው "ቅንጣጢትም ሞገድም" ነው:: ወደ ነገረ መለኮቱ ዓለም ስንመጣ ተመሳሳይ ነገር እናገኛለን:: ከእነዚህም ውስጥ አንዱ የእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና የሰዎች ተጠያቂነት ነው:: እግዚአብሔር ልዑል ነው ወይ ተብሎ ቢጠየቅ፣ መልሱ አዎን ነው (መዝ 103÷19፤ ዳን 4÷17:25:34፤ 5÷21፤ 7÷14፤ ማቴ 6÷13፤ 1ጢሞ 6÷15፤ ራእ 19÷16):: ሰዎች ተጠያቂ ናቸው ወይ ቢባል፣ መልሱ አዎን ነው (ሐሥ 3÷19፤ ሮሜ 2÷14-15፤ ሮሜ 5÷12፤ 7÷7፤ ጴጥ 1÷10-11):: አንድ ነገር እንርሳ! መጽሐፍ ቅዱስን ለመሐተት ስንነሣ፣ ተግባሩ ከሁሉ በፊት ከምንባቡ ጋር የምናደርገው ብርቱ ትግል ነው[40]:: ግን ምን ዐይነት ትግል? የተሰወረብንን ነገር ፈልቅቀን ለማውጣት የምናደርገው ትግል? አዎን እንዲህ ዐይነት ትግል አለ:: በእኛና በወዳጆችን መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት ለመፍታት የምናደርገው ትግል? አዎን እንዲህም ዐይነት ትግል አለ:: የእኔ ሐሳብ ከአንተ ሐሳብ ይበልጣል በሚል ፉክክር የምናደርገው የንጽሮተ ዓለም ትግል? አዎን እንዲህም መሰሉ ትግል አለ:: በአንድ በኩል "የጊዜ ክፍተቶችን" ወይም "ሁለት አድማሶችን" (ይኸውም የጥንቱን ዓለም አድማስና የእኛን አድማስ ለማያያዝ የሚደረግ ትግል ነው):: በሌላ በኩል ደግሞ ቋንቋዊ፣ ባህላዊ፣ ታሪካዊ፣ ልማዳዊ፣ ምግባራዊ፣ ወዘተ ጋሬጣዎችን ለማስወገድ የሚደረግ ትግል ነው:: እነዚህ ሁሉ የመጽሐፍ ቅዱስ አንባብያንና ሐታትያን የምንባቡን መልእክት እንዳይረዱ፣ ሐሳቡንም እንዳይጨብጡ ዕንቅፋት ይሆኑባቸዋል[41]:: ዕንቅፋቶቹ ምንም ያህል አስቸጋሪ ቢሆኑም፣ ትግሉ ግን ይቀጥላል - መልእክቱን ለመረዳት፣ ሐሳቡንም ለመጨበጥ::

ሁነኛ ሐቲት ራሱን ለመለወጥ ይጥራል:: በትንቢተ ኢሳይያስ 55÷11 ላይ እንዲህ የሚል ቃል እናነባለን:- "ከእኔ አንደበት የሚወጣውም ቃል የምሻውን ሁሉ ሳያደርግና ተልእኮውንም ሳይፈጽም በከንቱ ወደ እኔ አይመለስም":: ይህ ቃል ፍጹም እውነት መሆኑን ሌሎች ሁለት ምንባቦችን ጠቅሰን ማረጋገጥ እንችላለን:: በመጀመሪያ መጽሐፈ ነህሚያ ምዕ 8 እንመልከት:: ከምርኮ የተመለሰው ሕዝብ በኢየሩሳሌም ተሰብስቦ ነበር:: ዕዝራ መጽሐፉን ገልጦ ለሕዝቡ በሚያነብበት ጊዜ፣ ሕዝቡ ሁሉ ቆመው ነበር:: ይህን ክፍል/ሐረግ ቃል በቃል ብንተረጒመው:- "ሕዝቡም ሁሉ

1996) በተሰኘው መጽሐፉ ላይ ያቀረበውን ረቂቅ ነው::

[40] Paul Ricoeur, *A Ricoeur Reader: Reflection and Imagination*, Ed Mario J. Valdes (New York and Landon: Harvester Wheatsheaf, 1991), 494.

[41] Vonhoozer , *Is There a Meaning in This Text?* 407.



በተገለጠው መጽሐፍ ሥር ቆመው ነበር" የሚል እሳቤ አለው (ነህ 8÷5):: የሕዝቡ ምላሽ የሚያስደንቅ ነበር፤ "ሕዝቡም ሁሉ...በግምባራቸው ተደፍተው ለእግዚአብሔር ሰገዱ" (8÷6):: ሕዝቡ "የእግዚአብሔርን ሕግ መጽሐፍ ያነብብ" (8÷18) የነበረው በየዕለቱ ወይም በየቀኑ ለአንድ ሳምንት ነበር:: በስምንተኛው ቀን "የቀን ሩብ ያህል" ደግሞ ኀጢአታቸውን በመናዘዝ ለእግዚአብሔር ይሰግዱ ነበር (ነህ 9÷3):: እዚህ ላይ የምናስተውለው "የሕጉ መጽሐፍ" ምውት መጽሐፍ አለመሆኑን ነው:: ምንባቡ ምውት ምንባብ አይደለም:: ይልቁንም ሕያውና የሚሠራ ነው (ዕብ 4÷12)::

ከዚህ በመቀጠል የምንመለከተው የሐዋርያት ሥራ ምዕ 2 ነው:: በዚህ ክፍል የምናነበው የጴጥሮስን ንግግር/ስብከት ነው:: የስብከቱ ጭብጥ መሲሑ ማለትም ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን፣ እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ (2÷23) የሕዝቡን መድኅን እንዴት እንደላከውና የተላከውም መድኅን ሥራውን እንዴት እንዳከናወነ (2÷31-36) ይገልጻል:: ገለጻውን የሰሙ ሰዎች "ልባቸው ተነካ" (2÷37)፤ ከዚያም ሐዋርያቱን፣ "ወንድሞች ሆይ! እንግዲህ ምን እናድርግ" በማለት አበክረው ጠየቋቸው:: የሰሙት መልእክት ነፍስና ሥጋቸውን የሚለያይ በመሆኑ ሊቋቋሙት አልቻሉም:: ስል ቢላዋ ያገኘው ሥጋ እንደሚቈራረጥ ሁሉ፣ ለእግዚአብሔር ቃል የተጋለጠችም ነፍስ ሁለመናዋ ዕርቃኑን ይቀራል፤ ያላትን አንድ ብቸኛ ተስፋ እንድታይ - መሲሑን:: ሁነኛ ሐቲት እውነትን በተረዳ ጊዜ እጁን ለእውነት ይሰጣል:: ምክንያቱም እውነት ስጦታ ናት:: የሚያገኟትም ተግተው የሚፈልጓት ናቸው[42]:: "የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል" (ዮሐ 16÷13):: *በሐቲት/ በትርጓሜ ሂደት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ትርጒሙን መለወጥ ሳይሆን ትርጒም እንዲኖረው ማድረግ ነው*[43]:: በዚህ ዐይነት "...ቃሌ የላክሁትንም ይፈጽማል" (ኢሳ 55÷11) የተባለው እውን ይሆናል::

በመጨረሻም አንድ ነገር ለማስገንዘብ እንወዳለን:: ይኸውም መጽሐፍ ቅዱስን መሐተት ወይም መተርጐም በእምነት፣ በተስፋና በፍቅር ላይ የተመሠረተ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስን ገልጠን ስናነብ አንድ የሚያናግረን ድምፅ አለ፤ የሚመክረን ካስፈለገም የሚወቅሰን፤ የሚያጽናናን ካስፈለገም የሚኮንነን ሕያው አካል አለ:: በመሆኑም የምናነበውን መጽሐፍ በእምነት ስለምናነብ ለእኛ የሚሆን መልእክት አለው ማለት ነው:: በሌላ በሉል ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ እየተረጐምንና እየተነተንን ነው፤ ግን የምንተረጒመውና የምንተነትነው በመንፈስ ቅዱን ኀይል ነው:: በመሆኑም መንፈሱ ወደ እውነት ሁሉ እንደሚመራንና ነገሩን መረዳት እንድንችል እንደሚያግዘን ተስፋ እናደርጋለን:: ይህ ሁሉ የሚሆነው ግን ለቃሉ ፍቅር ሲኖረን

[42] የክርስቶስ እውነት (ዮሐ 16÷14) አንድም ስጦታ ነው፤ አንድም ተግባር ነው:: በሌላ አነጋገር በአንድ በኩል የተጻፈ ቃል አለን፤ ይህ ስጦታው ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ የተጻፈውን ቃል መተርጐም አለብን፤ ይህ ተግባሩ ነው:: ግን ልብ እንበል "እውነት የጊዜ ልጅ ናት":: በአገራችንስ "እውነትና ንጋት እያደር ይጠራሉ" ይባል የለ (Vanhoozer ፤ ገጽ 429)::

[43] Vanhoozer, *Is There a Meaning in This Text?* 428.

ነው:: ራሳችንን ሰጥተን ቃሉን በትጋት መመርመር ይኖርብናል:: እንዳንስትና ከእግዚአብሔር ሐሳብ ተሸቀንጥረን እንዳንወጣ የሚያደርጉን እምነት፣ ተስፋና ፍቅር ናቸው[44]::

በትርጓሜ ሂደት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ሦስት ተግባሮች አሉት:: አንደኛው መንፈስ ቅዱስ ያሳምነናል፤ ማለትም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል እንደሆነ ያሳስበናል:: የምናነበው ቃል የሰዎች ፍልስፍና ሳይሆን የራሱ የእግዚአብሔር መገለጥ እንደሆነ ይመሰክርልናል[45]::

ሁለተኛው መንፈስ ቅዱስ ያበራልናል፤ ማለትም ቃሉን ይገልጥልናል፤ ምን ማለት እንደሆነ ይተነትንልናል:: መንፈስ ቅዱስ የቃሉን ትርጕም ለውጦ ወይም አሻሽሎ አይነግረንም:: ይልቁንም የቃሉን ቀጥተኛና ትክክለኛ ትርጕም ይሰጠናል[46]::

ሦስተኛው መንፈስ ቅዱስ ቃሉ የሚያስተምረንን እንድንቀበል ያግዘናል:: በአንድ በኩል ቃሉን የሚሠራ ማለትም ሕያው ቃል ያደርግልናል:: በሌላ በኩል ደግሞ የእኛን ትርጓሜ ሳይሆን የራሱን የመንፈስ ቅዱስን ትርጓሜ እንድንቀበል ይረዳናል:: ቃሉን በመንፈስ መተርጐምና መሐተት ማለት አዲስና ባዕድ ሐሳብ ወደ ቃሉ መጐተት ማለት ሳይሆን ቃሉ ቃል እንዲሆንና ከሕይወታችን ጋር እንዲዛመድ ማድረግ ነው:: ቃሉን በትክክል እንድንረዳ የሚያስችለን መንፈስ ቅዱስ ነው:: እንዲህ ሲባል ግን መንፈሱ ቃሉን የሚያበራልንና የሚገልጥልን ያለ እኛ ጥረት ነው ማለት አይደለም:: እኛ ቃሉን ስንተረጕም፣ ስንመረምርና ከሕይወታችን ጋር ስናገናዝብ መንፈሱ ደግሞ ምንባቡ ምን እንደሚል ይገልጥልናል፤ ይተረትርልናል (ሐሥ 8÷31፤ ዮሐ 16÷13)[47]:: እና እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስን መሐተትና መተርጐም የሁለት ወገን ሥራ ሊሆን ነው—የመንፈሱና የእኛ::

በመንፈሱ ሥልጣን ሥር የሚኖሩ ሁሉ በመንፈሱ ለተጻፈው ቃል መገዛት አለባቸው፤ ደግሞም በቃሉ ሥልጣን ሥር የሚኖሩ ሁሉ መንፈሱ ቃሉን እንዲተረጕምላቸው መለመን አለባቸው[48]:: መንፈሱ ቃሉን እንዲገልጥልን ስለ ተሰጠን እጅግ እድለኞች ነን:: እናም ጸሎታችን Veni Spiritus Interpres (ተርጓሚው መንፈስ ሆይ ና) መሆን አለበት[49]:: እውነትም ተርጓሚው መንፈስ ሆይ ና አብራልን፤ ገላልጥልን!!

---

[44] Vanhoozer, *First Theology*. 231-233.

[45] John Stott, *Understanding the Bible* (Leicester: Scripture Union, 1988), 156-183.

[46] Fred H.Klooster, "*The Role of the Holy Spirit in the Hermeneutic Process*" in Hermeneutics, Inerrancy and the Bible, Eds. Earl D.Radmacher and Robert D.Preus (Grand Rapids: Zondervan, 1989), 468.

[47] J.I.Packer, *Keep in Step with the Spirit* (Leicester: InterVarsity Press, 1984), 239.

[48] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 240::

[49] Vanhoozer, *First Theology*. 468.

# ሙዳየ ቃላት

**ልዩ መገለጥ (Special Revelation)**

ለዩ መገለጥ ወጀአዊ መገለጥ ነው:: ቅዱስና መሐሪ የሆነው አምላክ፣ የሰው ልጅ ራሱን ማዳንም ሆነ ራሱን ለድኅነት ማዘጋጀት ያለመቻሉን ስለሚያውቅ በልጁ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ወጀአዊ ሥራ አማካይነት ዓለምን ያዳነበት መንገድ ነው:: እግዚአብሔር ራሱን በልጁና በመጽሐፍ ቅዱስ የገለጠበት መንገድ ልዩ መገለጥ ይባላል::

**ሕዝባዊ ሕግ (Civil and Criminal Law)**

ይህ የብሉያት ሕግ የእስራኤልን ሕዝብ ደኅንነት የሚያስጠብቅ ሕግ ነው:: አጥፊ እንዴት እንደሚቀጣ የሚገልጠው ሕግ ሕዝባዊ ወይም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ይባላል:: ይህ ሕግ በአዲስ ኪዳንዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተፈጻሚ የሚሆን ሕግ አይደለም::

**መለኮት ትእዛዝ ንድፈ ሐሳብ (Divine command theory) (የ—)**

እግዚአብሔር በማናቸውም ዐይነት ቦታ፣ ሁኔታና ጊዜ ሊለወጡ የማይችሉ ግብረገባዊ ትእዛዛትን ወይም ሕግጋትን ሰጥቶአል የሚል ንድፈ ሐሳብ ነው::

**መርሐ ተኩር፣ መርሐን ታሳቢ ያደረገ (Normative Ethics or deontological systems)**

መርሖ ተኩር ሥነ ምግባር፣ የአንድ ምግባር (ወይም ባሕርይ፣ ድርጊት፣ የልብ ፍላጎት) ሠናይነትና እኩይነት የሚወሰነው ሥነ ምግባራዊ መርሖችን መሠረት በማድረግ ነው፣ የሚል የግብረገብ አካሄድ ነው:: በመርሐ ተኩር ሥነ ምግባር ወስጥ የሚካተቱት (1) *የመለኮት ትእዛዝ ንድፈ ሐሳብ* (2) *የተፈጥሮ ሕግና* (3) *ሥነ ምግባራዊ ምክኑያዊነት* ናቸው:: ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር መሠረት የሚያደርገው ፍጹማን በሆኑት የአምላክ ትእዛዛት ላይ ስለሆነ፣ ክርስቲያኖች የሚከተሉት መርሖ ተኩር የሚባለውን የሥነ ምግባር አካሄድ ነው::

**መንሥኤና ተገብሮት (Cause and Effect)**

ተገብሮት ተገበረ ከሚለው ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጕሙም ድርጊት፣ ክንውን ማለት ነው:: መንሥኤ ማለት አዲስ ክሥተትን የሚያስገኝና ከእርሱም ጋር ካለው ግንኙነት አንጻር ሲታይ ቀድሞት የሚገኝ ክሥተት ነው:: ተገብሮት መንሥኤ የሚያስከተለውና የርሱም ድረጊት የሚፈጥረው ክሥተት ነው::

**መግቦት (Provision)**

ማለት መመገብ፣ መቀለብ፣ ማብላት፣ ማጠጣት፣ መጠበቅ፣ ለመጠበቅ መከበብ፣ መምራት፣ ማስተማር፣ በሥርዐት ማስሄድ ወዘተ ማለት ነው:: መግቦተ እግዚአብሔር ሲባል አምላክ ይህን ሁሉ እንደሚያደርግ ለማሳየት ነው::

**ሙግት (Argument)**

ሙግት ተራ ጭቅጭቅ ማለት አይደለም:: ነገር ግን ትክክለኛ ናቸው የሚባሉ የሙግት ነጥቦችን በማቅረብ ወደ ድምዳሜ መድረስ ነው:: ሙግትን ለማብራራት ሁለት መሠረታዊ ቃላትን

ማብራሪት ግድ ይላል:: እነዚህም ቃላት *ትክክለኛነትና* (validity) *ርቱዕነት* (soundness) ናቸው:: *ትክክለኛነት* የሚለውን ቃል የምንጠቀመው ማስረጃ በማቅረብ ወይም በሙግት ሂደት ውስጥ እንጂ፣ በአንድ የተወሰነ ዐረፍተ ነገረ ውስጥ አይደለም:: ለምሳሌ:- "ዝናቡ እየዘነበ ነው"፣ "ሐዲስ ዓለማየሁ በ49 ዓመታቸው ሞቱ"፣ "2+2=4" ወዘተ የሚሉት ዐዋጆች (አነጋገሮች) እውነት ወይም *ስሕተት* (invalid) አይደሉም::

ነገረ ሙግት የሚያጠነጥነው *ትክክለኛና ትክክለኛ* ባልሆኑ ሙግቶች ዙሪያ ነው:: አንድ ሙግት ትክክለኛ ነው የሚባለው የሙግት ነጥቦቹ (premises) እውነት ሆነው፣ ድምዳሚውም እውነት ሲሆን ነው:: ስለዚህ ትክክለኛ በሆነ ሙግት የሙግት ነጥቦቹ ደምዳሚውን እውነት እንዲሆን ያደርጉታል:: አስረጅ:-

ሀ)

1) ዝናብ የሚዘንብ ከሆነ ሣሩ ይረጥባል::
2) ዝናብ እየዘነበ ነው::
3) ስለዚህም ሣሩ ረጥቦአል::

ይህ ሙግት ትክክለኛ ሙግት ነው:: በቍጥር 1 እና 2 ላይ የተገለጹት የሙግት ነጥቦች በቍጥር 3 ላይ ለተቀመጠው ደምዳሜ በማስረጃነት ቀርበዋል:: የሙግት ነጥቦቹ ማለትም ቍጥር 1 እና 2 ትክክለኛ ከሆኑ ድምዳሜውም የግድ እውነተኛ ይሆናል::

ሌላ ሙግት እንመልከት:-

ለ)

1) ዝናብ የሚዘንብ ከሆነ ሣሩ ይረጥባል::
2) ሣሩ ረጥቦአል::
3) ዝናብ እየዘነበ ነው::

ይህ ደግሞ ትክክለኛ ያልሆነ ሙግት ነው:: አሁንም ቍጥር 1 እና 2 የሙግት ነጥቦች ሲሆኑ ቍጥር 3 ደግሞ ድምዳሜ ነው:: ቍጥር 1 እና 2 እውነተኞች ናቸው ብለን በናስብ ድምዳሜው ሐሰት ነው:: 1 እና 2 እውነት ሆነው ሳለ ድምዳሜው ግን ሐሰት ነው:: ሣሩ የረጠበው አትክልተኛው ስለጠጣው ሊሆን ይችላል:: ቍም ነገሩ እነዚህ የሙግት ነጥቦች እውነት ቢሆኑም እንኳ ድምዳሜው ግን ሐሰት ነው:: ይህን የሚመስሉ ሙግቶች ትክክለኛ ያልሆኑ ሙግቶች (invalid arguments) ይባላሉ::

አሁን ደግሞ ርቱዕ (sound) የሆነ ሙግት ምን እንሚመስል እንመልከት:: አንድ ሙግት *ርቱዕ* ነው የሚባለው *ትክክለኛና* የሙግት ነጥቦቹ ሁሉ እውነተኞች ሲሆኑ ነው:: ስለዚህ ርቱዕ መሆን ትክክል ከመሆን ይልቅ ጠንካራ ነው:: አንድ ሙግት ርቱዕነቱን ለማረጋገጥ የሙግት ነጥቦቹ እውነት ናቸው ወይስ ውሸት የሚለውን ጉዳይ ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

የሚከተለውን ሙግት እንመልከት:-

ሐ)

1) መንግሥቱ ንዋይ ከታነቀ ይሞታል::
2) መንግሥቱ ንዋይ ታንቄአል::
3) መንግሥቱ ንዋይ ሞቶአል::

ሙግት (ሐ) ከሙግት ከሙግት (ሀ) ጋር አንድ ዐይነት እንደ ሆነ ልብ ይሏል:: ድምዳሜውም የሙግት ነጥቦቹን (premises) የተከተለ ነው:: በተጨማሪም እያንዳንዱ የሙግት ነጥብ ትክክልና እውነት ነው፣ ስለዚህ ይህ ሙግት ርቱዕ ሙግት ነው::



## ምክኑያዊ እውነታ (Rational Truth)

ግብረገባዊ እውነታን ይመለከቷል::

## ምግባረ ተኮር (Action-oriented)

የሥነ ምግባር አካሄድ ሲሆን፣ አንድን ምግባር ከግብሩ በመነሣት (ከተከናወነው ሥራ በመነሣት) ድርጊቱ ሠናይ ነበር ወይስ እኩይ ነበር የሚለውን ብያኔ በመስጠት ላይ መሠረት ያደረገ የሥነ ምግባር አካሄድ ነው::

## ሠናይና እኩይ (Good and Evil)

ሰናይ ማለት መልካም፣ ውብ፣ ደግ በጎ፣ በጠባዩ ደስ የሚያሰኝ ማለት ሲሆን፣ እኩይ ማለት ደግሞ የከፋ ክፉ፣ መጥፎ ማለት ነው::

## ሥርዐታዊ ነገረ መለኮት (Systematic Theology) (የ—)

እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ንባባት ወይም መጻሕፍት በምን ይለያያሉ በምንስ ይመሳሰላሉ የሚለውን ጉዳይ ሳይሆን፣ የመጽሐፍ ቅዱስን አስተምህሮ ርእስ እየሰጠ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በርእስ ጉዳዩ ላይ ያለውን ትምህርት ደርዝ ባለው መልኩ የሚተነትን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት በትምህርታቸው ስምሙና ወጥ መሆናቸውን የሚያሳይ የነገረ መለኮት ጥናት ነው::

## ሥርዐት አምልኮ ሕግ (Ceremonial Law) (የ—)

ይህ የብሉይ ሕግ እስራኤል አምላኳ እግዚአብሔርን እንዴት ማምለክ እንዳለባት እንዲሁም በሥርዐት አምልኮዋ ምን ምን መካተት እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው የሚገልጸው ሕግ የሥርዐት አምልኮ ሕግ በመባል ይታወቃል:: ይህ ሕግ በአዲስ ኪዳንዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተፈጻሚ የሚሆን ሕግ አይደለም::

## ሥነ ምግባራዊ ምክኑያዊነት (Ethical rationalism)

ግብረገባዊ ሕጋጋት ፍጹማን እንደ ሆኑ የሚያምንና እነዚህ ሕጋጋት ምክንዩአዊ ስለሆኑም ልንታዘዛቸው ይገባል የሚል መርሖ ላይ ትኩረት የሚያደርግ የሥነ ምግባር አካሄድ ነው::

## ሥነ ምግባራዊ ፈቃደኝነት (Ethical Voluntarism)

ነገሮች መልካም የሚሆኑት እንዲያው እግዚአብሔር ስላዘዘ እንጂ ነገሮቹ በራሳቸው መጥፎም ሆነ ጥሩ ስለሆኑ አይደለም የሚል የመለኮት ትእዛዝ ንድፈ ሐሳብ ነው::

## ሥነ ምግባራዊ እኔነት፣ ምግባርዊ እኔነት፣ የሰብእውያንን ፍላጉት የሚያረካ ውጤት ተኩር አካሄድ (Ethical egoism)

በመባል የሚታወቀው የሥነ ምግባር መርሐ፣ ምግባሮች በአንድ ሰው የግል ፍላጎት የሚበየኑ ናቸው የሚል አመለካከት ነው:: የግለሰብን ፈላጎት የሚያረካው ምግባር ትክክለኛ ምግባር ነው፤ የግለሰብን ፍላጎት የማያረካው ደግሞ ኢግብረገባዊ ነው::

## ሥነ ኑባሬ (Ontology)

የኑባሬን አጠቃላይ መርሕ፣ አወቃቀርና ሕግጋት የሚያጠና ሲሆን፣ መሠረታዊ ሐሳቡም የማናቸውም ነገር የመኖር መሠረት የሚገለጸው በክሥተቱ ሳይሆን (ቀለሙ፣ መጠኑ፣ ወዘተ) የክሥተቶቹ ተሸካሚ በሆነው በሕርዮት ነው የሚል የፍልስፍና ዘርፍ ነው:: ዲበ አካልን ይመለከቷል::

## ሥነ አመክንዮ (Logic)

እርስ በርሳቸው የተያያዙና የማይፈለሱ ሐሳቦች ከአንድ መንደርደሪያ ሐሳብ በመመንጨትና ከርሱም ጋር በመያያዝ በተወሰኑ የአስተሳሰብ ሕግጋት መሠረት ወደ ትክክለኛው መደምደሚያ የሚያመሩበትን ሁኔታ የዚህም ውጤት ሆኖ የሚቀረጸውን የሐሳብ ቅርጽ ሥርዐት የሚያጠና ሳይንስ ነው::

## ሥነ ዕውቀትን (Epistemology)

የዕውቀት ጥናት ምርምር ንድፈ ሐሳብ ማለት ነው:: ጥናቱ የሚያተኩረው በዕውቀት ምንነትና መጠረቶች ላይ ሲሆን በተለይም የዕውቀትን ወሰንና ትክክለኛነቱን የሚመዝኑ ነጥቦችን ይመረምራል:: እውነት ከነባራዊ እውነታ ጋር ምን ግንኙነት አለው? የዕውቀት መነሻና መሠረቶች ምንድን ናቸው? የዕውቀት አመጣጡ እንዴት ነው? የዕውቀት ዳር ድንበሩ እስከየት ነው? እውነትነቱስ በምን ይለካል? የሚሉትን ጥያቄዎች የሚያጠና የፍልስፍና ክፍል ነው::

## ሥነ ምግባራዊ ምክኑያዊነት (Ethical Rationalism)

የሥነ ምግባር ሕግጋትን የመናገኘው ከአመክንዩ (Reason) ነው ወይም የሥነ ምግባር መርሖች የአመክንዩ አንድ አካል ናቸው የሚል፣ መርሖ ተኮር የሥነ ምግባር ንድፈ ሐሳብ ነው::

## ሥነ አመክንዩ (Logic)

እርስ በርሳቸው የተያያዙና የማይፋለሱ ሐሳቦች ከአንድ መንደርደሪያ ሐሳብ በመመንጨትና ከርሱም ጋር በመያያዝ በተወሰኑ የአስተሳሰብ ሕግጋት መሠረት ወደ ትክክለኛው መደምደሚያ የሚያመሩበትን ሁኔታና የዚህም ውጤት ሆኖ የሚቀረጸውን የሐሳብ ቅርጽና ሥርዐት የሚያጠና ሳይንስ ነው::

## ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ (Literary genres)

መጽሐፍ ቅዱስ ከዳር (ዘፍጥረት) እስከ ዳር (ራእየ ዮሐንስ) ድረስ የተጻፈው በአንድ ዐይነት የአጻጻፍ ስልት/ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ አይደለም:: ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ ስንል የጽሑፍ ዐይነት ማለታችን ነው:: ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ (ወይም የጽሑፍ ዐይነት) የምንለው ግጥምን፣ ትረካን፣ ተውኔትን፣ ተረትና ምሳሌን፣ ሕግን፣ አቡቀለምሲስን ወዘተ ያሉትን የአጻጻፍ ስልቶች ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በትንሹ ከዐሥር በላይ ዋና ዋና የሆኑ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጾችን እናገኛለን::

## ርቱዕ (sound)

እርቶዶክስ ለሚለው የግሪክ ቃል አቻ ነው:: የቀና፣ ቀጥ ያለ፣ የተስተካከለ፣ ሀባጣ ጉባጣ ያልሆነ ማለት ነው::



## ስሜታዊነት (Emotivism)

እኩይ፣ ሠናይ ወዘተ የሚሉት ቃላት የሰዎችን ፍላጎት ከመግለጽ ያለፈ ትርጉም የላቸውም የሚል አስተሳሰብ ነው::

## ቅራኔ አልባ ሕግ (Law of noncontradiction)

ቅራኔ አልባ ሕግ፣ አንድ ነገር በአንድ ጊዜ፣ በታና ሁኔታ ውስጥ የሆነውን ነገር ያለመሆን አይችልም::

## ባህላዊ (ተገላጭ) አንጻራዊነት (Cultural or Descriptive Relativisim)

ሰዎች የተለያየ ባህል አላቸው፣ እነዚህም ባህሎች መሠረታዊ በሆኑት ግብረገባዊ ፋይዳዎች ላይ ይለያያሉ የሚል አቋም ነው:: እያንዳንዱ ባህል የራሱ የሆነ፣ ከሌላው የተለየ ግብረገብ ስላለው፣ አንዱ ሌላውን የእኔ ግብረገብ ትክክል ነው፣ የአንተ ደግሞ ትክክል አይደለም ማለት አይችልም:: እንደዚህ አመለካከት ነባራዊ የሆነ ግብረገብ ወይም ፍጹማዊ የሆነ ግብረገብ የለም፤ ግብረገብ አንጻራዊ ነው::

## ብሔረ ኦሪትን (ፔንታቱክን)

አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት (ኦሪት ዘፍጥረት፣ ኦሪት ዘፀአት፣ ኦሪት ዘሌዋውያን፣ ኦሪት ዘኍልቍና ኦሪት ዘዳግም) ብሔረ ኦሪት ወይም ፔንታቱክ በመባል ይታወቃሉ::

## ብዝኃ ሃይማኖታዊነት (Religious pluralism)

ሃይማኖቶች ሁሉ ሰዎችን ወደ ድኅነት ያመጣሉ የሚል አስተሳሰብ ነው::

## ተገላጭ ሥነ ምግባር (Descriptive Ethics)

ተገላጭ ሥነ ምግባር፣ የሰዎችን ባህል በማጥናት የማኅበረሰብን ግብረገብ ይገልጻል:: ገላጭ ሥነ ምግባር የሚለውን ይመለከቷል::

## ተፈጥሮ ሕግ (Natural Law) (የ—)

## ተፈጥሮ ሕግ (Natural Law)(የ—)

የሥነ ምግባር ሕግጋትን የምናገኘው ከተፈጥሮ ሕግጋት ነው ወይም የሥነ ምግባር መርሖች የተፈጥሮ ሕግጋት አንድ አካል ናቸው የሚል፣ መርሖ ተኮር የሥነ ምግባር ንድፈ ሐሳብ ነው::

## ተገላጭ ሥነ ምግባር (describtive)

ገላጭ ሥነ ምግባር የሚለውን ይመለከቷል::

## ተሞክሮአዊ ዕውቀት (a posteriori knowledge)

ጭልታዊ ዕውቀት የሚለውን ይመለከቷል::

## ተጣራሽ ፍጹማዊነት (Conflicting Absolutism)

እግዚአብሔር በርካታ የሆኑ ፍጹማዊ ግዕዛንን ለሰው ልጆች መስጠቱን፣ እነዚህም ግብረገባዊ ግዕዛን በአንድ ሁኔታ ውስጥ ተደራርበው በመምጣት ሰዎችን ውጥረት ውስጥ ሊያስገቡ ይችላሉ የሚል የግብረገባዊ ፍጹማዊነት አንዱ ቅርንጫፍ ነው::

## ተዋረዳዊ ፍጹማዊነት (Graded Absolutism)

መጽሐፍ ቅዱስ ፍጹማዊ የሆኑ ግብረገባዊ መስፈርቶች እንዳሉት ያምናል። በሁለት ግብረገባዊ ሕግጋት ስንያዝ፣ የተሻለ ውጤት የሚያመጣውን ሕግ መከተል አስፈላጊ ነው ከሚለው ከተጣራሽ ፍጹማዊነት አመለካከት ጋር ተመሳሳይ አቋም ይጋራል። ነገር ግን ይህን አመለካከት ከተጣራሽ ፍጹማዊነት የሚለየው፣ በሁለት ሕግጋት ስንከበብ (ስንያዝ) ለከፍተኛው ሕግ በመታዘዝ ዝቅተኛውን ሕግ ማፍረሳችን መልካም ማድረጋችን እንጂ፣ መለስተኛ ክፋት (ኀጢአት) ማድረጋችን አይደለም፤ እግዚአብሔር የሰጠን ግብረገባዊ ሕግጋት ተዋረዳዊ ስለሆኑ፣ በማይወገዱ በግብረገባዊ ግጭቶች ውስጥ በምንወጠርበት ጊዜ፣ ከፍተኛውን ሕግ መታዘዝ ይኖርብናል የሚል ነው።

## ትረካያዊ ሥነ ምግባርን (Narrative Ethics)

ትረካያዊ ሥነ ምግባርን የሚከተሉ ምሁራን፣ ታሪክን መተረክ ነገረ መለኮትን ለማስተማር ዐይነተኛ መንገድ ነው የሚል እምነት አላቸው። ትረካያዊ ሥነ ምግባር ዐላማ ያደረገው፣ እጅግ ውስብስብና "የማይጨበጡ" ሥነ ምግባራዊ ችግሮችን መፍታት ሳይሆን፣ የሰዎችን ግብረገብ ማሳደግ ነው።

## ኀሊናዊ እውነታ (Subjective truth)

አንድ ሰው፣ "የኀመን ወጥ እወዳለሁ" ቢል፣ ግለሰቡ በምግቡ ላይ ያለውን የራሱን አስተያየት (ጣዕም) እየተናገረ እንጂ፣ ስለ ኀመን ወጥ እየተናገረ አይደለም። ይህ ኀሊናዊ እውነት ይባላል። አንድ ሰው ይህ ምግብ ይጣፍጠኛል፣ ያ ምግብ ደግሞ አይጣፍጠኝም ቢል፣ "እንዴት ሊጣፍጥህ ወይም ላይጣፍጥህ ቻለ? ይህ ትክክል አይደለም" ልንለው አንችልም። አንድ ሰው ሁለት ሲደመር ሁለት ይሆናል አራት ቢል፣ እየተናገረ ያለው የግሉን "ጣዕም" ሳይሆን ከግለሰቡ ውጪ ስላለው ነባራዊ እውነታ ነው። ይህ ደግሞ ነባራዊ እውነታ ይባላል።

## ነባራዊ እውነታ (objective truth)

ኀሊናዊ እውነታን ይመለከቷል።

## ንግሮች (Oracles)

ይህ ቃል በብሉይ ኪዳን ንባባት በተለይ በነቢያት መጻሕፍት ውስጥ የተለያዩ ትርጒሞችን ወክሎ የሚገኝ ሲሆን፣ ከእነዚህ በርካታ ትርጒሞች ውስጥ "ሸክም" በሚለው ትርጒሙ በሰፋት ጥቅም ላይ ውሎአል። በአዲስ ኪዳን ንባባት ግን የእምላክን ንግግር በሚያሳይ መልኩ ነው ጥቅም ላይ የዋለው።

## ንድፈ ሐሳብ፣ ትውርት (Theory)

የእውነታን የተለያዩ ክፍሎች ሥርዐት ባለውና በተቃለለ ሁኔታ የሚገልጽ ዕውቀት ንድፈ ሐሳብ ይባላል።

## ነጻዊነት አመለካከት (እሳቦት) [Liberterian or Freedom] (የ—)

ሕግ በሰዎች ነጻነት ላይ ድንበር የሚያበጅ ስለሆነ ሕግ አስፈላጊ አይደለም የሚል አስተሳሰብ ነው።



## ነባራዊ እውነታ (objective truth)

አንድ ሰው፣ "የኀመን ወጥ እወዳለሁ" ቢል፣ ግለሰቡ በምግቡ ላይ ያለውን የራሱን አስተያየት (ጣዕም) እየተናገረ እንጂ፣ ስለ ኀመን ወጥ እየተናገረ አይደለም። ይህ ኀሊናዊ እውነት ይባላል። አንድ ሰው ይህ ምግብ ይጣፍጠኛል፣ ያ ምግብ ደግሞ አይጣፍጠኝም ቢል፣ "እንዴት ሊጣፍጥህ ወይም ላይጣፍጥህ ቻለ? ይህ ትክክል አይደለም" ልንለው አንችልም።

ነገር ግን "የጣዕምን" ጉዳይ ወደ ጉን ትተን፣ ስለ ቍጥር እንነጋገር። አንድ ሰው ሁለት ሲደመር ሁለት ይሆናል አራት ቢል፣ እየተናገረ ያለው የግሉን "ጣዕም" ሳይሆን ከግለሰቡ ውጪ ስላለው ነባራዊ እውነታ ነው።

ሁለት ሲደመር ሁለት ይሆናል አምስት ቢባል ስሕተት ነው። ነገር ግን ስሕተት ነው ስንል፣ ግብረገብን ታሳቢ አድርገን አይደለም። የሒሳብ ስሌቶች ሁለት መልስ ብቻ ይኖራቸዋል፤ እውነት ወይም ሐሰት። የሒሳብ ስሌቶች በግለሰቦች "ጣዕም" የሚወሰን በርካታ (የተለያዩ) "እውነቶች" የሏቸውም። በስሌቱ ውጤት ላይ የማንግባባ ከሆነ፣ ልዩነቱን የምንፈታው፣ በቀመሩ መሠረት ሒሳቡን እንደ ገና በማስላት ነው። ይህን የምናደርገው ተመሳሳይ ስሜት ለመጋራት ሳይሆን፣ ትክክለኛውን መልስ ለማግኘት ነው። የስሌቱ እውነታ ያለው ግለሰቡ ዘንድ ሳይሆን፣ ነባራዊ በሆነው ድምር ላይ ነው።

ኀሊናዊ እውነቶች መሠረት ያደረጉት በግለሰቦች ምርጫ ላይ ነው፤ ይህም ምርጫ ስሕተት ነው ወይስ ትክክል ነው የሚለውን በአመክንዮ መመርመር የሚቻል አይደለም። በአንጻሩ ነባራዊ እውነታዎች በሰዎች ውስጣዊ ስሜት ላይ መሠረት ያደረጉ ስላልሆነ፣ በሁኔታዎች የሚለወጡ አይደሉም።

## ንጽሮተ ዓለም (Worldview)

ሰዎች ስለእግዚአብሔር፣ ስለራሳቸው፣ ስለኀጢአት፣ ስለድኅነትና ስለዘላለም ሕይወት ያላቸው ዕውቀትና ይህንን ዕውቀት መሠረት አድርገው የሚኖሩት ኑሮ ንጽሮተ ዓለም ይባላል።

## አቡቀለምሲስ (Apocalyptic)

የሥነ ጽሑፍ ቅርጽ ነው። ራእየ ዮሐንስ፣ ትንቢተ ሕዝቅኤል፣ ትንቢተ ዘካርያስና የትንቢተ ኢሳይያስ አቡቀለምሲሳዊ የሆነ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ አላቸው መጻሕፍት ናቸው። ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ ትንቢታዊ፣ ደበደቤያዊና አቡቀለምሲሳዊ የሆኑ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጾችን አጠቃሎ የያዘ ነው። ይህ ዐይነቱ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ፣ በራእዮች፣ በሕልሞችና በተምሳሌታዊ ገለጻዎች የተሞላ ነው።

## አመክንዩ (Reason)

አመክነየ ምክንያት ሰጠ፣ ምክንያት አቀረበ ከሚለው የግእዝ ቃል የመጣ ነው።

## አማኒነት (Theism)

ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ኀይል ማለትም በእግዚአብሔር፣ በአማልክት፣ በመናፍስተና ከሞት በኋላ ባለ ሕይወት የሚያምን ሃይማኖት ወይም የፍልስፍና ንድፈ ሐሳብ ነው።

## አምላከ ገዝ (Theocratic)

አምላከ ገዝ የጥንቷ እስራኤል ትተዳደርበት የነበረው ሕዝባዊና ሥርዐተ አምልኮ ሕግ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስለነበር፣ አምላከ ገዝ አገር ትባል ነበር። እንደ ኢራንና ሳውዲ ዐረብያ ያሉ እስላማዊ አገሮች ሕዝባዊና ሥርዐተ አምልኮ ሕጋቸው የእግዚአብሔር ቃል ነው በሚሉት በቍርዓን ላይ መሠረት ያደረገ ስለሆነ፣ አምላከ ገዝ መንግሥታት ተብለው ይጠራሉ።

## አርኤቲክ (Aretaic or Virtue)

ፍቅር፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ የዋህነት፣ ትሕትና፣ ርኅራኄ ወዘተ ያሉት ባሕርያት አርኤቲክ ይባላሉ::

## አርኤቲክ ሥነ ምግባር (Aretaic Ethics or Virtue Theory)

አርኤቲክ ሥነ ምግባር በሰዎች የባሕርይ ቀረጻ ላይ ትኩረት የሚያደርግ የሥነ ምግባር ዘርፍ ነው:: አርኤቲክ የሚለው ቃል የተወሰደው ከግሪክ ቃል ሲሆን በእንግሊዝኛ "Virtue Theory" በሚል ተተርጉሞአል:: ይህ የሥነ ምግባር ዘርፍ ግብረገባዊ ውሳኔዎችን እንዴት መወሰን ይቻላል በሚለው ሳይሆን፣ የሰዎችን ባሕርይ እንዴት ማሻሻል ይቻላል በሚለው ጕዳይ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው::

## አርኤቲክ ተኰር (Virtue-based)

በሥነ ምግባር ድርጊት ላይ ሳይሆን፣ ድርጊቱን በሚያካሂደው ሰው ባሕርይ ቀረጻ ላይ ትኩረት የሚያደርግ የሥነ ምግባር አካሄድ ነው::

## ኢተጣራሽ ፍጹማዊነት (Non-conflicting Absolutism)

እግዚአብሔር ፍጹማዊ የሆኑ በርካታ *ግብረገባዊ ግዕዛንን* (መርሖችን) ለሰው ልጆች ቢሰጥም፣ እነዚህ ግዕዛን ግን በዕለት ኑሮአችን ውስጥ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ (የሚጣረሱ) አይደሉም የሚል እምነት አላቸው::

## አንቀጸ ሃይማኖት (creed)

እንግሊዝኛው ቃል የተወሰደው "ክሬዶ" ከሚለው ከላቲን ቃል ሲሆን፣ ትርጕሙም "አምናለሁ" ማለት ነው:: አንቀጸ ሃይማኖት ማለት መሠረታዊና ዐበይት የሚባሉትን ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች በእጥርጥር መልክ ማስቀመጥ ማለት ነው:: "የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ" ጥንታዊ የሆነ አንቀጸ ሃይማኖት ነው::

## አጠቃላይ መገለጥ (General Revelation)

እግዚአብሔር ራሱን ለሰው ልጆች ሁሉ፣ በየትኛውም ጊዜና በማናቸውም ቦታ ራሱን የገለጠበት (ያስተዋወቀበት) መንገድ ነው:: በአጠቃላይ መገለጥ ውስጥ የሚካተቱት እግዚአብሔር ራሱን በሰዎች ኅሊና (ውስጣዊ በሆነ ግብረገባዊ ንቃት) እንዲሁም በተፈጥሮና በሰብአውያን ታሪክ ውስጥ የገለጠበት መንገድ ነው:: ይህ የመገለጥ ዐይነት እግዚአብሔር መኖሩን የሚያስገነዝብ ብቻ እንጂ፣ ሰዎች ድኅነት ወይም የዘላለም ሕይወት እንዴት እንደሚያገኙ የሚያሳይ አይደለም::

## አፍላጦን (Plato)

አፍላጦን በ426 ዓ.ቅ.ክ እስከ 347 ዓ.ቅ.ክ የኖረ ታላቅ የግሪክ ፈላስፋ ነው:: ቤተሰቦቹ ከንጉሣውያኑ ቤተሰብ ወገን ስለነበሩ ትምህርቱን እስከ ጻር ድረስ በመግፋት በትምህርት የሚገኘውን ጣዕምና እንዲያጣጥም ረድቶታል:: አፍላጦን በ370 ዓ.ቅ.ክ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በመክፈት በስፋት የሚታወቀውን "ተዋስአና ጥያቄ" (Dialogue and Questionging) የሚባለውን ትምህርቱን ማስተማር ጀመረ:: አርስጣጣሊስ ለ20 ዓመት የተቋሙ አባል በመሆን በመጭረሻዎቹ የአፍላጦን የሕይወት ዘመን አብሮት አሳልፎአል:: አፍላጦንና አርስጣጣሊስ በሥነ



ምግባር ብቻ ሳይሆን በፍልስፍናውም ረገድ ትተውት ያለፉት የፍልስፍናና የሥነ ምግባር ሥራ፣ በክላሲካሉ ዘመን ገነው እንዲታዩ እንዲሁም ትተውት ባለፉት ክቡር ሥራቸው በየዘመናቱ እንዲዘከሩ አድርጎአቸዋል:: አፍላጦን በርካታ ተዋስአዎችን የጻፈ ሲሆን፣ በብዙ ሰዎች የተነበበውና በስፋት የሚታወቀው "ዘ ሪፖብሊክ" በመባል የሚታወቀው ተዋስአ ነው:: በዚህም ሥራ አፍላጦን በረካታ የሥነ ምግባር ንድፈ ሐሳቦችን አቅርቦአል:: የአፍላጦን ሥነ ምግባር ትኩረት የሚያደርገው በግብረገባዊ ሕግጋት ላይና ሕግጋቱ በሚያስከትሉት ውጤት ላይ ሳይሆን፣ በነፍስ ርእሰ ጕዳይ ላይ ነው:: የአፍላጦን የግብረገብ ፍልስፍና የተወሰኑ ምግባሮች ሠናይ የተወሰኑ ምግባሮች ደግሞ እኩይ ናቸው በሚለው ላይ የሚያጠነጥን አይደለም:: በአጠቃላይ የአፍላጦን ፍልስፍና በባሕርይ ቀረጻ ላይ ትኩረት የሚያደርግ እንጂ ትክክለኛ የሆነ ግብረገባዊ ውሳኔ በመወሰን ዙሪያ የሚያተኩር አይደለም:: ይህ የግብረገብ አካሄድ አርኤቲክ ሥነ ምግባር በመባል ይታወቃል (አርኤቲክ ሥነ ምግባር የሚለውን ይመለከቷል)::

## ኢአማኒነት (Atheism)

ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ኀይል ማለትም በእግዚአብሔር፣ በአማልክት፣ በመናፍስተና ከሞት በኋላ ባለ ሕይወት የማያምን የፍልስፍና ንድፈ ሐሳብ ነው::

## ዐዋጃዊ (ግዕዛዊ) ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት (Conventionalism or Normative Ethical Relativism)

እያንዳንዱ ሰው መኖር ያለበት የማኅበረሰቡን ግብረገባዊ ፋይዳ በመጠበቅ ነው:: ለአንድ ኅብረተሰብ ትክክል የሆነው ነገር ለሌላው ኅብረተሰብ ትክክል ላይሆን ይችላል፤ ሰዎች ማድረግ የሚገባቸው፣ "ኅብረተሰባቸው" የበየነውንና የሚያደርገውን ግብረገባዊ *ግዕዝ* ነው::

## የበለጠ መልካምነት ለበለጠ ቍጥር (Utilitarianism)

በዚህ የሥነ ምግባር አካሄድ አንድ ግብረገብ ሠናይ ነው የሚባለው፣ የበለጠ መልካምነት ለበለጠ ቍጥር የሚያመጣ ከሆነ ነው::

## ዩቴፍሮ ውጥረት (Euthyphro dilemma) (የ—)

አፍላጦን ዩቴፍሮ በተባለው ተዋስአ (ቃለ ምልልስ) ላይ የጠየቀው ጥያቄ፣ *የተፈጥሮ ትእዛዝ ንድፈ ሐሳብን* የሚከተሉ ሰዎች ሁሉ ራሳቸውን ሊጠይቁ የሚገባ ተገቢ ያቄ ነው:: "አንድ ነገር ትክክል የሆነው እግዚአብሔር ስላዘዘው (ለአፍላጦን አማልክት) ነው ወይስ እግዚአብሔር ያዘዘው ነገሩ ትክክል ሆኖ ስለተገኘ ነው?" በሚለው ያቄ ላይ የሚያጠነጥን ነው:: በሌላ አገላለጽ የእግዚአብሔር ትእዛዝ አንድን ነገር መልካም እንዲሆን ያደርገዋል ወይስ የእግዚአብሔር ትእዛዝ አንድ ነገር መልካም መሆኑን ይጠቁማል?

## ዲበ ሥነ ምግባርና (Metaethics)

ዲበ ሥነ ምግባር የሚባለው የሥነ ምግባር ዘርፍ፣ የግብረገብ ቃላትን ትርጕም የሚመረምር የጥናት ዘርፍ ወይም የሥነ ምግባር *ሥነ ዕውቀት* ነው:: ዲበ ሥነ ምግባር በሥነ ምግባር ውስጥ የሚገኙትን መሠረታዊ ቃላት ማለትም ሠናይ፣ እኩይና ፍትሕ የሚሉትን በስፋት ይተነትናል:: ዲበ ሥነ ምግባር እነዚህ ቃላት የሰዎችን ምርጫ የሚያሳዩ ናቸው ስለሚል ግብረገብን አንጻራዊ ያደርገዋል::

## ዲበ አካል (Metaphysics)

በግእዝ ቋንቋ ዲበ ማለት ባሻገር ማለት ሲሆን፣ አካል ማለት ደግሞ የሚዳሰስ የመጨበጥ ማለት ነው:: ስለዚህ ዲበ አካል ማለት ከቍሳዊ ነገሮች ባሻገር የሚገኙ የረቂቅ ነገሮች ጥናት ማለት ነው::

## ገላጭ (prescribtive)

ባህል የገለጠውን ነገር (ያፈራውን ፍሬ) የሚናገር እንጂ፣ አንድ ባህል መሠረት ያደረጋቸውን ግብረገባዊ ግዕዛን (መርሖ) የሚተነትን አይደለም:: ምክንያቱም በባሕርይ ወይም በጠባይ ላይ ብያኔ የሚሰጥ ወይም ለግብረገባዊ ምግባር አቅጣጫ የሚጠቁም አይደለም:: በሌላ አነጋገር ነገሮች ምን መሆን እንዳለባቸው (እንደሚገባቸው) የሚገልጽ አይደለም::

## ገላጭ ሥነ ምግባር (Normative Ethics)

ገላጭ ሥነ ምግባር በግብረገብ ሕግጋት ላይ ትኩረት በማድረግ ውጤቱን ይተልማል:: ገላጭ ሥነ ምግባር ለአንድ ማኅበረሰብ ወይም ግለሰብ ሠናይ ወይም እኩይ የሆነው ሥነ ምግባር የቱ ነው የሚለውን ጉዳይ ይተነትናል:: ገላጭ ሥነ ምግባር የሥነ ምግባር መሠረት የሆኑትን ግብረገባዊ ሕግጋት (መርሖ) ሲያጠና፣ ተገላጭ ሥነ ምግባር ግን፣ እነዚህ ሕግጋት መሠረት ያደረጉበት ባህል እንዴት ይገለጻል የሚለውን ጉዳይ ይተነትናል::

## ግላጼ (definition)

አንድ ቃል፣ ሐረግ ወይም ዐረፍተ ነገር ምን ትርጉም እንደሚወክል የሚገልጽ ወይም ዐዋጅ ማለት ነው::

## ግብረገባዊ ሕግ (Moral Law)

ግብረገባዊ ሕግጋት የሚባሉት ለሠናይነትና ለእኩይነት ዳር ድንበር የሚያበጁ ወይም ዳር ድንበሩን የሚጠቁሙ ሕጎች ናቸው:: አትግደል፣ አታመንዝር፣ አትስረቅ፣ አትዋሽ፣ ወዘተርፈ::

## ግብረገብ (Morality)

ብዙ ጊዜ ግብረገብንና ሥነ ምግባርን አንዱ ሌላውን ተክቶ ይነገራል:: ግብረገብ ማለት የአንድን ምግባር የሠናይነትና የእኩይነት ይዞታ የሚመለከት ሲሆን፣ ሥነ ምግባር ግን እኩይነትንና ሠናይነትን የመወሰን ሂደት ነው::

## ግብረገባዊ ሕግ (Moral Law)

ግበረገባዊ ሕግጋትን የሚዘረዝር ሕግ ነው:: ይህ ሕግ በብሉያትም ሆነ በአዲሳት ተፈጻሚ እንዲሆን የሚጠበቅ ሕግ ነው::

## ግብረገብ ሕግጋት ሰጪ (Moral law giver) (የ—)

በተፈጥሮ ትእዛዝ ንድፈ ሐሳብ መሠረት እግዚአብሔር የግብረገብ ሰጪ ነው::

## ግብረገባዊ አንጻራዊነት (Moral Relativism)

ግብረገባዊ እውነታዎች እንደ ምግብ ጣዕም በግለሰቦች ኅሊናዊ ብያኔ (ኅሊናዊ እውነታ የሚለውን ይመለከቷል) ይወሰናሉ ያሚለው አመለካከት፣ ግብረገባዊ አንጻራዊነት ይባላል:: እንደ ግብረገባዊ አንጻራዊነት፣ ግብረገባዊ ፋይዳዎች በሰዎች ፍላጎት (ስሜት ወይም ጣዕም) ላይ ሙሉ ለሙሉ መሠረት ስለሚያደርጉ ግለሰቡ፣ "ይህ ለእኔ (Subject) እውነት ነው" እያለ ፋይዳዎቹን ኅሊናዊ (Subjective) ያደርጋቸዋል:: ግብረገባዊ ፍጹማዊነት ደግሞ፣ ግበረገባዊ ሕግጋት ነባራዊ ስለሆኑ በጊዜ፣ በቦታና በሁኔታ አይለወጡም የሚል ነው::

## ግብረገባዊ ፍጹማዊነት (Moral Absolutism)

ግብረገባዊ አንጻራዊነትን ይመለከቷል::



## ግብረገባዊ ሙግቶች አካሄድ (Ways of moral Reasoning)

የግብረገባዊ ሙግቶች አካሄድ የሚባለው የተለያየ ዐይነት የሥነ ምግባር መርሖ በመጠቀም፣ አንድ ምግባር ሠናይ ነው ወይም እኩይ ነው ወደሚል ድምዳሜ መድረስ ነው::

## ግላዊ ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት (ሥነ ምግባራዊ ኅሊናዊነት) (Individual Ethical Relativism or Ethical Subjectivism)

የግል ምርጫ የግብረገብ መሠረት ነው የሚል አመለካከት ነው::

## ግብረገባዊ እውነታ (Moral Truth)

ግብረገባዊ እውነታንና ምክኑያዊ እውነታን ሊያስረዱ የሚችሉ፣ ሁለት ዐረፍተ ነገሮችን እንመልከት:- 1. "አንድ ሰው በደል አልባ የሆነውን ሰው ሊገድል አይገባውም" 2. "አንድ ሰው ጅማ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚገኝ ሊያምን ይገባዋል":: እነዚህ ሁለት ዐረፍተ ነገሮች የተለያዩ ናቸው:: ሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ትክክል ናቸው:: የመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ግብረገባዊ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ምክኑያዊ ነው:: የመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ግብረገባዊ ግዴታን ሲያመለክት፣ ሁለተኛው ዐረፍተ ነገር ደግሞ ምክኑያዊነትን መሠረት ያደረገ ነው::

## ግብረገባዊ ግጭቶች (Moral Dilemma or Moral Conflict)

ከአንድ በላይ የሆኑ ግብረገባዊ ግዕዛን ፋይዳዎች በአንድ በተወሰነ ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ ውስጥ ሰዎች እንዲታዘዙአቸው በሚከሠቱበት ጊዜ ግብረገባዊ ግጭት ተፈጠረ ይባላል::

## ግብረገባዊ አንጻራዊነት (Moral relativism)

የሥነ ምግባር አካሄድ ሲሆን፣ ሠናይነትና እኩይነት ፍጹማንና የማይለወጡ አይደሉም፤ ነገር ግን እንደየ ባህሉና (ባህላዊ ወይምተገላጭ አንጻራዊነት)፣ እንደየ ሰዉ ምርጫ (ግላዊ ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት ወይም ሥነ ምግባራዊ ኅሊናዊነት) የሚለያዩ ናቸው የሚል ንድፈ ሐሳብ ነው::

ግብረገባዊ አንጻራዊነት፣ ግብረገባዊ ፋይዳዎች በሰዎች ወይም በግለሰቦች ፍላጎት ላይ መሠረት ያደረጉ ናቸው የሚል አመለካከት ነው:: ግብረገባዊ አንጻራዊነት ሰዎች ሁሉ ተመሳሳይ በሆነ ግብረገባዊ ሁኔታዎች ውስጥ ሲሆኑ፣ የተወሰነን ግብረገብ ብቻ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል አይልም::

ለሁለት ሰዎች ተመሳሳይ የሆነ ግብረገባዊ ምርጫ ሲቀርብላቸው፣ አንደኛው የመረጠውን ተቃራኒ ሌላው ሊመርጥ ይችላል:: በሁሉም ሰው ላይ ተግባራዊ የሚሆን ግብረገባዊ መመሪያ የለምና:: እንዲያውም አንድ ሰው ትላንት ያደረገውን ነገር ተቃራኒ ዛሬ ቢያደርግ፣ ተሳስተሓል ማለት አይቻልም (አንዳንድ አንጻራውያን፣ ወጥነት ያለው ሕይወት ለመኖር፣ ተመሳሳይ የሆነ አካሄድ ሊኖረን ይገባል ባዮች ናቸው)::

## ግንዛቤያዊ (cognitive)

ግንዛቤያዊ አንጻራዊነት የሚባለው፣ ከግብረገብ ርእስ ጉዳይ ውጪ ባለው ነባራዊ እውነታ ውስጥ ያሉ ነገሮች አንጻራዊነት አለባቸው የሚል አስተሳሰብ ነው:: አንጻራዊ ናቸው የተባሉት ጉዳዮች ግን ፍጹማዊ በሆነው እውነታ ላይ መሠረት ያደረጉ ናቸው:: የዚህ መጽሐፍ ትኩረት የሆነው ግን ግብረገባዊ አንጻራዊነት የሚለው ርእስ ጉዳይ ነው::

### ጠርጣሪነት (Skepticism)

በስሜት ሕዋሳቶቻችን የምናገኛቸውን መረጃዎች ጨምሮ ማናቸውንም ዕውቀቶች ያለአንዳች ልዩነት አጠራጣሪና ሊታመኑ የማይችሉ ናቸው የሚል አስተሳሰብ ነው።

### ጥቅላሌነት

ጥቅላሌነት ዓለም ዐቀፍ ወይም ፍጹም የሆኑ ሕግጋት የሉም፤ ነገር ግን አንዳንድ ሥነ ምግባራዊ ሕግጋት ሁሉን ዐቅፈው የሚይዙ ናቸው። እንደዚህ አመለካከት ውሸትን መናገር በሁሉ ዘንድ ስሕተት ነው፤ በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ (ለምሳሌ:- የሰውን ሕይወት ማዳን) ግን ውሸትን መናገር ትክክል ይሆናል እንደዚህ አመለካከት ሁሉ ዐቀፍ የሆኑት የእግዚአብሔር ሕግጋት (ለምሳሌ:- አትስረቅ፣ አትዋሽ ወይም አትግደል የሚሉት) ዐልፎ ዐልፎ በሚከሠቱ አንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ በፍጹም ተፈጻሚ ሊሆኑ አይችሉም።

### ጥልታዊ ዕውቀት (a priori knowledge)

አንድ ሰው የአንድ ነገር ጥልታዊ ዕውቀት አለው የሚባለው:-

1) የሚታወቀው ነገር እውነት መሆን አለበት።
2) የሚታወቀው ነገር ያለምንም ማስረጃ (ማረጋገጫ) በስሜት ሕዋሳቶች ብቻ የሚታወቅ መሆን አለበት። ይህም ዕውቀት የሥነ ዕውቀት መሠረት ነው።

ቍጥር 1 ዲበ አካል ሲሆን፣ ቍጥር 2 ደግሞ ሥነ ዕውቀት ነው። ይህ ማለት አንድ ሰው ጥልታዊ ዕውቀት አለው የሚባለው የሚያውቀው ነገር በራሱ ትክክል ነው፤ ለምሳሌ:- አንድ ነገር ቀይ ከሆነ ቀለም (ከለር) አለው ማለት ነው። አንድ ነገር 2+2 ከሆነ ውጤቱ 4 ነው ማለት ነው። አንድ ሰው ተሞክሮአዊ ዕውቀት (a posteriori knowledge) አለው የሚባለው ደግሞ:-

1) ነገሩ ይታወቃል እንዲሁም
2) ነገሩ የሚታወቀው በጥልታዊ ዕውቀት አይደለም

### ጽንፈ ዓለም፣ መላለም (Universe)

ዳር ድንበር፣ መነሻና መድረሻ የሌለውን ተፈጥሮ አጠቃሉ የያዘ ነው። ዓለማትን (ፕላኔቶችን)፣ ህዋን፣ ከዋክብትንና ሌሎችን ኅልቁ መሳፍርት (ቍጥር ስፈር) የሌላቸውን ነገሮች ሁሉ ያጠቃልላል።

### ፀረ—አይሁድነት (Anti-Semitism)

አይሁድን ከፉኛ የሚያጥላላና የሚያናንቅ አስተምህሮ ነው። ቀድሞ በሃይማኖት ሳቢያ የተመሠረተው ፀረ አይሁድነት ከ19ኛው ምዕት ዓመት አጋማሽ ጀምሮ ንጹሕ የአርያን ዘርና የኖርዲክ ዘር ከሚሉ የዘረኝነት ንድፈ ሐሳቦች ጋር በተያያዘ መንገድ ይበልጥ በዘር ጥላቻ ላይ የተመሠረተ ሆነ።

### ፋይዳዎች (value)

ነገሮች፣ ክሥተቶች፣ ሐሳባች፣ ደንቦች፣ ሕጎች ወዘተ ለሰዎች የሚሰጡ ት ጠቀሜታ ያላቸው ጥሩነትና ተፈላጊነት፣ የሚያፈሩት ብያኔ በአጠቃላይ ፋይዳ ይባላል።

### ፋይዳዎች፣ መርሖች፣ ግዕዛን፣ (values, norms, paradigms, laws)

የከፋም ሆነ የበጎ መንገድ፣ ጉዞ፣ አካኼድ፣ አረማመድ፣ አኳኋን፣ ልማድ ማለት ነው።

# ዋቢ መጻሕፍት (Bibliography)


Barclay, William. *Ethics in a Permissive Society.* Glasgow: William Collins Sons & Co Ltd, 1971.

Beauchamp, Tom L. *Philosophical Ethics: an Introduction to Moral Philosophy.* New York: McGraw-Hill, 1991.

Beckwith, Francis J and Koukl, Gregory. *Relativism: Feet Firmly Planted in Mid-Air.* Grand Rapids: Baker, 1998.

Bloom, Allan. *The Closing of the American Mind.* New York: Simon and Schuster, 1987.

*Ethical Theory: Classical and contemporary Readings,* Ed. Louis B. Pojman. Belmont, California: Wadsworth, 1995.

Frankena, William. *Ethics.* New York: Prentice-Hall, 1973.

Geisler, Norman L and Turek, Frank S. III. *Legislating Morality.* Minneapolis: Bethany House, 1998.

Harris, James F. *Against Relativism.* Chicago: Open Court, 1992.

Helm, Paul. *The Divine Command Theory of Ethics.* New York: Oxford University Press, 1979.

Holmes, Arthur. *Ethics: Approaching Moral Decisions.* Downers Grove, Ill.: Inter Varsity Press, 1984.

Kaiser, Walter C., Jr. *Toward Old Testament Ethics.* Grand Rapids: Zondervan, 1979.

Lewis, C. S. Mere Christianity. New York: Collier Macmillan, 1960.

_________. *The Abolition of Man.* New York: collier Macmillan, 1955.

Longenecker, Richard. *New Testament Social Ethics for Today.* Grand Rapids: Eerdmans. 1984.

Mill, John Stuart. *Utilitarianism.* Indianapolis: Bobbs-Merrill, 1957.

Moreland, J. P. *Scaling the Secular City.* Grand Rapids: Baker, 1987.

Pojman, Louis P. *Ethics: Discovering Right and Wrong.* Belmont. California: Wadsworth. 1990.

Quinn, Philip. *Divine Commands and Morality.* New York: Oxford University Press, 1981.

Rachels, James. *The Elements of Moral Philosophy.* Philadelphia: Temple University Press, 1986.

Rae, Scott B. *Moral Choices: An Introduction to Ethics.* Grand Rapids: Zondervan, 1995.

*Readings in Moral Theology, Vol. 7: Natural Law and Theology.* Eds. Curran, Charles E and Richard C. McCormick, New York: Paulist Press, 1992.

Sumner, William Graham. *Folkways.* Chicago: Ginn and Company, 1906.

Wright, Christopher J. H. *An Eye for an Eye: The place of Old Testament Ethics Today.* Downers Grove, Ill.: Inter Varsity Press, 1983.

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፤ *መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፤* አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤ *1948*፡፡

*የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት፤* አዲስ አበባ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፤ *1978*፡፡

ደስታ ተክለ ወልድ፤ *ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፤* አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤ *1962*፡፡